# መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ።

## በግእዝና ፡ በአማርኛ ።

ይህ ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ በብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ጳውሎስ ፡ ፓትርያርክ ፡
ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ፤ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዘአክሱም ፤ ወዕጨጌ ፡ ዘመንበረ ፡
ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በ፲፭ኛው ፡ ዘመነ ፡ ፓትርያርክነት ፡ ለመጀመሪያ ፡
ጊዜ ፡ በግእዝና ፡ በአማርኛ ፡ ታተመ ።

አሳታሚ ፡– ትንሣኤ ፡ ማሳተሚያ ፡ ድርጅት፡
አ·አ· ፲፱፻፺፯ ፡ ዓ·ም

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡ሌሊት፡ዘረቡዕ።

አስመ : ሶበ : ቀርበ : በዐለ : ፋሲካሆሙ :
የዐርጉ፡ብዙኃን፡እምበሐውርት፡ኀበ፡ኢየሩ
ሳሌም፡ከመ፡ይንጽሑ።
፲፪ ወሶበ : ሐሩ : በከመ : ልማድ : ኢርእይዎ :
ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡በህየ።
ወይቤሎ : ካልእ : ለካልኡ : እንዘ : ሀለዉ :
፲፫ በቤተ : መቅደስ : ኢመጽአኑ : ኀበ : በዐል :
በኀሊና፡ጕሕሉት፡ዘምልእት፡እድልዎ።
፲፬ ተሐዘቡ፡ኪያሁ፡እልክቱ፡ረሲዓን።

፲፭ ወሊቃነ፡ካህናት፡ኮኑ፡ምስለ፡ፈሪሳውያን፡
የአዝዙ : ከመ : ለእመ : አእመረ : አሐዱ :
አይቴ፡ውእቱ፡ይዜንዎሙ፡ከመ፡የአኀዝዎ።
እ፡ዛቲ፡እበድ፡ወዝንቱ፡ልብ፡ዕጽው፡ወዛቲ፡
ግብር፡ዘላዕለ፡ርኩሳን፡አልባብ።

፲፮ ለበዐለ፡ኃይል፡ወጽንዕ፡ዘይትለአከዎ፡ኵሉ፡
ኃይለ : ሰማያት : አንበሩ : ሎቱ : ዐላውያን :
መሥገርተ : ይትአሰሩ : በልሳኖሙ :
ወይበውኡ፡ኀበ፡ገሃነም፡ወኵነኔ።

ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡ መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ
ማማቲሁ፡አድኃነነ።
ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ከመ፡ቀዳሚ።

## ምዕራፍ፡፴፩።

ትእዛዝ፡ወይትጋብኡ፡ካህናት፡ውስተ፡ቤተ፡
ክርስቲያን፡ቅድስት፡በዕለተ፡ረቡዕ፡በጊዜ፡
ነግህ፡ወይጸልዩ፡ጸሎተ፡ነግህ፡ከመ፡ሰኑይ።

ክፍል፡፩።
ምንባብ።
ኦሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፡፲፯፡፩–፯።
፩ ወእንሥኡ : ትዕይንቶሙ : ኵሉ : ውሉደ :
እስራኤል፡ እምገዳም : ዘሲን : በበትዕይ
ንቶሙ፡ በቃለ : እግዚአብሔር : ወበጽሑ :
ኀበ፡ ራፊድ : ወአልቦ : ህየ : ማይ : ዘይ
ሰትዩ።

ረቡዕ፡ሌሊት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ብዙዎች : ወደ : ኢየሩሳሌም : ወጥተው :
ይነጹ፡ ዘንድ : ለአይሁድ : ሁሉ : ቀዋሚ :
የሆነ፡ልማድ፡ነበራቸው።
፲፪ እንደ : ልማዳቸውም : በወጡ : ጊዜ : ጌታ :
ኢየሱስን፡በዚያ፡አላዩትም።
፲፫ በቤተ : መቅደስም : ሳሉ : ባልንጀራ : ባልንጀ
ራውን : አድልዎን : በተመላች : በሽንገላ :
ኀሳብ፡አልመጣምን፡ይለው፡ነበር።
፲፬ እነዚህ : ዝንጉዎች : ኀሳባችንን : አውቆ :
ይሠወር፡ይሆን፡ብለው፡ተጠራጠሩ።
፲፭ ወዴት፡እንዳለ፡አንድ፡ሰው፡የአወቀ፡ቢኖር፡
ሊይዙት፡ይነግራቸው፡ዘንድ፡ሊቃነ፡ካህናቱ፡
ከፈሪሳውያን፡ጋራ፡ሁነው፡ያዝዙ፡ነበር።
ይህቺ : ድንቍርና : ይህ : የተዘጋ : ልብ :
ልባቸው፡ርኩሳን፡የሆኑ፡የአይሁድ፡ይህች፡
ሥራ፡ወዮ!
፲፮ በሰማያት፡ያሉ፡የመላእክት፡ሠራዊት፡ሁሉ፡
የሚያገለግሉት፡የኃይል፡የጽንዕ፡ባለቤት፡ለሆነ፡
ለእርሱ : ወንጀለኞች : አይሁድ : ወጥመድ :
አኖሩለት ፤ ግን : በአንደበታቸው : ታሥረው :
ወደ፡ገሃነም፡ቅጣት፡ተፈርዶባቸው፡ይገባሉ።
መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡ ሰው፡ሆኖ፡መከራ፡
ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።
ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
የጸሎቱ፡ፍጻሜ፡እንደ፡ፊተኛው፡ነው።

## ምዕራፍ፡፴፩።

ትእዛዝ፡ ካህናቱ፡ ረቡዕ፡ በነግህ፡ በከበረች፡ ቤተ፡ ክር
ስቲያን፡ውስጥ፡ይሰብሰቡ፤ሰኞ፡ጥዋት፡በነግህ፡
እንደተደረገውም : የነግሁን : ጸሎት : ይጸልዩ።

ክፍል፡፩።
ምንባብ።
ኦሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፡፲፯፡፩ ፯።
፩ የእሥራኤል፡ልጆች፡ሁሉ፡በእግዚአብሔር፡
ቃል፡ ታዝዘው፡በሰፈራቸው፡ያለ፡ጓዛቸውን፡
በደብረ፡ሲና፡ካለ፡ምድረ፡በዳ፡አንሡ፡ወደ፡
ራፊድም፡ደረሱ፡በዚያ፡የሚጠጡት፡ውኃ፡
አልነበረም።

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

፪፡ ወግዕዝዎ፡ሕዝብ፡ለሙሴ፡ወይቤልዎ፡ሀበነ፡
ማየ፡ዘንስቲ፡ወይቤሎሙ፡ሙሴ፡ምንተ፡
ትግዕዙ፡ኪያየ፡ወታሜክርዎ፡ለእግዚአ
ብሔር።

፫፡ ወፀምዑ፡በህየ፡ሕዝብ፡ማየ፡ወአንጐርጐሩ፡
ዲበ፡ሙሴ፡ወይቤልዎ፡ለምንት፡አውፃእከነ፡
እምድረ፡ግብጽ፡ከመ፡ትቅትለነ፡ምስለ፡
ውሉድነ፡ወምስለ፡እንስሳነ፡በጽምእ።

፬፡ ወጸርሐ፡ሙሴ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡ወይቤ፡
ሚ፡እግበሮ፡ለዝ፡ሕዝብ፡ንስቲተ፡ከመ፡
ተርፎሙ፡ወይዌግሩኒ፡በዕብን።

፭፡ ወይቤሎ፡እግዚአብሔር፡ለሙሴ፡ሑር፡
ቅድሜሆሙ፡ለሕዝብ፡ወንሣእ፡ምስሌከ፡
መላሕቅተ፡ሕዝብ፡ወበትረከ፡ዘቦቱ፡
ዘበጥከ፡ፈለገ፡ጽብጥ፡በእዴከ፡

፮፡ ወትመጽእ፡ለፌ፡ኀበ፡አነ፡እቀውም፡
መንገለ፡ኮኵሕ፡ዘኮሬብ፡ወትዘብጦ፡
ለኰኵሕ፡ወይወጽእ፡እምውስቴቱ፡ማይ፡
ወይስተዩ፡ሕዝብ፡ወገብረ፡ሙሴ፡በከመ፡
አዘዞ፡እግዚአብሔር፡በቅድሜሆሙ፡
ለደቂቀ፡እስራኤል።

፯፡ ወሰመዮ፡ለውእቱ፡መካን፡ፍና፡መንሱት፡
ወጋዕዝ፡በእንተ፡ግዕዘት፡ዘግዕዝዎ፡ውሉደ፡
እስራኤል፡ወአመከሩ፡ፈጣሬ፡ኵሉ፡
ወይቤሉ፡ለእመ፡ሀሎ፡እግዚአብሔር፡
ምስሌነ፡ወለእመ፡ኢሀሎ፡ምስሌነ።
ዘያመልክ፡በፍጡር፡ርጉም፡ውእቱ።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፪፡፩–፲፩።

፩፡ ቃል፡ዘኮነ፡ኀበ፡ኢሳይያስ፡ወልደ፡አሞጽ፡
ዘርእየ፡በእንተ፡ይሁዳ፡ወበእንተ፡ኢየሩሳሌም።
፪፡ ወይከውን፡በደኀሪ፡መዋዕል፡ያስተርኢ፡
ደብረ፡እግዚአብሔር፡ወቤተ፡እግዚአ
ብሔር፡ውስተ፡አርእስተ፡አድባር፡ወይት
ሌዓል፡መልዕልተ፡አውግር፡ወየሐውሩ፡
ኀቤሁ፡ኵሎሙ፡አሕዛብ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

፪፡ እስራኤልም፡የምንጠጣው፡ውኃ፡ስጠን፡
ብለው፡ሙሴን፡ነቀፉት፤ ሙሴም፡እኔን
ለምን፡ ትነቅፉኛላችሁ? እግዚአብሔርንስ፡
ለምን፡ትፈታተኑታላችሁ?አላቸው።

፫፡ ሕዝቡም፡በዚያ፡ውኃ፡ተጠምተው፡በሙሴ፡
ላይ አንጐራጐሩ፤ ከእንስሶቻችንና፡ከልጆ
ቻችን፡ጋራ፡በውሀ፡ጥም፡ትገድለን፡ዘንድ፡
ከግብጽ፡ምድር፡ለምን፡አወጣኸን፡አሉት።

፬፡ ሙሴም፡በደንጊያ፡ሊወግሩኝ፡ጥቂት፡ብቻ፡
ቀርቷቸዋል፤ይህን፡ሕዝብ፡ምን፡ላድርገው፡
ብሎ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ጮኸ።

፭፡ እግዚአብሔርም፡ሙሴን፡የሕዝቡን፡
አለቆች፡ከአንተ፡ጋራ፡ይዘህ፡በሕዝቡ፡ፊት፡
ሂድ፤ውኃውን፡የመታህበትን፡በትርህንም፡
በእጅህ፡ያዝ።

፮፡ እኔ፡ወደቆምኩበት፡ወደዚያ፡ወደ፡ኮሬብ፡
ዋሻ፡ና፤ ደንጊያውንም፡ምታው፤ከደንጊ
ያውም፡ውኃ፡ይወጣል፤ሕዝቡም፡ውኃውን፡
ይጠጡ፡አለው፤ ሙሴም፡በእስራኤል፡
ልጆች፡ፊት፡እግዚአብሔር፡እንዳዘዘው፡
አደረገ።

፯፡ የእስራኤል፡ልጆች፡ስለነቀፉት፡ነቀፌታ፡
እግዚአብሔር፡ከእኛ፡ጋራ፡እንዳለ፡እንደ
ሌለም፡ብለው፡ሁሉን፡የፈጠረ፡እግዚአብሐ
ርንም፡ስለ፡ተፈታተኑ፡ያንን፡ቦታ፡የክር
ክርና፡የጥፋት፡ቦታ፡ብሎ፡ጠራው።
በፍጡር፡የሚያመልክ፡ርጉም፡ነው።

የነቢዩ፡የኢሳይያስ፡ትንቢት፡የአምላኩ፡
በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፡፪፡፩–፲፩።

፩፡ ስለ፡ኢየሩሳሌምና፡ስለ፡ይሁዳ፡ወደ፡አሞጽ፡
ልጅ፡ወደ፡ኢሳይያስ፡የመጣ፡ቃል፡ይሀ፡ነው።

፪፡ በኋላ፡ዘመን፡እንዲህ፡ይሆናል፤የእግ
ዚአብሔር፡ማደሪያ፡ቤተ፡መቅደስ፡በከረ
ብቶች፡ላይና፡በተራሮች፡ላይ፡ከፍ፡ብሎ፡
ይታያል፤ አሕዛብም፡ሁሉ፡ወደ፡እርሱ፡
ይሄዳሉ።

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

፫ ወይመጽኡ ፡ ብዙኃን ፡ አሕዛብ ፡ ወይብሉ ፡
ንዑ፡ንዕርግ፡ውስተ፡ደብረ፡እግዚአብሔር፡
መውስተ፡ቤተ፡አምላከ፡ያዕቆብ፡ይንግሩነ፡
ፍኖቶ፡ወንሑር፡በአሠሩ፡ለእግዚአብሔር፡
እስመ፡እምጽዮን፡ይወጽእ፡ሕግ፡ወቃለ፡እግ
ዚአብሔር፡እምኢየሳሌም።

፬ ወይኴንን፡በማእከለ፡አሕዛብ፡ወይዛለፎሙ፡
ለብዙኃን ፡ አሕዛብ ፡ ወይመትሩ ፡ መጣብ
ሒሆሙ፡ለምሳር፡ወኲያንዊሆሙ፡ለማዕፀድ፡
ወኢያነሥኢ ፡ እንከ ፡ ሕዝብ ፡ ዲበ ፡ ሕዝብ ፡
መጥባሕተ፡ወኢይትሜሀሩ፡እንከ፡ቀትለ።

፭ ወይእዜኒ ፡ ቤተ ፡ ያዕቆብ ፡ ንዑ ፡ ንሑር ፡
በብርሃነ፡እግዚአብሔር፡ እስመ ፡ ሜጠሙ ፡
ለሕዝቡ፡እስራኤል፡(ተረስዐት፡ሕዝበቶሙ፡
ለእስራኤል።)

፮ እስመ ፡ መልአ ፡ በሓውርቲሆሙ ፡ ከመ ፡
ትካት፡ ዘያስግሉ ፡ ከመ ፡ ኢሎፍሊ ፡ ወከመ ፡
ትውልደ ፡ ነኪር ፡ ኮኑ ፡ ወተወልዱ ፡ ሎሙ ፡
ብዙኃን፡ደቂቅ፡ወካልእ፡ሕዝብ።

፯ ወመልአ ፡ ብሔሮሙ ፡ ወርቀ ፡ ወብሩረ ፡
ወአልቦ ፡ ኍልቍ ፡ ለመዛግብቲሆሙ ፡
ወመልአት፡ምድሮሙ፡አፍራሰ፡ወአልቦ፡
ኍልቍ፡ለሠረዊቶሙ።

፰ ወመልአት፡ምድሮሙ፡ጣዖተ፡ዘገብሩ፡በእ
ደዊሆሙ ፡ ወሰገዱ ፡ ለዘገብሩ ፡ በአፃብ
ዒሆሙ።

፱ ወተቀጽዐ ፡ ሰብእ ፡ ወኅሥረ ፡ ዕጓለ ፡
እመሕያው፡ወኢያሥሕቶሙ።

፲ ወይእዜኒ፡ባኡ፡ውስተ፡ኰኵሕ፡ወተኀብኡ፡
ውስተ፡ግበ፡ምድር፡እምፍርሃተ፡ገጸ፡እግዚአ
ብሔር ወእምግርማሁ ፡ ወእምስብሐተ ፡
ኃይሉ፡አመ፡ተንሥአ፡ይቀጥቅጣ፡ለምድር።

፲፩ እስመ፡አዕይንተ፡ልዑላን፡ሰብእ፡የኀሥራ፡
ወየኀሥር፡ልዕልናሁ፡ለዕጓለ፡እመሕያው፡
ወይትሌዓል፡እግዚአብሔር፡ባሕቲቱ፡ይእተ፡
አሚረ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

፫፤ ብዙዎች፡አሕዛብ፡መጥተው፡ከጽዮን፡ሕግ፡
ከኢየሩሳሌም ፡ የእግዚአብሔር ቃል ፡
ይወጣልና፡ኑ፡ዳናውን፡ይነግሩን፡ዘንድ፡በእ
ግዚአብሔርም ፡ ፍለጋ ፡ (በአምልኮቱ)፡
እንሄድ፡ዘንድ፡ወደ፡ያዕቆብ፡ፈጣሪ፡ወደ፡
እግዚአብሔር፡ማደሪያ፡ቤተ፡መቅደስ፡ኑ፡
እንውጣ፡ይላሉ።

፬፤ በአሕዛብ፡መካከል፡ይፈርዳል፤(ዘሩባቤል)፡
ብዙዎች፡አሕዛብንም፡ይዘልፋቸዋል፤ሰይፎ
ቻቸውን፡ምሳር፡ጦሮቻቸውንም፡ማጭድ፡
አድርገው ፡ ያሠራሉ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አንዱ ፡
ወገን ፡ በአንዱ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ሰይፍን ፡
አያነሣም፤እንግዲህም፡ሰልፍ፡አይማሩም።

፭፤ የእግዚአብሔር ፡ ወገንነታቸው ፡ ተዘንግ
ቷልና፤አሁንም፡የያዕቆብ፡ወገኖች፡ኑ፡በእግ
ዚአብሔር ፡ ብርሃን ፡ ረድኤት ፡ ጸንተን ፡
እንኑር።

፮፤ ኢሎፍላውያን ፡ ቀድሞ ፡ እንደሚያስጠነ
ቍሉት ፡ ያለ ፡ ጥንቈላ ፡ በአገራቸው ፡
መልቷልና ፤ እንደ ፡ ከነዓንም ፡ ልጆች ፡
ሁነዋልና ፡ ብዙ ፡ ልጆችም ፡ ተወልደውላቸ
ዋልና።

፯፤ አገራቸው፡ወርቅን፡ብርን፡መልቷልና፤ለሪቅ፡
ለጐተራቸውም፡ስፍር፡ቍጥር፡የለውም፤አገ
ራቸውም፡ፈረሶችን፡ተመልታለችና፡ለሠራዊ
ቶቻቸውም፡ቍጥር፡የላቸውም።

፰፤ አገራቸውም ፡ በእጆቻቸው ፡ የሠሩት ፡
ጣዖትን ፡ ተመልታለችና ፡ በጣቶቻቸው ፡
ለሠሩትም፡ጣዖት፡ሰግደዋልና።

፱፤ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በመከራ ፡ ተሰነካከለ፤ ሰውም ፡
ሁሉ፡ጐሰቈለ፤ሞትም፡አያሳርፋቸውም።

፲፤ አሁንም፡ወደ፡ዋሻው፡ግቡ፤ምድርን፡እንደ፡
ሰም፡ያቀልጣት፡ዘንድ፡በተነሣ፡ጊዜ፡የእግ
ዚአብሔርን፡ፊት፡ከመፍራት፡ከግርማውና፡
ኃይሉን፡ከሚገልጥበት፡ጌትነቱ፡የተነሣ፡
ወደ፡ምድር፡ጕድጓድ፡ገብታችሁ፡ተሠወሩ።

፲፩፤ የታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ዓይኖች ፡ ይፈሳሉና ፤
የሰውም ፡ ክብር ፡ ይዋረዳልና፤ የዚያን ፡
ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡
ይላል።

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

ዘተወክፈ ፡ ነቢየ ፡ በስመ ፡ ነቢይ ፡ አሥበ ፡ ነቢይ ፡ ወዕሤተ ፡ ነቢይ ፡ ይነሥእ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር፡አምላኩ።

ምሳሌያተ ፡ ሰሎሞን ፡ በረከተ ፡ አምላኩ፡ ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፫፡፭-፲፭።

፭፡ ሀሉ ፡ ተወኪለከ ፡ በእግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡ ልብከ፡ወበጥበብከ፡ኢትትዓበይ።

፮፡ በኵሉ ፡ ፍናዊከ ፡ አክብሮ ፡ ከመ ፡ ታርትዕ ፡ ፍናዊከ።

፯፡ ኢትኩን፡ጠቢበ፡ዘበርእስከ፡አላ፡ፍርሆ፡ለእግዚአብሔር፡ወተገኀሥ፡እምኵሉ፡እኩይ።

፰፡ ወሶቤሃ ፡ ፈውሰ ፡ ይከውነከ ፡ ለሥጋከ ፡ ወሥራየ፡ለአዕፅምቲከ።

፱፡ አክብሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምዘበጽድቅ ፡ ጥሪትከ ፡ ወአብእ ፡ ሎቱ ፡ ቀዳሜ ፡ ማእረርከ ፡ ወእምፍሬ፡ጽድቅከ።

፲፡ ከመ፡ይስፍፉ፡መዛግብቲከ፡ብዙኀ፡ሥርናየ፡ወወይነ፡ማኅበብቲከ፡ይስፍፍ።

፲፩፡ ወልድየ ፡ ኢትትአንተል ፡ተግሣጸ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢትድከም ፡ እምኀቤሁ ፡ በተዛልፎቱ።

፲፪፡ እስመ ፡ ዘአፍቀረ ፡ ይጌሥፅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ አብ ፡ ዘይሠምር ፡ ወልዶ ፡ ወይቀሥፍ ፡ ኵሎሙ፡ውሉዶ፡ዘኢይትዌከፉ፡ተግሣፀ።

፲፫፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘይረክባ ፡ ለጥበብ ፡ ወኢ ፡ መዋቲ፡ዘአእመረ፡ሐኒከ።

፲፬፡ ይኄይስ፡ኪያሃ፡ተገብሮ፡እምተገብሮ፡ወርቅ፡ ወብሩር፡ወእምብዝኀ፡መዛግብት።

፲፭፡ ክብርት ፡ ይእቲ ፡ እምዕንቍ ፡ ዘብዙኀ ፡ ሤጡ።

ትርጓሜ ፡ ምሳሌያተ ፡ ሰሎሞን ፡ ሀሉ ፡ ተወኪለከ ፡ እስከ ፡ ኀበ ፡ ይብል ፡ ዘብዙኀ ፡ ሤጡ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ

በነቢይ ፡ ስም ፡ ነቢይን ፡ የተቀበለ ፡ የነቢዩን ፡ ዋጋ ፡ ከአምላኩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይቀበላል።

የሰሎሞን ፡ ምሳሌዎች ፡ የአምላኩ ፡ በረከት ፡ ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፡፫፡፭-፲፭።

፭፡ በፍጹም፡ልቡናህ፡በእግዚአብሔር፡እምነህ፡ ኑር፤በጥበብህም፡አትታበይ።

፮፡ ሥራህን ፡ ታቀናልህ ፡ ዘንድ ፡ በሥራህ ፡ ሁሉ፡ አክብራት።

፯፡ እግዚአብሔርን ፡ ፍራው ፡ ከክፉ ፡ ሥራም ፡ ራቅ ፡ እንጂ ፡ ከራስህ ፡ ባነቃኸው ፡ ጥበብ ፡ ብልህ፡ነኝ፡አትበል።

፰፡ ያን፡ጊዜ፡ለአንተ፡ድኅነት፡ይሆንልሃል፡ለልጆችህም፡ድኅነት፡ይሆንላቸዋል።

፱፡ ወጥተህ ፡ ወርደህ ፡ ካገኘኸው ፡ ገንዘብህ ፡ ሰጥተህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አክብረው፤ያገመራህንም፡መጀመሪያ፡ከእውነተኛ፡ገንዘብህ፡ አግባለት።

፲፡ ጎተራዎችህ፡ብዙ፡ስንዴን፡ይመሉ፡ዘንድ፡ ፊቀኖችህም፡ወይንን፡ይመሉ፡ዘንድ፡አግባ።

፲፩፡ ልጄ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ተግሣጽ ፡ ቸል ፡ አትበል፤ መከራ ፡ በማምጣቱም ፡ ከሱ ፡ ዘንድ፡ ንስሓ፡መግባትን፡አትድከም።

፲፪፡ አባት ፡ የሚወደውን ፡ ልጅ ፡ ይገሥጻል፤እግዚአብሔርም ፡ የሚወደውን ፡ ይገሥጻልና ፡ አባት፡ ትእዛዙን ፡ የማይቀበሉ ፡ ልጆቹን ፡ እንዲገርፍ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በመከራ ፡ ይገሩልና፡አትድከም።

፲፫፡ ጥበብን ፡ የሚያገኛት ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው፤ ኀፊረ ፡ ገጽንም ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ሕያው፡ነው፤(በነፍስ)።

፲፬፡ ብርና ፡ ወርቅን ፡ መናገጃ ፡ ከማድረግ ፡ ይልቅ፡ ጥበብን ፡ መናገጃ ፡ ማድረግ ፡ ይሻላል፤ከብዙ፡ ድልብም፡ይሻላል።

፲፭፡ ዋጋው ፡ ብዙ ፡ ከሆነ ፡ ከዕንቍም ፡ የከበረች፡ ናት።

የሰሎሞን ፡ ምሳሌዎች ፡ ትርጓሜ ፡ በፍጹም፡ልቡናህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምነህ ፡ ኑር፤ ከሚለው፡ ጀምሮ፡ዋጋው፡ብዙ፡የሆነ፡እስከሚለው፡ድረስ

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

ይቤ፡መተርጉም። ሀሉ፡ተወኪለከ፡በኵሉ፡
ልብከ፡በእግዚአብሔር፡ይተረጐም፡ከመ፡
ለብእሲ፡ኢይኩን፡ተወክሎ፡ሎቱ፡በውስተ፡
ዓለም፡ኢ፡ላዕለ፡ንዋይ፡ወኢ፡ላዕለ፡ገጸት፡
ወኢ፡ኀሢሠ፡ሢመት።
ዳእሙ፡ይሚጥ፡ኀሊናሁ፡ወኵሎ፡ኀይላቲሁ፡
ለእግዚአብሔር፡ልዑል፡ወይፈጽም፡ኵሎ፡
በከመ፡ይቤ፡በወንጌል፡ኅሡ፡መንግሥቶ፡
ወጽድቆ፡ለእግዚአብሔር፡ዘውእቱ፡ኅሥዎ፡
ለእግዚአብሔር፡በኵሉ፡አልባቢክሙ፡
ወዝንቱሰ፡ኵሉ፡ይትዌሰከክሙ።

ይቤ፡ኢትትዐበይ፡በጥበብከ፡ይተረጐም፡
እስመ፡ብእሲ፡ለእመ፡ኮነ፡ጠቢበ፡ወይት
ሜከህ፡በጥበቡ፡ውእቱሰ፡ጽኑስ፡ወምኑን፡
በከመ፡ይቤ፡ሐዋርያ፡ምኑን፡ዕቡይ፡በኀበ፡
እግዚአብሔር።
ወካዕበ፡ይቤ፡ዘሰ፡ይትሜካህ፡በዝ፡ለይት
መካህ፡በእግዚአብሔር፡እስመ፡እግዚአ
ብሔር፡ውእቱ፡ወሀቤ፡ጥበብ፡ለጠቢባን።
ይቤ፡እስመ፡ለእመ፡ኮነ፡ጠቢብ፡ትሑተ፡
ወይሁብ፡ለርእሱ፡ተፅናሰ፡እግዚአብሔርኒ፡
ይዌስኮ፡ጥበበ፡ወሰብእኒ፡ያዐብዮ፡
ወያከብሮ፡ፈድፋደ።

ወይደሉ፡ለጠቢብ፡ካዕበ፡ከመ፡ኢይቈቂ፡
ጥበቢሁ፡እምነ፡ካልኡ፡ወኢይረስያ፡ከመ፡
መዝገብ፡ዘመትሕተ፡ምድር፡ወኢይበቍዖ፡
ቦቱ።
ዳእሙ፡ይትመሰሎ፡ለፈጣሪሁ፡ወይት
መሰሎ፡በኵሉ፡ተጋድሎቱ፡ከመ፡
ይርብሐሙ፡ለደቂቀ፡ትዝምዱ፡ዘጸገዎ፡እግ
ዚአብሔር፡እምኵሉ፡ጥበብ።
ወይከውኖ፡እንከ፡በእንተ፡ውእቱ፡ዕሴተ፡
ዐቢየ፡በከመ፡ይቤ፡በወንጌል፡ቅዱስ፡
ዘይሜህር፡ወይገብር፡ከመዝ፡ዐቢየ፡
ይከውን፡በመንግሥተ፡ሰማያት።
ይቤ፡ወኵሎ፡ፍናዊከ፡ክሥት፡ሎቱ፡ከመ፡
ያርትዕ፡ፍናዊከ፡ወኢትትዐቀፍ፡በእብን፡

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

፩፤ ተርጓሚው፡በፍጹም፡ልቡናህ፡በእግዚአ
ብሔር፡ታምነህ፡ኑር፡አለ። ሰው፡በዚህ፡
ዓለም፡ሳለ፡እምነቱና፡ተስፋው፡በገንዘብ፡
ላይ፡ወይም፡በሌላ፡ወገን፡ወይም፡ሹመት፡
በመሻት፡አይሁን፡በማለት፡ይተረጐማል።
፪፤ ነገር፡ግን፡ሀሳቡንም፡ችሎታውንም፡ሁሉ፡
ወደ፡ልዑል፡እግዚአብሔር፡ይመልስ፡
እንጂ። በወንጌልም፡የእግዚአብሔርን፡መን
ግሥቱንና፡ጽድቁን፡ፈልጉ፡የተባለውን፡
ይፈጽም፡ይኸውም፡በፍጹም፡ልቡናችሁ፡
እግዚአብሔርን፡ፈልጉት፡ማለት፡ነው።ይህ፡
ሁሉ፡ግን፡ይጨመርላችኋል።
፫፤ በጥበብህ፡አትታበይ፡አለ፤ ይህን፡ይተረ
ጐማል፤ሰው፡ጥበበኛ፡ሁኖ፡በጥበቡ፡ቢመካ፡
እርሱም፡ችግረኛና፡የተናቀ፡ይሆናል፤
ሐዋርያው፡ትዕቢተኛ፡በእግዚአብሔር፡
ዘንድ፡የተናቀ፡ነው፡እንዳለ።
፬፤ ዳግመኛም፡የሚመካ፡በእግዚአብሔር፡
ይመካ፡አለ፤ እግዚአብሔር፡ለጥበበኞች፡
ጥበብን፡የሚገልጽ፡እሱ፡ነውና።
፭፤ ጥበበኛ፡ሰው፡ራሱን፡ዝቅ፡ዝቅ፡የሚአ
ደርግ፡ራሱንም፡እንደ፡ችግረኛ፡የሚቆጥርን፡
እግዚአብሔር፡ጥበብን፡ይጨምርለታል፤
ሰውም፡ከፍ፡ከፍ፡ያደርገዋል፤እጅግም፡ያከ
ብረዋል፤
፮፤ ጥበበኛ፡ጥበቡን፡ከባልንጀራው፡ሠውሮ፡
እንደ፡ቅርስ፡ሣጥን፡ከምድር፡በታች፡
ሊቀብራት፡አይገባም፤አይረባውም፤አይጠቅ
መውም።
፯፤ ነገር፡ግን፡ፈጣሪውን፡ይምሰለው፡እንጂ፡
በትሩፋቱ፡ሁሉ፡ይምሰለው፡እግዚአብሔር፡
በገለጠለት፡ጥበብ፡የወገኖቹን፡ልጆች፡ይጠ
ቅማቸው፡ዘንድ፡ይምሰለው፡አለ።
፰፤ ስለዚህም፡ታላቅ፡ዋጋ፡ይሆንለታል፤
በቅዱስ፡ወንጌል፡እንደዚህ፡የሚያስተምር፡
የሚአደርገውም፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡
ታላቅ፡ይሆናል፡እንዳለ።
፱፤ መንገድህን፡ያቀናልህ፡ዘንድ፡ሥራህን፡
(ልመናህን)፡ ግለጥ፤ እግርህም፡በደንጊያ፡

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

እግርከ፡ ይተረጕም፡ ብእሲ፡ ፈራሂ፡ እግዚአ
ብሔር፡ተላዌ፡ትእዛዛቲሁ፡ዘየሐውር፡ውስተ፡
ፍናዊሁ፡ወዘይዜከር፡በኵሉ፡ጊዜ፡ትእዛዛቲሁ፡
ለይኩን፡እንከ፡ዘየአምን፡ድቀታቲሁ።

፲፤ በከመ፡ይቤ፡እግዚእን፡በአፈ፡ነቢይ፡ለእመ፡
ኮነ፡ ብእሲ፡ ዘይዜከር፡ ኃጣውኢሁ፡ አንሰ፡
እረሥዓ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ወትርጓሜሁ፡
ለርስዓት፡ በዝየ፡ ኅድገት። እስመ፡ ኃጥእ፡
ለእመ፡ነስሐ፡ኀበ፡ እግዚእ፡ በኵሉ፡ ልቡ፡
ወኮነ፡ ይዜክር፡ ለዝሉፉ፡ ዘገብሮ፡ ንስሓሁ፡
እንቲአሁ፡ እስመ፡ የኀድግ፡ ሎቱ፡ እግዚአ
ብሔር፡ኃጣውኢሁ፡ወኢይገብእ፡ይዝክራ፡
እስመ፡ መሐሪ፡ ውእቱ፡ እግዚአብሔር።
ወለሊሁ፡ነገረ፡በእንተ፡ውእቱ።

፲፩፤ ወብሂሎቱሰ፡ ከመ፡ ያርትዕ፡ ፍናዊከ፡
ይተረጕም፡ በእንተ፡ ውእቱ፡ እንበይነ፡
ፍኖተ፡መድኃኒት፡ዘትበቍዓ፡ለነፍስከ፡

፲፪፤ ወዘይቤ፡ከመ፡ኢትትዐቀፍ፡በእብን፡እግርከ፡
ዘውእቱ፡ ለእመ፡ ጸናእከ፡ ላዕለ፡ ዝንቱ፡
ተጋድሎት፡ኢትወድቅ፡ለዓለም።

፲፫፤ ዳእሙ፡ትከውን፡ተዐቅበከ፡ረድኤተ፡እግዚአ
ብሔር፡ ከመ፡ ኢትድኀፅ፡ በከመ፡ ይቤ፡
ሐዋርያ፡ እስመ፡ ዘተወልደ፡ እምእግዚአ
ብሔር፡ኢይኤብስ።

፲፬፤ ይተረጕም፡ካዕበ፡እስመ፡ብእሲ፡ለእመ፡ኮነ፡
መፍቀሬ፡ እግዚአብሔር፡ እምኵሉ፡ ልቡ፡
ወተላዌ፡ ሕጉ፡ ወትእዛዛቲሁ፡ እስመ፡
ኢየኀጥእ፡ውእቱ፡ምንተኒ።

፲፭፤ ወአምጣነሰ፡ ሀለወ፡ ላዕለ፡ ዝንቱ፡ እስመ፡
ረድኤተ፡ እግዚአብሔር፡ ተዐቅቦ፡ ከመ፡
ኢይደቅ።

፲፮፤ ይቤ፡ ፍርሆ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወተገኀሥ፡
እምኵሉ፡እኩይ፡ይተረጕም፡እስመ፡እግዚአ
ብሔር፡ ኢይሠምር፡ ኀዲገ፡ እከይ፡

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

እንዳትሰነካከል፡ አለ፤ እግዚአብሔርን፡ የሚ
ፈራ፡ ትእዛዞቹን፡ የሚከተል፡ በመንገዶቹ፡
የሚሄድ፡ ሁልጊዜ፡ ሕጉን፡ የሚአስብ፡
እንግዲህ፡ኃጢአቱን፡የሚአስብና፡የሚያምን፡
ይሁን፡ብሎ፡ይተረጕማል።

፲፤ በነቢይ፡አፍ፡ጌታችን፡እንዲህ፡ብሎ፡ተናገረ፡
ሰው፡ኃጢአቱን፡አስቦ፡የሚጸጸት፡ከሆነ፡እኔ፡
ኃጢአቱን፡ እረሳለታለሁ፤ ይቅር፡ እለዋለሁ፡
ይላል፡ እግዚአብሔር፡ በዚህም፡ የመርሳት፡
ትርጓሜው፡ ይቅርታ፡ ነው፤ ኃጢአተኛ፡
በፍጹም፡ ልቡናው፡ ወደ፡ ጌታ፡ ንስሓ፡ ከገባ፡
ዘወትርም፡ የሠራውን፡ አስታውሶ፡ የሚጸጸት፡
ከሆነ፡ንስሓውን፡ተቀብሎ፡ኃጢአቱን፡ያስተሰ
ርይለታል፤ ተመልሶም፡ አያስብበትም፤ እግዚአ
ብሔር፡ይቅር፡ባይ፡መሐሪ፡ነውና። ስለዚህም፡
ራሱ፡ጌታ፡እኔ፡ይቅር፡ባይ፡መሐሪ፡ነኝ፡ብሎ፡
ተናግሮአል።

፲፩፤ መንገድህንም፡ ያቀናልህ፡ ዘንድ፡ ማለቱ፡
ነው፤ ስለዚህ፡ ለነፍስህ፡ የምትጠቅማት፡
የድኅነት፡ መንገድ፡ እንደሆነች፡ ይተረ
ጕማል።

፲፪፤ በደንጊያ፡እግርህ፡እንዳትሰናከል፡ያለውም፡
ይህ፡አንተ፡በትሩፋት፡ሥራ፡ላይ፡የጸናህ፡
እንደሆነ፡ለዘላለሙ፡አትወድቅም፤

፲፫፤ እንዳትሰናከል፡ረድኤተ፡እግዚአብሔር፡የም
ትጠብቅህ፡ትሆናለች፡እንጂ። ሐዋርያው፡እግ
ዚአብሔር፡የተወለደ፡አይበድልም፡እንዳለ።

፲፬፤ ሁለተኛም፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ ይተረጕማል፡
ሰው፡ በፍጹም፡ ልቡናው፡ እግዚአብሔርን፡
የሚወድና፡ሕጉንና፡ትእዛዞቹን፡የሚከተል፡
የሆነ፡ እንደሆነ፡ ከጸጋው፡ ምንም፡ ምን፡
አያጣም።

፲፭፤ በዚህም፡ጸንቶ፡በሚኖር፡መጠን፡እንዳይሰ
ናከል፡ የእግዚአብሔር፡ ረድኤት፡ ትጠብቀ
ዋለች።

፲፮፤ እግዚአብሔርን፡ ፍራው፤ ከክፉ፡ ነገርም፡
ራቅ አለ፤ ይህን፡ ይተረጕማል። እግዚአ
ብሔር፡ ክፉ፤ ነገርን፡ ብቻ መተው፡

በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

ባሕቲታ ፡ ዳእሙ ፡ ሶበ ፡ ጎደግነኒ ፡ ክሂሎ ፡ ንግበር ፡ ሠናየ ። በከመ ፡ ይቤ ፡ ዳዊት ፡ ተገኀሥ ፡ እምኩይ ፡ ወግበር ፡ ሠናየ።

፲፯ ይብል፡ይከውነከ፡ፈውስ፡ለሥጋከ፡ወሥራየ፡ ለአዕፅምቲከ ፡ ይተረጐም ፡ እስመ ፡ ብእሲ ፡ ለእመ፡ኀደገ፡እከየ፡ወገብረ፡ሠናየ፡ይከውን፡ ሥጋሁ፡ውስተ፡ሣኅት፡ወይድኅን፡እምኵሉ፡ ዝብጠት፡ማሕመሚት፡ወእምኀሊና፡እኪት፡ እንተ፡ታሐሥም።

፲፰ ይቤ ፡ አብእ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምፍሬ ፡ ጽድቅከ፡ከመ፡ይምልኣ፡መዛግብቲከ፡ብዙኀ፡ ሥርናየ፡ወወይነ፡ማኀበብቲከ፡ይስፍፍ፤

፲፱ ይተረጐም ፡ ለእመ ፡ አብዝኀ ፡ ብእሲ ፡ ተጸግዎተ ፡ ወአፈድፈደ ፡ ይደሉ ፡ ሎቱ፡ከመ፡ያብእ፡እምኔሁ፡ቍርባነ፡በእንተ፡ ነፍሱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ወየኀ ርዮሙ፡ ለጽኑሳን፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያፈደፍድ ፡ ለዘጸገዎ ፡ ወይመልእ ፡ መዛግብቲሁ፡በከመ፡ይቤ።

፳ ወካዕበ፡ኢያቅድም፡ብእሲ፡ምንተኒ፡እምነ፡ ግብራተ፡ዓለም፡እስከ፡ያቀድም፡መቅድመ፡ ጸሎተ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ወይስእሎ፡ረድኤተ፡ወረባሐ፡ሠናየ።እስመ፡ እግዚአብሔር፡ልዑል፡ለእመ፡ኮነ፡ዝንቱ፡ ሰአለት፡ወአስተብቍዖት፡እምጽኑዪ፡ግዕዝ፡ ይሁብ፡ዘየኀሥሥ።

፳፩ ይቤ ፡ ወልድየ ፡ ኢይሕጽጽ ፡ ልብከ ፡ እምተግሣጸ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይተረጐም ፡ በእንተ፡ዝ፡ከመ፡ለእመ፡ረከበቶ፡ተግሣጽ፡ ለብእሲ፡እምእግዚአብሔር፡ልዑል፡ኢይት አንተል፡ወኢየኀሊ፡ዳእሙ፡ይኩን፡መስተ ዐግሥ ፡ ወአእኳቴ ፡ ከመ ፡ ያስተካዕብት ፡ ላዕሌሁ ፡ ምሕረቶ ፡ በከመ ፡ ገብረ ፡ ላዕለ ፡ ኢዮብ፡ጻድቅ፤

፳፪ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ትዕግሥቶ ፡ ላዕለ ፡ መንሱታት፡መሐሮ፡ወአካዕበተ፡ላዕሌሁ፡ ጸጋሁ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

አይወድም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ በምንተው፡ጊዜ፡መልካም፡ሥራ፡እንሠራ፡ ዘንድ፡ነው፡እንጂ።ዳዊት፡ከክፉ፡ሥራ፡ራቅ፡ በጎውን፡ነገር፡ሥራ፡እንዳለ፤

፲፯፤ ለሥጋህ ፡ ፈውስ ፡ ለአጥንትህም ፡ ድኅነት ፡ ይሆንሃል፡አለ፤ሰው፡ክፉ፡መሥራትን፡ትቶ፡ መልካም፡ቢሠራ፡ሥጋው፡ከችግር፡ከመከራ፡ ያርፋልና ፡ ጽኑ ፡ ከሆነች ፡ ከመቅሠፍት ፡ በትርም፡ነፍስን፡ከምታጠፋ፡ከክፉ፡ኃሳብ፡ ሁሉ፡ይድናል፡ብሎ፡ይተረጉማል።

፲፰፤ ከእውነተኛው፡ከአዝመራህ፡ፍሬ፡ለእግዚአ ብሔር፡አግባ፤ጎተራዎችህ፡ብዙ፡ሥንዴን፡ ፊቀኖችህ፡ወይንን፡ይሞሉ፡ዘንድ፡አለ፤

፲፱፤ ይኸን፡ይተረጉማል፤ሰው፡እጅግ፡ብዙ፡ሀብት፡ ቢአገኝ፡ስለ፡ነፍሱ፡ድኅነት፡ለልዑል፡እግዚአ ብሔር፡መሥዋዕት፡ማቅረብ፡ለእርሱ፡ይገባል፤ ችግረኞችንም፡መርዳት፡ምርጫው፡መሆን፡ ይገባል ፤ መባዐውን ፡ ላቀረበለትና ፡ ለመጸወ ተለት፡ሰው፡እግዚአብሔር፡ጎተራውን፡እህል፡ ማጥኑን፡ወርቅ፡ይሞላለታልና፤

፳፤ ዳግመኛም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ርዳታንና ፡ በጎ ፡ ጥቅምን ፡ በመለመን ፡ ወደ ፡ ልዑል ፡ እግዚአ ብሔር፡ጸሎቱን፡እስከሚአስቀድም፡ድረስ፡ ከዓለማዊ ፡ ተግባር ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አያስ ቀድም ፡ እንዳለ ፡ እንዲሁ ፡ ያለው ፡ ልመና ፡ በንጹሕና ፡ በጠራ ፡ ልቡና ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የሚፈልገውን፡ይሰጠዋል።

፳፩፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሚያመጣው ፡ ፈተና ፡ የተነሣ ፡ ልብህ ፡ ከተስፋው ፡ አይናወጽ፡ አለ ፤ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ፡ ፈተና ፡ ቢአገኘው ፡ ከበጎ ፡ ሥራው ፡ ቸል፡እንዳይልና፡እንዳያስብ፡ስለዚህ፡ይተረ ጉማል ። በጻድቁ ፡ ኢዮብ ፡ ላይ ፡ እንዳደረገ ፡ ቸርነቱን፡አጽፍ፡ድርብ፡ያደርግለት፡ዘንድ፡ የሚታገሥና፡የሚያመሰግን፡ይሁን፡እንጂ።

፳፪፤ በመከራዎቹ ፡ ላይ ፡ ያደረገውን ፡ የኢዮብን ፡ ትዕግሥት ፡ በአየ ፡ ጊዜ ፡ ጸጋውን ፡ አጽፍ ፡ ድርብ፡አድርጎለታልና።

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ፡/ነግህ።

፳፫፤ ይቤ ፡ ዘአፍቀረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጌሥጽ ፡
ይተረጎም ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡
ሶበ፡አእመረ፡አፍቅሮተ፡ብእሲ፡ሎቱ፡እስመ፡
ያሜክሮ ፡ ለሊሁ ፡ ከመ ፡ ያእምር ፡ ትዕግሥቶ ፡
ወይሬስዮ፡አርዓያ፡ለካልኡ፡ከመ፡ይብቊዑ፡
ቦቱ፡ሰብእ፡እስመ፡ለዘርእዮ፡ውስተ፡እንትኩ፡
መከራ፡አእኳቴ፡ለእግዚአብሔር፡በእንተ፡ዝ፡
ይበቊዖ፡ፈድፋደ።

፳፬፤ ይቤ ፡ ብፁዕ ፡ ዘረከበ ፡ ጥበበ ፡ ወዘወሀበ ፡
ምጽዋተ፡ለእለ፡የአምኑ፡በክርስቶስ፡እስመ፡
ይብል፡ዝንቱኬ፡ኮነ፡ይፈቱ፡ከመ፡ይርአይ፡
ዘኮነ ፡ እምዘርእይዎ ፡ መሀይምናን ፡ በክር
ስቶስ፡ወኢርእዩ።

፳፭፤ ወበእንተ ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ እግዚእ ፡ ለአር
ዳኢሁ፡ ብፁዓት ፡ አዕይንቲክሙ ፡ ወእዕዛ
ኒክሙ፡እብለክሙ።

፳፮፤ እስመ፡ብዙኃን፡ነቢያት፡ወጻድቃን፡ፈተዉ፡
ይርአዩ ፡ ዘርኢክሙ ፡ አንትሙ ፡ ወኢርእዩ ፡
ወይስምዑ፡ዘሰማዕክሙ፡ወኢሰምዑ።

፳፯፤ ይቤ፡ይኄይስ፡ኪያሃ፡ተገብሮ፡እመዛግብተ፡
ወርቅ፡ወዕንቍ፡በአማን፡እንከ፡ሃይማኖት፡
በክርስቶስ፡ትኄይስ፡እምኵሉ፡ዘኮነ፡እስመ፡
ይእቲ፡ታበጽሖ፡ለብእሲ፡ኀበ፡ተፍጻሜተ፡
ጸጋ።

ዘሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

ዘሆሴዕ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፭፤፲፫-፲፭።

፲፫፤ ወሐረ ፡ ኤፍሬም ፡ ኀበ ፡ ፋርስ ፡
ወፈነዉ ፡ ተናብልተ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡
ኢያሬም ፡ ወውእቱኒ ፡ ኢክህለ ፡ ፈው
ሶተክሙ ፡ እስከ ፡ ኀልቀ ፡ ሕማም፡ በላዕ
ሌክሙ።

፲፬፤ እስመ ፡ አነ ፡ እከውኖሙ ፡ ከመ ፡ ነምር ፡
ለኤፍሬም፡ወከመ፡አንበሳ፡ለቤተ፡ይሁዳ፡
ወአነ፡እመሥጦሙ፡ወእነሥአሙ፡ወአልቦ፡
ዘያድኅኖሙ።

ረቡዕ መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

፳፫፤ እግዚአብሔር፡የወደደውን፡ይገሥጻል፡አለ፡
ሰው ፡ እርሱን ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡
የሚወደው ፡ መሆኑን ፡ በአወቀ ፡ ጊዜ ፡ ትዕግ
ሥቱን ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ለሌሎችም ፡ አርአያ ፡
ሁኖ ፡ ሰዎች ፡ በአርአያነቱ ፡ ይጠቀሙበት ፡
ዘንድ ፡ በመከራ ፡ ውስጥ ፡ ሁኖ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ ሲአመሰግን ፡ ለሚአየው ፡ ስለዚህ ፡
እጅግ፡ይጠቅማል፡ብሎ፡ይተረጉማል።

፳፬፤ ጥበብን ፡ የአገኘና ፡ በክርስቶስ ፡ ለሚያምኑ ፡
ምዕመናን ፡ የመጸወተ ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡
አለ ፤ ስለዚህ ፡ በክርስቶስ ፡ ከሚያምኑ ፡
ከሚአዩት ፡ ምእመናን ፡ የሚሆነውን ፡ ያይ ፡
ዘንድ፡ወዶ፡አላየም፡ይላልና።

፳፭፤ ስለዚህ ፡ ጌታ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ዓይኖቻ
ችሁና ጆሮቻችሁ ፡ የተመሰገኑ ፡ ንዑዳን ፡
ክቡራን፡ናቸው።

፳፮፤ ብዙዎች፡ነቢያትና፡ጻድቃን፡እናንተ፡የምታ
ዩትን ፡ ሊያዩ ፡ ወደው ፡ አላዩም ፤ የምትሰሙ
ትንም፡ሊሰሙ፡ወደው፡አልሰሙምና፡አለ።

፳፯፤ ወርቅን ፡ ዕንቊን ፡ መናገሻ ፡ ከማድረግ ፡
ይሻላል ፤ በክርስቶስ ፡ የሆነች ፡ ሃይማኖት ፡
ጥበብ ፡ ከሆነው ፡ ሁሉ ፡ በእውነት ፡ ትሻላ
ለችና፡አለ።እርሷ፡ሰውን፡ወደ፡ፍጹም፡ጸጋ፡
ታደርሰዋለችና።

ለእርሱም ፡ ለጌታ ፡ ለዘላለሙ ፡ ክብር ፡
ምሥጋና፡ይሁን፡አሜን።

የነቢዩ ፡ የሆሴዕ ፡ ትንቢት ፡ በረከቱ ፡ ከእኛ ፡
ጋር፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፤፭፤፲፫-፲፭።

፲፫፤ ኤፍሬም ፡ (ንጉሡ) ፡ ርዳኝ ፡ አድኑኝ ፡ ብሎ ፡
ወደ ፡ ፋርስ ፡ ሄደ ፤ ኢያሬም ፡ ወደሚባለውም ፡
ንጉሥ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ፤ እርሱም ፡
መከራው ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ እስኪፈጸም ፡
ድረስ፡እናንተን፡ማዳን፡አልቻለም።

፲፬፤ እኔ፡በዐሥሩ፡ነገድ፡እንደ፡ነምር፡በሁለቱም፡
ነገድ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ እሆንባቸዋለሁና ፡
በሞት ፡ ነጥቄ ፡ እወስዳቸዋለሁ ፤ የሚያድና
ቸውም፡የለም።

Scanned by CamScanner

በ፰፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

መሠወጥ፡ወእሐውር፡ቤትየ፡እስከ፡አመ፡
ያጠፍኡ፡ወየኅሥሡ፡ገጽየ፡በዕለተ፡ምንዳ
ቤሆሙ።

ምዕ፤፮፤፩–፫።

ወይገይሡ ፡ ኀቤየ ፡ ወይብሉ ፡ ንዑ ፡
ንሑር፡ወንትመየጥ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡
አምላክነ።
እስመ፡ውእቱ ፡ ቀሠፈነ ፡ ወይፌውሰነ ፡
ወውእቱ፡አቍሰለነ፡ወይሤርየነ።
ወያሐይወነ፡በሰኑይ ፡ መዋዕል ፡ ወአመሣ
ልስት ፡ ዕለት ፡ ንትነሣእ ፡ ወነሐዩ ፡
በቅድሜሁ፡ ናእምር ፡ ወንዴግን ፡ ከመ ፡
ናእምሮ፡ለእግዚአብሔር፡ ወከመ ፡ ጎህ ፡
ድልው፡ንረክቦ፡ወይመጽእ፡ከመ፡ዝናመ፡
ክረምት፡ዘቀዳሚ፡ወዘደኀሪ፡ላዕለ፡ምድር።

ትርጓሜ፡ትንቢተ፡ሆሴዕ።

ወሖረ፡ኤፍሬም፡እስከ፡ኀበ፡ይብል፡ላዕለ፡
ምድር።

ይቤ፡መተርጕም፡በእንተ፡ፋርስ፡ለኀበ፡
ጸዋዌ፡ናቡከደነፆር፡ሎሙ፡ሶበ፡እምውሳ
ንያተ፡እግዚአብሔር ፡ ወትእዛዛቲሁ ፡
ተራሐቁ፡እሙንቱ፡እስከ፡መጠዎሙ፡ለዕድ
ዋኒሆሙ፡ወአውጽአሙ፡እምርስቶሙ።
ይቤ፡ፈነወ፡ተናብልተ፡ኀበ፡ንጉሥ፡
ወውእቱ ፡ ኢክህለ ፡ ፈውሶተክሙ ፡
ወኢኀልቀ፡ሕማም፡እምኔክሙ፡ይተረጐም፡
በእንተ፡ዝ፡እስመ፡ብእሲ፡ለእመ፡ወጽአ፡
እምውሣንያተ፡እግዚአብሔር፡ ወተለወ፡
ካልአ፡እንዘ፡የኀሥሥ፡ረድኤተ፡እምዕጓለ፡
እመሕያው፡ ፈድፋደ፡እምእግዚአብሔር፡
እስመ፡ውእቱ፡ያንጌጊ፡ወይከውን፡ልቡ፡
ዘይዜክር፡ዘኮነ፡ውስቴቱ፡ቀዲሙ፡ወኢይ
ረክብ፡ሎቱ፡ፍሥሓ።
ወለእመ፡ኮነ፡ተድላ፡ዓለም፡ያዐርፆ፡
እምዝንቱ፡እስመ፡ኢትፈቅድ፡ነፍሱ፡ዝክተ፡
ወኢትፈቱ፡ይእቲሰ፡ከመ፡ትፃእ፡እም
ሥርዓታ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት/ነግህ።

፲፩፤ ጨርሰው፡እስኪጠፉ፡ድረስ፡በመከራቸው፡ቀን፡
ገጹ፡ረድኤቴን፡እስኪፈልጉ፡ድረስ፡ተመልሼ፡
ወደ፡ቤቴ፡(ወደ፡ሰማይ)፡እሄዳለሁ፡አለ።

ምዕ፤፮፤፩–፫።

፩፤ ወደ፡እኔ፡ይገሠግሣሉ፤ወደ፡ፈጣሪያችን፡
ወደ፡እግዚአብሔር፡ኑ፡እንሂድ፤እንመለስ፡
ይላሉ።
፪፤ እርሱ፡በመከራ፡ገርፎናልና፡ይፈውሰናል፤
እርሱም፡በመከራ፡አቍስሎናልና፡ያድነናል።
፫፤ ሲያድነንም፡በሁለት፡ቀን፡ነው፤በሦስተ
ኛውም፡ቀን፡ድነን፡በሱ፡ፊት፡እንነሣለን፤
እግዚአብሔርንም፡አውቀን፡እንከተለው፡
ዘንድ፡እንደ፡ጎህም፡የተዘጋጀ፡ሆኖ፡እናገኘ
ዋለን፤ወደዚህም፡ዓለም፡እንደ፡ኋለኛውና፡
እንደፊተኛው፡ዝናም፡ሆኖ፡ይመጣል።

የሆሴዕ፡ትንቢት፡ትርጓሜ።

ኤፍሬም፡ወደ፡ፋርስ፡ሄደ፡ከሚለው፡ጀምሮ፡
በምድር፡ላይ፡እስከሚለው፡ድረስ።

፩፤ እግዚአብሔር፡ ከወሰነላቸው፡ ከሕጉ፡
ከትእዛዙ፡እነርሱ፡በራቁ፡ጊዜ፡ከርስታቸው፡
አስወጥቶ፡ለጠላቶቻቸው፡እስከ፡ሰጣቸው፡
ድረስ፡በናቡከደነጾር፡እጅ፡ወደ፡ፋርስ፡ስለ፡
አስማረካቸው፡ተርጓሚው፡ተናገረ።
፪፤ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ መልክተኛን ፡ ላከ ፤ እር
ሱም ፡ ያድናችሁ ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፤
መከራ፡ከእናንተ፡አልተፈጸመም፡አለ።
ሰው ፡ እግዚአብሔር፡ ከወሰነለት ፡ ሕግ ፡
ወጥቶ ፡ ከእግዚአብሔር፡ ይልቅ ፡ ከሰው ፡
ዘንድ፡ርዳታ፡እየፈለገ፡ሌላውን፡የተከተለ፡
እንደሆነ፡እርሱ፡ይቅበዘበዛልና፡ልቡም፡
አስቀድሞ፡በውስጡ፡የነበረውን፡ያስባል፡
እንጂ፡የድል፡አድራጊነት፡ተድላ፡ደስታን፡
አያገኝም።
፫፤ ዓለማዊ፡ተድላ፡ከዚህ፡የሚለየው፡ቢሆንም፡
ነፍሱ ፡ ይህን ፡ አትሻምና ፡ እርሷም ፡
ከሥርዐቷ፡ ትወጣ ፡ ዘንድ ፡ አትወድምና ፡
በፈቃደ፡ነፍሱ፡ይጸና፡ሲል፡ይተረጐማል።

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግሀ።

፱፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ እከውኖ ፡ ከመ ፡ ነምር ፡
ለኤፍሬም ፡ ወከመ ፡ አንበሳ ፡ ለቤተ ፡ ይሁዳ ፡
ይትረጐም፡ከመ፡ብእሲ፡ዘይወድቅ፡ውስተ፡
አፈ፡አንበሳ፡መሣጢ፡ኢይድኅን፡እምኔሁ፡
እስከ፡ያሀጕሎ፡ከማሁኬ፡ይቤ፡ነቢይ፡ከመ፡
እግዚአብሔር፡ይፌኑ፡ላዕሌሆሙ፡መዐቶ፡
አምጣነ፡ሀለዉ፡ላዕለ፡ዝንቱ፡ወኢይድኅኑ፡
እመቅሠፍቱ።

፲፡ ይቤ፡እትመዐዕ፡ላዕሌሆሙ፡በፍኖተ፡ፋርስ፡
ከመ፡አንበሳ፡ምምዕት፡ይትረጐም፡በእንተ፡
ዝንቱ፡እስመ፡አምጣነ፡ውፁአኒሆሙ፡እም
ውሳንያተ፡እግዚአብሔር፡ሖሩ፡ውስተ፡
ዘኢኮነ፡ፍኖቱ። ወይፌኑ፡ላዕሌሆሙ፡ኵላ፡
ዝብጠተ፡መምዋቲተ።

፲፩፡ እስመ፡ይቤ፡ውእቱ፡አነ፡እነሥኦሙ፡ወእመ
ሥጦሙ፡ይትረጐም፡ከመ፡ውእቱ፡ይፌኑ፡
ላዕሌሆሙ፡ሞተ፡ድንቀተ፡ወአልቦ፡ዘያነ
ግፎሙ፡ወያድኅኖሙ፡እምእዴሁ፡በውእቱ፡
ጊዜ፡ወለእመኒ፡ዐውየዉ፡ኢይተዌከፍ፡
እምኔሆሙ፡ወኢይሰምዖሙ።

፲፪፡ ይቤ፡እሠወጥ፡ወአሐውር፡ውስተ፡ቤትየ፡
ይትረጐም፡ከመ፡ውእቱ፡ይመይጥ፡ገጾ፡
እምኔሆሙ፡ወይትገሐሥ፡እምኀቤሆሙ፡
እስከ፡አመ፡ይጠፍኡ፤

፲፫፡ ይቤ፡ወየኀሥሡ፡ገጽየ፡በምንዳቤሆሙ፡
ወይገይሡ፡ኀቤየ፡እንዘ፡ይብሉ፡ንሖር፡
ንትመየጥ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡አምላክነ፡
ይትረጐም፡እስመ፡እሉ፡ሕዝብ፡በእንተ፡
እከየ፡አልባቢሆሙ፡ወኢኮኑ፡ዘየኀሥሥዎ፡
ለእግዚአብሔር፡ወኢየዐወይዉ፡ቦቱ፡
ዘእንበለ፡እምድኅረ፡ዝብጠት፡ማሕመሚት፡
ከመ፡ዘፈነወ፡ላዕሌሆሙ፡አክይስተ፡መምዋ
ትያተ፡በገዳም፡እስመ፡እምንዳቤ
ዘረከቦሙ፡ዐውየዉ፡ኀበ፡ሙሴ፡ወይቤሉ፡
ንሕነ፡ኃጥአን፡ቅድመ፡እግዚአብሔር፡ወበ
ለአሌተ፡ሙሴ፡ምስለ፡ተአምኖ፡ኃጣው
ኢሆሙ፡ፈወሶሙ፡በከይሲ፡ዘብርት።

፲፬፡ ይቤ፡እስመ፡ውእቱ፡ቀሠፈነ፡ወውእቱ፡

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግሀ።

፱፡ ለኤፍሬም፡እንደ፡ነብር፡ለይሁዳ፡ወገን፡እንደ፡
አንበሳ፡እሆናለሁ፡አለ፤በነጣቂ፡አንበሳ፡አፍ፡
የወደቀ፡ሰው፡እስከሚበላው፡ድረስ፡ከአን
በሳው፡አፍ፡የመዳን፡ተስፋ፡እንደሌለው፡
እንደዚሁ፤በዚህ፡በኃጢአታቸው፡ጸንተው፡
በሚኖሩበት፡መጠን፡እግዚአብሔር፡መዐቱን፡
በላያቸው፡እንደሚልክ፡ከመቅሠፍቱም፡እንደ
ማይድኑ፡ይተረጐማል።

፲፡ እንደ፡ተጣላች፡አንበሳ፡በፋርስ፡መንገድ፡
በእነሱ፡ላይ፡እቈጣለሁ፡አለ፤እግዚአብሔር፡
ከወሰነላቸው፡ሕግ፡ወጥተው፡የእርሱ፡
መንገድ፡ባልሆነ፡በመሄዳቸው፡መጠን፡የም
ታጠፋቸውን መቅሠፍት፡ሁሉ፡በላያቸው፡
ይልካልና፡ስለዚህ፡ይተረጐማል።

፲፩፡ በሞት፡ነጥቄ፡እወስዳቸዋለሁ፡አለ፡
በእነርሱ፡ላይ፡ድንገተኛ፡ሞትን፡እንዲልክ፡
በዚያን፡ጊዜ፡ከእጁ፡የሚአድናቸው፡የሚዝ
ግላቸው፡እንደሌለ፡ቢጮኹም፡ከእነርሱ፡
ልመናቸውን፡እንደማይቀበልም፡ጩኸታቸ
ውንም፡እንደ፡ማይሰማ፡ይተረጐማል።

፲፪፡ ወደ፡ቤቴ፡ተመልሼ፡እሄዳለሁ፡አለ፡እሱ፡
እስከሚጠፉ፡ድረስ፡ከእነርሱ፡ገጸ፡
ረድኤቱን፡እንደሚመልስ፡ከእነሱም፡እንደ
ሚርቅ፡ይተረጐማል።

፲፫፡ እንሂድ፤ወደ፡ፈጣሪያችን፡ወደ፡እግዚአ
ብሔር፡እንመለስ፡እያሉ፡በመከራቸው፡ገጸ፡
ረድኤቱን፡ይሻሉ፡አለ፤እነዚያ፡ወገኖች፡ስለ
ልቡናቸው፡ክፋት፡እግዚአብሔርን፡የሚፈ
ልጉት፡አልሆኑምና፡ጽኑ፡መከራ፡ከደረሰ
ባቸው፡በኋላ፡ነው፡እንጂ፤ያለዚያ፡ወደእርሱ፡
አይጮኹም፤የሚገድሉ፡እባቦችን፡በበረኻ፡
እንደላከባቸው፡ከደረሰባቸውም፡መከራ፡
የተነሣ፡እኛ፡በእግዚአብሔር፡ፊት፡ኃጢአ
ተኞች፡ነን፡ብለው፡ወደ፡ሙሴ፡ጮኸዋልና፡
ኃጢአታቸውን፡ከማመናቸው፡ጋራ፡በሙሴ፡
ልመና፡ከናስ፡በተሠራ፡እባብ፡እንደ
ፈወሳቸው፡ይተረጐማል።

፲፬፡ እርሱ፡በመከራ፡ገረፈን፤እርሱም፡መልሶ፡

ይሜርየነ፡ወውእቱ፡ይፈውሰነ፡ይተረጐም፡
ከመ፡ሶበ፡ነስሑ፡በእንተ፡ኃጣውኢሆሙ፡
ወተመይጡ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡በኵሉ፡
አልባቢሆሙ፡ወተአመኑ፡ቦቱ፡በእግዚአ
ብሔር፡ወበምጽአቱ፡ለመድኀኒነ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ።
፲ አስመ፡ይቤ፡ያነግፈነ፡እምድኅረ፡ሰኑይ፡
መዋዕል፡ወአመ፡ሣልስት፡ዕለት፡ያነሥአነ፤
ይተረጐም፡ከመ፡ነበሩ፡እሙንቱ፡እንዘ፡
ይሴፈውዎ፡ለክርስቶስ፡እስመ፡እግዚእ፡
ክርስቶስ፡አስተርአየ፡አመ፡ሣልስ፡ሺሕ፡
(፴፱)፡ዘውእቱ፡እምዓመታተ፡አብርሃም፡
እስመ፡እሙንቱ፡ነበሩ፡በሕማመ፡ግብርናት፡
ውስተ፡ሰኑይ፡ዕለታት፡ወእሉ፡እሙንቱ፡
ክልኤቱ፡ሽሐት፡ዓመታት፡ወአመ፡ሣልስ፡
አግዐዞሙ፡እግዚእ፡ክርስቶስ፡ወአንሥአሙ፡
እምድቀታተ፡ኃጢአት።
፲፩ ይቤ፡ወነሐዩ፡በቅድሜሁ፡ዘው
እቱ፡በእግዚእ፡ክርስቶስ፡ዘአምነ፡ወተለወ፡
ትእዛዛቲሁ፡ኢይመውት፡እምድኅሬሁ፡
በሞተ፡ኃጢአት፡በከመ፡ይቤ፡እግዚእነ፡
በወንጌል፡ዘአምነ፡ብየ፡ኢይሬእዮ፡ለሞት፡
ይተረጐም፡በእንተ፡ውእቱ፡ሞታ፡ለነፍስ፡
ዘበዕልወት።
፲፪ ይቤ፡ናእምር፡ወንዴግን፡ከመ፡ናእምሮ፡
ለእግዚአብሔር፡ይተረጐም፡እሙንቱ፡
እምከመ፡አምኑ፡ቦቱ፡አእመሩ፡ከመ፡
ዝንቱ፡ውእቱ፡ዘያመልክዎ፤ወውእቱ፡
መድኀን፡ወአልቦ፡ባዕድ፡አምላክ፡ዘእን
በሌሁ።
፲፫ ወዛቲ፡ረብሐ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡
ለመሀይምናን፡እለ፡በክርስቶስ፡እስመ፡
ለሊሃ፡ትሜህሮሙ፡ከመ፡ዝንቱ፡
ውእቱ፡አምላክ፡ወበእንቲአሁ፡ይቤ፡
ጳውሎስ፡ሐዋርያ፡አልቦ፡ዘይክል፡
መኑሂ፡ከመ፡ይበል፡ክርስቶስ፡ውእቱ፡
ወእግዚእ፡ዘእንበለ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡
ባዕሌሁ።
፲፬ ይቤ፡ከመ፡ጎህ፡ድልወ፡ንረክቦ፡ይተረ
ጐም፡እስመ፡በከመ፡ይሰድዶ፡ጎህ፡





ያድነናል ፤ ይፈውሰናል ፡ አለ ፤ ንስሐ ፡
ገብተው፡ ስለ ፡ ኃጢአታቸውም ፡ እንደ ፡
ተጸጸቱ፡በፍጹም፡ልቡናቸው፡ወደ፡እግዚአ
ብሔር፡እንደ፡ተመለሱ፡በመድኃኒታችን፡
በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡መምጣትና፡በእግዚአ
ብሔር፡እንዳመኑ፡ይተረጎማል።
፲፤ ከሁለት ፡ ቀኖች ፡ በኋላ ፡ ያድነናል ፤ በሦስተ
ኛውም፡ቀን፡ያነሣናል፡አለ፤እነርሱ፡የጌታ፡ክር
ስቶስን፡መምጣት፡ተስፋ፡እያደረጉ፡እንደ፡ኖሩ፡
ይተረጎማል፤ጌታ፡ክርስቶስ፡በሦስተኛው፡ሺህ፡
በሥጋ፡ተገልጦአልና፡ይኸውም፡ከአብርሃም፡
ዘመን፡ጀምሮ፡ያለው፡ነው፤እነርሱ፡በሁለቱ፡
ዕለታቶች በግዞት ፡ መከራ ፡ ውስጥ ፡ ነበሩና ፡
እነዚህ፡ሁለት፡ቀኖች፡ሁለት፡ሺሕ፡ዓመታት፡
ናቸው ፡ በሦስተኛውም ፡ ሺሕ ፡ ጌታችን ፡
ክርስቶስ፡ ነጻ ፡ እንዳወጣቸውና ፡ ከድቀተ ፡
ኃጢአትም፡እንዳነሣቸው፡ይተረጎማል።
፲፩፤ በፊቱ፡እንድናለን፡አለ፤ይኸውም፡በጌታ፡
ክርስቶስ ፡ የአመነ ፡ ትእዛዛቱን ፡ የጠበቀ ፡
አይሞትም፤በሥጋ፡ከሞተ፡በኋላ፡በነፍሱ፡
የኃጢአት ፡ ሞት ፡ አይሞትም ፤ ጌታችን ፡
በወንጌል ፡ ያመነብኝ ፡ ሞትን ፡ አያየውም ፡
እንዳለ ። ይህ ፡ ስለ ፡ ክህደት ፡ የሚደረግ ፡
የነፍስ፡ሞት፡እንደ፡ሆነ፡ይተረጎማል።
፲፪፤ እግዚአብሔርንም፡እውቀን፡እንከተለዋለን፡
አለ ፤ እነርሱ ፡ እንዳመኑበት ፡ አምልኮት ፡
የሚገባው ፡ ፈጣሪያቸው ፡ እርሱ፡ መሆኑን ፡
እንዳወቁ ፤ እርሱም ፡ የዓለም ፡ መድኃኒት ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ከእርሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡
እንደ፡ሌለ፡ይተረጎማል።
፲፫፤ ይችም ፡ በክርስቶስ ፡ ለሚያምኑ ፡ ምእመናን ፡
የምትጠቅም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸጋ ፡ ናት ፡
እርስዋም ፡ ጌታ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ታስተምራቸዋለችና ፡ ስለ ፡ እርሱም ፡
ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ካደረበት ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ ክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡
ገዥና ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ ማንም ፡
የሚችል፡የለም፡ብሎ፡እንደ፡ተናገረ።
፲፬፤ እንደ፡ንጋት፡ብርሃን፡የተዘጋጀ፡ሆኖ፡እናገኘ
ዋለን ፡ አለ ፤ የንጋት ፡ ብርሃን ፡ ጨለማን ፡

Scanned by CamScanner

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ። | ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ። |
|---|---|
| ለጽልመት ፡ ከማሁኬ ፡ ሃይማኖትኒ ፡ ዘበክርስቶስ ፡ ታዋኪ ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ሰብእ ፡ ወትሰድድ ፡ እምኔሁ ፡ ጽልመተ ፡ እበድ። | እንዲያርቅ ፡ እንደዚሁም ፡ በክርስቶስ ፡ የምትሆን ፡ ሃይማኖት ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ታበራለች፤ ከእርሱም ፡ የድንቁርና ፡ ጨለማን ፡ ታርቃለች። |
| ፲፩፡ ወበእንተ ፡ ውእቱኬ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ብርሃኑ ፡ ለዓለም ፡ ወአንሶሰዉ ፡ በብርሃን፡እንዘብክሙ፡ብርሃን። | ፲፩፡ ስለዚህም ፡ ጌታችን ፡ እኔ ፡ የዓለም ፡ ብርሃን ፡ ነኝ፤ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ብርሃን ፡ ሳለላችሁ ፡ በብርሃን ፡ ተመላለሱ ፡ ብሎ ፡ ይተረጉማል። |
| ፲፪፡ ወይቤ ፡ ካዕበ ፡ እስመ ፡ ብርሃን ፡ ምስሌክሙ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ። በአማንኬ ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ውእቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘበአማን ፡ ወውእቱ ፡ ዘያበርሀ፡አልባቢሆሙ፡ለእለ፡የአምኑ፡ቦቱ። | ፲፪፡ ሁለተኛም ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኖራል ፡ አለ ። በእውነት ፡ መቸም ፡ መቸ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሚያምኑበት ፡ በልቡናቸው ፡ ውስጥ ፡ የሚያበራ ፡ እውነተኛ ፡ ብርሃን ፡ ነው። |
| ፲፫፡ ይቤ ፡ ወይመጽእ ፡ ከመ ፡ ዝናም ፡ ዘቀዳሚ ፡ ወዘደኃሪ ፡ ዛቲ ፡ ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ልደቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ ወበእንተ ፡ ትንሣኤሁ ፡ እምነ ፡ ምውታን ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ዳዊት ፡ ነቢይ ፡ ወይወርድ ፡ ከመ ፡ ዝናም። | ፲፫፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ፊተኛውና ፡ እንደ ፡ ኋለኛው ፡ ዝናም ፡ ሁኖ ፡ ይመጣል ፡ አለ፤ ይች ፡ ትንቢት ፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ልደትና ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ስለ ፡ ተነሣባት ፡ ትንሣኤው ፡ ናት፤ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ዝናም ፡ ይወርዳል ፡ እንዳለ። |
| ፲፬፡ ወከመ ፡ ዝናም ፡ ያመጽእ ፡ ምሥጢረ ፡ መንክረ፡ ከማሁ ፡ ኮነ ፡ ምጽአቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ እምድንግል ፡ በምሥጢር ፡ ዐቢይ ፡ ቀዳሚ። | ፲፬፡ ዝናምም ፡ ድንቅ ፡ ምሥጢርን ፡ እንደሚያመጣ ፡ እንዲሁ ፡ ጌታ ፡ አስቀድሞ ፡ ከድንግል፡ መወለዱ ፡ በማይመረመር ፡ በታላቅ፡ምሥጢር፡ሆነ። |
| ፲፭፡ ወመንክር ፡ ትንሣኤሁ ፡ ደኃሪ ፡ በምሥጢር ፡ መንክር ፡ ዘኢይትዐወቅ ፡ እፎ ፡ ዘእንበሌሁ ፡ ባሕቲቱ። | ፲፭፡ በኋላም ፡ ከእርሱ ፡ ከብቻው ፡ በቀር ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ በማይታወቅ ፡ ድንቅ ፡ በሆነ ፡ ምሥጢር፡መነሣቱ፡ነው። |
| ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እስከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን። | ለእርሱም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ክብር ፡ ምሥጋና ፡ ይሁን፡አሜን። |

| ክፍል፡፪። ሃይማኖተ፡አበው። | ክፍል፡፪። የአባቶች፡ሃይማኖት። |
|---|---|
| ምዕ፡፺፩፡፩–፲፮። | ምዕ፡፺፩፡፩–፲፮። |
| ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለእስክንድርያ ፡ በጠማረ ፡ መልእክቱ ፡ ኀበ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአንጾኪያ፤ | የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ በላከው ፡ መልእክቱ፡እንዲህ፡አለ። |
| ፩፡ አአምን ፡ ከመ ፡ ቃል ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ፡ዋሕድ፡ ዘተወልደ፡እመለኮተ፡እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ዘእንበለ ፡ ጥንት ፡ ወኢመዋዕል ፡ ፈጣሬ ፡ ዓለም ፡ ዘቦቱ ፡ ኮነ ፡ ሀልዎተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ በብዝኀ ፡ ሣህሉ ፡ ሰበ ፡ መሐረ ፡ ትውልደ ፡ አዳም ፡ አጽንኖ ፡ ሰማያተ ፡ ወወረደ ፡ ኀቤነ ፡ እንዘ ፡ ኢይት | ፩፡ በቅድምና ፡ የነበረ ፡ ቃል ፡ ጥንት ፡ ሳይኖረው ፡ ዘመን ፡ ሳይቀድመው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ አካል ፡ ዘእምአካል ፡ ባሕርይ ፡ ዘእምባሕርይ ፡ የተወለደ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ዓለምን ፡ የፈጠረ ፡ የሁሉ ፡ መኖር ፡ በእርሱ ፡ የሆነ ፡ በይቅርታው ፡ ብዛት ፡ የአዳምን ፡ ልጆች ፡ ይቅር ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ከምላቱ ፡ ሳይወሰን ፡ ከአብ ፡ ባሕርይ ፡ ሳይለይ ፡ |

ፋለስ ፡ ወእንዘ ፡ ኢይትፈለጥ ፡ እመለ
ኮት፡አብ።

፲፩ ወነደረ ፡ ውስተ ፡ ከርሣ ፡ ለንጽሕት ፡
ማርያም ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ወትረ ፡
ወእምድመ ፡ ድግልናሃ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ፈጠረ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡
ዘከመ ፡ አርአየነ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡
ወለባዊት ፡ ማእምርት ፡ እምዘርዐ ፡
አብርሃም ፡ ወከመዝ ፡ ኮነ ፡ ቃል ፡
ሥጋ ፡ ወነደረ ፡ ላዕሌነ ፡ በተዋ
ሕዶተ ፡ ህላዌ ፡ አካል ፡ ወተወክፈ ፡
አርአያ ፡ ዚአነ ፡ ዘእንበለ ፡ ውላጤ ፡
ወኢትድምርት ፡ ወነበረ ፡ ርቱዐ ፡
ዘእንበለ ፡ ውላጤ ፡ ወኢቱስሕት ፡
በመለኮቱ።

፲፪ ወዓዲ ፡ አመ ፡ ነሥአ ፡ ዘዚአነ ፡ ወኮነ ፡
ሰብአ ፡ በእንቲአነ ፡ ኢሐፀ ፡ ህላዌ ፡
መለኮቱ ፡ ወለዘሂ ፡ ነሥአ እምህላ
ዌነ ፡ ረሰዮ ፡ ሎቱ ፡ በሥርዓት ፡
ዘኅብረት ፡ ወተዋሕዶ ፡ ሕላዌ ፡ ወአካል ፡
ወዘአልቦቱ ፡ ጥንት ፡ ወኢመዋዕል ፡ ወኢ
ሥጋ ፡ ዘውእቱ ፡ እምእግዚአብሔር ፡
አብ ፡ ለሊሁ ፡ ዓዲ ፡ በህላዌሁ ፡ ተሠገወ ፡
ወተወልደ፡ዳግመ፡ልደተ፡እምድንግል፡በዘ
ኢይረከቦ፡ልቡና።ወበእንተዝ፡ነበረት፡ዓዲ፡
ወላዲቱ፡ድንግለ፡ዘበአማን።

፲፫ ወንሕነ፡ነአምራ፡ወነአምን፡ከመ፡ይእቲ፡
ወለደት፡አምላከ፡ዘበአማን፡ወዘኒ፡ተወልደ፡
እምኔሃ፡ሥግወ፡አምላክ፡ፍጹም፡በህላዌሁ፡
ወሰብእ፡ፍጹም።

ወኪያሁ፡ነአምር፡ከመ፡ውእቱ፡አሐዱ፡
ህላዌ፡ወአሐዱ፡አካል፡እምክልኤቱ፡
ህላዌያት።ወእምድኅረ፡ትሥጉትሂ፡አሐዱ፡
ወልድ፡ወአሐዱ፡እግዚእ፡ውእቱ፡እንዘ፡ኢይ
ትዌለጥ፡ውስተ፡ሥላሴ፡ራብዓይ፡ጉልቍ።

፲፬ ወውእቱ ፡ ኢሐማሚ ፡ እስመ ፡ ይት
ዔረይ ፡ ለአብ ፡ በመለኮት ፡ ወንሌብዎ ፡
ሐሙመ ፡ በሥጋ ፡ ሶበ ፡ ኮነ ፡ እምህላዌነ ፡





ልዑል ፡ ባሕርዩን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ባሕርያ
ችንን፡እንደ፡ተዋሐደ፡አምናለሁ።

፲፩፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ንጽሕት ፡ ድንግል ፡ በምትሆን ፡
በድንግል ፡ ማርያም ፡ ማሕፀን ፡ እንደ ፡ አደረ ፡
ከአብርሃም ፡ ከተገኘ ፡ በድንግልና ፡ ከጸና ፡
ባሕርይዋ ፡ የምታውቅ ፡ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡
ያለችው ፡ የእኛን ፡ ሥጋ ፡ የሚመስል ፡
የአዳምን፡ ሥጋ ፡ በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ሊዋሐደው ፡ እንደ ፡ ፈጠረ ፡ አምናለሁ ።
እንዲህ፡ቃል፡ሥጋ፡ሆነ፡በባሕርይ፡በአካል፡
ተዋሕዶ ፡ ከሥጋችን ፡ ሥጋን ፡ ከነፍሳችን ፡
ነፍስን ፡ ነሥቶ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሰው ፡ ሆነ ። ያለ ፡
መለወጥ ፡ ያለ ፡ መጠፋፋትም ፡ እኛን ፡
መምሰልን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጎ ፡ ያለ ፡ መለወጥ ፡
ያለ፡መቀላቀል፡በባሕርዩ፡ጸንቶ፡ኖረ።

፲፪፡ የእኛን ፡ ባሕርይ ፡ ነሥቶ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሰው ፡
በሆነ፡ ጊዜም ፡ ባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ አልተለ
ወጠም ፡ ከእኛ ፡ ባሕርይ ፡ የነሣውን ፡ ሥጋም ፡
በተዋሕዶ ፡ ምሥጢር ፡ በባሕርይ ፡ በአካል ፡
ተዋሕዶ፡ገንዘብ፡አደረገው፤ጥንት፡የሌለው፡
ዘመን ፡ ያልቀደመው ፡ ሥጋም ፡ ያልነበረው ፡
ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የተወለደ ፡ እርሱ ፡
በተለየ፡አካሉ፡ሰው፡ሆኖ፡ልቡና፡በማይመረ
ምረው ፡ ምሥጢር ፡ ዳግም ፡ ልደትን፡
ከድንግል ፡ ተወለደ ። ስለዚህም ፡ እናቱ ፡
በእውነት፡በድንግልና፡ጸንታ፡ኖረች።

፲፫፡ እኛም ፡ እውነተኛ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክን ፡
እንደ፡ ወለደች ፡ አውቀን ፡ እናምናለን፤ ሰው ፡
ሁኖ ፡ ከእርስዋ ፡ የተወለደውም ፡ በባሕርይ ፡
ፍጹም፡ አምላክ፡ፍጹም፡ሰው፡ነው።
ከሁለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ከሁለት፡
አካል፡አንድ፡አካል፡እንደ፡ሆነ፡እርሱን፡እና
ውቃለን፤ሰውም፡ከሆነ፡በኋላ፡እሱ፡በሦስተ
ኛነት፡ዐራተኛ፡ቍጥር፡ሳይጨምር፡አንድ፡
ልጅ፡አንድ፡ገዥ፡ነው።

፲፬፡ እርሱም ፡ የማይታመም ፡ ነው ፡ በመለ
ኮት ፡ ከአብ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነውና ፤ ባሕ
ርያችንንም ፡ በተዋሐደ ፡ ጊዜ ፡ በሥጋ ፡

Scanned by CamScanner

### በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

እስመ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢሐመ ፡
በህላዌ፡ መለኮቱ ፡ ወባሕቱ ፡ ሐመ ፡ ከማነ ፡
በአርአያ ፡ ሥጋ ፡ ዘውእቱ ፡ አሐዱ ፡ እምህ
ላዌነ።
፲፭ ወናሁ ፡ ዐቀመ ፡ ዘንተ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ነባቤ ፡
መለኮት፡እንዘ፡ይብል፡ውእቱ፡ሐማሚ፡በት
ስብእት ፡ ወውእቱ ፡ ይገብር ፡ መንክራተ ፡
በህላዌሁ ፡ ወከማሁ ፡ ዓዲ ፡ ይትዌከፍ ፡
ሕማማተ ፡ በህላዌሁ ፡ ወበፈቃዱ ፡ ረሰየ ፡
ሕማመነ፡ሕማመ፡ዚአሁ፡ዘአልቦቱ፡ነውር፡
ዘበሥርዐት ፡ በሥጋ ፡ ሐማሚ ፡ ወመዋቲ ፡
ዘውእቱ፡እምህላዌነ፡ዘቦቱ፡ነፍስ፡ወልቡና፡
ወንባብ።
፲፮ ወእብል፡ከመ፡ውእቱ፡ሐመ፡እሙነ፡ወአኮ፡
በምትሐት ፡ በሥጋሁ ፡ ዘድልው ፡ ከመ ፡
ይሕምም ፡ ወበፈቃዱ ፡ ተዐገሠ ፡ ሕማማተ ፡
እንተ፡አልባቲ፡ነውር፡ወኢ፡ሐሜት።
በረከቱ፡ለዝንቱ፡መምህር፡የሀሉ፡ምስሌነ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

### ተግሣጽ፡ዘይትነበብ፡
### በዕለተ፡ረቡዕ፡ዘነግህ።

፩ አ ፡ ለዝንቱ ፡ ግዝፈተ ፡ ክሣድ ፡ ዐቢይ ፡
ወለዝንቱ ፡ ሕዝብ ፡ አብድ ፡ ወለጽንዐ ፡
ቅንአቶሙ፡ወለብዝኀ፡እበዶሙ፡ወዑረተ፡
ልበሙ።
፪ ሰማዕክሙ ፡ እፎ ፡ ይትዋቀሥዎ ፡ በእ
ንተ ፡ ብዝኀ ፡ ተአምራት ፡ ወይትማከሩ ፡
ለቀቲሎቱ።
፫ ርኢክሙኑ፡ዘይቤ፡ቀያፋ፡ይኄይሰነ፡ከመ፡
ይሙት፡አሐዱ፡ብእሲ፡በእንተ፡ሕዝብ፡እም
ይትሀጐል፡ኵሉ፡ሕዝብ።
፬ ወለእመ፡ኀደግናሁ፡ንሕነ፡ከመ፡ዝ፡ናሁ፡
አሉ፡ኵሉ፡የአምኑ፡ቦቱ።
፭ ርኢክሙኑ፡እፎ፡አንሥአ፡ሎሙ፡ሙታነ፡
እምድር፡ወአቀመ፡ሕሙማነ፡ወረሰየ፡ዐይነ፡
ለዕውራን ፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ገብሩ ፡
ላዕሌሁ፡እኩየ፡ከመዝ።

### ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

እንደ፡ታመመ፡እናውቃለን፤የእግዚአብሔር፡
ቃል ፡ በባሕርዩ ፡ መለኮቱ ፡ አልታመመምና፡
እኛን፡በሚመስል፡ከባሕርያችን፡ጋራ፡አንድ፡
በሚሆን፡በሥጋ፡እንደ፡እኛ፡ታመመ፡እንጂ።
፲፭ አንድነትን ፡ ሦስትነትን ፡ የተናገረ ፡ ጎርጎ
ርዮስ ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ ይታመማል ፡
በባሕርዩ፡ ታምራትን ፡ ያደርጋል ፤ በባሕርዩ፡
መከራን ፡ ይቀበላል ፤ በፈቃዱም ፡ ሕይወት፡
ዕውቀት፡ቃል፡ባለው፡ሕመም፡ሞት፡በሚስ
ማማው ፡ ሥጋ ፡ የተሠራ ፡ ሥርዐት ፡ እንደ፡
መሆኑ ። ሕማማችንን ፡ ነውር ፡ የሌለበት፡
የእርሱ ፡ ሕማም ፡ አደረገው ፡ ብሎ ፡ እነሆ፡
ይህን፡አስረዳ።
፲፮ ይታመምበት ፡ ዘንድ ፡ በተገባ ፡ በሥጋ፡
በሐሰት ፡ ያይደለ ፡ በእውነት ፡ እንደታመመ፡
እናገራለሁ ፤ ነውር ፡ ነቀፋና ፡ መታማት፡
የሌለበት፡መከራን፡በፈቃዱ፡ተቀበለ፤የዚህ፡
መምህር ፡ በረከት ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

### በዕለተ፡ረቡዕ፡በነግህ፡
### የሚነበብ፡ተግሣጽ።

፩ ለዚህ ፡ ለደነደነ ፡ ክሣደ ፡ ልቡና ፡ ለዚህም፡
ደንቆሮ ፡ ሰነድ ፡ ሕዝብ ፡ ለቅናታቸውም፡
ጽናት፡ለድንቍርናቸው፡ብዛትና፡ለአእምሮ
አቸው፡መደንዘዝ፡ወዮታ፡ይገባል።
፪ ብዙ ፡ ስለሆነ ፡ ተአምራቱ ፡ እንዴት ፡ እንደ፡
ተከራከሩት፡እርሱንም፡ለመግደል፡እንዴት፡
እንደ፡ተማከሩ፡ሰምታችኋል።
፫ ቀያፋ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ከሚጠፋ ፡ አንድ፡
ሰው ፡ ቢሞት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብንገድል፡
ይሻለናል።
፬ እኛ፡ብንተወው፡እነዚህ፡ሁሉ፡እነሆ፡ያምኑ
በታል፡ያለውን፡ሰምታችኋልን?
፭ ሙታኖችን ፡ ከመቃብር ፡ እንዳስነሣላቸው፡
ሕሙማንን፡እንዳዳነ፡ለዕውራንም፡ዐይንን፡
እንደ፡ፈጠረላቸው፡አያችሁን?ከዚህ፡ሁሉ፡
በኋላ፡በእርሱ፡ላይ፡እንዲሁ፡ክፉ፡ሠሩ።

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ፡/ነግህ።

ሰሎሙ፡እኮ፡ይእዜ፡ዝንቱ፡ላዕሌሆሙ፡ወእ
ሮሆሙ፡ቅሩብ፡ወአኮ፡ድንቀት፡ለርእ
ሆሙ።

እሙ፡ቀዳሚ፡ገብረ፡ተአምረ፡በቅድ
ሚሆሙ፡ለግብጽ፡ወፈነወ፡ጸልዐ፡ዲበ፡
ፀሮሙ፡ወአመንደበ፡ልበ፡ለፈርዖን፡
ወማቀያ፡ለሀገር፡በይእቲ፡ዝብጠት፡
ለጽብት።

ጊዜ፡ወለጠ፡ማዮሙ፡ደመ፡ወጊዜ፡
ግቀዮሙ፡በቈርነናዓት፡ወጊዜ፡በጽ
ልመት፡ጊዜ፡በጽንጽንያ፡ከልብ፡ዘእን
በለዝ።

ወእምድኅሬሁ፡ነፈቀ፡ባሕረ፡በቅድ
ሚሆሙ፡ወጼሐ፡ሎሙ፡ፍኖተ፡ማይ፡
ወወሰዶሙ፡ማእከለ፡ማዕምቅ፡ወአስተ
ኃብአ፡ባሕረ፡ዲበ፡ፀሮሙ፤ወሴሰዮሙ፡
በበድው፡ኅብስተ፡ሠናየ፡ወአንቅዐ፡
እምኰኵሕ፡ጽኑዕ፡ማየ፡ወጸለሎሙ፡
መዐልተ፡በደመና፡ወኵሎ፡ሌሊተ፡በብርሃነ፡
እሳት።

ወእምድኅረ፡ዝንቱ፡ኵሉ፡ሀብት፡
ዝብሩ፡ሎሙ፡ስብኮ፡ላሕም፡ወሰገዱ፡
ሎቱ፡በገጸሙ፡ወአቅረቡ፡ሎቱ፡
ቍርባኖሙ።

ወይቤሉ፡በበይናቲሆሙ፡ነዋ፡አማ
ልክቲከ፡እስራኤል፡እለ፡አውጽኡከ፡
እምድረ፡ግብጽ።

ወኮኑ፡ይጸውሩ፡ግልፍዋተ፡በውስተ፡ፍኖት፡
ወይሰግዱ፡ሎሙ፡በኀቡእ።

ወኢይትመየጡ፡እምእከዮሙ፡ወኢይት
ከልኡ፡እምጌጋዮሙ።

ሰሙ፡ሰማዕኩ፡ዘይቤ፡ሙሴ፡እንዘ፡
ይገሥጾሙ፡ወይዘልፍ፡ዕልወቶሙ፡ወኢተእ
ንተለ፡እምዐመፃሆሙ፡ወአስምዐ፡ግዝፈተ፡
ከግጾሙ፡እንዘ፡ይብል።

ኦ፡ትውልድ፡ዕሉት፡ወግፍትዕት፡ከመዝኑ፡

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

፮፤ ነገር፡ግን፡ይህ፡ከፋታቸው፡በእነርሱ፡ላይ፡
ዛሬ፡የሆነ፡አይደለም፤ምንጊዜም፡ለእነርሱ፡
ቅርብ፡ነው፡እንጂ፤በሽምግልናቸው፡
ድንገት፡የመጣ፡ነገር፡አይደለም።

፯፤ ቀድሞም፡ቢሆን፡በግብጻውያን፡ፊት፡
ተአምራት፡አድርጓልና፡በጠላቶቻቸው፡በግ
ብጻውያን፡ላይ፡ቍስልን፡አመጣ፤የፈርዖ
ንንም፡ልብ፡አስጨነቀ፤በዚችም፡ጭንቅ፡
በሆነች፡መቅሠፍት፡አገሪቱን፡መታት።

፰፤ ውኃቸውን፡ለውጦ፡ደም፡በአደረገ፡ጊዜ፡በጓ
ጉንቸርም፡በአሠቃየቸው፡ጊዜ፡
በጨለማም፡በአሠቃያቸውጊዜ፡ከዚህም፡
ሌላ፡በውሻ፡ዝንብ፡በአሠቃያቸው፡ጊዜ።

፱፤ ከዚህ፡በኋላ፡በፊታቸው፡ባሕሩን፡ከፍሎ፡
ውኃ፡በነበረበት፡መንገድን፡ጠረገላቸው፤
በጥልቁም፡መካከል፡አሻገራቸው፡
ባሕሩንም፡በጠላቶቻቸው፡ላይ፡መለሰ
ባቸው፤በበረሃም፡መልካም፡እንጀራን፡
መገባቸው፤ጽኑ፡ከሆነ፡አለትም፡ውኃን፡አፈ
ለቀላቸው፤ቀን፡በደመና፡ጋረዳቸው፡መላ፡
ሌሊቱንም፡በእሳት፡ብርሃን፡መራቸው።

፲፤ ከዚህ፡ሁሉ፡ስጦታ፡በኋላ፡ለራሳቸው፡በጥጃ፡
አምሳል፡ጣዖት፡ሠሩ፤በግንባራቸውም፡
ተደፍተው፡ሰገዱለት፤መሥዋዕትም፡አቀረ
ቡለት።

፲፩፤ እርስ፡በርሳቸውም፡እስራኤል፡ሆይ!
ከግብጽ፡ምድር፡ያወጡህ፡አማልክቶችህ፡
እነሆ፡ተባባሉ።

፲፪፤ ጣዖቶቻቸውን፡በመንገድ፡ተሸክመው፡
በመሄድ፡በሥውር፡ይሰግዱላቸዋል።

፲፫፤ ከክፋታቸው፡አይመለሱም፤ከበደላቸውም፡
አይከለከሉም።

፲፬፤ ነገር፡ግን፡ሙሴ፡ሲገሥጻቸውና፡ከዳታቸውን፡
ሲዘልፍ፡ያላቸውን፡ስማ፤ዐመፃቸውን፡
ከመዝለፍ፡ቸል፡አላለም፤የክሣደ፡ልቡናቸ
ውንም፡ድንዳኔ፡እንዲህ፡ብሎ፡አዳኘባቸው።

፲፭፤ ከዳተኛ፡ወንጀለኛ፡ግልብጥብጥ፡ትውልድ፡

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

ተዐሰይዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አ ፡ ሕዝብ ፡
እብድ ፡ ወአኮ ፡ ጠቢብ ። እፎኑ ፡ ከመ
ዝኑ ፡ ትግብር ፡ አኮኑ ። ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡
አቡከ ፡ ወሊቅከ ፡ ዘውእቱ ፡ ፈጠረከ ፡ ወገ
ብረከ ፡ ወባረከ ፡ ላዕሌከ ፡ ወዐቀበከ ፡ ከመ ፡
ብንተ ፡ ዐይን ፡ ወጾረከ ፡ ዲበ ፡ እንግድ
ዓሁ ፡ ከመ ፡ ንስር ፡ ወሰወረከ ፡ በጽላሎተ ፡
ክነፊሁ።
፲፮፡ ወሴሰየከ ፡ እክለ ፡ ገራውህ ፡ ወአውጽአ ፡
ለከ ፡ መዐረ ፡ እምኰኵሕ ፡ ወቅብዐ ፡ እም
እብን ፡ ጽንዕት ፡ ወሐሊበ ፡ እምዕጐልት ፡ ወአ
ጽገበከ ፡ እምሥብሐ ፡ አባግዕ ፡ ወሐ
ራጊት ፡ ወአሥዋር ፡ ሥቡሐን ፡ ወበደመ ፡
ቀምሕ።
፲፯፡ ወሶበ ፡ በላዕከ ፡ አ ፡ ያዕቆብ ፡ ወጸገብከ ፡
ወገዘፍከ፡ወከበርከ፡ወከበድከ፡ረሳዕከ፡ለእግ
ዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ዘፈጠረከ ፡ ወርኀቀ ፡
እምእግዚአብሔር፡መድኃኒትከ።
፲፰፡ ወወሀኩኒ፡በዝ፡ነኪር፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ወአ
ምዕዑኒ፡በአማልክቲሆሙ፡ወሦዑ፡ደቂቆሙ፡
ወአዋልዲሆሙ፡ለአጋንንት፡ወትቀንዩ፡ለአማ
ልክት፡እለ፡ኢየአምሩ፡አበዊሆሙ።
፲፱፡ ወርእየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወቀንአ ፡
ወተምዐ ፡ መዐተ ፡ ላዕለ ፡ ደቂቆሙ ፡ ወአ
ዋልዲሆሙ።
፳፡ ወይቤ ፡ እመይጥ ፡ ገጽየ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወእሬ
እዮሙ ፡ ዘይከውኑ ፡ በደኃሪቶሙ ፡ እስመ ፡
ውሉድ ፡ ዐላውያን ፡ እሙንቱ ፡ ወግፉቱዓን ፡
ውሉድ፡እለ፡አልቦሙ፡ሃይማኖት።
፳፩፡ ወአምዕዑኒ ፡ በአማልክቲሆሙ ፡ ወወሀኩኒ ፡
በግልፎሆሙ።
፳፪፡ ወአነ ፡ አቀንአሙ ፡ በዘኢይሴብዉ ፡ ሕዝብ ፡
ወአምዕዖሙ፡በሕዝብ፡እብድ።
፳፫፡ እስመ ፡ እሳት ፡ ትነድድ ፡ እመዐትየ ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

ሆይ! ለእግዚአብሔር፡እንዲህ፡ያለ፡ወረታ፡ትመ
ልሱለታላችሁን? ይህ ፡ ወገን ፡ ጥበብ ፡ የሌለው፡
አላዋቂ፡ሰነፍ፡ነው፤እንዴት፡እንዲህ፡ትሠራለህ?
የፈጠረህ ፡ ፈጣሪህ ፡ ያስገኘህ ፡ አባትህ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ አይደለምን ? ያከበረህ ፡ እንደ ፡ ዐይን፡
ብሌን ፡ የጠበቀህ ፡ እርሱ ፡ አይደለምን? በዩረቱ፡
ተሸከመህ፤ንስርም፡ግላግሎቹን፡በክንፉ፡እንዲ
ሰውር፡በክንፈ፡ረድኤቱ፡ሰወረህ።
፲፮፡ የእርሻውን ፡ (የኩዳዱንም) ፡ እህል ፡ መገበህ፤
ከአለትም ፡ ማርን ፡ አወጣልህ ፤ ከጸናች ፡
ደንጊያም ፡ ቅባትን ፡ ከጊደርም ፡ ወተትን ፡
ከሰቡት ፡ በጎችና ፡ ሽህሮች ፡ ስብን ፡ ከሰቡ ፡
በሬዎች ፡ (ላሞችም) ፡ ያጠገበህ ፡ አይደለምን?
የወይኑንም፡ዘለላ፡ደም፡አጠገበህ።
፲፯፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ! በልተህ ፡ በጠገብክ ፡ ጊዜ፡
በወፈርክ ፡ በከበርክ ፡ በገዘፍክና ፡ በከበድክ፡
ጊዜ ፡ የፈጠረህን ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔርን፡
ረሳኸው፤ከአዳኝህ፡እግዚአብሔርም፡ራቅህ።
፲፰፡ በዚህ፡በጣዖቱ፡አሳዘኑኝ፤ወንዶችና፡ሴቶች፡
ልጆቻቸውን ፡ ለአጋንንት ፡ ሰዉ ፤ አባቶቻ
ቸውም ፡ ለማያውቋቸው ፡ ጣዖታት ፡ ተገዙ፡
አለ።
፲፱፡ እግዚአብሔርም ፡ ይህን ፡ አይቶ ፡ ለአምላ
ክነቱ፡ ቀና ፤ በወንዶች ፡ ልጆቻቸውና ፡
በሴቶች፡ልጆቻቸው፡ላይ፡ቁጣን፡ተቆጣ።
፳፡ ከእነርሳቸው ፡ ገጸ ፡ ረድኤቴን ፡ እመልሳለሁ፤
እነዚህ፡ግልብጥብጦች፡ሃይማኖት፡የሌላቸው፡
ወንጀለኞች ፡ ትውልድ ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመናቸው፡
ምን፡እንደሚሆኑ፡አያቸዋለሁ፡አለ።
፳፩፡ እነርሱ ፡ በአማልክቶቻቸው ፡ አሳዘኑኝ፤በጣዖ
ታቸውም፡አወኩኝ።
፳፪፡ እኔንም ፡ ያጠፉናል ፡ ብለው ፡ ልብ ፡ በማያደር
ጓቸው ፡ ዋዘኞች ፡ አስቀናቸዋለሁ ፤ ሰነፍ ፡
በሆነ፡ሕዝብም፡አሳዝናቸዋለሁ።
፳፫፡ ከመዐቴ፡የተነሣ፡እሳት፡ትነዳለችና፡በነበልባ

ወትበልዕ፡ለምድር፡በነበልባላ፡ወታውዒ፡
መሠረታተ፡አድባር።
ወትትአኀዝ፡እኩየ፡ወሙስና፡ዲቤሆሙ፡ወእፌኑ፡
ላዕሌሆሙ፡ወውስቴቶሙ፡አሕጻ፡መዐት።

ወይትመሰዉ፡በረኀብ፡ወይከውኑ፡
መብልዐ፡ለአዕዋፈ፡ሰማይ፡ወለአውስት፡
ዘኢይደኀብ።
ወእፌኑ፡ስነነ፡አናብስት፡ወሕምዘ፡እፍዖት፡
ዘይደብእ።
ወእመኒ፡ጕዩ፡ያኀልቆሙ፡ሰይፍ፡በፍርሃት፡
ወረኃብ፡እምውስጥ፡ወአኃጕል፡ወራዙተ፡
ወደናግለ፡ወጠባዊተ፡ምስለ፡አረጋዊ፡
ብሉይ።
ወለእመ፡ኮነ፡ለውእቶሙ፡ሶበ፡ገሠፆሙ፡
ወኢሰምዑ፡ገብረ፡ዲቤሆሙ፡ዘንተ፡ኵሎ፡
ሥቃየ፡ወአብልዖሙ፡ኅብስቶሙ፡በአንብዕ፡
ወረሰዮሙ፡መብልዐ፡ለአናብስት፤ወፈነወ፡
ዲቤሆሙ፡አሕዛበ፡ጽኑዓነ፡ልብ፡ወጽል
ሐዋነ፡ወሰደዶሙ፡እምውስተ፡ዐጸደ፡
መቅደሱ።

ወአርሐቆሙ፡እምጸጋሁ፡ወዘረዎሙ፡
ውስተ፡ምድር፡ወረሰየ፡ስሞሙ፡ነገረ፡
ወመርገመ።
ሶበሰ፡ለእሉ፡እለ፡ተሰብአ፡ለመድኃኒቶሙ፡
ወሐመ፡ከመ፡ይባልሖሙ፡እምፀሮሙ፡ሶበ፡
ወለጡ፡ክብሮሙ፡ወገደፉ፡ሥርዐተ፡ሕጎሙ፡
ወሐሩ፡በፍትወተ፡ልቦሙ፡ወተመሰሉ፡ከመ፡
አሕዛብ፡በምግባሮሙ፡ደለዎሙ፡ዘመጠነዝ፡
ኀሳር፡ወኀፍረት።

መፍትውኬ፡እ፡አኃው፡ከመ፡ንትነሣእ፡እም
ኃኬትነ፡ከመ፡ንትባላህ፡ወንንበር፡በጸጋሁ፡
ለእግዚእነ።

ዘሎቱ፡ክብር፡ወስብሐት፡እስከ፡ለዓለም፤
አሜን።

ምንተኑ፡በል

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡
በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡



ልዋም፡ምድርን፡ትበላታለች፤የተራሮ
ችንም፡መሠረት፡ታቃጥላለች።
፳፱፤ አስከፊ፡የሆነውን፡መቅሠፍት፡ሁሉ፡
በላያቸው፤የመዓት፡ፍላጻ፡በውስጣቸው፡
እልክባቸዋለሁ።
፳፰፤ በረኃብም፡ያልቃሉ፤ለሰማይ፡ወፎችና፡ለማ
ይጠግብ፡ጥንብ፡አንሳ፡አሞራ፡መብል፡
ይሆናሉ።
፳፪፤ የሚገድል፡የእፉኝት፡መርዝንና፡የሚያደቅ፡
የአንበሶችን፡ጥርስ፡እልክባቸዋለሁ።
፳፪፤ ከፍርሃት፡የተነሣ፡ቢሸሹም፡ሰይፍ፡ይፈጽማ
ቸዋል፤ከውስጥም፡ረኃብ፡ጎልማሶቹን፡
ደናግሉን፡የምትጠባውን፡ከአረጀው፡
ሽማግሌ፡ጋር፡አጠፋለሁ።
፳፫፤ እነዚህንም፡መከሮና፡ገሥጾአቸው፡
ባልሰሙ፡ጊዜ፡ይህን፡ሁሉ፡ሥቃይ፡
በላያቸው፡ላከባቸው፤እንጀራቸውንም፡
ከእንባ፡ጋራ፡አበላቸው፤ለአንበሶችም፡
ሲሳይ፡አደረጋቸው፤ጨካኞችና፡ተንኰ
ለኞች፡የሆኑ፡አሕዛብን፡በእነሱ፡ላይ
አስነሥቶ፡ከመመስገኛው፡ከኢየሩሳሌም፡
አስወጥቶ፡ሰደዳቸው።
፳፱፤ ከጸጋው፡አራቃቸው፤በምድር፡ሁሉ፡
በተናቸው፤ስማቸውንም፡ተረትና፡መሣለ
ቂያ፡አደረገ።
፴፤ ለእነርሱ፡ለድኅነታቸው፡ሰው፡ሁኖ፡ከጠላ
ታቸው፡ያድናቸው፡ዘንድ፡መከራ፡በተቀበለ
ላቸው፡ጊዜ፡ክብራቸው፡የሚሆን፡አምል
ኮቱን፡በለወጡ፡ጊዜ፡ሕጉንና፡ሥርዓቱን፡
ጥለው፡በሥራቸው፡ሁሉ፡አሕዛብን፡መስለው፡
ልባቸው፡በወደደው፡ሥራ፡በጸኑ፡ጊዜ፡ይህን፡
ያህል፡ፍርድና፡ኃፍረት፡የተገባቸው፡ሆኑ።
፴፩፤ ወንድሞች፡ሆይ፡ከስንፍናችን፡ተነሥተን፡
በጌታችን፡ድነን፡በጸጋው፡እንኖር፡ዘንድ፡
ይገባናል።

ለዘላለም፡ክብር፡ምስጋና፡ለእርሱ፡የሚሆን፤
ይሁን፡ይደረግ።

ምንተኑ፡በል፡

ልመናዋ፡በረከቷ፡በእኛ፡ላይ፡ለዘላለሙ፡
ይደርብንና፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡

Scanned by CamScanner

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግሀ። | ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግሀ። |
| --- | --- |
| ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን። | የጸናች፡አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመቤታችን፡ማርያም፡ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው። |
| ፩፤ ወሀለወት ፡ እሐቲ ፡ ሐመር ፡ ዘተሐውር ፡ ማእከለ፡ባሕር፤ | ፩፤ በባሕር ፡ መካከል ፡ የምትጓዝ ፡ አንዲት ፡ መርከብ፡ነበረች። |
| ፪፤ ወጸልመ፡ላዕሌሃ፡መዐልት፡ወጸንዐ፡ነፋስ፡ ወተቈጥዐ ፡ ባሕር ፡ ወተለዐለ ፡ ማዕበል ፡ ወቀብጹ፡ሕይወቶሙ፡እለ፡ሀለዉ፡ውስቴታ፡ ወአልጸቁ ፡ ለመዊት ፡ ወለስጥመት ፡ ወለሙስና። | ፪፤ በእርሷም ፡ ላይ ፡ የቀኑ ፡ ብርሃን ፡ ጨለመ፤ ከነፋሱ፡ጽናት፡የተነሣ፡ባሕሩ፡ታወከ፤ማዕበሉም ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ፤ በውስጥዋም፡ያሉት፡ሁሉ፡የመዳን፡ተስፋቸውን፡ቆረጡ፤ስጥመው፡ለመሞትና፡ለመጥፋት፡ደርሰው፡ነበር። |
| ፫፤ ወጸርሁ፡ኵሎሙ፡ለለአሐዱ፡አሐዱ፡ኀበ፡ አምላኮሙ፡ወአስተብቍዑ። | ፫፤ ሁሉም፡እያንዳንዳቸው፡ወደ፡አምላካቸው፡ እየጮኹ፡ማለዱ፤ለመኑ። |
| ፬፤ ወሀሎ፡እሐዱ፡ብእሲ፡ኄር፡ዘያፈቅራ፡ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡በኵሉ፡ልቡ። | ፬፤ በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡ አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመቤታችን፡ ማርያምን ፡ በፍጹም ፡ ልቡ ፡ የሚወዳት ፡ አንድ፡ደግ፡ሰው፡ነበረ። |
| ፭፤ ወሶበ፡ርእየ፡ኵሉ፡እንዘ፡ያንቀዓዱ፡ኀበ፡ አምላኩ ፡ ቀንአ ፡ ቅንአተ ፡ መንፈሳዊተ ፡ ወሐመየሙ ፡ ወገሠፆሙ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ለምንት፡ኢተኀሥሡ፡ረድኤተ፡እምእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡ ወላዲተ፡አምላክ፡እስመ፡ይእቲ፡ገባሪተ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት ፡ ወአፍጣኒት ፡ ወሰማዒት፡እምኵሎሙ፡ቅዱሳን። | ፭፤ ሁሉም፡ወደ፡አምላኩ፡አንጋጦ፡ሲለምን፡በአየ፡ ጊዜ፡መንፈሳዊ፡ቅንዓትን፡ቀንቶ፡ገሠፃቸው፤ በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡ወደ፡ጸናች፡ አምላክን፡ወደ፡ወለደች፡ወደ፡ክብርት፡እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ለምን፡ ርዳታ ፡ አትሹም፤ እርስዋ፡ከቅዱሳን፡ሁሉ፡ድንቅ፡ድንቅ፡ተአምራትን ፡ የምታደርግ ፡ ፈጥና ፡ የምትደርስ ፡ ልመናን፡የምትሰማ፡ናትና፡አላቸው። |
| ፮፤ ወበይእቲ ፡ ጊዜ ፡ ጸለዩ ፡ ኀበ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ገባሪተ፡ተአምራት። | ፮፤ በዚያችም ፡ ጊዜ ፡ ተአምራትን ፡ ወደምታደርግ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ ወደጸናች ፡ ወደ ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም፡ ለመኑ። |
| ፯፤ ወእምድኅረ ፡ ሰአሉ ፡ ሠሉስ ፡ መዋዕለ ተመንደቡ፡ወእምዝ፡ይቤሉ፡ብዕዕት፡አንቲ፡ እ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ወንጽሕት ፡ ይደልወኪ፡ኵሉ፡ስብሐት፡እስመ፡ሠረቀ፡ ብርሃን፡እምኔኪ፡ወፀሐየ፡ጽድቅ፡ዝ፡ውእቱ፡ አምላክነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሰአሊ፡ለነ፡ ኀቤሁ፡በእንተ፡ሕዝብ፡ወካህናት፡ፈድፋደ፡ ወበእንተ፡አንስት፡ጸልዪ፡ወአስተብቍዒ፡ እስመ፡ሠናይት፡ወረዳኢት፡ለዘይጼውዓኪ። | ፯፤ ሦስት፡ቀን፡ያህል፡ከለመኑ፡በኋላ፡ተጨነቁ፤ ከዚህም፡በኋላ፡እንዲህ፡አሉ፤ የተመሰገንሽ፡ እመቤታችን ፡ ሆይ ፡ ንጽሕት ፡ ክብርት ፡ የምትሆኚ፡ፍጹም፡የሆነ፡ምሥጋና፡ክብር፡ ይገባሻል፤ እውነተኛ ፡ ብርሃን ፡ እውነተኛ ፡ ፀሐይ፡ከአንቺ፡ተገኝቷልና፤ይኸውም፡ፈጣሪያችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ነው፤ ስለ፡ሕዝቡ፡ ስለ ፡ ካህናቱ ፡ ስለ ፡ ሴቶችም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አብዝተሽ ፡ ለምኝልን ፤ አንቺ ፡ ለሚጠራሽ፡ ሁሉ፡ሰምተሽ፡የምትረጂ፡ርኅርኅት፡ነሽና። |

በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

፰ ወሶበ፡ፈጸሙ፡ዘንተ፡ጸሎተ፡ናሁ፡ብርሃን፡
ዐቢይ፡ወረደ፡መልዕልተ፡ሐመር፡ወሰደዶ፡
ለጽልመት፡ወሀድአ፡ነፋስ፡ወአርመመ፡
ማዕበል፡ወመዋግደ፡ባሕር፡ወሠረቀ፡
ብርሃን፡ፀሐየ፡መዐልት።

፱ ወርእዩዎን፡ለደሰያት፡ወበጽሑ፡ኀበ፡
መርሶ፡ወድኅኑ።

፲ ወእምድኅረ፡ወረዱ፡ኀበ፡ፈቀዱ፡ነገርዎሙ፡
ለሰብእ፡ኵሎ፡ዘረከቦሙ፡ወዘከመ፡አድኀ
ኖሙ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡በ፪ኤ፡
ማርያም፡(ማሪሃም)፡መስተሣህልት፡ወአብ
ርሃት፡ሎሙ፡ውስተ፡ጽልመት፡ወበከመ፡
አድኀነቶሙ፡እምንዳቤ።

፲፩ ወሰብሕዎ፡ለእግዚአብሔር፡ኵሎሙ፡ሰብአ፡
ሀገር፡ወወደስዋ፡ለእግዝእትነ፡ማርያም፡
(ማሪሃም)።

፲፪ ወይቤሉ፡አንቲ፡በአማን፡ተዐብዩ፡
እምኵሎሙ፡ቅዱሳን፡ወለኪ፡ይደሉ፡
ስብሐት፡ወክብር፡እ፡እመ፡ክርስቶስ።

፲፫ ወንሕነኒ፡ናስተበቍዓኪ፡ከመ፡ትስአሊ፡በእ
ንቲአነ፡ከመ፡ይምሐረነ፡ወይሣሃለነ፡
በሣህሉ፡ወበምሕረቱ፡ለኵልነ፡ሰማዕያን፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ወኵሉ፡ሥርዐቱ፡ከመ፡ቀዳሚ።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
በብእሲ፡ዘየሐምም፡በሕማመ፡ዝልጋሴ፡
ወጽሙም፡ውስተ፡ሀገረ፡እልህዳር፡ሣህሉ፡
ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

፩ ወበአሐቲ፡ዕለት፡እንዘ፡የሐውር፡እግዚእነ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በምድረ፡እልህዳር፡ርእየ፡
ብእሴ፡ዝልጉሰ፡ወሕሙመ፡እንዘ፡ያስቆቁ፡
ወይበኪ፡አልዒሎ፡አዕይንቲሁ፡ውስተ፡
ሰማይ፡ሰፊሖ፡እደዊሁ፡ወይቤሎ፡እግዚእ፡
ኢየሱስ፡ምንት፡ያበክየከ፡አ፡ብእሲ፡እንዘ፡
ሀሎ፡መድኅንከ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ። 

፰፤ ይህን፡ጸሎት፡በፈጸሙ፡ጊዜ፡እነሆ፡ታላቅ፡
ብርሃን፡በመርከቡ፡ላይ፡ወረደ፡ጨለማ
ውንም፡አስወገደው፤ነፋሱም፡ጸጥ፡አለ፡
ማዕበል፡ሞገዱም፡ጸጥ፡አለ፡የፀሐይ፡
ብርሃንም፡ወጣ።

፱፤ ደሴቶቹንም፡አዩአቸው፡ከስጥመትም፡
ድነው፡ወደ፡ወደቡ፡ደረሱ።

፲፤ ወደ፡ፈለጉትም፡ቦታ፡ከወረዱ፡በኋላ፡የደረሰ
ባቸውን፡ሁሉና፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡
በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡ይቅር፡ባይ፡
ክብርት፡እመቤታችን፡ማርያም፡(ማሪሃም)፡
እንዳዳነቻቸው፤ለሰዎች፡ተናገሩ።

፲፩፤ የሀገሩም፡ሰዎች፡እግዚአብሔርን፡አመሰ
ገኑት፤አከበሩት፤እመቤታችን፡ማርያምንም፡
(ማሪሃምንም)፡አመሰገኑዋት።

፲፪፤ በእውነት፡አንቺ፡ከቅዱሳን፡ሁሉ፡በላይ፡
ነሽ፤የክርስቶስ፡እናት፡ሆይ፡ላንቺም፡ክብር፡
ምሥጋና፡ይገባል፡አሉ።

፲፫፤ የሰማነውን፡ሁላችንን፡በይቅርታውና፡
በቸርነቱ፡ፈጽሞ፡ይቅር፡ይለን፡ዘንድ፡ስለ፡
እኛ፡እንድትለምኚልን፤እኛም፡እንማልድ
ሻለን፤ለዘላለሙ፡አሜን።

ሥርዓቱ፡ሁሉ፡እንደ፡ፊተኛው፡ነው።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡ለዘላለሙ፡ከእኛ፡ጋር፡
ይኑርና፡ጌታችን፡ፈጣሪያችን፡መድኃኒ
ታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በቢስ፡ገላ፡
ቊስል፡በታመመና፡በደነቈረ፡ሰው፡ላይ፡
እልህዳር፡በሚባል፡አገር፡ያደረገው፡ድንቅ፡
ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፤ በአንዲት፡ቀን፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
እልህዳር፡በሚባል፡ሀገር፡ውስጥ፡ሲሄድ፡
በቢስ፡ገላ፡ቊስል፡የታመመ፡ዓይኖቹን፡
ወደ፡ሰማይ፡አቅንቶ፡እጆቹን፡ዘርግቶ፡
እየጮኸ፡ሲያለቅስ፡አገኘው፡ጌታ፡
ኢየሱስም፡አንተ፡ሰው፡መድኃኒትህ፡እያለ፡
ለምን፡ታለቅሳለህ?አለው።

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

፩ ወቀርበ፡ኀቤሁ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ወአንበረ፡
እዴሁ፡ዲበ፡ልሳኑ፡ወተናገረ፡ሶቤሃ፡ወሰገደ፡
ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡
ወይቤሎ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡
እግዚአብሔር።

፪ ወይቤሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ምንተ፡ትፈቅድ፡
ይእዜ፡ሑር፡በሰላም።

፫ ወይቤሎ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ እግዚእየ ፡
ተሣሃለኒ፡ እስመ ፡ ኮንኩ ፡ ትዕይርተ ፡ ማእከ
ሌሆሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ወአልቦ ፡ ዘያበልዐኒ ፡
እምኔሆሙ ፡ ኀብስተ ፡ ዳእሙ ፡ ይሰድዱኒ ፡
በእንተ ፡ ቍስልየ ፡ ወኢይቀርቡ ፡ ኀቤየ ፡
ለግሙራ ፡ እስመ ፡ አልብየ ፡ አዕዳው ፡
ወአእጋር።

፬ ወይቤሎ ፡እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ሑር ፡ ኀበ ፡
ኵኵሕ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምኔሁ ፡ ነቅዐ ፡ ማይ ፡
ዘይሰመይ ፡ ስሙ ፡ ስልዋን ፡ ወሀየ ፡ ኀፅብ ፡
ሥጋከ፡ሠለስተ፡ጊዜ፡እንዘ፡ትብል፡ለለኵሉ
ኀፅበት ፡በስመ፡አብ፡ አሚን ፡በስመ፡ወልድ፡
አሚን ፡በስመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሕይወት ፡
ዘለዓለም፡አሚን።

፭ ወዝንቱ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ኵሉ ፡ ዘውስተ ፡
ሰማያት፡ወምድር።

፮ ወሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወክብር ፡ ወአኰቴት ፡
ወዕበይ፡ለዓለም።

፯ ወለእመ፡ገበርከ፡ዘንተ፡ተሐዩ፡እምደዌከ።

፰ ወበጊዜሃ ፡ ሖረ ፡ ውእቱ ፡ ኀበ ፡ ነቅዐ ፡ ማይ ፡
ዘስልዋን ፡ ወገብረ ፡ በከመ ፡ አዘዞ ፡እግዚእ ፡
ኢየሱስ።

፱ ወሐይወ ፡ ሶቤሃ ፡ ወወፅአ ፡ ኀበ ፡ ጉባኤሆሙ ፡
ለአይሁድ።

፲ ወሶበ ፡ ርእይዎ ፡ ሕያዎ ፡ ይቤልዎ ፡ መኑ ፡
ፈወሰከ ፡ ወይቤሎሙ ፡እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡
መድኃኔ፡ዓለም፡ ፈወሰኒ።

፲፩ ወይቤልዎ ፡ ማእዜ ፡ ፈወሰከ ፡ ወይቤሎሙ ፡
ፈወሰኒ፡ወአሕየወኒ፡በዕለተ፡ሰንበት።

፲፪ ወይቤሉ ፡ አይሁድ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ዝንቱሰ ፡
ሠዓሬ፡ሰንበት፡ውእቱ፡ወአብጠለ፡ሕገ፡ወበእ

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

፩ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡
እጁን ፡ በአንደበቱ ፡ ላይ ፡ አደረገ ፤ ወዲያውኑ ፡
ተናገረ ፤ከጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ እግር ፡ በታችም ፡
ሰገደ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡
አንተ፡ነህ፡አለው።

፪ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ትፈልጋለህ፤
በሰላም፡ሂድ፡አለው።

፫ ያም ፡ ሰው ፡ በእስራኤል ፡ መካከል ፡ መቀጣ
ጠቢያ ፡ ሁኛለሁና ፡ ከእርሳቸው ፡ ውስጥ ፡
ቁራሽ፡እንጀራ፡የሚያበላኝ፡የለምና፡አቤቱ፡
ይቅር ፡ በለኝ ፡ ስለ ፡ ቍስሌም ፡ ያበሩኛል ፡
እንጂ፡ ወደ ፡ እኔም ፡ ከቶ ፡ የሚቀርብ ፡ የለም፤
እጅና፡እግር፡የለኝምና።

፬ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ስሙ ፡ ስልዋን ፡ የሚባል ፡
ውኃ ፡ ወደሚመነጭበት ፡ ዓለት ፡ ሂድ ፡
ከዚያም ፡ በእጥበትህም ፡ ሁሉ ፡በአብ ፡ ስም ፡
አሜን ፡በወልድ ፡ ስም ፡ አሜን ፡ ሕይወት ፡
በሚሆን ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ ለዘላለሙ፡
አሜን ፡ እያልክ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሰውነትህን፡
እጠብ፡አለው።

፭ ይህም ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ላለው ፡ ሁሉ፡
ፍጻሜ፡ነው።

፮ ለእርሱም ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ጌትነት ፡
ለዘላለሙ፡ይገባል።

፯ ይህንንም ፡ ካደረግህ ፡ ከደዌህ ፡ ትድናለህ፡
አለው።

፰ ወዲያውኑ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ስልዋን ፡ የውኃ፡
ምንጭ ፡ ሄደ ፤ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ እንዳዘዘው፡
አደረገ።

፱ ያን ፡ ጊዜም ፡ ዳነ ፤ ወደ ፡ አይሁድም ፡ ጉባኤ፡
ወጣ።

፲ ድኖ ፡ በአዩትም ፡ ጊዜ ፡ ማን ፡ አዳነህ ፡ አሉት፡
እርሱም ፡ የዓለም ፡ መድኃኒት ፡ ጌታችን ፡
ኢየሱስ፡ አዳነኝ፡አላቸው።

፲፩ እነርሱ ፡ መቼ ፡ አዳነህ ፡ አሉት ፤ እርሱም ፡
በሰንበት፡ቀን፡ፈጽሞ፡አዳነኝ፡አላቸው።

፲፪ አይሁድም፡እርስ፡በርሳቸው፡ይህስ፡ሰንበት፡
ሻሪ ፡ ነው ፤ ሕግንም ፡ አፍርሶአል ፡ ስለዚህ፡

Scanned by CamScanner

ነተዝ፡ይደልዎ፡ቀትል።
፲፬ ወጸውዕዎሙ፡ካህናት፡ወረበናት፡ለሕዝብ፡
ወይቤልዎሙ፡እመ፡አእመርክሙ፡መካኖ፡
ዘንቤነ፡ሰበ፡መጽአ፡ኢየሩሳሌም።
፲፭ ወይቤሎሙ፡ውእቱ፡ሕሙም፡ዘሐይወ፡አነ፡
አእምር፡ከመ፡ነበርኩ፡ቍሱለ፡ወበሐመ፡
ወጽሙመ፡ወፈወሰኒ፡ዝንቱ፡ብእሲ።
፲፮ ሰበሰ፡አልቦቱ፡ክሂል፡ወኃይል፡ዐቢይ፡እም
ኢክሀለ፡ፈውሶትየ።
፲፯ እስመ፡ኢሰማዕነ፡ግሙራ፡በነቢያት፡ወኢበ
መዋዕሊሆሙ፡ከመ፡ተገብረ፡ዘከመ፡ዝ፡
ምግባር።
፲፰ ወይቤሉ፡ጸሐፍት፡ወፈሪሳውያን፡ኢትቅ
ትልዎ፡ለዝንቱ፡ብእሲ፡ዘእንበለ፡አሕዛብ፡
እለ፡አልቦሙ፡ልቡና፡ወእለ፡ኢየአምሩ፡
ሕገ።
፲፱ ወእንዘ፡ይትናገሩ፡ዘንተ፡መጽአ፡ኀቤሆሙ፡
እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎሙ፡እመ፡አእመ
ርክሙ፡ወልደ፡መኑ፡አነ፡እምድኅንክሙ፡
እምኃጢአትክሙ፡ወባሕቱ፡በእንተ፡ኢያእ
ምሮትክሙ፡ንቡር፡ኃጢአትክሙ፡እስመ፡
ኢተአምኑ፡ብየ።
፳ ኢትሌብዉኑ፡አ፡ደቂቀ፡አፍዖት፡ትንቢተ፡
ዳዊት፡ነቢይ፡ዘይቤ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡
እብን፡ዘመነንዋ፡ነደቅት፡ወይእቲ፡ኮነት፡
ውስተ፡ርእስ፡ማእዘንት፡እምኀበ፡እግዚአ
ብሔር፡ኮነት፡ዛቲ፡ወነካር፡ይእቲ፡ለአዕይ
ንቲነ።
፳፩ አ፡ደቂቀ፡አፍዖት፡ትብሉ፡አንትሙ፡
ዘዐረፈ፡ላዕለ፡እኁሁ፡ኢይትኴነን፡ወአንሰ፡
እብለክሙ፡ዘይቤሎ፡ለእኁሁ፡ርሑሕ፡
ይደልዎ፡ገሃነም።
፳፪ አ፡ትውልደ፡አራዊተ፡ምድር፡አንትሙ፡
ትኀፅብዎ፡ለጽዋዕ፡ውስጡ፡እንዘ፡ተዐቅቡ፡
ሕገ፡አሪት። ወታነውኁ፡ጸሎተ፡በውስተ፡
ምሥያጣት፡ ወትስሕቡ፡ አልባሲክሙ፡
ወታነውኁ፡ዘፈረ፡አልባሲክሙ፤ከመ፡
ትግሥ፡ንዋየ፡ዕጓለ፡ማውታ፡ወመበለታት፡



ሞት፡ይገባዋል፡አሉ።
፲፬፤ መምህራኑና፡ካህናቱ፡ሕዝቡን፡ጠርተው፡
ቦታውን፡ያወቃችሁ፡እንደ፡ሆነ፡ኢየሩ
ሳሌም፡በመጣ፡ጊዜ፡ንገሩን፡አሉአቸው።
፲፭፤ ያ፡የዳነውም፡ሰው፡እኔ፡ዝልጉስና፡ዲዳ፡
ደንቆሮ፡ሁኜ፡እንደ፡ኖርኩ፡አውቃለሁ፡
ይህም፡ሰው፡አዳነኝ።
፲፮፤ አምላክነት፡ከሌለው፡እኔን፡ማዳን፡ባልተቻ
ለውም፡ነበር።
፲፯፤ እንዲህ፡ያለ፡ሥራ፡እንደ፡ተሠራ፡በነቢ
ያትም፡ሆነ፡በዘመናቸውም፡ከቶ፡አልሰማ
ንምና፡ብሎ፡መለሰላቸው።
፲፰፤ ጸሐፍት፡ፈሪሳውያንም፡አእምሮና፡ሕግ፡
የሌላቸው፡አሕዛብ፡ከሚገድሉት፡በቀር፡
እናንተ፡ይህን፡ሰው፡አትግደሉት፡አሉ።

፲፱፤ ይህንንም፡ሲነጋገሩ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ወደ፡
እነርሱ፡መጥቶ፡እኔ፡የማን፡ልጅ፡እንደ፡
ሆንኩ፡ ብታውቁ፡ ከኃጢአታችሁ፡
በዳናችሁ፡ነበር፤ነገር፡ግን፡ባለማወቃችሁ፡
ኃጢአታችሁ፡በራሳችሁ፡ነዋሪ፡ነው፤በእኔ፡
አላመናችሁምና፡አላቸው።
፳፤ እናንተ፡የእፉኝት፡የእባብ፡ልጆች፡ነቢዩ፡
ዳዊት፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ተገልጾለት፡
አናጢዎች፡የናቋት፡ደንጊያ፡የማእዘን፡ራስ፡
ሆነች፤እርስዋም፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡
ሆነች፤ለዓይኖቻችንም፡ድንቅ፡ናት፡
ያለውን፡አታስተውሉምን?
፳፩፤ እናንተ፡የእፉኝት፡የእባብ፡ልጆች፡
ወንድሙን፡የሰደበ፡አይፈረድበትም፡
ትላላችሁ፤እኔ፡ግን፡ባልንጀራውን፡ጎስቋላ፡
ብሎ፡የሰደበ፡የገሃነም፡ፍርድ፡ይገባዋል፡እላ
ችኋለሁ።
፳፪፤ እናንተ፡የምድር፡እባብ፡ልጆች፡የኦሪትን፡
ሕግ፡ስትጠብቁ፡ጽዋውን፡ውስጡን፡ታጥቡ
ታላችሁ፤በገበያ፡ውስጥም፡ጸሎታችሁን፡
ታስረዝማላችሁ፤የልብሳችሁንም፡ዘርፍ፡አስ
ታስረዝማላችሁ፤ታንዘረፍፉላችሁ፤
ፍታችሁ፡ልብሳችሁን፡ታንዘረፍፉላችሁ፡
ጸሎታችሁን፡በማስረዘማችሁ፡ምክንያት፡

## በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

በአመክንዮ፡ጸሎትክሙ።

፳፫፤ ወታበውዑ ፡ ዓሥራተ ፡ እጼሁ ፡ ለአዛብ ፡ ወለከሚን፡ወለመለንስ፡ወተኀድጉ፡ትእዛዘ፡ እግዚአብሔር።

፳፬፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኢትበውዕዋ ፡ ለመንግሥተ፡እግዚአብሔር፡እስመ፡ኢትበውዑ፡ አንትሙ፡ወለእለሂ፡ይበውዑ፡ትከልዕዎሙ፡ በዊዖታ፡ለመንግሥተ፡እግዚአብሔር።

፳፭፤ አ፡ደቂቀ፡አፍዖት፡ጸሐቂ፡ከመ፡ትግበሩ፡ ግብረ ፡ ዘይፈሪ ፡ ለክሙ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት።

፳፮፤ አ፡ለክሙ፡ጸሐፍት፡ወካህናተ፡እስራኤል፡ ዘታበጥሉ፡ሕገ፡ወክሕድክምዎ፡ለክርስቶስ፡ እንዘ፡ትጤይቁ፡ምጽአቶ፡ወትቤልዎ፡መኑ፡ ውእቱ፡ወእምአይቴ፡መጽአ።

፳፯፤ ወይቤልዎ ፡ አይሁድ ፡ ለእመ ፡ መጽአ ፡ ክርስቶስ ፡ ነአምን ፡ ቦቱ ፡ ወነአምር ፡ ከመ ፡ ውእቱ፡ወልደ፡ዳዊት።

፳፰፤ ወይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ፡ወልደ፡ዳዊት፡በከመ፡ትቤሉ፡እፎ፡ ይቤ ፡ ዳዊት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚእ፡ለእግዚእየ፡ ንበር፡በየማንየ፡እስከ፡ አገብእሙ ፡ ለጸላእትከ ፡ ታሕተ ፡ መከየደ ፡ እገሪከ። ይቤሎ ፡

፳፱፤ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ አይሁድ ፡ እምኔሁ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ፡ኮነ፡ማእከሌሆሙ፡ተኃሥሦ፡ወኢተክ ሀሎሙ፡ያውሥእዎ፡አሐደ፡ቃለ።

፴፤ ወይቤሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ቦኑ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘትሴፈውዎ፡ይገብር፡ዘይበዝኅ፡እምዝንቱ፡ ተአምር፡ዘይገብር።

፴፩፤ ወበዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ኢረከብነ ፡ ላዕሌሁ ፡ ኃጢአተ፡ወኢ፡ነገረ፡ዘርቅ፡ወሐሰት።

፴፪፤ ወበይእቲ ፡ ጊዜ ፡ አምኑ ፡ ቦቱ ፡ ብዙኃን ፡ ሕዝብ።ወሰብሐት፡ለእግዚአብሔር።

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

የድኃ፡አደጉንና፡የጠም፡አዳሪዎችን፡ገንዘብ፡ ትነጥቁ፡ዘንድ።

፳፫፤ የእንዶድ፡የፌጦ፡የኑግ፡ከዐሥር፡አንድ፡ታገ ባላችሁ፤የሚበልጠውን፡የእግዚአብሔርን፡ ትእዛዝ፡ትተዋላችሁ።

፳፬፤ ስለዚህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ እናንተ፡አትገቡባትም፤ወደ፡እግዚአብሔር፡ መንግሥት ፡ የሚገቡትንም ፡ ትከለክሏቸዋላ ችሁና።

፳፭፤ የእፉኝት ፡ የእባብ ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፡ ለመን ግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚያበቃ ፡ ሥራ ፡ ትሠሩ፡ ዘንድ፡ትጉ።

፳፮፤ እናንት ፡ ጸሐፍትና ፡ የእስራኤል ፡ ካህናት፡ ሕግን ፡ የምታፈርሱ ፡ መምጣቱንም ፡ እየተረ ዳችሁ፡ክርስቶስን፡እርሱ፡ማነው?ከወዴት፡ መጣ፡እያላችሁ፡የምትክዱት።

፳፯፤ አይሁድም ፡ ክርስቶስ ፡ ከመጣ ፡ እናምንበ ታለን፤የዳዊትም፡ልጅ፡እንደ፡ሆነ፡እናው ቃለን፡አሉት።

፳፰፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ እናንተ ፡ እንደምትሉት፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ከሆነ ፡ ዳዊት ፡ ራሱ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ ተገልጾለት፡ጌታዬ፡አብ፡ ጌታዬ ፡ ወልድን ፡ ጠላቶችህን ፡ በእጅህ፡ ጭብጥ፡በእግርህ፡እርግጥ፡አድርጌ፡እስካስገ ዛልህ ፡ ድረስ ፡ በቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡ እንዴት፡ አለው?አላቸው።

፳፱፤ አይሁድ፡ይህን፡ነገር፡ከእርሱ፡በሰሙ፡ጊዜ፡በመ ካከላቸው ፡ ክርክርና ፡ መለያየት ፡ ሆነ ፤ አንድ፡ ቃልም፡ይመልሱለት፡ዘንድ፡አልተቻላቸውም።

፴፤ እርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ተስፋ ፡ የምታደርጉት፡ ክርስቶስ ፡ በውኑ ፡ ይህ ፡ ከሚያደርገው ፡ ተአምር፡የሚበልጥ፡ያደርጋልን?

፴፩፤ ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ኃጢአት ፡ ወይም ፡ ዋዛ፡ ፈዛዛ፡ወይም፡ሐሰት፡አላገኘንበትም፡አሉ።

፴፪፤ በዚ ዕኖ ... ብዙ ... አመኑበት፡

Scanned by CamScanner

በ፰፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

ግሁሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ክፍል፡፫።
ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፣፹፪፣፭።
እስመ፡ተማከሩ፡ኅቡረ፡ወዐረዩ።

ላዕሌከ፡ተሰካተዩ፡ወተካየዱ።
ተአይኒሆሙ ፡ ለኤዶምያስ ፡ ወለእስማኤላ
ውያን።

ወንጌል፡ዘዮሐንስ።

ምዕ፣፲፩፣፵፮–፶፬።
ወቦ፡እምውስቴቶሙ፡እለ፡ሖሩ፡ኀበ፡ፈሪሳ
ውያን፡ወአስተዋደይዎ፡ወነገርዎሙ፡ኵሎ፡
ዘገብረ፡እግዚእ፡ኢየሱስ።
ወአስተጋብእዎሙ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ወፈሪሳ
ውያን ፡ ለሕዝብ ፡ ወይቤልዎሙ ፡ ምንተ ፡
ንሬሲ፡ናሁ፡ዝንቱ፡ብእሲ፡ብዙኀ፡ተአምረ፡
ይገብር።
ወእመ፡ኀደግናሁ፡ከመዝ፡ኵሉ፡የአምን፡
ቦቱ፡ወይመጽኡ፡ሰብአ፡ሮሜ፡ወይነሥኡነ፡
ብሔረነ፡ወሕዝበነኒ።
ወይቤሎሙ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘስሙ ፡
ቀያፋ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ዘዕብሬቱ ፡ ይእቲ ፡
ዓመት ፡ አንትሙሰ ፡ ኢተአምሩ ፡ ወኢም
ንተኒ፡ወኢሂ፡ትመክሩ።

ይኄይሰነ ፡ አሐደ ፡ ብእሴ ፡ ንቅትል ፡
ወይሙት፡ ሀየንተ ፡ ሕዝብ ፡ እምይትኀጐል ፡
ኵሉ፡ሕዝብ።
ወዘንተሰ፡አኮ፡እምልቡ፡ዘይቤ፡አላ፡እስመ፡
ሊቀ፡ካህናት ፡ ውእቱ ፡ ወእብሬቱ ፡ ይእቲ ፡
ዓመት ፡ ተነበየ ፡ ዘንተ ፡ እስመ ፡ ሀለዎ ፡
ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ ይሙት ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡
ሕዝብ።
ወአኮ፡በእንተ፡ሕዝብ፡ባሕቲቶሙ፡አላ፡ከመ፡

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት/ነግህ።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

ክፍል፡፫።
ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፣፹፪፣፭።
አንድ፡ሁነው፡በአንድነት፡ተካክለው፡ተማ
ክረዋልና።
በአንተ፡ላይ፡ፈጽመው፡ተማማሉ።
የኤዶምያስና ፡ የእስማኤላውያን ፡ ወገኖች ፡
ይበል።

የዮሐንስ፡ወንጌል።

ምዕ፣፲፩፣፵፮–፶፬።
፵፮፤ ከእነርሱም፡ወገን፡ወደ፡ፈሪሳውያን፡ሂደው፡
ጌታ፡ኢየሱስ፡ያደረገውን፡ሁሉ፡ለእነርሱ፡
ነግረው፡ያጣሉት፡ነበሩ።
፵፯፤ የካህናት ፡ አለቆችና ፡ ፈሪሳውያንም ፡
ሕዝቡን፡ ሰብስበው ፡ እንዲህ ፡ አሏቸው ፤
እነሆ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ተአምራትን ፡
ያደርጋል፤ምን፡እናድርግ።
፵፰፤ እንዲህ፡ብንተወውም፡ሁሉ፡ያምንበታል፤
የሮም፡ሰዎችም፡መጥተው፡አገራችንንና፡
ወገናችንን፡ይወስዱብናል።
፵፱፤ ከእነርሱም፡አንዱ፡የሹመቱ፡ተራ፡በዚያ፡
ወራት፡የሆነችው፡ስሙ፡ቀያፋ፡የሚባል፡
የካህናት ፡ አለቃ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤
እናንተስ፡ ምንም፡ምን፡አታውቁም፤የምት
መክሩትንም፡አታውቁም።
፶፤ ሕዝቡ፡ሁሉ፡ከሚጠፉ፡ስለ፡ሕዝብ፡ቤዛ፡
አንድ፡ሰው፡ቢሞት፡አንድ፡ሰው፡ብንገድል፡
ይሻላል።
፶፩፤ ይህንንም፡የተናገረው፡ከልቡ፡አይደለም፤
ሊቀ፡ካህናት፡ነበረና፡ሹመቱም፡በዚያ፡
ወራት፡ነበረችና፡ይህን፡ትንቢት፡ተናገረ፡
እንጂ፤ጌታ፡ኢየሱስ፡ስለ፡ሕዝብ፡ሁሉ፡ቤዛ፡
ሆኖ፡ይሞት፡ዘንድ፡ነበረውና።
፶፪፤ ስለ፡ሕዝብ፡ብቻ፡አልነበረም፤የተበተኑትን፡

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

ያስተጋብአሙ ፡ ለውሉደ ፡ እግዚአብሔር ፡
እለ፡ተዘርዉ፡እሐተኔ።

፶፫፡ ወእምይእቲ፡ዕለት፡ተማከሩ፡ሊቃነ፡ካህናት፡
ከመ፡ይቅትልዎ።

፶፬፡ ወኢያንሶሰወ፡እንከ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ገሀደ፡
ማእከለ ፡ አይሁድ ፡ አላ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ሀገር ፡
እንተ፡ ትሰመይ ፡ ሀገረ ፡ ኤፍሬም ፡ ዘቅር
ብት ፡ ለበድው ፡ ወነበረ ፡ ሀየ ፡ ምስለ ፡ አርዳ
ኢሁ።
ዘየአምን፡በወልድ፡ቦ፡ሕይወት፡ዘለዓለም።

ድኅረ፡ወንጌል፡ጽባሕ፡ዘዕለተ፡ረቡዕ፤
ዘየኀብር፡ምስለ፡ትንቢት።

፩፡ ኵሉ፡ማኅበረ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡ተንሥኡ፡
ወወጽኡ፡ገዳመ፡ሲና፡ምስለ፡ተዓይኒሆሙ፡
በከመ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡
ወተዓየኑ ፡ በረፋዜን ፡ ወአልቦ ፡ ማይ ፡ በሀየ ፡
ከመ፡ይስተዩ፡ሕዝብ።

፪፡ ወዐውየዉ፡ወጸዐልዎ፡ለሙሴ፡እንዘ፡ይብሉ፡
ሀበነ፡ማየ፡ከመ፡ንስተይ።

፫፡ ወይቤሎሙ ፡ ሙሴ ፡ ለምንት ፡ ትጼዕሉኒ ፡
ወለምንት፡ታሜክርዎ፡ለእግዚአብሔር።

፬፡ ወመጽኡ ፡ ሕዝብ ፡ ወዐውየዉ ፡ ፊድፋደ ፡
እንዘ፡ ይብሉ ፡ ለምንት ፡ አውፃእከነ ፡ ወአዕ
ረገነ፡እምግብጽ፡ከመ፡ትቅትለነ፡ለነ፡ወለው
ሉድነ፡በጽምእ።

፭፡ ወጸርሐ ፡ ሙሴ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዘ ፡
ይብል ፡ ምንተ ፡ እግበር ፡ እስመ ፡ ይዌግሩኒ ፡
በእብን።

፮፡ ወይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ ሑር ፡
ቅድሜሆሙ፡ለሕዝብ፡ወንሣእ፡ምስሌከ፡እም
አዕሩግ፡እስራኤል፡ወንሣእ፡ምስሌከ፡በትረከ፡
እንተ ፡ ዘበጥከ ፡ ባቲ ፡ ባሕረ ፡ ንሣእ ፡ በእዴከ ፡
ወሑር ፡ ቅድሜሆሙ ፡ ኀበ ፡ ኰኵሕ ፡ ኰሬብ ፡
ወአነ፡እጸንሐከ፡በሀየ፡ዝብጥ፡ባቲ፡ወይወፅእ፡
ማይ፡ወይሰቲ፡ሕዝብ፤ወከመዝ፡ገብረ፡ሙሴ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

የእግዚአብሔርን፡ልጆች፡በአንድነት፡ይሰበ
ስባቸው፡ዘንድ፡ነው፡እንጂ።

፶፫፡ ከዚያች ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡
ሊገድሉት፡ተማከሩ።

፶፬፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ በአይሁድ ፡
መካከል፡ተገልጦ፡አልኖረም፤ለምድረ፡በዳ፡
አቅራቢያ ፡ ወደሆነችው ፡ የኤፍሬም ፡ አገር ፡
ወደምትባል ፡ ሄደ ፤ በዚያም ፡ ከደቀ ፡
መዛሙርቱ፡ጋር፡ተቀመጠ።
በወልድ፡ያመነ፡የዘላለም፡ሕይወት፡አለው።

ረቡዕ፡ጥዋት፡ከወንጌል፡በኋላ፡የሚነበብ፤
ከትንቢቱ፡ቃል፡ጋር፡የሚስማማ።

፩፡ የእስራኤል፡ልጆች፡ማኅበር፡ሁሉ፡በእግዚአ
ብሔር፡ቃል፡ታዝዘው፡በደብረ፡ሲና፡ካለ፡
ምድረ፡በዳ፡ከወገኖቻቸው፡ጋራ፡ተነሥተው
፡ወጡ፤በረፋዜንም፡ሰፈሩ፤በዚያም፡ሕዝቡ፡
የሚጠጡት፡ውኃ፡አልነበረም።

፪፡ ሙሴንም፡የምንጠጣው፡ውኃ፡ስጠን፡እያሉ፡
በጩኸታቸው፡ሰደቡት፤አስጨነቁት።

፫፡ ሙሴም ፡ ለምን ፡ ትሰድቡኛላችሁ? እግዚአብ
ሔርንስ ፡ ለምን ፡ ትፈታተኑታላችሁ ፡
አላቸው።

፬፡ ሕዝቡም ፡ ተሰብስበው ፡ እኛንም ፡ ልጆቻች
ንንም፡በውኃ፡ጥም፡ትገድለን፡ዘንድ፡ለምን፡
ከግብጽ ፡ አወጣኸን ፡ ብለው ፡ እጅግ ፡
ጮኹበት።

፭፡ ሙሴም ፡ በድንጋይ ፡ ይወግሩኛልና ፡
እንግዲህ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ጮኸ ፡(አመለከተ)።

፮፡ እግዚአብሔርም፡ ሙሴን ፡ ከእስራኤል ፡ ሽማግ
ሌዎች፡ካንተ፡ጋራ፡ይዘህ፡በሕዝቡ፡ፊት፡ሂድ፡
ባሕሩንም ፡ የመታህበትን ፡ በትርህን ፡ በእጅህ፡
ያዝ፤በፊታቸውም፡ወደ፡ኰሬብ፡አለት፡ሂድ፡
እኔም፡በዚያ፡እቆይሃለሁ፤በበትርህም፡አለቱን፡
ምታበት ፤ ውኃም ፡ ይወጣል ፤ ሕዝቡም ፡
ይጠጣል፡አለው፤ሙሴም፡እንዲሁ፡አደረገ።

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ/ነግህ።

...ማትት ፡ ዝንቱ ፡ ምሥጢር ፡ ዘገበርካሁ ፡
...በትርከ፡ቅድስት፡አ፡ሊቀ፡ነቢያት።

...ተርጕሞ ፡ መምህራን ፡ ዘገበርካሁ ፡
በመንፈስ፡ ቅዱስ ፡ እስመ ፡ ዘቢጦትከ ፡
...ሎሁ፡ ክልኤተ ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡
...ይለቲ።

...ወንሕነኒ፡ምእመናን፡ንጽራሕ፡እንዘ፡ንብል፡
...፡ዘተወከፍከ፡ሕማማተ፡መስቀል፡ስረይ፡
...ለነ፡ኃጣውኢነ፡ወአበሳነ፡በእንተ፡እምከ፡
ድንግል።

ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ
ማማቲሁ፡አድኃነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ከመ፡ቀዳሚ።

## ምዕራፍ፡፴፩።

ትእዛዝ፡ወይትጋብኡ፡ካህናት፡ውስተ፡ቤተ፡
ክርስቲያን፡ቅድስት፡በዕለተ፡ረቡዕ፡በጊዜ፡
መለስቱ፡ሰዓተ፡መዓልት፡ወይጸልዩ፡ጸሎተ፡
በከመ፡ጸለዩ፡በዕለተ፡ሰኑይ፡በ፫፡ሰዓት።

### ክፍል፡፩።
### ምንባብ።
### ኦሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፡፲፫፡፲፯–፳፪።

፲፯ ወሶበ ፡ ፈነዎሙ ፡ ፈርዖን ፡ ለሕዝብ ፡
ኢመርሆሙ፡እግዚአብሔር፡ፍኖተ፡ፍልስ
ጥኤም፡እስመ፡ቅርብት፡ይእቲ፡እስመ፡ይቤ፡
እግዚአብሔር፡የጊ፡ይኔስሕ፡እምከመ፡ርእየ፡
ቀትለ፡ወይገብእ፡ውስተ፡ግብጽ።
፲፰ ወአዖዶሙ፡እግዚአብሔር፡ለሕዝብ፡ላዕለ፡
ፍኖተ፡ሐቅለ፡ባሕረ፡ኤርትራ፡ወበኀምስ፡
ትውልድ፡ዐርጉ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡እምድረ፡
ግብጽ።
፲፱ ወነሥአ ፡ ሙሴ ፡ አዕፅምቲሁ ፡ ለዮሴፍ ፡
ምስሌሁ ፡ እስመ ፡ መሐላ ፡ አምሐሎሙ ፡
ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ወይቤሎሙ ፡ አመ ፡

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ።

፯፤ የነቢያት ፡ አለቃ ፡ ሆይ ፡ ልዩ ፡ በሆነች ፡
በትርህ፡ ያደረግኸው ፡ ይህ ፡ ምሥጢሩ ፡
ምንድነው?

፰፤ ያደረግኸውን ፡ መምህራን ፡ በመንፈስ ፡
ቅዱስ፡ ተረጐሙ ፤ ዐለቱን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡
መምታትህ፡የመስቀል፡ምልክት፡ናትና።

፱፤ እኛም ፡ በእምነታችን ፡ ጸንተን ፡ ሕማማተ ፡
መስቀልን፡የተቀበልክ፡ሆይ፡ስለ፡ድንግል፡
እናትህ፡ኃጢአታችንና፡በደላችንን፡አሥተስ
ርይልን፡እያልን፡እንጮህ።

መድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡
መከራ፡ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
የጸሎቱ፡መፈጸሚያ፡እንደ፡ፊተኛው፡ነው።

## ምዕራፍ፡፴፩።

ትእዛዝ ፡ ካህናቱ ፡ በከበረች ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ ውስጥ ፡ ረቡዕ ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡
ይሰብሰቡ፤ሰኞ፡በሦስት፡ሰዓት፡እንደ፡ጸለዩ፡
ይጸልዩ።

### ክፍል፡፩።
### ምንባብ።
### ኦሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፡፲፫፡፲፯–፳፪።

፲፯፤ ፈርዖን፡እስራኤልን፡ከግብጽ፡አሰናብቶ፡በሰደ
ዳቸው፡ጊዜ፡እግዚአብሔር፡ወደ፡ፍልስጥኤም፡
መንገድ፡አልመራቸውም፤ቅርብ፡ስለሆነች፡
እግዚአብሔር፡ሰልፉን፡ባየ፡ጊዜ፡ተፀፅቶ፡ወደ፡
ግብጽ፡እንዳለ፡ይመለሳል፡ብሎአልና።

፲፰፤ እግዚአብሔርም ፡ እስራኤልን ፡ በኤርትራ ፡
ባሕር፡ዳር፡ባለው፡ጎዳና፡አዞራቸው፤የእስራ
ኤልም፡ልጆች፡በአምስተኛው፡ትውልድ፡
ከግብጽ፡ወጡ።

፲፱፤ ዮሴፍም ፡ እስራኤልን ፡ እግዚአብሔር ፡
በረድኤት፡መጐብኘትን፡በጐበኘችሁ፡ጊዜ፡
ከናንተ፡ጋራ፡አጥንቴን፡ይዛችሁ፡ከግብጽ፡

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ሐውጾ፡ሐወጸከሙ፡እግዚአብሔር፡ንሥኡ፡ አዕፅምትየ ፡ ወአውጽኡ ፡ ምስሌክሙ ፡ እምዝየ።

፴፱፡ ወግዕዙ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ እምሰኮት ፡ ወኀደሩ፡ውስተ፡ኤቶም፡ዘመንገለ፡በድው።

፵፡ ወእግዚአብሔር ፡ መርሆሙ ፡ መዐልተ ፡ በደመና፡ወሌሊተ፡በብርሃነ፡እሳት።

፵፩፡ ወኢሰሰለ፡ዓምደ፡ደመና፡መዐልተ፡ወኢ፡ ዓምደ፡እሳት፡ሌሊተ፡እምቅድመ፡ኵሉ፡ ሕዝብ።

ጥበበ፡ሲራክ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፵፪፡፮–፲፰።

፮፡ መቅሠፍት፡ወተግሣጽ፡በኵለሄ፡ያጠብብ።

፯፡ ከመ ፡ ዘያስተጣግዕ ፡ አግልዕተ ፡ ከማሁ ፡ ዘይሜህሮ፡ለአብድ፡አንቅሖ፡እምዐቢይ፡ ንዋም፡ለዘይነውም።

፰፡ ከማሁ፡ዘይነግሮ፡ለአብድ፡ከመ፡ዘይነግሮ፡ ለድቁስ። ወሶበ፡አኅለቀ፡ነጊሮቶ፡ይብለከ፡ ምንተ፡ትቤ።

፱፡ ብኪ፡ላዕለ፡ዘሞተ፡እስመ፡ኀለፈ፡ብርሃኑ፡ ወብክዮ፡ለአብድ፡እስመ፡አምሠጠ፡ልቡ።

፲፡ ርቱዕ፡ትብክዮ፡ለዘሞተ፡እስመ፡አልቦ፡ ምግባዕ።

፲፩፡ ወለአብድሰ፡ብክዮ፡በሕይወቱ፡እስመ፡ ሐዪው፡የአክዮ፡እምነ፡መዊት።

፲፪፡ ብክዮ፡ለአብድ፡ወለኃጥእ፡በኵሉ፡መዋዕሊ፡ ሕይወቱ።

፲፫፡ ኢታብዝኅ ፡ ተናግሮ ፡ ምስለ ፡ አብድ ፡ ወኢትሑር፡ምስለ፡ዘአልቦ፡ልብ፡ወተዐቀብ፡ ከመ፡ኢያብእከ፡ውስተ፡ጻሕብ፡ወከመ፡ኢት ትኀየስ ፡ አንተ ፡ በእበደ ፡ ዚአሁ ፡ ረኀቅ ፡ እምኔሁ፡ወታዓርፍ፡ነፍስከ፡ወይቀልለከ፡ ወአልቦ፡ዘትትነከይ፡አንተ፡በእበደ፡ዚአሁ።

፲፬፡ ምንት፡ይከብድ፡እምነ፡ዐረር፡ወምንት፡ ስሙ፡ዘእንበለ፡አብድ።

፲፭፡ ይኄይስ፡ትፁር፡ኖፃ፡ወጼወ፡ወዘብርታተ፡ ኀጺን፡እምትንበር፡ምስለ፡አብድ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ውጡ፡ብሎ፡መሐላን፡አምሎአቸው፡ነበርና፡ ሙሴም፡ከእርሱ፡ጋራ፡የዮሴፍን፡አጥንት፡ ይዞ፡ወጣ።

፴፱፡ የእስራኤልም፡ልጆች፡ከሰኮት፡ተጉዘው፡ በምድረ፡በዳ፡ባለች፡በኤቶም፡አደሩ።

፵፡ እግዚአብሔርም፡ቀን፡በደመና፡ሌሊት፡ በእሳት፡ብርሃን፡ይመራቸው፡ነበር።

፵፩፡ ዓምደ፡ደመናው፡በቀን፤ዓምደ፡እሳቱ፡ በሌሊት፡ከሕዝቡ፡ፊት፡አልራቀም።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ትሁንና፡ ጥበበኛው፡ሲራክ፡የተናገረው፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፵፪፡፮–፲፰።

፮፡ በትርና፡ቁጣ፡ሁል፡ጊዜ፡ያሠለጥናል።

፯፡ ሰነፍ፡ሰውን፡የሚያስተምር፡የተሰበረ፡ገል፡ አንድ፡እንደሚያደርግ፡ሰው፡ነው፡የተኛን፡ ሰውን፡ከጽኑ፡እንቅልፍ፡ቀስቅሶአልና።

፰፡ እንደዚሁ፡ሁሉ፡ሰነፍን፡የሚያስተምር፡ሰው፡ ለተኛ፡ሰው፡እንደሚነግር፡ያለ፡ነው። ነግረኸው፡ ከጨረስክ፡በኋላ፡ምን፡አልክ፡ይልሃል።

፱፡ ለሞተ፡ሰው፡አልቅስ፤ሕይወቱ፡አልፎ አልና፡ ይልቁንም፡ለሰነፍ፡አልቅስለት፡ ዕውቀት፡ተለይቶታልና።

፲፡ ለሞተ፡ሰው፡ታለቅስለት፡ዘንድ፡የተገባ፡ ነው፤መመለሻ፡የለውምና።

፲፩፡ ለሰነፍ፡ሰው፡ግን፡በሕይወቱ፡ሳለ፡አልቅ ስለት፤ከሞት፡መኖር፡ከፍቶበታልና።

፲፪፡ ዕውቀት፡ለሌለው፡ሰነፍና፡ኃጢአተኛ፡ በሕይወት፡ዘመኑ፡ሁሉ፡አልቅስለት።

፲፫፡ ከሰነፍ፡ሰው፡ጋራ፡ነገር፡አታብዛ፡ዕውቀትም፡ ከሌለው፡ሰው፡ጋራ፡አብረህ፡አትሂድ፡ወደ፡ ጽኑም፡መከራ፡እንዳያደርስህ፡ተጠበቅ፡ በእርሱም፡ድንቁርና፡አንተ፡እንዳትነቀፍ፡ ከእርሱ፡ራቅ፡ሰውነትህንም፡ከመከራ፡ ታድናለህ፤ላንተም፡ይቀልልሃል፤በእርሱም፡ ድንቁርና፡አንተ፡የምትጎዳበት፡ነገር፡የለም።

፲፬፡ ከእርሳስ፡የሚከብድ፡ምን፡አለ? ሰነፍ፡ ከመባልስ፡ምን፡የሚከፋ፡አለ?

፲፭፡ ከሰነፍ፡ሰው፡ጋራ፡ከመኖር፡አሸዋ፡ጨውን፡ ናስና፡ብረትንም፡መሸከም፡ይሻላል።

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

መሠንየ፡ማእሰር፡ዘእሱር፡ውስተ፡ንድቀ፡
ሻር፡ወኢይትፌታሕ፡ቀኖናሁ፡እመኒ፡አድ
ለቶቀ፡ከማሁ፡ምክረ፡ጠቢብ፡ውስተ፡ልብ፡
ደንሶ።

ወኢይትፌታሕ፡ቀኖናሁ፡ለዝሉፉ፡ለልብ፡
ደንዕ፡ወለምክረ፡ጠቢብ፡ወከመ፡ምረገ፡
ኖ፡በውስተ፡አረፍት።

ወከመ፡ሐሠር፡ቅድመ፡ዓውሎ፡ዘኢይ
ቀውም፡እምከመ፡መጽአ፡ነፋስ፡ከማሁ፡
ዝኒናሁ፡ለአብድ፡ውስተ፡ልበ፡ፈራህ፡ዘኢ
ይቀውም፡ለእመ፡ከመ፡ቦ፡ዘረገሞ።

ክፍል፡፪።

አንቀጽ፡ዕሥራ፡ወተሰዓቱ።

እመጽሐፈ፡ዲድስቅልያ፡ዘአበዊነ፡ሐዋር
ያት፡በረከቶሙ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ወበረቡዕ፡ዕለት፡ፈጸሙ፡ምክረ፡ከመ፡
ያግብእዎ፡ለሞት፡በዲበ፡ዕፀ፡መስቀል።

ወይሁዳ፡አእመረ፡ዘንተ፡ምክሮሙ፤እስመ፡
ሰራቂ፡ውእቱ።

ወእምአሚሃ፡አውደቆ፡ሰይጣን፡በፍቅረ፡
ንዋየ፡ወርቅ፡እስመ፡ሙዓአ፡አስከሬን፡
ውእቱ፡የዐቅብ፡ወይመሥጥ፡ንዋየ፡ነዳያን።

ወዘንተ፡ኵሎ፡ገቢሮ፡ኢሰደዶ፡**እግዚእነ፡**
እስመ፡የአምር፡እከየ፡ልቡ።

አንቀጽ፡ዘዕሥራ፡ወኃምስቱ።

በእንተ፡ሰማዕታት፡እለ፡ይወስድዎሙ፡ኀበ፡
ምኵናን፡ወያመነድብዎሙ፡በዐቢይ፡ኵነኔ፡
ወበእንተ፡በዓላት፡ወፋሲካ።

እመቦ፡ክርስቲያናዊ፡ዘይወስድዎ፡ኀበ፡
ምኵናን፡ዘዐልዋን፡እመሂ፡ለቀቲል፡አው፡
ለተሰዶ፡አው፡ለተሞቅሖ፡አው፡የሀብዎ፡
ለአራዊት፡በእንተ፡ስመ፡**እግዚእነ፡ኢየሱስ፡**
**ክርስቶስ፡**ወርትዕት፡ሃይማኖት፡ወፍቅረ፡እግ
ዚአብሔር፡ኢትሚጡ፡ገጸክሙ፡እምኔሆሙ፤



ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፲፩፤ በአጥርና፡በቅጥር፡መካከል፡የተማገረና፡
ያማረ፡ይሎ፡ቅጽሩም፡ተናውጦ፡ቢወድቅ፡
አብሮ፡እንዳይወድቅ፡ማገሩም፡እንዳይፈታ፡
እንደዚሁም፡ሁሉ፡በዕውቀት፡በጸና፡ሰው፡
ልቡና፡ያለ፡የብልህ፡ሰው፡ምክር፡ጽኑ፡ነው።
፲፪፤ ጽናቱም፡ለዘላለም፡አይፈታም፤በዕውቀት፡
የጸና፡ልብና፡የብልህ፡ሰው፡ምክር፡ምሳሌ
ያቸው፡ካብና፡ይሎ፡ናቸው።በግድግዳ፡ላይ፡
ያለ፡ያሸዋ፡ምርግ፡እንዲፍረከረክ።
፲፫፤ በነፋስም፡ፊት፡ያለ፡ገለባ፡ነፋስ፡ሲመጣ፡
እንዲበተን፡እንደዚሁም፡ሁሉ፡የሰነፍ፡
ሰው፡አሳብ፡የሰደበው፡ሰው፡ቢኖር፡ቆሞ፡
እንደማይዋጋ፡እንደ፡ፈሪ፡ሰው፡ልብ፡ነው።

ክፍል፡፪።

ሃያ፡ዘጠነኛ፡አንቀጽ።

በረከታቸው፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይሁ
ንና፡አባቶቻችን፡ሐዋርያት፡ከጻፉት፡
ከሥርዓት፡መጽሐፍ፡የተገኘ።

፩፤ በአራተኛውም፡ቀን፡በዕንጨት፡መስቀል፡
ሰቅለው፡ሊገድሉት፡ለሞት፡አሳልፈው፡
ይሰጡት፡ዘንድ፡ምክርን፡ፈጸሙ።
፪፤ ይሁዳም፡ይህን፡ምክራቸውን፡አወቀ፤ሌባ፡
ነበርና።
፫፤ ከዚያችም፡ቀን፡ጀምሮ፡ሰይጣን፡በገንዘብ፡
ፍቅር፡አጠመደው፤እርሱ፡የመዳየ፡ምፅዋቱን፡
ቋልፍ፡ጠባቂ፡ነበረና፡ከውስጡም፡
የድሖችን፡ገንዘብ፡ይሠርቅ፡ነበርና።
ይህን፡ሁሉ፡ሠርቶ፡ሳለ፡**ጌታችን፡**አላበረ
፬፤ ረውም፤የልቡን፡ክፋት፡ያውቅ፡ነበርና።

ሃያ፡አምስተኛ፡አንቀጽ።

፩፤ ወደ፡ፍርድ፡አደባባይ፡ስለሚወስዱአቸውና፡
መከራ፡ስለሚአጸኑባቸው፡ሰማዕታት፡ስለ፡
በዓላትና፡ስለ፡ፋሲካ፡የሚናገር፡አንቀጽ።
**በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡**ስም፡በቀናች፡
፪፤ ሃይማኖት፡ስለ፡ጸና፡ስለ፡እግዚአብሔርም፡
ፍቅር፡ወደ፡ዓላውያን፡ፍርድ፡አደባባይ፡
ለመገደል፡ወይም፡ለስደት፤ወይም፡ለእ
ስራት፡ወይም፡ለአራዊት፡ሊሰጡት፡የሚ
ወስዱት፡ክርስቲያን፡ቢኖር፡ከእነርሱ፡

Scanned by CamScanner

| በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ። | ረቡዕ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት። |
|---|---|

አላ ፡ ባሕቱ ፡ ፈንዉ ፡ ሲሳዮሙ ፡ እምንዋ
ይከሙ፡ወሀፈ፡ገጽከሙ።

ፈታችሁን ፡ አትመልሱ ፤ ከገንዘባችሁ ፡
ወዘችሁን፡አንጠፍጥፋችሁ፡ካገኛችሁት፡ሁበት፡
ስንቃቸውንና፡ምግባቸውን፡ላኩ፡እንጂ።

፫፡ ወዓዲ፡ለእለ፡የዐቅብዎሙ፡መስተራትዓተ፡
ሐራ፡ሀቡ፡ሲሳዮሙ፡ከመ፡ኢያክብዱ፡ፃዕረ፡
ዝንጉ፡ላዕሌሆሙ።

፫፡ ዳግመኛም ፡ ሥቃይ ፡ እንዳያጸኑባቸው ፡ ለሚ
ጠብቁአቸው ፡ ዘበኞች ፡ ምግባቸውን ፡
ስጡአቸው።

፬፡ ወኢትግድፍዎ ፡ ለክርስቲያናዊ ፡ እትክሙ ፡
ዘሰሐብዎ ፡ ኀበ ፡ ዐውደ ፡ ምኵናን ፡ በእንተ ፡
ስመ፡እግዚአብሔር፡አምላክነ።

፬፡ ስለ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ስም፡
ወደ ፡ ፍርድ ፡ አደባባይ ፡ የተወሰደው ፡ ክርስቲ
ያናዊ፡ወንድማችሁን፡አትጣሉት።

፭፡ ዝኬ፡ውእቱ፡ቅዱስ፡ሰማዕት፡እኁሁ፡ለእግ
ዚእነ ፡ ወልዱ ፡ ለልዑል ፡ ወማኅየቱ ፡
ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ። ዝ ፡ ውእቱ ፡ ምእመን ፡
ዘዐቀበ፡ትእዛዘ፡ወንጌል፡ወወረሰ፡አክሊለ፡
ሕይወት።

፭፡ ይህም ፡ የከበረ ፡ ሰማዕት ፡ የልዑል ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ልጅ ፡ የጌታችን ፡ ወንድም ፡ የሆነ፡
የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፋና ፡ ነው ። ይህም ፡ የወን
ጌልን፡ ትእዛዝ ፡ የጠበቀ ፡ የሕይወትንም ፡
አክሊል፡የተቀዳጀ፡እውነተኛ፡ታማኝ፡ነው።

፮፡ ወኮነ ፡ ስምዐ ፡ በእንተ ፡ ሕማመ ፡ እግዚእነ ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወፍቁር፡በደሙ፡ክቡር።

፮፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መከራ፡
የሚመሰክር፡በከበረ፡ደሙም፡የተወዳጀ፡ነው።

### ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፡፺፭፡፱-፴።

ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ቆዝሞስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡
ዘሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ውስተ ፡ ጦማረ ፡
መልእክቱ፡ኀበ፡አባ፡ዮሐንስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡
ዘአንጾኪያ፤

፩፡ ወይደልወነ፡ንዝክር፡ትስብእቶ፡ለቀዳማዊ፡
ለአሐዱ፡ዘእምሥላሴ፡ኢፍጡር፡ወኢፍሉጥ፡
እግዚአብሔር፡ቃል።
ወለእመኒ ፡ ጊጉይ ፡ አነ ፡ ዳእሙ ፡ ዘንተሰ ፡
ዘእሬእዮ፡አነ፡አአምን፡ሃይማኖተ፡እንበለ፡
ዕቅፍት ፡ በዘይትዔረዮ ለአብ ፡ በቅድምና ፡
ዘውእቱ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡አብ፡ወልድ፡
ዘይትዔረዮ ፡ በመለኮት ፡ ዘኢይትገመር ፡
ዘተወልደ ፡ እምአብ ፡ እምቅድመ ፡ ኵሉ ፡
ዓለም።

፪፡ ወለሊሁ፡በደኃሪ፡መዋዕል፡በእንተ፡መድኃ
ኒትነ፡ተወልደ፡እምድንግል፡ማርያም፡ሥግወ፡
ዘእንበለ ፡ ተፋልሶ ፡ ወኢሚጠት ። በከመ ፡
መሀረነ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ንጹሕ ፡ ወቅዱስ ፡
ወይቤ፡እስመ፡ሶበ፡ተፈጸመ፡መዋዕል፡ፈነወ፡
እግዚአብሔር ፡ ወልዶ ፡ ወተወልደ ፡ እምብ
እሲት፡ወአስተርአየ፡ምስሌነ።

### የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፡፺፭፡፱-፴።

የእስክንድርያው፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ቅዱስ፡አባ፡
ቆዝሞስ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡
ወደ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ በላከው ፡ መልእክቱ፡
እንዲህ፡አለ።

፩፡ በቅድምና ፡ ፍጡር ፡ ልዩ ፡ ያይደለ ፡ ከሦስቱ፡ ፲
አካላት፡አንዱ፡አካል፡እግዚአብሔር፡ቃል፡
ሰው ፡ መሆኑን ፡ እንናገር ፡ ዘንድ ፡ ይገባናል፤
እኔ፡ምንም፡ኃጥእ፡ብሆን፡ይህን፡እኔ፡የማው
ቀውንስ፡አብን፡በቅድምና፡በሚተካከለው፡
ያለ፡ጥርጥር፡ማመንን፡አምናለሁ፤
ይኸውም፡በጌትነት፡የሚመስለው፡የሚተካ
ከለው፡የማይወሰን፡ዓለም፡ሁሉ፡ሳይፈጠር፡
ከአብ፡የተወለደ፡እግዚአብሔር፡አብ፡ቃል፡
ወልድ፡ነው።

፪፡ እርሱ ፡ እኛን ፡ ለማዳን ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ያለ፡
መለወጥ፡ያለ፡መናወጥ፡ከድንግል፡ማርያም፡
ነፍስን ፡ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ተወለደ፤
ዘመኑ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜም ፡ እግዚአብሔር ፡
ልጁን፡ ላከ ፤ ከድንግልም ፡ ተወለደ ፡ ብሎ ፡
ንጹሕ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዳስተማረን ፡
ከእኛ፡ጋራ፡ታየ።

Scanned by CamScanner

ዘ፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ሙላቱ ፡ አምላክ ፡ ወልደ ፡ እግዚ
ብሔር ፡ በመንፈስ ፡ ወወልደ ፡ ዕጓለ ፡
እመሕያው ፡ በሥጋ ፡ አኮ ፡ ዘንብል ፡ ቦቱ ፡
ለገቱ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ፩ቱ ፡ ህላዌ
ያቱ ፡ አሐዱ ፡ ዘይሰገድ ፡ ወካልኡ ፡ ዘኢይ
ሰገድ ። ዳእሙ ፡ አሐዱ ፡ ህላዌ ፡ ዘእግዚአ
ብሔር ፡ ቃል ፡ ዘተሠገወ ፡ ወይሰገድ ፡ ሎቱ ፡
ምስለ፡ሥጋሁ።

ዘተነ ፡ ነገረ ፡ ይቤ ፡ አትናቴዎስ ፡
ቢጸ፡ሐዋርያት፡ዘወጽአ ፡ ስሙዐተ ፡ ትም
ሀርቱ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አኮ ፡ እሙንቱ ፡
አሐዱ ፡ ዘእምእግዚአብሔር ፡ ዘበአማን ፡
ሎቱ ፡ ይሰገድ ፡ ወካልኡ ፡ ብእሲ ፡ እማ
ርያም ፡ ወኢይሰገድ ፡ ሎቱ ፡ ዘከመ ፡ ውእቱ ፡
ኮነ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ በጸጋ ። ወባሕቱ ፡
ውእቱ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ አምላክ፡
ውእቱ፡በከመ፡ንቤ፡እስመ፡ወልደ፡እግዚአ
ብሔር ፡ ውእቱ ፡ አምላክ ፡ ወአኮ ፡ ካልእ፡
ዘተወልደ ፡ በደኀሪ ፡ መዋዕል ፡ እማርያም ፡
ቅድስት፡ድንግል።

በከመ ፡ ትቤሎ ፡ ንጽሕት ፡ በኵሉ ፡ ግብራ ፡
ማርያም፡ድንግል፡ወላዲተ፡አምላክ፡ለሊቀ፡
መላእክት ፡ ገብርኤል ፡ እፎኑ ፡ ይከውነኒ ፡
ዝንቱ፡እንዘ፡ኢየአምር፡ብእሴ።
አውሥአ ፡ መልአክ ፡ ወይቤላ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ፡ ይመጽእ ፡ላዕሌኪ ፡ ወኃይለ ፡ ልዑል ፡
ይጼልለኪ።

ወዘኒ ፡ ይትወለድ ፡ እምኔኪ ፡ ቅዱስ ፡ ውእቱ ፡
ወይሰመይ ፡ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ።
ማሕነኒ፡ነአምር፡እሙነ፡ከመ፡ቃል፡ወልደ፡
እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ወሕያው ፡ በአካሉ ፡
ተሠገወ ፡እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወእማርያም ፡
ድንግል ፡ ንጽሕት ፡ ዘእንበለ ፡ ዘርዐ ፡ ብእሲ ፡
ሥጋ ፡ ዘይትዔርዮ ፡ ለህላዌነ ፡ ወየሐምም ፡
ሎነ፡እንበለ፡ምትሐት፡ወኢጽላሎት፡ዘቦቱ፡

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፲፩፤ በመለኮት ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ በሥጋ ፡ የሰው ፡ (የአብርሃም ፡ የዳዊት ፡ ልጅ) ፡ የሆነ፡አምላክ፡ ነው ። ለዚህ፡ለአንድ፡ለወልድ፡ አንዱ፡የሚሰገድለት፡አንዱ፡(ሌላው)፡የማይሰገ ድለት ፡ ሁለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ የምንል፡ አይደለም ። ሰው ፡ የሆነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አካላዊ፡ቃል፡ አንድ፡ባሕርይ፡ነው፡እንጂ፡ከሥ ጋውም፡ጋር፡አንድ፡ስግደት፡ይሰገድለታል።

፲፪፤ ይኸንንም ፡ ነገር ፡ ሐዋርያትን ፡ የመሰለ ፡ የትም ህርቱ ፡ ዜና ፡ የታወቀለት ፡ አትናቴዎስ ፡ አንዱ ፡ ከእግዚአብሔር፡ የተወለደ ፡ በእውነት ፡ የሚሰገ ድለት ፡ አንዱ ፡ ከማርያም፡ የተወለደ ፡ በጸጋ ፡ የእ ግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ የማይሰገድለት ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የሚከፈል ፡ ሁለት ፡ ባሕርያት ፡ ያሉት ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ከእግዚአብሔር፡ የተወለደ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ ከእግዚአ ብሔር ፡ የተወለደ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ በኋላ ፡ ዘመንም ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ የተወ ለደው ፡ ሌላ ፡ አይደለም።

፲፫፤ በሥራዋ ፡ ሁሉ ፡ ንጽሕት ፡ የሆነች ፡ አምላክን ፡ የወለደች፡ድንግል፡ማርያም፡ለሊቀ፡መላእክት፡ ገብርኤል፡ ወንድ፡ሳላውቅ፡ይህ፡እንደምን፡ይሆ ንልኛል ፡ እንዳለችው ። መልአኩም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ያድርብሻል ፡ የልዑል ፡ የአብ ፡ ኃይል ፡ ይጋ ርድሻል ፡ ወልድ፡ ሥጋሽን ፡ ይዋሐዳል ። ከአንቺ፡ የሚወለደው፡ የባሕርይ፡ አምላክ፡ ነው።

የልዑል፡እግዚአብሔርም፡ልጅ፡ ይባላል ፡ ብሎ፡ እንደ ፡ መለሰላት ። እኛም ፡ የሕያው ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ልጅ ፡ ቃል ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ በግብረ ፡ መንፈስ፡ቅዱስ፡ከቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡ ያለ፡ዘርአ፡ብእሲ፡የእኛን፡ባሕርይ፡የሚመስል፡ ምትሐት ፡ ጽላሎት ፡ ባለመሆን ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ የሚታመም ፡ የምትናገር ፡ የምታውቅ ፡ ነፍስ ፡ ያለችው ፡ በአካል ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ የተዋሐደ ፡

## በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ዘይትዋሐድ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ፡ ምስሌሁ፡በእኩል።

፲፬፡ ወወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ እምድኅረ ፡ ልደቱ ፡ ንጹሕ ፡ እማርያም ፡ ድንግል ፡ ዘይትሌዓል ፡ ንባበ ፡ ወልቡና ፡ ውእቱ ፡ ይትዔረዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በመለኮቱ ፡ ወይትዔረይ ፡ ህላዌነ ፡ በሥጋሁ ። ኢያምጽአ ፡ ኅቤነ ፡ ሥጋ ፡ እምህላዌ ፡ መለኮቱ ፤ ወኢክዋኔ ፡ መለኮቱ ፡ ወንእምአመ ፡ ተፈጥረ ፡ ህላዌ ፡ ሥጋሁ ፤ ወሕነ ፡ ንብል ፡ ከመ ፡ ተአምራት ፡ ወሕማማት ፡ ወንባብኒ ፡ ዘነበበ ፡ ዘይደሉ ፡ ለመለኮቱ ፡ ወትስብእቱ ፡ ዘዚአሁ ፡ ውእቱ ፤ ወኢንፈልጦ ፡ በዘኢይደሉ ፡ ኀበ ፡ ክልኤቱ ፡ ህላዌያት፡ወኢ፡ኀበ፡ክልኤቱ፡አካላት፡ወኢ፡ኀበ ፡ ክልኤቱ ፡ ገጻት ፡ ወኢ ፡ ኀበ ፡ ክልኤቱ፡ ግብራት ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ። ወዳእሙ ፡ ንብል ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አሐዱ ፡ መሢሕ ፡ ይእዜኒ፡ወበኵሉ፡ጊዜ።

በረከቱ፡ለዝንቱ፡መምህር፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

### ምንተኑ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ። ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፡ ወሀለወት ፡ አሐቲ ፡ መበለት ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ደብር ፡ ዘትትለአካ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ (ማሪሃም) ፡ ወታከብራ ፡ ወታፈቅራ ፡ በኵሉ ፡ ልባ።

፪፡ ወኮነት ፡ ይእቲ ፡ መበለት ፡ የዋሂት ፡ ትጼሊ ፡ ወትጸውም ፡ ወበተፍጻሜተ ፡ ጸሎታ ፡ ትጼሊ ፡ ጸሎተ፡ምውታን።

፫፡ ወሰይጣንሰ፡ጸላኤ፡ሠናያት፡አኀዘ፡ያመክራ፡በአምሳለ፡ወሬዛ፡ለመበለት፡ወያስተጥዕም፡ላቲ ፡ ግብረ ፡ ኃጢአት ፡ ወአጥፍአ ፡ ድንግልናሃ።

፬፡ ወእምድኅረ፡ውእቱ፡ግብር፡ነስሐት፡ላዕለ፡

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ሥጋን፡ነሥቶ፡እንደ፡እኛ፡በእውነት፡ሰው፡እንደ፡ሆነ፡እናውቃለን።

፲፬፡ የእግዚአብሔር፡አብ፡ልጅ፡ከመነገርና፡ከመመርመር ፡ ከራቀ ፡ ከዘር ፡ ንጹሕ ፡ ከሚሆን፡ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ ከተወለደው ፡ ልደቱ፡ በኋላም ፡ እርሱ ፡ በመለኮቱ ፡ እግዚአብሔር፡ አብን ፡ ይተካከለዋል ፤ ሰው ፡ በመሆኑም፡ እኛን፡ ይመስላል ። ከመለኮቱ ፡ ባሕርይ፡ አስገኝቶ ፡ ሥጋን ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ አላመጣም። የመለኮቱ ፡ መገኘትም ፡ የሥጋው ፡ ባሕርይ፡ በተፈጠረ፡ጊዜ፡አይደለም፤ታምራት፡ስለማድረግ ፡ መከራ ፡ ስለ ፡ መቀበል ፡ የተናገረው፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለመለኮቱ ፡ ለትስብእቱ፡ የሚስማማ፡የእርሱ፡ገንዘብ፡እንደ፡ሆነ፡እንናገራለን። ከተዋሕዶ፡በኋላም፡በማይገባ፡ወደ፡ሁለት፡ባሕርያት፡ወደ፡ሁለት፡አካላት፡ወደ፡ሁለት፡ገጻት፡ወደ፡ሁለት፡ግብራት፡አንለየውም፤ዛሬም፡ሁልጊዜም፡አንድ፡ክርስቶስ፡እንደ፡ሆነ፡እንናገራለን፡እንጂ።

የዚህ ፡ መምህር ፡ በረከት ፡ ከሁላችን ፡ ጋራ፡ ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

### ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑርና፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የጸናች፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን፡ ማርያም፡ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፡ በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመቤታችን፡ማርያምን፡በፍጹም፡ልቧ፡የምትወዳት፡የምታከብራትና ፡ የምታገለግላት ፡ አንዲት፡ መበለት፡ነበረች።

፪፡ ይህቺም ፡ የዋሂት ፡ መበለት ፡ ትጾምና፡ ትጸልይ፤ በጸሎቷም ፡ ፍጻሜ ፡ ስለ ፡ ሙታን፡ ትጸልይ፡ነበር።

፫፡ የበጎ ፡ ሥራ ፡ ጠላት ፡ የሆነ ፡ ሰይጣን ፡ግን፡ በጎልማሳ ፡ ተመስሎ ፡ ይፈትናት ፡ ዘንድ፡ ጀመረ ፤ የኃጢአትንም ፡ ሥራ ፡ ጣፋጭ፡ አድርጎ፡በማሳሰብ፡ድንግልናዋን፡አጠፋ።

፬፡ ከዚህም፡ሥራ፡በኋላ፡ስለ፡ሥራዋ፡በታላቅ፡

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ሰማበሬ፡በዐቢይ፡ብካይ፡ወወሀባ፡መምህር፡
ፃናና፡በከመ፡ይደሉ።
ወእምድኅረዝ፡እዕረፈት፡ይእቲ፡መበለት፡
እምቅድመ፡ይትፌጸም፡ቀኖናሃ፡ዘወሀባ፡
ቀሲስ፡ወወረደት፡ውስተ፡ሲኦል።
ወእምድኅረዝ፡እስተርአየታ፡ለእመ፡ምኔት፡
ውስተ፡ሕልማ፡እምድኅረ፡ኅዳጥ፡መዋዕል፡
ወትቤላ፡እንዘ፡በውስተ፡እሳት፡ሀሎኩ፡
መጽአት፡እግዝእትነ፡ማርያም፡ንጽሕት፡
ወትቤለኒ፡ኢትፍርሂ፡እመጽእ፡ወእድኅነኪ፡
ወለኵሎሙ፡እለ፡ይገብሩ፡ፈቃድየ፡ወትእ
ዛዝየ።
ወትቤላ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡
ማርያም፡እስመ፡ጸሎትኪ፡ዘትጼልዪ፡
ኮነተኒ፡በቍዔተ።
ወሶበ፡ነቅሐት፡እምንዋማ፡እመ፡ምኔት፡
እመ፡ይጠቅዑ፡መጥቅዐ፡አዘዘት፡
ይትጋብኡ፡ኵሎን፡መነኮሳዪያት።
ወነገረቶን፡ይእቲ፡መበለት፡ዘከመ፡አስተር
አየታ፡ወአዘዘቶን፡ዘከመ፡ይትለአካሃ፡ለእግ
ዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡
(ማሪያም)፡በተጠናቅቆ።
ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።
ወእንዘ፡ሀሎ፡ናትናኤል፡በብሔረ፡
ባቲላስ፡እንተ፡ይእቲ፡ምድረ፡ቃና፡
ዘገሊላ።
ወእመ፡ከብካብ፡ኮነ፡እስተብቍዕዎ፡ለናት
ናኤል፡አገልግሎ፡ከመ፡ይምጻዕ፡እግዚእ፡
ኢየሱስ፡ውስተ፡ምሳሐሆሙ፡ወይባርክ፡
ለዕሌሆሙ።ወስሙ፡ለመርዓዊ፡ዶኪማስ፡
ወልደ፡ዮካን።
ወሖረ፡ናትናኤል፡ኀበ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡
ወይቤሎ፡እስእለከ፡ኦ፡እግዚእነ፡
ትምጻእ፡ኀቤነ፡ውስተ፡ከብካበ፡ዶኪማስ፡

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ልቅሶ፡ንስሐ፡ገባች፡መምህረ፡ንስሓዋም፡
እንደሚገባ፡ቀኖና፡ሰጣት።
፫፤ ከዚህም፡በኋላ፡ያቺ፡መበለት፡ቄሱ፡
የሰጣትን፡ቀኖናዋን፡ሳትፈጽም፡አረፈች፡
ወደ፡ሲኦልም፡ወረደች።
፬፤ ከጥቂት፡ቀንም፡በኋላ፡ለእመ፡ምኔቷ፡
በሕልሟ፡ታየቻት፤በእሳት፡ውስጥ፡ሳለሁ፡
ንጽሕት፡የሆነች፡እመቤታችን፡ማርያም፡
መጣች፤አይዞሽ፡መጥቼ፡አድንሻለሁ፤
ፈቃዴን፡የሚፈጽሙትንና፡ትእዛዜን፡የሚ
ጠብቁትን፡ሁሉ፡አድናቸዋለሁ፡አትፍሪ፡
አለችኝ።
፭፤ እመቤታችን፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያምም፡
የምትጸልዪው፡ጸሎት፡ጠቅሞሻልና፡ብላ፡
ነገረቻት።
፮፤ ደወል፡ሲደወል፡እመ፡ምኔቷ፡በነቃች፡ጊዜ፡
መነኮሳዪያቱ፡ሁሉ፡ይሰበሰቡ፡ዘንድ፡
አዘዘች።
፯፤ ያች፡መበለትም፡እንደታየቻት፡ነግራቸው፡
ቅድስት፡ድንግል፡እመቤታችን፡ማርያምን፡
በጥንቃቄ፡ሁነው፡በፍጹም፡ልባቸው፡ያገለ
ግሉአት፡ዘንድ፡አዘዘቻቸው።
ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑርና፡ጌታችን፡ፈጣሪያችን፡መድኃኒ
ታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ያደረገው፡ድንቅ፡
ተአምር፡ይህ፡ነው።
፩፤ ናትናኤልም፡ባቲላስ፡በሚባል፡አገር፡ሳለ፡
ይችውም፡በገሊላ፡አውራጃ፡የምትገኝ፡
የቃና፡ምድር፡ናት።
፪፤ በዚያች፡በቃና፡ሠርግ፡በተደረገ፡ጊዜ፡ጌታችን፡
ወደ፡ሠርጉ፡ግብዣ፡ይመጣና፡ይባርካቸው፡
ዘንድ፡ናትናኤል፡ለምኖ፡እንዲአመጣው፡
ዘመዶቹ፡ማለዱት፡የሙሽራውም፡ስሙ፡
ዶኪማስ፡ይባላል፡እርሱም፡የዮካን፡ልጅ፡ነው።
፫፤ ናትናኤልም፡ወደ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ሂዶ፡
ጌታችን፡ሆይ፡የአባቴ፡የወንድም፡ልጅ፡
ወደሆነው፡ወደ፡ዶኪማስ፡ሠርግ፡

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ወልደ፡እጉሁ፡ለአቡየ፡ወባርክ፡ቤቶ።

፬ ወተወከፈ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ቃሎ ፡ ወሖረ፡ምስሌሁ፡ሀየ። ወሶበ፡ቦአ፡ውስተ፡ ከብካብ፡ ፈነዉ ፡ ሰብአ ፡ ኀበ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡ ወኀበ፡ ሰሎሜ ፡ ከመ ፡ ይምጽአ ፡ ውስተ ፡ ከብካብ ፡ ወመጽአ።

፭ ወአንበርዎ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ውስተ ፡ መካን፡ልዑል፡ወአምጽኡ፡ሎቱ፡መባልዕተ።

፮ ወአንበርዎ ፡ ለጴጥሮስ ፡ በየማኑ ፡ ወለእንድ ርያስ፡በፀጋሙ።

፯ ወሀለዉ ፡ በህየ ፡ ሕዝብ ፡ ብዙኃን ፡ እምሊ ቃናተ፡ካህናተ፡አይሁድ፡ምስለ፡አርዳኢሁ፡ ለእግዚእ፡ኢየሱስ።

፰ ወሶበ ፡ ፈጸሙ ፡ ምሳሐ ፡ አምጽኡ ፡ ወይነ ፡ ወሰትዩ ፡ እምኔሆሙ ፡ ብዙ ኃን።

፱ ወእምዝ ፡ ኃጥአ ፡ በዐለ ፡ ከብካብ ፡ ወይነ ፡ ዘያሰቲ ፡ እስመ ፡ ኀልቀ ፡ ወይን ፡ ወተከዘ፡ጥቀ።

፲ ይበውእ ፡ ወይወፅእ ፡ እምቤት ፡ እምብዝኀ ፡ ሐዘን ፡ በእንተ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ወይን ፡ ዘያሰቲ ። ወኀፍረ ፡ እምሕዝብ ፡ እለ ፡ መጽኡ ፡ ውስተ ፡ ከብካብ።

፲፩ ወርእዮቶ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ እንዘ ፡ ይቴክዝ ፡ ጥቀ ፡ ወመሐረቶ።

፲፪ ወሖረት፡ኀበ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ወትቤሎ፡እስመ፡ለበዓለ፡ከብካብ፡አልቦቱ፡ ወይን፡ወውእቱ፡ይቴክዝ፡በእንተ፡ዝንቱ።

፲፫ ወይቤላ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምንት፡ ብየ ፡ ምስሌኪ ፡ አ ፡ ብእሲቶ ፡ ዓዲ ፡ ኢበጽሐ፡ጊዜ፡ዘትስእሊዮ።

፲፬ ዘውእቱ ፡ በእንተ ፡ ወይነ ፡ ደሙ ፡ ሰቴ ፡ ሕይወት፡ ለእለ ፡ ይሰትይዎ ፡ በርትዕት ፡ ሃይማኖት።

፲፭ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ይሁዳ ፡ አስቆሮታዊ ፡ እስመ፡ኢሀሎ፡አሚሃ፡ውስተ፡ከብካብ።

፲፮ ወእግዚእነሰ ፡ ይጸንሕ ፡ ምጽአቶ ፡ ከመ ፡

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ትመጣልን ፡ ዘንድ ፡ የሠርጉን ፡ ቤትም ፡ ትባርክ፡ዘንድ፡እለምንሃለሁ፡አለው።

፬ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ጥሪውን ፡ ተቀብሎ ፡ አብሮ፡ ወደ ፡ ሠርጉ ፡ ሄደ ፤ ወደዚያም ፡ በገባ ፡ ጊዜ፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡ወደ፡ ጻናች፡ወደ፡ክብርት፡እመቤታችን፡ማርያምና፡ ወደ ፡ ሰሎሜ ፡ ወደ ፡ ሠርጉ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ፡ የሚጠራ፡ሰው፡ተላከ፤እነርሱም፡መጡ።

፭ ጌታ ፡ ኢየሱስንም ፡ በከፍታ ፡ ቦታ ፡ አስቀ ምጠው፡ምግብ፡አቀረቡለት።

፮ ጴጥሮስን ፡ በቀኙ ፡ እንድርያስን ፡ በግራው ፡ አስቀመጡአቸው።

፯ በዚያም ፡ ከአይሁድ ፡ ካህናት ፡ አለቆች ፡ ጭምር፡ከጌታ፡ ደቀ፡መዛሙርት፡ጋራ፡ብዙ፡ ሕዝቦች፡ነበሩ።

፰ ምሳም ፡ በልተው ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ የወይን፡ ጠጅ ፡ አቀረቡላቸው ፤ ከእነርሱም ፡ የወይን፡ ጠጅ፡ጠጥተው፡የረኩ፡ብዙዎች፡ናቸው።

፱ ከዚህ፡በኋላ፡ባለ፡ሠርጉ፡የወይን፡ጠጅ፡ስላለ ቀበት ፡ ለመጠጥ ፡ የሚያቅርበው ፡ ወይን፡ በማጣቱ፡እጅግ፡ተከዘ፤

፲ የሚያቀርበው ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ስለሌለው ፡ ከሐዘኑም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ከቤት ፡ ይወጣ ፡ ይገባ ፡ ነበር ፤ ፈጽሞም ፡ አዘነ ። ወደ ፡ ሠርጉም፡ ተጠርተው፡ከመጡት፡ሕዝብ፡የተነሣ፡አፈረ።

፲፩ እጅግም ፡ ሲተክዝ ፡ አይታ ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የጻናች ፡ ክብርት ፡ እመቤ ታችን፡ማርያም፡ ራራችለት።

፲፪ ወደ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ሄዳ ፡ ባለ፡ ሠርጉ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አልቆበታል ፡ እኮን፡እርሱም፡እጅግ፡ይተክዛል፡አለችው።

፲፫ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስም፡ አንቺ፡ሆይ፡ ካንቺ፡ምን፡አለኝ፡የምትለምኚው፡ጊዜው፡ ገና፡አልደረሰም፡አላት።

፲፬ ይኸውም ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ሁነው ፡ ለሚጠጡት ፡ የሕይወት ፡ መጠጥ ፡ የሚሆን፡ በወይን፡ስለሚሰጠው፡ደሙ፡ነው።

፲፭ ዳግመኛም ፡ ስለ ፡ አስቆሮቱ ፡ ይሁዳ ፡ ተና ገረ፤ያን፡ጊዜ፡በሠርጉ፡ቤት፡አልነበረምና።

፲፮ ይሁዳ ፡ ጌታን ፡ አሳልፎ ፡ ለአይሁድ ፡

ይገብር ፡ ተአምረ ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ወርእዮ ፡
ተአምረ ፡ እመ ፡ የኀድግ ፡ እከዮ ፡ ዘይኄሊ ፡
ለገነ፡አግብእቶ፡ኀበ፡አይሁድ።

፲፯ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ በጽሐ ፡ ይሁዳ ፡ ይቤሎሙ ፡
እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ለሰብእ ፡ ከብካብ ፡
ምልዕዎን፡ለእላ፡መሳብክት፡ማየ።

፲፰ ወሶበ ፡ መልዕዎን ፡ ይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡
ኢየሱስ ፡ ለላዕካነ ፡ ከብካብ ፡ ቅድሕዎንኬ ፡
ወአስትይዎሙ፡ለሰብእ።

፲፱ ወቀድሑ ፡ ላእካን ፡ እመሳብክት ፡ እለ ፡
መልእዎን፡ማየ፡ወአቅረቡ፡ለሰብእ፡በከመ፡
ይቤሎሙ፡እግዚእ።

፳ ወሶበ ፡ ጥዕሙ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ውእተ ፡
ማየ ፡ ዘኮነ ፡ ወይነ ፡ አንከሩ ፡ ጥቀ ፡ እስመ ፡
ኢለትዩ ፡ እምአመ ፡ ኮነ ፡ ዘከመ ፡ ውእቱ ፡
ስታይ።

፳፩ ወይቤልዎ ፡ ለመርዓዊ ፡ ዘምስለ ፡ ሊቀ ፡
ኀእት፡ኵሉ፡ሰብእ፡ያስቲ፡ዘይሤኒ፡ወይነ፡
ቅድመ ፡ ለአዕርክቲሁ ፡ እለ ፡ ጸውዖሙ ፡
ውስተ፡ ምሳሐ ፡ ወእምድኅረ ፡ ሰክሩ ፡
ያመጽእ፡ዘይቴሐት።

፳፪ ወአንተሰ፡አስተደኀርከ፡ዘይሤኒ፡ወይነ፡ወአ
ቅደምከ፡ለነ፡ዘይቴሐት።

፳፫ ወሶበ፡ጸገብነ፡ወረወይነ፡አምጻእከ፡ዘይሤኒ፡
እስመ ፡ ይቤሉ ፡ ዘንተ ፡ በኢያእምሮቶሙ ፡
ከመ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ረሰዮ ፡
ለማይ፡ወይነ፡ጥዑመ።

፳፬ እስመ ፡ ዓዲሁ ፡ ኢያእመሩ ፡ ዘንተ ፡ መንክረ ፡
እለ፡ሀለዉ፡ውስተ፡ከብካብ፡ዘእንበለ፡እግዝ
እትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡
ወላዲተ፡አምላክ፡ወአርዳኢሁ፡ወዶኪማስ፡
ወልደ ፡ ዮካን ፡ ወላእካነ ፡ ከብካብ ፡ እለ ፡
ቀድሑ፡ማየ።

፳፭ ወለኵሎሙ፡እለ፡አእመሩ፡ዘንተ፡መንክረ፡
አምኑ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ዘሎቱ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።



መስጠቱን ፡ ከማሰብ ፡ ምናአልባት ፡ ቢተው ፡
በፊቱ ፡ ተአምራትን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡
የይሁዳን፡መምጣት፡ይጠብቅ፡ነበር።

፲፯፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይሁዳ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በሠርግ ፡
ቤት ፡ የሚያገለግሉትን ፡ እነዚያን ፡ ጋኖች ፡
ውኃ፡ምሉአቸው፡አላቸው።

፲፰፤ በመሉአቸውም፡ጊዜ፡ቀድታችሁ፡ለሰዎች፡
አጠጡአቸው፡አላቸው።

፲፱፤ አገልጋዮችም፡ጌታ፡እንዳላቸው፡ውኃ፡ከመ
ሉአቸው፡ጋኖች፡ውስጥ፡ቀድተው፡ለሰዎች፡
አቀረቡ።

፳፤ የካህናት ፡ አለቆችም ፡ ያንን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡
የሆነውን ፡ ውኃ ፡ በቀመሱ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡
አደነቁ ፤ ከሆነ ፡ ጀምሮ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡
መጠጥ፡አልጠጡምና።

፳፩፤ ሙሽራውንም፡ከአሳዳሪው፡ጋራ፡ሰው፡ሁሉ፡
ወደ ፡ ግብዣው ፡ የጠራቸውን ፡ ወዳጆቹን፡
መልካሙን ፡ ጠጅ ፡ አስቀድሞ ፡ ያጠጣል ፤
ከሰከሩ፡በኋላ፡ዝቅተኛውን፡ያመጣል።

፳፪፤ አንተ፡ግን፡ዝቅተኛውን፡አስቀደምክልን፡የተ
ሻለውንም፡አቆይተህ፡አመጣህልን፡አሉት።

፳፫፤ ጠግበን፡በረካን፡ጊዜ፡የተሻለውን፡አመጣህ፤
ይህንንም ፡ ያሉ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ውኃውን ፡ ጣፋጭ ፡ ጠጅ ፡ እንዳደረገው ፡ ባለ
ማወቃቸው፡ነውና።

፳፬፤ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ ከጸናች ፡
አምላክን፡ከወለደች፡ከክብርት፡እመቤታችን፡
ማርያምና፡ከደቀ፡መዛሙርቱ፡ከዮካን፡ልጅ፡
ከዶኪማስ፡በሠርጉ፡ቤት፡ውኃ፡በመቅዳት፡
ከሚያገለግሉት ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ ድንቅ ፡
ተአምራት፡ገና፡አላወቁም፡ነበርና።

፳፭፤ ይህን ፡ ድንቅ ፡ ተአምር ፡ ያወቁ ፡ ሁሉ ፡
በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አመኑ ።
ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

Scanned by CamScanner

ክፍል፡፫።

ዲ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፡፵፡፯።

ይባእ ፡ ወይርአይ ፡ ዘከንቶ ፡ ይነብብ ። ልቡ፡አስተጋብአ፡ኃጢአተ፡ላዕሌሁ። ይወጽእ፡ ላዕ አፍኣ ፡ ወይትናገር ፡ ወየኀብር ፡ ላዕ ሌየ።

ወንጌል፡ዘሉቃስ።

ምዕ፡፳፪፡፩-፮።

፩፡ ወቀርበ፡በዐለ፡መጸለት፡ዘስሙ፡ፋሲካ።
፪፡ ወየኀሥሡ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ወጸሐፍት፡በዘ ይቀትልዎ፡ለእግዚእ፡ወኮኑ፡ይፈርህዎሙ፡ ለሕዝብ።
፫፡ ወቦአ ፡ ሰይጣን ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ይሁዳ ፡ አስቆሮታዊ ፡ ዘእምዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ትልቍ።
፬፡ ወሖረ፡ወተናገሮሙ፡ለሊቃነ፡ካህናት፡ወለጸ ሐፍት፡ዘከመ፡ያገብእ፡ሎሙ።
፭፡ ወተፈሥሑ፡ወተሰነዐዉ፡ምስሌሁ፡ወተና ገርዎ፡የሀብዎ፡ሠላሳ፡ብሩረ፡ወአስተኀለቁ፡ ነገረ።
፮፡ ወየኀሥሥ፡ሳሕተ፡ያግብእ፡ሎሙ፡እንዘ፡ አልቦ፡ሰብእ።

ድኅረ ፡ ወንጌል ፡ በሠለስቱ ፡ ሰዓተ ፡ መዐልት፡ዘረቡዕ።

፩፡ ሶበ ፡ ቀርበ ፡ በዐለ ፡ ናእት ፡ ዘውእቱ ፡ ፋሲካሆሙ፡ለአይሁድ፡ኮኑ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ ወጸሐፍት ፡ የኀሥሡ ፡ በዓይ ፡ ግብር ፡ ይቅትልዎ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ።
፪፡ ወኢያእመሩ፡ምንተ፡ዘይገብርዎ፡እስመ፡ እሙንቱ፡ኮኑ፡ይፈርሁ፡እምሕዝብ።
፫፡ ወረከበ፡ሰይጣን፡ማኅደረ፡ውስተ፡ልበ፡ ይሁዳ፡አስቆሮታዊ፡ዐርኩ።
፬፡ ወኮነ፡ዝንቱ፡ኍሉቍ፡ምስለ፡አርድእት፡ ወውእቱ፡እንዘ፡ሰይጣን፡በከመ፡ቃለ፡እግዚ አብሔር ፡ ወሖረ ፡ ወተናገረ ፡ ምስለ ፡ ዐበይቶሙ ፡ ለካህናት ፡ ወለሰዱቃውያን ፡ ከመ፡ያግብእ፡ሎሙ።
፭፡ ወኀለየ፡ርኩስ፡ምስለ፡ኅሊናሁ፡ከመ፡ ያግብእ፡ውስተ፡እደዊሆሙ፡ለመድኅነ፡ ዓለም።

ክፍል፡፫።

ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡አስቀድሞ።

መዝ፡፵፡፯።

ከንቱ፡ነገርን፡የሚናገር፡ገብቶ፡ይይ። ልቡናው፡ ዕዳ፡የሚሆንበትን፡ኃጢአት፡ሰበሰበ። ወደ፡ውጭ፡ ወጥቶ፡ኃጢአትን፡ይናገራል። በእኔ፡ላይም፡ያስተ ባብራል፡ይበል።

የሉቃስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፪፡፩-፮።

፩፡ ፋሲካ፡የሚባለው፡የቂጣ፡በዐል፡ቀርቦ፡ነበር።
፪፡ የካህናት፡አለቆችና፡ጸፎች፡ጌታን፡ሊገሉት፡ ይሹ ፡ ነበር ፤ ግን ሕዝቡን ፡ ይፈሩአቸው፡ ነበር።
፫፡ ቍጥሩ ፡ ከዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሐዋርያት፡ በሆነው፡በአስቆሮቱ፡ይሁዳ፡ልብ፡ሰይጣን፡ አደረ።
፬፡ ሂዶም፡አሳልፎ፡እንዲሰጣቸው፡የካህናት፡ አለቆችንና፡ጸፎችን፡ተነጋገራቸው።
፭፡ ደስ፡ብሏቸው፡ከእርሱ፡ጋራ፡ተስማምተው፡ ሠላሳ፡ብር፡ሊሰጡት፡ተነጋገሩትና፡ነገር፡ ቈረጡ።
፮፡ ሰው፡ሳይኖር፡ለነሱ፡አሳልፎ፡ሊሰጠው፡ ምቹ፡ጊዜ፡ይሻ፡ነበር።

ረቡዕ፡ከቀኑ፡በሦስት፡ሰዓት፡ከወንጌል፡ በኋላ፡የሚነበብ።

፩፡ የአይሁድ ፡ ፋሲካቸው ፡ የሆነ ፡ የቂጣው፡ በዐል ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የካህናት ፡ አለቆችና፡ ጸፎች ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስን ፡ በምን ፡ አይነት፡ ሥራ፡ይገድሉት፡ዘንድ፡ይሹ፡ነበር።
፪፡ ምን፡እንደሚያደርጉት፡አላወቁም፤እነርሱ፡ ከሕዝቡ፡የተነሣ፡ይፈሩ፡ነበርና።
፫፡ ሰይጣንም ፡ በወዳጁ ፡ በአስቆሮቱ ፡ ይሁዳ፡ ልብ፡ማደሪያ፡አገኘ።
፬፡ እርሱም፡ከሐዋርያት፡ጋር፡የተቈጠረ፡ነበር፡ እንደ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ባላጋራ፡ሲሆን፡ ጌታን ፡ ለነርሱ ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጠው፡ሂዶ፡ ከካህናት ፡ አለቆችና ፡ ከሰዱቃውያን፡ጋር፡ ተነጋገረ።
፭፡ የዓለም ፡ መድኃኒት ፡ ጌታን ፡ በእጃቸው፡ ሊአስገባላቸው ፡ ይህ ፡ ርኩስ ፡ ይሁዳ፡ አሰበ።

ክፍል፡፫።

ዲ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፡፵፱፡፯።

ይባእ ፡ ወይርአይ ፡ ዘከንቶ ፡ ይነብብ ። ልቡ ፡ አስተጋብአ፡ ኃጢአተ ፡ ላዕሌሁ ። ይወጽእ ፡ አፍኣ ፡ ወይትናገር ፡ ወየኀብር ፡ ላዕ ሌየ።

## ወንጌል፡ዘሉቃስ።

ምዕ፡፳፪፡፩-፮።

፩፤ ወቀርበ፡በዐለ፡መጸለት፡ዘስሙ፡ፋሲካ።

፪፤ ወየኀሥሡ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ወጸሐፍት፡በዘ ይቀትልዎ፡ለእግዚእ፡ወኮኑ፡ይፈርህዎሙ፡ ለሕዝብ።

፫፤ ወቦአ ፡ ሰይጣን ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ይሁዳ ፡ አስቆሮታዊ ፡ ዘእምዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ኍልቍ።

፬፤ ወሖረ፡ወተናገሮሙ፡ለሊቃነ፡ካህናት፡ወለጸ ሐፍት፡ዘከመ፡ያገብእ፡ሎሙ።

፭፤ ወተፈሥሑ፡ወተሰነዐዉ፡ምስሌሁ፡ወተና ገርዎ፡የሀብዎ፡ሠላሳ፡ብሩረ፡ወአስተኀለቁ፡ ነገረ።

፮፤ ወየኀሥሥ፡ሳሕተ፡ያግብአ፡ሎሙ፡እንዘ፡ አልቦ፡ሰብእ።

ድኅረ ፡ ወንጌል ፡ በሠለስቱ ፡ ሰዓት ፡ መዐልት፡ዘረቡዕ።

፩፤ ሶበ ፡ ቀርበ ፡ በዐለ ፡ ናእት ፡ ዘውእቱ ፡ ፋሲካሆሙ፡ለአይሁድ፡ኮኑ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ ወጸሐፍት ፡ የኀሥሡ ፡ በዓይ ፡ ግብር ፡ ይቅትልዎ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ።

፪፤ ወኢያእመሩ፡ምንተ፡ዘይገብርዎ፡እስመ፡ እሙንቱ፡ኮኑ፡ይፈርሁ፡እምሕዝብ።

፫፤ ወረከበ፡ሰይጣን፡ማኅደረ፡ውስተ፡ልበ፡ ይሁዳ፡አስቆሮታዊ፡ዐርኩ።

፬፤ ወኮነ፡ዝንቱ፡ኍሉቍ፡ምስለ፡አርድእት፡ ወውእቱ፡እንዘ፡ሰይጣን፡በከመ፡ቃለ፡እግዚ አብሔር ፡ ወሖረ ፡ ወተናገረ ፡ ምስለ ፡ ዐበይቶሙ ፡ ለካህናት ፡ ወለሰዱቃውያን ፡ ከመ፡ያግብአ፡ሎሙ።

፭፤ ወነሰየ ፡ ርኩስ ፡ ምስለ ፡ ኀሊናሁ ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ለመድኅነ ፡ ዓለም።

ክፍል፡፫።

ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡አስቀድሞ።

መዝ፡፵፱፡፯።

ከንቱ፡ነገርን፡የሚናገር፡ገብቶ፡ይይ። ልቡና... ዕዳ፡የሚሆንበትን፡ኃጢአት፡ሰበሰበ። ወደ፡ውጭ... ወጥቶ፡ኃጢአትን፡ይናገራል። በእኔ፡ላይም፡ያ... ባብራል፡ይበል።

## የሉቃስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፪፡፩-፮።

፩፤ ፋሲካ፡የሚባለው፡የቂጣ፡በዐል፡ቀርቦ፡ነበ...

፪፤ የካህናት፡አለቆችና፡ጸሮች፡ጌታን፡ሊገሉት፡ ይሹ ፡ ነበር ፤ ግን ሕዝቡን ፡ ይፈሩአቸው፡ ነበር።

፫፤ ቍጥሩ ፡ ከዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሐዋርያት፡ በሆነው፡በአስቆሮቱ፡ይሁዳ፡ልብ፡ሰይጣን፡ አደረ።

፬፤ ሂዶም ፡ አሳልፎ ፡ እንዲሰጣቸው፡የካህናት፡ አለቆችንና፡ጸሮችን፡ተነጋገራቸው።

፭፤ ደስ፡ብሏቸው፡ከእርሱ፡ጋራ፡ተስማምተው፡ ሠላሳ፡ብር፡ሊሰጡት፡ተነጋገሩትና፡ነገ... ቈረጡ።

፮፤ ሰው ፡ ሳይኖር ፡ ለነሱ ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጠው፡ ምቹ፡ጊዜ፡ይሻ፡ነበር።

ረቡዕ፡ከቀኑ፡በሦስት፡ሰዓት፡ከወንጌል፡ በኋላ፡የሚነበብ።

፩፤ የአይሁድ ፡ ፋሲካቸው ፡ የሆነ ፡ የቂጣው፡ በዐል ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የካህናት ፡ አለቆችና፡ ጸሮች ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስን ፡ በምን ፡ አይነት፡ ሥራ፡ይገድሉት፡ዘንድ፡ይሹ፡ነበር።

፪፤ ምን፡እንደሚያደርጉት፡አላወቁም፡እነርሱ ከሕዝቡ፡የተነሣ፡ይፈሩ፡ነበርና።

፫፤ ሰይጣንም ፡ በወዳጁ ፡ በአስቆሮቱ ፡ ይሁዳ ልብ፡ማደሪያ፡አገኘ።

፬፤ እርሱም፡ከሐዋርያት፡ጋር፡የተቈጠረ፡ነበር... እንደ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ባላጋራ፡ሊሆን... ጌታን ፡ ለነርሱ ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጠው ፡ ሄደ... ከካህናት ፡ አለቆችና ፡ ከሰዱቃውያን ፡ ጋር... ተነጋገረ።

፭፤ የዓለም ፡ መድኃኒት ፡ ጌታን ፡ በእጃቸው... ሊአስገባላቸው ፡ ይህ ፡ ርኩስ ፡ ይሁዳ... አሰበ።

Scanned by CamScanner

ወርኩስስ፡ዘምሉእ፡ጕሕሉት፡ተፈሥሐ፡
ወሊየ፡ፍሥሐ፡ፈድፋደ፡እስመ፡ዐቀሙ፡
ሎቱ፡ከመ፡የሀብዎ፡ሠላሳ፡ብሩረ፡ከመ፡
ያማስኑ፡ውስተ፡እደዊሆሙ፡እንተ፡ባሕቲቱ፡
እምሕዝብ።
ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ
ማሜሁ፡አድኃነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።

ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ከመ፡ቀዳሚ፡ፈጽም።

# ምዕራፍ፡፴፪።

## ክፍል፡፩።

በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

አሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፡፲፬፡፲፫—፴።

ወይቤሎሙ፡ሙሴ፡ለሕዝብ፡ተአመኑ፡
ወቁሙ፡ወትሬእዩ፡መድኃኒተ፡እንተ፡
እምኀበ፡እግዚአብሔር፡ዘይገብር፡ለነ፡ዮም፡
እስመ፡በከመ፡ትሬእይዎሙ፡ዮም፡ለግብጽ፡
ዳግመ፡ኢትሬእይዎሙ፡እንከ፡ጕንዱየ፡
ለዓለም።
ወእግዚአብሔር፡ይፀብዕ፡ለክሙ፡ወአን
ትሙሰ፡አርምሙ።
ወይቤሎ፡እግዚአብሔር፡ለሙሴ፡ለምንት፡
ትጸርህ፡ኀቤየ፡በሎሙ፡ለደቂቀ፡እሥራኤል፡
ይንድዑ፡እንስሳሆሙ።
ወአንተ፡ንሣእ፡በትረከ፡ወሰፋሕ፡እዴከ፡
ላዕለ፡ባሕር፡ወዝብጣ፡ወይባኡ፡ደቂቀ፡
እስራኤል፡ውስተ፡ማእከለ፡ባሕር፡በየብስ።
ወናሁ፡አነ፡አጸንዕ፡ልበ፡ለፈርዖን፡
ወለኵሉ፡ግብጽ፡ወይበውኡ፡ድኅሬሆሙ፡
ወእሴባሕ፡አነ፡በፈርዖን፡ወበኵሉ፡
ሐራሁ፡ወበሠረገላቲሁ፡ወበኵሉ፡
አፍራሲሁ።
ወያእምሩ፡ኵሉ፡ግብጽ፡ከመ፡አነ፡
ውእቱ፡እግዚአብሔር፡ከመ፡ተሰባሕኩ፡
በፈርዖን፡ወበሠረገላቲሁ፡ወበኵሉ፡
አፍራሲሁ።
ወለለ
...ብሔር፡መልአከ፡እግዚአ
...ሎሙ፡ዘየሐውር፡ቅድመ፡ትዕይ
...ለእሥራኤል፡ወቆመ፡



፮፤ ይህን፡ሽንገላ፡የተመላ፡ርኩስ፤ሕዝብ፡
በሌሊበት፡በጽሙና፡ጌታን፡ለብቻው፡
አሳልፎ፡በእጃቸው፡ሊሰጣቸውና፡
እነርሱም፡ሠላሳ፡ብር፡ሊሰጡት፡ቈርጠ
ዋልና፡እጅግ፡ደስ፡አለው።
መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡ሰው፡ሆኖ፡መከራ፡
ተቀበለ፡በመከራውም፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።

ማኅተመ፡ጸሎትስ፡ከመ፡ቀዳሚ፡ፈጽም።

# ምዕራፍ፡፴፪።

## ክፍል፡፩።

ረቡዕ፡ከቀኑ፡በስድስት፡ሰዓት፡የሚነበብ።

ኦሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፡፲፬፡፲፫—፴።

፲፫፤ ሙሴም፡እስራኤልን፡የግብጽ፡ሰዎችን፡
አሁን፡እንደምታዩአቸው፡ዳግመኛ፡
እንግዲህ፡ብዙ፡ቀን፡ፈጽማችሁ፡አታዩአቸ
ውምና፡አምናችሁ፡ቁሙ፤አሁን፡የሚደረ
ግልን፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡የሚመጣ፡
ድኅነትን፡ታያላችሁ።
፲፬፤ እግዚአብሔርም፡ይዋጋላችኋል፤እናንተ፡
ግን፡ዝም፡በሉ፡አላቸው።
፲፭፤ እግዚአብሔርም፡ሙሴን፡ወደኔ፡ለምን፡
ትጮኻለህ?የእስራኤልን፡ልጆች፡ከብቶቻ
ቸውን፡ይነዱ፡ዘንድ፡ንዱ፡በላቸው።
፲፮፤ አንተ፡ግን፡በትርህን፡ይዘህ፡እጅህን፡
ዘርግተህ፡ባሕርን፡ምታት፤የእስራኤልም፡
ልጆች፡በደረቅ፡ወደ፡ባሕር፡መካከል፡ይግቡ።
፲፯፤ እነሆ፡እኔም፡የፈርዖንን፡ልብ፡የግብጽንም፡
ሰዎች፡ልቡና፡ሁሉ፡አጸናለሁ፤እስራኤ
ልንም፡ተከትለው፡ይገባሉ፤እኔም፡ሠራዊ
ቶቹን፡ሁሉና፡ፈርዖንን፤ፈረሶቹንና፡ሠራገላ
ዎቹንም፡ሁሉ፡አጥፍቼ፡እመሰገናለሁ።
፲፰፤ ፈርዖንን፡ፈረሶቹን፡ሁሉና፡ሠረገላዎቹን፡
አጥፍቼ፡በተመሰገንኹ፡ጊዜ፡እኔ፡ፈጣሪ፡
እግዚአብሔር፡እንደሆንኩ፡የግብጽ፡ሰዎች፡
ሁሉ፡ያውቃሉ።
፲፱፤ በእስራኤል፡ሠራዊት፡ፊት፡የሚሄድ፡
የእግዚአብሔር፡መልአክ፡ቅዱስ፡
ሚካኤልም፡ተመልሶ፡በኋላቸው፡

Scanned by CamScanner

እምድኅሬሆሙ ፡ ወሰሰለ ፡ ዓምደ ፡ ደመናሂ ፡
እምቅድሜሆሙ፡ወቆመ፡እምድኅሬሆሙ።
፳፡ ወቦአ ፡ ማእከለ ፡ ትዕይንቶሙ ፡ ለግብጽ ፡
ወማእከለ፡ትዕይንቶሙ፡ለእስራኤል፡ወኮነ፡
ቆባር ፡ ወጽልመት ፡ ወኢተደመሩ ፡ በበይና
ቲሆሙ፡ኵላ፡ይእተ፡ሌሊተ።
፳፩፡ ወሰፍሐ ፡ ሙሴ ፡ እዴሁ ፡ ዲበ ፡ ባሕር ፡
ወአምጽአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕለ ፡ ባሕር ፡
ነፋሰ፡አዜብ፡ጽኑዐ፡ኵላ፡ሌሊተ፡ወገብሮ፡
ለባሕር፡የብሰ፡ወሰጠጠ፡ለማይ።
፳፪፡ ወቦኡ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡ማእከለ፡ባሕር፡
ላዕለ ፡ የብስ ፡ ወማይሰ ፡ ኮነ ፡ ዓረፍተ ፡
በየማኖሙ፡ወዓረፍተ፡በፀጋሞሙ።
፳፫፡ ወዴገንዎሙ ፡ ግብጽ ፡ ወቦኡ ፡ ድኅ
ሬሆሙ፡ወኵሉ፡አፍራሰ፡ፈርዖን፡ወሠረገ
ላቲሁ ፡ ወመስተፅዕናን ፡ ቦኡ ፡ ማእከለ ፡
ባሕር።
፳፬፡ ወሶበ፡ኮነ፡ዕቅበተ፡ሌሊት፡እንተ፡አፈ፡
ጽባሕ፡ ነጸረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡
ትዕይንቶሙ ፡ ለግብጽ ፡ በዐምደ ፡ እሳት ፡
ወደመና ፡ ወአዘዘ ፡ ላዕለ ፡ ትዕይንቶሙ ፡
ለግብጽ።
፳፭፡ ወአሰረ ፡ ማእሰረ ፡ ሠረገላቲሆሙ ፡
ወወሰዶሙ፡ በሥቃይ ፡ ወይቤሉ ፡ ግብጽ ፡
ንንፍጽ፡እምገጾሙ፡ለእስራኤል፡እስመ፡እግ
ዚአብሔር፡ይጽብእ፡ሎሙ።
፳፮፡ ወይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ ስፋሕ ፡
እዴከ፡ዲበ፡ባሕር፡ወይትጋባእ፡ማይ፡ዲበ፡
ግብጽ፡ወዲበ፡ሠረገላቲሆሙ፡ወመስተፅዕና
ኒሆሙ።
፳፯፡ ወሰፍሐ ፡ ሙሴ ፡ እዴሁ ፡ ዲበ ፡ ባሕር ፡
ወከደኖሙ ፡ ባሕር ፡ በጊዜሁ ፡ ወዐገቶሙ ፡
እምድኅር ፡ ወጐዩ ፡ ግብጽ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡
ወወገሮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለግብጽ ፡
ማእከለ፡ባሕር።
፳፰፡ ወተመይጠ፡ባሕር፡ወተሰጥሙ፡ምስለ፡ሠረ
ገላቲሆሙ፡ወምስለ፡ጽኑዓኒሆሙ፡ወኵሉ፡
ኃይለ ፡ ፈርዖን ፡ በከመ ፡ መጽኡ ፡ ውስተ ፡



ቆመ ፤ ደመናውም ፡ ከፊታቸው ፡ ተመልሶ፡
ከኋላቸው፡ተጋረደ።
፳፡ በእስራኤልና፡በግብጽ፡ሠራዊት፡መካከል፡
ገባ፤ጨለማና፡ጭጋግም፡ሆነ፤የዚያን፡ጊዜ፡
መላ፡ሌሊቱን፡እስራኤል፡ከግብጽ፡ሰዎች፡
ጋራ፡አልተገናኙም።
፳፩፡ ሙሴም፡እጁን፡ዘርግቶ፡ባሕርን፡መታው፡
እግዚአብሔርም ፡ መላ ፡ ሌሊቱን ፡ የጸና፡
የአዜብን፡ነፋስ፡አመጣ፤ውኃውን፡ከፍሎ፡
ባሕሩን፡ደረቅ፡አደረገው።
፳፪፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በደረቅ ፡ ወደ፡ባሕር፡
መካከል ፡ ገቡ ፤ ውኃው ፡ ግን ፡ በቀኛቸውም፡
በግራቸውም፡እንደ፡ግድግዳ፡ሆነ።
፳፫፡ የግብጽም ፡ ሰዎች ፡ ተከትለው ፡ በኋላቸው፡
ገቡ ፤ ሠረገላዎቹና ፡ የፈርዖን ፡ ፈረሶች፡
በፈረስ፡ በሠረገላም ፡ የተቀመጡ ፡ ወደ፡
ባሕር፡መካከል፡ገቡ።
፳፬፡ መንፈቀ፡ሌሊት፡ከሆነ፡በኋላ፡በነጋ፡ጊዜ፡
እግዚአብሔር፡በደመናና፡በእሳት፡አድሮ፡
የግብጻውያንን፡ሰፈር፡ተመለከተ፤በግብጽ፡
ሠራዊትም ፡ በባሕር ፡ መስጠምን ፡ አዘዘ
ባቸው።
፳፭፡ ሠረገላውንም ፡ አስተሳሰሮ ፡ በመከራ፡
ወሰዳቸው ፤ የግብጽም ፡ ሰዎች ፡ እግዚአ
ብሔር፡ይዋጋላቸዋልና፡ከእስራኤል፡ፊት፡
እንሽሽ፡አሉ።
፳፮፡ እግዚአብሔርም፡ሙሴን፡እጅህን፡ዘርግተህ፡
ባሕሩን ፡ ምታው ፤ ውኃውም ፡ በግብጽ፡
ሰዎች፡ ላይ ፡ በሠረገላቸውም ፡ በፈረስ፡
በሠረገላ፡በተቀመጡት፡ይመለስባቸው።
፳፯፡ ሙሴም፡እጁን፡ዘርግቶ፡ባሕሩን፡መታው፤
በመታውም፡ጊዜ፡ባሕሩ፡ሸፈናቸው፤በኋላ
ቸውም፡ከበባቸው፤የግብጽም፡ሰዎች፡ወደ፡
ባሕር ፡ ሸሹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የግብጽን፡
ሰዎች፡በባሕር፡መካከል፡ጣላቸው።
፳፰፡ ውኃውም፡ተመለሰ፤ከሠረገላቸው፡ጋራ፡ከአር
በኞቻቸውም ፡ ጋራ ፡ ከፈርዖን ፡ ሠራዊቶች፡
ሁሉ፡ጋራ፡ወደ፡ባሕር፡እንደ፡መጡ፡ሰጠሙ፤

Scanned by CamScanner

...ሐር፡ወአልቦ፡ዘተርፈ፡እምኔሆሙ፡እለ፡
...ማእከሎሙ፡ወኢ፡አሐዱ፡እምኔሆሙ።
...ደቂቀ፡እስራኤል፡ሖሩ፡ውስተ፡ይብስት፡
...ሕር፡ወባሕርሰ፡ዓረፍተ፡ኮኖሙ፡
...የማኖሙ፡ወእምፀግሞ።
...ዐዶሙ፡እግዚአብሔር፡ለእስ
...ኤል፡በይእቲ፡ዕለት፡እምእዴ
...ሙ፡ለግብጽ፡ወርእዩ፡እሥራኤል፡ከመ፡
...ቀ፡ግብጽ፡በውስተ፡ድንጋገ፡ለባሕር።
...ዐየ፡ዐቢየ፡ዘገብረ፡እግዚአ
...ብሔር፡በግብጽ፡ወፈርሁ፡ወአምኑ፡
...በእግዚአብሔር፡ወሙሴሃኒ፡ላእኮ፡
...አሰበዩ።

ምዕ፡፲፭፡፩።

...ሰብሖ፡ዘ፡ቡራኬ፡ሙሴ፡ወደቂቀ፡
...እስራኤል፡ለእግዚአብሔር፡በፍትሐተ፡
...ቃል፡እንዘ፡ይብሉ፡ንባርኮ፡ለእግዚአብሔር፡
...እስመ፡ክቡር፡ውእቱ፡ወሎቱ፡ይደሉ፡
...ስብሐ።

...በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
...ዓለም፡አሜን።

...ነበበ፡ሲራክ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፳፫፡፯-፲፬።

...ሰምዑኒ፡ደቂቅየ፡ተግሣጸ፡አፉየ፡ወዘሰ፡
...ዐቀበ፡ቃልየ፡ኢይድኅጽ፡ወዘአጽንዐ፡
...ከናፍሪሁ፡ኢይወድቅ።

...ኃጥእ፡ወዕቡይ፡ወፀአሊ፡ይትዐቀፉ፡
...ሎሙ።

...ወልድየ፡ኢታልምድ፡መሐላ፡
...ለአፉከ፡ወስሞ፡ለቅዱስ፡ኢትዝክር፡ሶበ፡
...ትምሕል።

...ከመ፡ገብር፡ዘኵሎ፡ጊዜ፡የኀትትዎ፡ወይቀ
...ሥፍዎ፡ኢይደጸምም፡ቍስለ...
...ኵሎ፡ዘ...

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፯፡ሰዓት።

ከመጡትም፡ሁሉ፡አንድ፡ሰው፡ስንኳን፡
የቀረ፡የለም።

፳፱፤ የእስራኤል፡ልጆች፡ግን፡በደረቀች፡ባሕር፡
መካከል፡ሄዱ፤ባሕሩም፡በቀኝ፡በግራ፡እንደ፡
ግድግዳ፡ሆነላቸው።

፴፤ እግዚአብሔርም፡በዚያች፡ቀን፡እስራኤልን፡
ከግብጽ፡ሰዎች፡እጅ፡አዳናቸው፤እስራ
ኤልም፡በባሕሩ፡ዳርቻ፡ሁነው፡የግብጽ፡
ሰዎች፡በባሕሩ፡እንደ፡ሞቱ፡አዩ።

፴፩፤ እግዚአብሔርም፡በግብጽ፡ሰዎች፡ላይ፡ያደረ
ገውን፡ጽኑ፡ሥልጣንን፡አዩ፤በእግዚአብ
ሔርም፡አመኑ፤መልእክተኛው፡ሙሴንም፡
አከበሩ፤ከፍ፡ከፍ፡አደረጉ።

ምዕ፡፲፭፡፩።

፩፤ ክቡር፡ነውና፡ለእርሱ፡ምስጋና፡ይገባል፤እግ
ዚአብሔርን፡እናመስግነው፡እያሉ፡
በተፈታ፡አንደበታቸው፡የእስራኤል፡
ልጆችና፡ሙሴ፡ይህንን፡ምስጋና፡ለእግዚአ
ብሔር፡አቀረቡ።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ትኑር፡አሜን።

የአምላኩ፡በረከት፡ለዘለዓለሙ፡ከኛ፡ጋራ፡ትሁ
ንና፡ጥበበኛው፡ሲራክ፡የተናገረው፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፳፫፡፯-፲፬።

፯፤ ልጆቼ፡ከአንደበቴ፡የተገኘውን፡ምክር፡
ስሙኝ፤ነገሬንም፡ሰምቶ፡የሚጠብቀው፡አይ
ሰናከልም፤አንደበቱን፡የሚጠብቅ፡ሰው፡
በመከራ፡አይወድቅም።

፰፤ ኃጢአተኛ፡ትዕቢተኛና፡ተሳዳቢ፡ባንደበ
ታቸው፡ይሰናከላሉ።

፱፤ ልጄ፡ላንደበትህ፡መሐላን፡አታስለምድ፤
በማልህም፡ጊዜ፡የእግዚአብሔርን፡ስም፡
በሐሰት፡አትጥራ።

፲፤ ጥዋትና፡ማታ፡ዕዳውን፡ጥፋቱን፡እየመረመሩ፡
...

ኀጢአቱሰ፡ኢይትኀደን፡ወእመሂ...

ኀጢአቱሰ፡ኢይትኀደን፡ወኢይጸድቅ ፡ ካዕበተ ፡ ይከውኖ ፡ ጌጋዩ ፡ ወኢይጸድቅ ፡ በዘመሐለ፡እስመ፡ምሉዕ፡ፍዳሁ፡ዲበ፡ቤቱ።

፲፪፤ ቦ ፡ ቃል ፡ እንተ ፡ ታመጽእ ፡ ለሞት ፡ ወኢትሄሉ፡ ውስተ ፡ ርስተ ፡ ያዕቆብ ፡ ዝንቱ ፡ ዙሉ፡ኢሀለወ፡ኀበ፡ጻድቃን፡ወኢይትዐቀፉ፡ በኃጢአት።

፲፫፤ ነገረ፡ ስላቅ ፡ ኢይፃእ ፡ እምአፉከ ፡ እስመ ፡ ቦ ፡ ውስቴቱ፡ብዙኀ፡ኃጢአት።

፲፬፤ ተዘከሮሙ፡ ለአቡከ ፡ ወለእምከ ፡ ወተፀመድ ፡ መኳንንቲከ ፡ ወኢትስሐት ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ወኢትልሳሕ፡ በአበድከ፡ ከመ፡ ኢትበል፡ ሶበ፡ ኢተወለድኩ ፡ ወከመ ፡ ኢትርግም ፡ ዕለተ ፡ ልደትከ።

## ክፍል፡፲፪።
## ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፤፺፮፡፲፪–፳፩።

ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአን ጾኪያ ፡ ውስተ ፡ ጦማረ ፡ መልእክቱ ፡ ኀበ ፡ ቅዱስ፡ማሪ፡ቆዝሞስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእለእስ ክንድርያ።

፲፪፤ ነአምን፡ወንትአመን፡ከመ፡ዝንቱ፡ተወልደ፡ እምአብ ፡ ቅድመ ፡ ዘእንበለ ፡ መዋዕል ፡ ወኢሕማም ፡ ዘርጉቅ ፡ እምዙሉ ፡ ዘመን ፡ ወፍልጠት ፡ ወበደኀሪ ፡ መዋዕል ፡ በእንተ ፡ መድኃኒትነ ፡ ወሐድሶ ፡ ፍጥረትነ ፡ ወሚጠትነ፡ ኀበ ፡ ዘኮነ ፡ ቅድመ ፡ ተሰብአ ፡ ወተሠገወ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወእማርያም ፡ ድንግል ፡ ንጽሕት።

፲፫፤ እስመ ፡ ሶበ ፡ ይቤላ ገብርኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት፡ ተፈሥሒ ፡ አ ፡ ምልዕተ ፡ ጸጋ ፡ እግዚ አብሔር፡ ምስሌኪ ፡ ነአምን ፡ ከመ ፡ ቃል ፡ ኀደረ፡ ውስቴታ ፡ ወተሠገወ ፡ እምኔሃ ፡ ፍጡነ ፡ ከመ ፡ ቅጽበተ ፡ ዐይን ፡ በዘኢይተረጐም ፡ ወዘከመ ፡ ለሊሁ ፡ የአምር ፡ ኀደረ ፡ ውስተ ፡ ከርሠ ፡

...ቢልም፡ በደሉ፡ እጽፍ፡ ይሆንበታል፤ ስለማለ፡ እውነተኛ፡ አይባልም፤ በቤቱም፡(በወገኑም)፡ የሚታዘዝበት፡ መቅሠፍት፡ ብዙ፡ ነውና።

፲፪፤ ሞትን ፡ የምታመጣው ፡ ቃል ፡ አለች ፤ ይችውም ፡ መሐላ ፡ ናት ፤ በያዕቆብ ፡ ርስትና፡ ሕግ፡ ኃጢአቱም፡ መቅሠፍቱም፡ የለም፤ ይኸ፡ ሁሉ፡ በጻድቃን፡ ዘንድ፡ የለም፤ በኃጢአትም፡ አይሰነካከሉም።

፲፫፤ የዋዛና ፡ የከበሬታ ፡ ነገር ፡ ካንደበትህ ፡ አይውጣ፤ ብዙ፡ ኃጢአት፡ አለበትና።

፲፬፤ አባትህንና ፡ እናትህን ፡ በምግብ ፡ አስባቸው፤ መኳንንቶችህንም ፡ (መምህራኖችህንም) ፡ አገልግል ፤ በፊታቸውም ፡ አትሳት ፤ በስንፍናህ፡ እንዳትነቀፍ፡ ሁን ፤ መከራ፡ መጥቶብህ፡ ባልተፈ ጠርሁ፡ በተሻለኝ፡ ነበር፡ እንዳትል፡ እንደ፡ ኢዮ ብም፡ የተወለድክበትን፡ ቀን፡ እንዳትረግም።

## ክፍል፡፲፪።
## የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፤፺፮፡፲፪–፳፩።

የአንጾኪያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደሚያገለግል፡ ወደ ፡ እስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱስ፡ ቆዝሞስ ፡ ጽፎ ፡ በላከው ፡ መልእክቱ ፡ እንዲህ፡ አለ።

፲፪፤ በልብ ፡ እንደምናምን ፡ በአነጋገር ፡ በቃልም፡ እንዲህ ፡ እናምናለን ፤ መቀዳደም ፡ ሳይኖር፡ አጋዥ ፡ ሳይሻ ፡ ተድኅሮ ፡ ተፈልጦ ፡ ሳይኖርበት፡ እሱ ፡ ከአብ ፡ እንደተወለደ ፡ በኋላ ፡ ዘመንም፡ እኛን ፡ ስለማዳን ፡ ባሕርያችንን ፡ ስለማደስ፡ እኛን ፡ ወደቀድሞ ፡ ርስታችን ፡ ስለ ፡ መመለስ፡ በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከንጽሕት ፡ ድንግል፡ ማርያም ፡ ነፍስን ፡ ሥጋን፡ ነሥቶ ፡ ሰው፡ እንደሆነ፡ እናምናለን፤ እንታመናለን።

፲፫፤ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤልም፡ ጸጋን፡ የተመላሽ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር፡ ከሥጋሽ ፡ ሥጋን ፡ ከነፍስሽ ፡ ነፍስን ፡ ነሥቶ፡ ሰው ፡ ይሆናልና ፡ ደስ ፡ ይበልሽ ፡ በአላት ፡ ጊዜ፡ ቃል ፡ በማሕጸኗ ፡ እንደ ፡ አደረ ፡ በማይመረመር፡ ምሥጢርም ፡ እንደ ፡ ዐይን ፡ ጥቅሻ ፡ ፈጥኖ፡

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

የንባብ ፡ ወኢተፈልጠ ፡ ተዋሕዶተ ፡
ማስነት፡ ዘኢይትከፈል ፡ በትስብእቱ ፡
ለሃሕድ።

ለሐዱ፡ውእቱ፡ቃል፡አመ፡ተሠገወ፡ወእም
ቅድመ፡ዓለም፡አሐዱ፡ውእቱ፡መንፈስ፡
ዘንበለ፡ሥጋ፡ከመ፡አብ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡
ወበደኅረ፡መዋዕል፡ሶበ፡ተሰብአ፡በእንተ፡
መድኃኒትነ፡ኢኮነ፡መንፈሰ፡ዘከመ፡ኮነ፡
እምቅድመ፡ትሥጉት፡አላ፡አሐዱ፡ውእቱ፡
እምክልኤቱ፡መለኮት፡ወትስብእት፡ወእሙ
ንቱ፡ፍጹማን፡በዘዚአሆሙ፡ወዘቦቱሂ፡
ኢኮነ፡ካልእ፡እምዘነበረ፡ቦቱ፡ቅድመ፡
መንፈስ፡ወባሕቱ፡ጸንዐ፡በዘዚአሁ፡ህላዌ፡
ዘከመ፡ቀዳሚ፡አመ፡ተወከፈ፡ተዋሕዶተ፡
በሥጋ፡ወኮነ፡ሰብአ፡በእንቲአነ።

ዘከመ፡ባቲ፡ለነፍስ፡ነባቢት፡ጽንዕ፡እንዘ፡
ለዕለት፡ትትዋሐድ፡ምስለ፡ሥጋ፡ወኢት
ገድፍ፡እምኔሃ፡መንፈስናሃ፡ለህላዌ፡እንተ፡
ኢኮነት፡ሥጋ፡አላ፡በዕሪና፡እንዘ፡ጽኑዓን፡
ክልኤቱ፡ኅቡረ፡በበህላዌሆሙ፡ኮኑ፡አሐደ፡
ህላዌ፡ወአሐደ፡አካለ፡ወአሐደ፡ብእሴ፡
ፍጹመ፡ወከማሁ፡ወልደ፡እግዚአብሔርሂ፡
ቀዳማዊ፡ዘተዋሐደ፡በሥጋ፡ዘውእቱ፡
መትሕተ፡መዋዕል፡በአሐዱ፡አካል፡እንበለ፡
ውላጤ፡ወለውእቱሂ፡ሥጋ፡ቦቱ፡ነፍስ፡
ነባቢት፡ወለባዊት።

፡ ወተሰምየ፡ዐማኑኤልሃ፡ዘበትርጓሜሁ፡እግዚ
አብሔር፡አምላክነ፡ምስሌነ፡እንዘ፡አሐዱ፡
ኅ፡ወአሐዱ፡አካል፡ወአሐዱ፡ህላዌ፡
ሥግው፡እንበለ፡ውላጤ፡ወኢቱስሕት፡
ዘከነ፡እምኔሆሙ፡ተዋሕዶ፡ዘኢይተ
ረጉም፡ወዘኢይትነገር፡ዘሰ፡ይደልዎን፡
ቃሌ፡ዘበርትዕ፡እማንቱ፡ሥጋት፡ርጡባት፡
ማንቱሂ፡ነኪራት፡እምህላዌ፡ዘአልቦቱ፡
ሥጋ፡

፡ ወዳጊ፡ኢይትከፈል፡ኅበ፡ክልኤቱ፡ህላዌያት፡
እምድኅረ፡ተዋሕዶ፡እስመ፡ለምንታዌ፡

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ከእርሷ፡ሥጋን፡ነሥቶ፡ሰው፡እንደሆነ፡እናምናለን፤
እሱ፡ባወቀም፡በድንግል፡ማሕፀን፡አደረ፤ዋሕድ፡
ቃለ፡እግዚአብሔር፡ሰው፡በመሆኑም፡የማ
ይከፈል፡የመለኮት፡አንድነት፡አልተከፈለም።

፲፬፤ ቃል፡ሰው፡በሆነ፡ጊዜም፡አንድ፡ነው፤ሰው፡
ከመሆኑ፡በፊትም፡አንድ፡ነው፤እንደ፡አብ፡
እንደ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ግዘፍ፡የሌለው፡ረቂቅ፡
ነው፤በኋላ፡ዘመን፡ግን፡እኛን፡ለማዳን፡ሰው፡
በሆነ፡ጊዜ፡ሰው፡ከመሆኑ፡አስቀድሞ፡እንደነ
በረው፡የማይዳሰስ፡አይደለም፤ከመለኮትና፡
ከትስብእት፡ከሁለት፡አንድ፡ነው፡እንጂ።
እነርሱም፡በገንዘባቸው፡ፍጹማን፡ናቸው፤
አምላክ፡ኋላ፡የተገለጠበት፡ባሕርይ፡ቀድሞ፡
ከነበረበት፡ረቂቅ፡ባሕርዩ፡ልዩ፡አይደለም፤
ከሥጋ፡ጋር፡ተዋሕዶን፡ገንዘብ፡በአደረገ፡ጊዜ፡
ስለ፡እኛም፡ሰው፡በሆነ፡ጊዜ፡እንደቀደመው፡
በገንዘቡ፡ባሕርይ፡ጸንቶ፡ኖረ፡እንጂ።

፲፭፤ ለነባቢት፡ነፍሳችንም፡ረቂቅ፡ስትሆን፡
ከሥጋ፡ጋር፡ትዋሐድ፡ዘንድ፡ኃይል፡
እንዳላት፡ሥጋ፡ያይደለች፡የባሕርይ፡ረቂቅ
ነቷን፡ከእርሷ፡እንዳትለቅ፡ሁለቱም፡በየገንዘ
ባቸው፡የጸኑ፡ሲሆኑ፡በተዋሕዶ፡አንድ፡
አካል፡አንድ፡ባሕርይ፡አንድ፡ፍጹም፡ሰው፡
እንደሆኑ፡ከዘመን፡በኋላ፡ከተገኘ፡ከሥጋ፡
ጋር፡ያለ፡መለወጥ፡አንድ፡አካል፡በመሆን፡
የተዋሐደ፡ቀዳማዊ፡የእግዚአብሔር፡
ልጅም፡እንዲሁ፡ነው።ለተዋሐደው፡
ሥጋም፡የምትናገር፡የምታውቅ፡ነፍስ፡
አለችው።

፲፮፤ ዐማኑኤልም፡ተባለ፤ትርጓሜውም፡እግዚአ
ብሔር፡አምላካችን፡ከእኛ፡ባሕርይ፡ጋር፡
አንድ፡ሆነ፡ማለት፡ነው፤ያለ፡መቀላቀል፡
አንድ፡ሆነ፡ማለት፡ነው፤ያለ፡መቀላቀል፡
ያለ፡መለወጥ፡ሰው፡የሆነው፡አንድ፡ገጽ፡
አንድ፡አካል፡አንድ፡ባሕርይ፡ነው፤ከመለ
ኮትና፡ከትስብእት፡የሆነ፡ተዋሕዶ፡የማይ
ነገር፡የማይመረመር፡ነው፤በእውነት፡
መቀላቀል፡የሚገባቸውስ፡ርጥበት፡ያላቸው፡
ሥጋዎች፡ናቸው፤እነዚህም፡ግዘፍ፡ከሌለው፡
ባሕርይ፡የተለዩ፡ናቸው።

፲፯፤ ከተዋሕዶ፡በኋላ፡ወደሁለት፡ባሕርይ፡አይከ
ፈልም፤ተዋሕዶ፡መንታነትን፡አጥፍቷልና፡

## በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

አዕተታ፡ተዋሕዶ፡ወተዋሕዶኒ፡ያግሕሥ፡ ዙነኔሁ ፡ ለምንታዌ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተዋሕዶ፡ አካላዊ፡ዘኢይትከፈል፡ወመኑ፡ ዘይኄሊ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ግብር ፡ ጽዱቅ ፡ ተናግሮ፡ከመ፡ይትወለጥ፡እግዚአብሔር፡ ቃል፡ዘኢኮነ፡ፍጡረ፡ኀበ፡ሥጋ፡ወሥጋሂ፡ ዓዲ፡ዘነሥአ፡እምቅድስት፡ድንግል፡ዘይትዔ ረየ፡በህላዌሁ፡ፈለሰ፡እምህላዌሁ፡ኀበ፡ ህላዌ፡መለኮት።

፲፰፤ ወአኮ፡ዘከመ፡ኮነት፡በትሩ፡ለሙሴ፡አርዌ፡ ምድር፡ወማየ፡ተከዚ፡ደመ፡ወብርሃነ፡ ግብጽኒ ፡ ጽልመተ ፡ ወከማሁ ፡ አኮ ፡ ዘተወለጠ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ኀበ፡ህላዌ፡ ዕጓለ፡እመሕያው፡እስመ፡እሉሰ፡ፍጡራን፡ እሙንቱ፡ወእሙራን፡በክዋኔ፡ወመትሕተ፡ ዘመን ፡ ወበእንተዝ ፡ ረከቦሙ ፡ ውላጤ ፡ ወህላዌ፡መለኮትሰ፡ጽኑዕ፡ውእቱ፡ወይሄሉ፡ ዘልፈ፡እንበለ፡ማኅለቅት፡ወኢይትገመር፡ ወኢይረክቦ፡ውላጤ፡ወኢሚጠት።

፲፱፤ ወለእመ፡ኮነ፡አርአያ፡ክህነት፡በእደዊሆሙ፡ ለነቢያት፡በከመ፡ተብህለ፡በአፈ፡ሆሴዕ፡ ነቢይ፡ወባሕቱ፡አርአያሰ፡ኢኮነ፡ተውላጠ፡ ህላዌ ፡ አላ ፡ ትእምርቱ ፡ ያበጽሕ ፡ ኀበ ፡ መሥፈርተ፡ጽድቅ፡ወበእንተ፡ዝንቱ፡ይቤ፡ ሕዝቅኤል፡ነቢይ፡እስመ፡ዝንቱ፡አርአያ፡ አምሳለ፡ስብሐተ፡እግዚአብሔር፡ያዔውቅ፡ እስመ፡አምሳል፡ዘስብሐተ፡እግዚአብሔር፡ ውእቱ ፡ ወአኮ ፡ ውላጤ ፡ ወኢሚጠት ፡ ወኅልዮሰ፡ወአምሳል፡ከንቱ፡ወምትሐት፡ ሕሰው፡ርኁቅ፡ውእቱ፡እምትሰብእተ፡ቃለ፡ እግዚአብሔር።

፳፤ ወዘንተ፡ንባበ፡መሀረነ፡ጳውሎስ፡ዘኮነ፡ ክርስቶስ፡ይነብብ፡በልሳኑ፡እንዘ፡ይሰብክ፡ ዝኩ፡ዘውእቱ፡አርአያሁ፡ለእግዚአብሔር፡ እንዘ፡ይብል፡አኮ፡ኀይደ፡ዘኮነ፡እግዚአ ብሔር፡አላ፡አትሒቶ፡ርእሶ፡ወነሥአ፡ አርአያ፡ገብር።

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ተዋሕዶም፡ከሁለት፡የተገኘ፡ሁለት፡መባል፡ አለበት፡የሚለውን፡ፍርድ፡ይለውጣል፤ይህ፡ ተዋሕዶ ፡ የማይከፈል ፡ አካላዊ ፡ ነውና፡ ፍጡር፡ያይደለ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ሥጋ፡ ወደ፡መሆን፡ይለወጣል፤በባሕርይ፡የሚመ ስለን፡ከንጽሕት፡ድንግል፡የተገኘ፡ሥጋም፡ ከባሕርዩ፡የመለኮት፡ባሕርይ፡ወደመሆን፡ ተለወጠ፡ብሎ፡መናገር፡እውነተኛ፡ነገር፡ እንደሆነ፡የሚአስብ፡ማነው?

፲፰፤ የሙሴ፡በትር፡ተለውጣ፡የምድር፡አባብ፡እንደ ሆነች፡የፈሳሽ፡ውኃም፡ተለውጦ፡ደም፡እንደ ሆነ፡የግብጽ፡ብርሃንም፡ተለውጦ፡ጨለማ፡እን ደሆነ፡እንዲሁ፡የእግዚአብሔር፡ቃልም፡የሰው፡ ባሕርይን፡ወደ፡መሆን፡የተለወጠ፡አይደለም፤ እነርሱ፡የተፈጠሩ፡ናቸውና፡በመፈጠርም፡ የታወቁ፡ናቸውና፡ከዘመንም፡በኋላ፡የተገኙ፡ ናቸውና ፡ ስለዚህም ፡ መለወጥ ፡ አገኛቸው፤ የመለኮት፡ባሕርይ፡ግን፡መለወጥ፡የለበትም፡ ፍጻሜ፡ሳይኖረው፡ሁልጊዜ፡ይኖራል፡አይወ ሰንም፡መለወጥ፡መናወጥ፡የለበትም።

፲፱፤ የክህነት፡ራእይ፡እንደ፡ነቢያት፡አነጋገር፡ ከሆነ፡ነቢዩ፡ሆሴዕ፡እንደተናገረው፡ነው፤ ነገር ፡ ግን ፡ አርአያ ፡ የባሕርይ ፡ ለውጥ፡ አይደለም ፤ ምልክቱ ፡ እውነትን ፡ ወደ፡ መረዳት፡ያደርሳል፡እንጂ፤ስለዚህ፡ነቢዩ፡ ሕዝቅኤል፡ይህ፡ራእይ፡የእግዚአብሔርን፡ የጌትነቱን፡ነገር፡ያስረዳል፡አለ፤የእግዚአ ብሔር ፡ የጌትነቱ ፡ መታወቂያ ፡ ነውና፡ መለወጥ፡ባሕርይን፡መልቀቅ፡አይደለምና፡ ተለውጧል ፤ ታይቶ ፡ ጠፍቷል ፡ ብሎ፡ ማሰብና፡መናገር፡ግን፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ ሰው፡ሆነ፡ከማለት፡የራቀ፡ነው።

፳፤ ክርስቶስ ፡ በእርሱ ፡ አድሮ ፡ የተናገረበት፡ ጳውሎስ፡እግዚአብሔር፡አብን፡በመልክ፡ የሚመስለውን፡በባሕርይ፡የሚተካከለውን፡ ክርስቶስን ፡ ለምእመናን ፡ ሲያስተምር፡ አምላክ፡ሰው፡የሆነ፡በኀድረት፡በውላጤ፡ አይደለም፤ራሱን፡ዝቅ፡አድርጎ፡የተገኘ፡ብሎ፡ ባሕርይንም፡ነሥቶ፡ነው፡እንጂ፡ብሎ፡ ይህን፡ነገር፡አስረዳን።

Scanned by CamScanner

በ፯ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

...ውእቱ፡አምሳሊሁ፡ ለእግዚአብሔር፡ እግዚአብሔር ፡ ...ኮት ፡ ወለሊሁኒ ፡ በምትሐት ፡ ወአምሳል ፡ ...ቱ፡ ወእኮ ፡ ... ፡ አካል ፡ ከማሁ ፡ አመሂ ፡ ...ቱ፡ዘአልቦቱ ፡ ... ፡ ህላዌ፡ መለኮት ፡እሙን፡ ...ወተሰብአ፡ህላዌ፡ መለኮት ፡እሙን፡ ...፡ተዋሐደ ፡ በሥጋ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ...ት ፡ ወለባዊት ፡ ተዋሕዶ ፡ አካላዊ ፡ ...ተዋሕዶ፡ውእቱ፡ዘክልኤሆሙ፡ኅቡረ።

...ዘንተ፡ሰመዮ፡ጳውሎስ፡አርአያሁ፡ ለእ ግዚአብሔር፡ዘዚአሁ፡ህላዌ፡ መለኮት ፡ወበ ...ትሕትና፡ትስብእትሂ፡ዘተወክፎ፡በፈቃዱ፡ ...እኮ፡በኀልዮ፡እላ፡ዘበጽድቅ፡ለሊሁ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ቃል ፡ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ዘእንበለ ፡ ...ሳጤ።

...፡ሥጋነ፡አመ፡ተዋሐደ፡ቦቱ፡በከርሠ፡ ድንግል፡ቅድስት፡ወተወክፈ፡ፍጻሜ፡ፅንስ፡ ...ደት ፡ ዘበአማን ፡ አመ ፡ ኀልቀ ፡ ...ተፈጸመ፡መዋዕሊሃ፡ከመ፡ትለድ፡በከመ፡ ...፡ወንጌል፡ወልደቱኒ፡ኮነ፡ብርሃነ፡መድ ...ኒትነ ፡ አሚሃ ፡ አእመርዎ ፡ መላእክት ፡ ...ኖዎ፡ስምዐ፡በኀበ፡ኖሎት፡ከመ፡ውእቱ፡ ...ውን፡ፍሥሐ፡ዐቢየ፡ለኵሉ፡ዓለም።

...፡ግብረ ፡ ህላዌነ ፡ ዘፈቃድ ፡ እንተ ፡ ...ባቲ ፡ ሐሜት ፡ ተዐገሠ ፡ በሥርዓት ፡ መድኃኒ ፡እንተ ፡ ባቲ ፡ ተመሰለ ፡ ኪያነ ፡ ...በለ ፡ኃጢአት ፡ አመ ፡ ጸውዐ ፡ ኀቤሁ ፡ ...፡ አምላክ ፡ወተዋሐደ ፡ ቦቱ ፡ ወሐመ ፡ ...፡ ሰብእ ፡ በሥጋ ፡ ዚአሁ ፡ ተወክፈ ፡ ...ማት ፡ እስመ ፡ ለሊሁ ፡ ፈጸመ ፡ ጽድቀ ፡ ...ሰብእ፡ዘውእቱ፡ረኃብ፡ወጽምእ፡ወንዋም፡ ...ም ፡ እምሐዊረ ፡ ፍኖት ፡ መከራ ፡ ...ቅለት።

...ቱ፡ለዝንቱ፡መምህር፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ ...ለመ፡ዓለም፡አሜን።

ተፈጸመ፡መጽሐፈ፡ስንክሳር።

...ት፡ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ አፈድፈዱ ፡ ምክረ ፡ ...፡ እግዚእነ ፡ማኅበረ ፡ አይሁድ ፡ ከመ ፡ ...ትልዎ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፯፡ሰዓት።

፳፩፤ እርሱ፤ እግዚአብሔር፡አብን፡በመለኮት፡እንዲ መስለው ፡ እንዲተካከለው ፡ እርሱ ፡ ራሱም ፡ አምላክ ፡እንደሆነ፡አካል፡የሌለው፡ምትሐት፡ ውላጤ ፡ እንዳይደለ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ በእውነት፡ ሰው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በአካላዊ ፡ ተዋሕዶም ፡ የምታውቅ ፡ የምትናገር ፡ ነፍስ፡ ያለችው ፡ ሥጋን ፡ በተዋሐደ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፤ (አልተለወጠም) ፤ ተዋሕዶም ፡ በአን ድነት፡ የመለኮትና፡የትስብእት፡ገንዘብ፡ነው።

፳፪፤ ስለዚህም ፡ ገንዘቡ ፡ በሚሆን ፡ በባሕርየ ፡ መለኮት ፡ወዶ፡በተቀበለው፡ሰው፡በመሆን፡ ትሕትናም ፡ አርአያሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አለው ፤ አስቦ ፡ የቀረ ፡ አይደለም ፤ የባሕርይ፡ አምላክ ፡ የሚሆን ፡ እርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ያለ፡መለወጥ፡ሰው፡ሆነ፡እንጂ።

፳፫፤ ሰው፡ልሁን፡ባለ፡ጊዜ፡ በንጽሕት፡ድንግል፡ ማሕፀን፡ሥጋን፡ተዋሕዶ፡ወንጌል፡እንደተ ናገረ ፡ የዕለት ፡ ፅንስ ፡ መሆንን ፡ ትወልድ ፡ ዘንድም ፡ የፅንሷ ፡ ወራት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ መወለድን፡ገንዘብ፡አደረገ፤ልደቱም፡የድኅ ነታችን ፡ መታወቂያ ፡ ሆነ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ መላእክት፡ዐወቁት፤እርሱ፡ለዓለሙ፡ሁሉ፡ ፍጹም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እንደሚሆንም ፡ በከብት፡ጠባቆች፡ዘንድ፡መሰከሩለት።

፳፬፤ ሐሜት፡የሌለበትን፡ወዶ፡የተዋሐዳትን፡የባሕ ርያችንን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ መድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ ፡ከኃጢአት ፡ በቀር ፡ እኛን ፡ በመሰ ለባት፡በሰውነቱ፡ገንዘብ፡አደረገ፤ አምላክ፡እን ደመሆኑ፡ሥጋን፡ለተዋሕዶ፡በአበቃው፡ጊዜ፡ በተዋሐደውም ፡ ጊዜ ፡ ሰውም ፡ እንደመሆኑ ፡ መከራ ፡ በሚስማማው ፡ በተዋሐደው፡ ሥጋ ፡ ታመመ ፤ እርሱ ፡ ሰው ፡ መሆኑን፡ የሚገልጥ በትን ፡ ሥራ ፡ ሠርቷልና ፡ ይኸውም ፡ መራብ ፡ መጠማት ፡ መተኛት ፡ መንገድ ፡ በመሄድ ፡ መድከም፡መከራ፡መቀበል፡መሰቀል፡ነው።

የዚህ ፡ መምህር ፡ በረከት ፡ ከሁላችን ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

ከስንክሳር፡መጽሐፍ።

በዚችም፡ቀን፡ይገድሉት፡ዘንድ፡የአይሁድ፡ ማኅበር ፡ በጌታችን ፡ ላይ ፡ ዳግመኛ ፡ አጽንተው፡መከሩ።

## በ፲፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡
ዓለም፡አሜን።

### ምንተኑ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፨ጸሎታ፡ ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፩ ወሀሎ፡አሐዱ፡መነኮስ፡ዘስሙ፡ማቴዎስ፡
መጋቢ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ዘያፈቅራ፡ለእግዝ
እትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡
ወላዲተ፡አምላክ፡በኵሉ፡ልቡ።

፪ ወአሐተ፡ዕለተ፡ሰትየ፡ወይነ፡ወሰክረ፡
ወኖመ፡ወኢተክህሎ፡ይትነሣእ፡ለጸሎት፡
ጊዜ፡መንፈቀ፡ሌሊት።

፫ ወሶበ፡ጽሕወ፡እምስካሩ፡ተንሥአ፡በጽባሕ፡
ለገይሥ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን።

፬ ወእንዘ፡የሐውር፡መጽአ፡ኀቤሁ፡አንበሳ፡
ወጥሕረ፡ከመ፡የኀጠ፡ወሶቤሃ፡መጽአት፡
ወለት፡ብርህት፡ጥቀ፡ወገሠፀቶ፡ለአንበሳ፡
ወሰደደቶ፡እምኔሁ።

፭ ወሖረ፡ውእቱ፡መነኮስ፡ኀበ፡ቤተ፡ክርስ
ቲያን፡እንዘ፡ያነክር፡በእንተ፡ይእቲ፡ወለት፡
ዘአድኀነቶ፡እምአንበሳ፡ወፈጺሞ፡ጸሎቶ፡
ሖረ፡ኀበ፡ግብሩ፡እስከ፡ምሴት።

፮ ወመስዮ፡ፈቀደ፡ይባእ፡ውስተ፡ምስካቢሁ፡
ወያዕርፍ፡ሶቤሃ፡ተንሥአ፡ላዕሌሁ፡ከልብ፡
እቡድ፡እምአንቀጸ፡ቤቱ፡ወሰረረ፡ከመ፡
ይንስኮ።

፯ ወመጽአት፡ዳግመ፡ይእቲ፡ወለት፡ብርህት፡
ወሰደደቶ፡ለከልብ፡ወአብአቶ፡ለውእቱ፡
መነኮስ፡ውስተ፡ምስካቡ፡ወአስከበቶ፡ወአን
በረት፡ትርአሶ፡ታሕተ፡ርእሱ፡ወከደነቶ፡
ዐጽፎ፡ወአተበት፡ላዕሌሁ፡በትእምርተ፡
መስቀል።

፰ ወይቤላ፡ውእቱ፡መነኮስ፡አ፡እግዝእትየ፡
እስእለኪ፡ከመ፡ትንግርኒ፡ስመኪ፡ወመኑ፡
አንቲ፡ወትቤሎ፡አነ፡ማርያም፡እመ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

### ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑርና፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡
የጸናች፡አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመ
ቤታችን፡ማርያም፡ያደረገችው፡ተአምር፡
ይህ፡ነው።

፩ በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡
አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመቤታችን፡
ማርያምን፡በፍጹም፡ልቡናው፡የሚወዳት፡
ስሙ፡ማቴዎስ፡የሚባል፡አንድ፡መነኮስ፡
ነበር።

፪ አንድ፡ቀንም፡ወይን፡ጠጥቶ፡ሰክሮ፡ተኛ፤
መንፈቀ፡ሌሊት፡ሲሆን፡ለጸሎት፡መነሣት፡
አልተቻለውም።

፫ ከስካሩም፡በነቃ፡ጊዜ፡ወደ፡ቤተ፡ክርስ
ቲያን፡ሊገሠግሥ፡በጥዋት፡ተነሣ።

፬ ሲሄድም፡አንበሳ፡ወደ፡እርሱ፡መጣ፤
ይበላውም፡ዘንድ፡ጮኸ፤ያንጊዜም፡እጅግ፡
ብርህት፡የሆነች፡ብላቴና፡መጣች፤አንበሳ
ውንም፡ገሥጻ፡ከእርሱ፡ዘንድ፡አባረረችው፡

፭ ከአንበሳ፡ስለ፡አዳነችው፡ወለት፡(እመቤታ
ችንን)፡እያደነቀ፡ወደ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡
ሄደ፤ጸሎቱንም፡በፈጸመ፡ጊዜ፡ወደ፡ተግባሩ፡
ሄዶ፡እስከ፡ምሽት፡ቆየ።

፮ ሲመሽም፡ወደማደሪያው፡ገብቶ፡ያርፍ፡
ዘንድ፡ወዶ፡ሲመጣ፡ከቤቱ፡መግቢያ፡ያበደ፡
ውሻ፡ተነሣበት፤ይነክሰውም፡ዘንድ፡ሮጠ፡

፯ ያቺ፡ብርህት፡የሆነች፡ብላቴና፡ሁለተኛ፡
መጥታ፡ውሻውን፡አባረረችው፡ያንንም፡
መነኵሴ፡ወደ፡ማረፊያው፡አስገብታ፡አስተ
ኛችው፤ከራሱ፡በታችም፡ትራስ፡አደረገ
ችለት፤ዐጽፉንም፡አለበሰችው፤በላዩም፡
በመስቀል፡ምልክት፡አማተበችበት።

፰ ያ፡መነኵሴም፡እመቤቴ፡ሆይ፡አንቺ፡ማን፡
እንደሆንሽ፡ስምሽን፡ትነግሪኝ፡ዘንድ፡እለም
ንሻለሁ፡አላት፤እርሷም፡እኔ፡የኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡እናት፡ማርያም፡ነኝ፡አለችው።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ወሰ፡ሰምዐ፡ነገራ፡ፈቀደ፡ከመ፡ይስግድ፡
ሁ፡ወየአምኅ፡እገሪሃ፡ወሶቤሃ፡ተሰወረቶ።

ወተንሢኦ፡በጽባሕ፡ኀለየ፡በልቡ፡በእንተ፡
ዘርእየ፡ወአእመረ፡ከመ፡እልክቱ፡ከልብ፡
ወእንበሳ፡እምትምይንቱ፡ለሰይጣን፡
እሙንቱ።

ወጠየቀ፡ከመ፡ዘአድኀነቶ፡እግዝእትነ፡
ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡
ወላዲተ፡አምላክ፡መስተሣህልት፡ዘትትራ
ድአሙ፡ለእለ፡ይትለአክዋ።

ወአምገ፡ነስሐ፡በእንተ፡ዘሰክረ፡ወኢተ
መይጠ፡ኀበ፡ስካር፡ግሙራ፡ወነበረ፡እንዘ፡
ይፀመዱ፡ለእግዚአብሔር፡ወይትለአክ፡
ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ዘእግዝእትነ፡
ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡
ወላዲተ፡አምላክ፡በኵሉ፡መዋዕለ፡
ሕይወቱ።

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ወይእቲ፡ብእሲት፡ዘዘከርናሃ፡ቀዳሚ፡ሶበ፡
ቀብዐቶ፡ዕፍረተ፡ለእግዚእነ፡ይቤሎ፡
እግዚእ፡ለስምዖን፡አ፡ስምዖን፡አስተጋብእ፡
ጠንተ፡ቅብዐ፡ወተዐቀብ፡ቦቱ፡ይኩን፡ኀቤከ፡
ለተዝካርየ።
ተዘከረኒ፡ቦቱ፡እስከ፡ዕለተ፡ምጽአትየ፡
ለዘነኒ።
አእምር፡አ፡ስምዖን፡እስመ፡ኵሉ፡ዘኢይት
ቀባዕ፡እምዝንቱ፡ቅብዕ፡ኢይክል፡ይባእ፡
ለመንግሥትየ።
አ፡ስምዖን፡ኢትትከዝ፡ባሕቱ፡ይብዛኅ፡አንክ
ሮትከ፡እስመ፡ጸዋዕከኒ፡ውስተ፡ቤትከ፡ወኢያ
ምጻእከ፡ሊተ፡ማየ፡ከመ፡እኅፅብ፡ቦቱ፡እገርየ፡
ወባቲሰ፡ብእሲት፡ኀፀበተኒ፡በአንብዓ።
አ፡ስምዖን፡ኢያምጻእከ፡ሊተ፡መንዲለ፡
ከመ፡እመዝምዝ፡ቦቱ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፱፤ ነገርዋንም፡በሰማ፡ጊዜ፡ይሰግድላት፡ዘንድ፡
እግሮቿንም፡ይስም፡ዘንድ፡ወደደ፤ያን፡ጊዜ፡
ተሰወረችው።

፲፤ ማለዳም፡በተነሣ፡ጊዜ፡ስለ፡አየው፡ራእይ፡
አሰበ፤እነዚያ፡አንበሳና፡ውሻ፡ከሰይጣን፡
ተንኰል፡እንደሆኑ፡ዐወቀ።

፲፩፤ ያዳነችውም፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡
ነፍስ፡የጸናች፡አምላክን፡የወለደች፡የሚአገለግ
ሏትን፡የምትረዳቸው፡ክብርት፡እመቤታችን፡
ድንግት፡ማርያም፡እንደሆነች፡ተረዳ።

፲፪፤ ከዚህም፡በኋላ፡ስለ፡መስከሩ፡ንስሓ፡ገባ፤
ወደ፡መስከርም፡ሁለተኛ፡ከቶ፡አልተመ
ለሰም፤በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡
በጸናች፡አምላክን፡በወለደች፡በክብርት፡እመ
ቤታችን፡ማርያም፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ውስጥ፡
ትሩፋት፡በመስራት፡መላ፡ዘመኑን፡እግዚአ
ብሔርን፡እያገለገለ፡ኖረ።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ይኑርና፡ጌታችን፡ፈጣሪያችን፡መድኃኒ
ታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ያደረገው፡ድንቅ፡
ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፤ ያስታወስናት፡ሴት፡ጌታ
ያቺ፡አስቀድመን፡ያስታወስናት፡ሴት፡ጌታ
ችንን፡ሽቱ፡በቀባችው፡ጊዜ፡ጌታ፡ስምዖንን፡
እንዲህ፡አለው፤ስምዖን፡ሆይ፡ይህን፡የሽቱ፡
ቅባት፡ሰብስበህ፡አኑረው፤ተጠንቀቅበትም፡
ለመታሰቢያየም፡በአንተ፡ዘንድ፡ይሁን።

፪፤ ለፍርድ፡እስከምመጣባት፡ቀን፡ድረስ፡
በእርሱ፡አስበኝ።

፫፤ ስምዖን፡ሆይ፡ከዚህ፡ቅባት፡ያልተቀባ፡ሁሉ፡
ወደ፡መንግሥቴ፡ይገባ፡ዘንድ፡እንደማ
ይችል፡ዕወቅ።

፬፤ ስምዖን፡ሆይ፡አትዘን፤ነገር፡ግን፡አድና
ቆትህ፡ይብዛ፤ወደቤትህ፡ጠራኸኝ፤
እግሮቼን፡አጥብበት፡ዘንድ፡ውኃ፡አላመጣህ
ልኝም፤ይቺ፡ሴት፡ግን፡በዕንባዋ፡አጠበችኝ።

፭፤ ስምዖን፡ሆይ፡አሸበት፡ዘንድ፡መሐረብም፡
አላመጣህልኝም።

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

፲፩፤ ወዛቲሰ ፡ ብእሲት ፡ መገመዘተኒ ፡ እገርየ ፡ በሥርዐተ፡ርእሳ።
፲፪፤ አ ፡ ስምዖን ፡ እስመ ፡ ፍላዊ ፡ ጌር ፡ ለእመ ፡ ተነገረ ፡ አሐዱ ፡ በግዕ ፡ እምነ ፡ ምዕት ፡ አባግዒሁ ፡ የኀድግ ፡ ተሰዓ ፡ ወተሰዓተ ፡ አባግዐ ፡ እለ ፡ ኢተገድፉ ፡ ወየሐውር ፡ ይኅሥሥ፡በግዐ፡ህጉለ።
፲፫፤ አ፡ስምዖን፡ምንተ፡ትብል፡በእንተ፡ብእሲ፡ ዘቦቱ፡ላዕለ፡ብእሲ፡ኀምስቱ፡ምዕት፡ዲናር፡ ወላዕለ፡ካልዕ፡ብእሲ፡ኀምሳ፡ዲናር፡ኀደገ፡ ሎሙ ፡ ኵሎ ፡ ንዋየ ፡ ዘላዕሌሆሙ ፡ መኑ ፡ ርቱዐ፡ ያፈቅሮ ፡ ወየአኵቶ ፡ እምኔሆሙ ፡ በዓለ፡ ኀምስቱ ፡ ምዕትኑ ፡ ወሚመ ፡ በዐለ ፡ ኀምሳ።
፲፬፤ ወይቤ ፡ ስምዖን ፡ እብልሰ ፡ **እግዚእየ** ፡ በዐለ ፡ ኀምስቱ፡ምዕት፡ዲናር።
፲፭፤ ወይቤሎ ፡ **እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ አእምር ፡ አ ፡ ስምዖን ፡ እስመ ፡ ዛቲ ፡ ብእሲት ፡ በዐለ ፡ ኀምስቱ ፡ ምዕት ፡ ዲናር ፡ ወካልእ ፡ ዘከማሃ፡በዐለ፡ኀምሳ፡አንተ፡ውእቱ።

ማህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ክፍል፡፫።
**ይ፡ዲ**፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፤፵፣፭።
ጸላእትየሰ፡እኩየ፡ይቤሉ፡ላዕሌየ።
ማእዜ፡ይመውት፡ወይሤዓር፡ስሙ።
ይባእ፡ወይርአይ፡ዘከንቶ፡ይነብብ።

ወንጌል፡ዘሉቃስ።

ምዕ፤፯፣፴፮-፶።
፴፮፤ ወይቤሎ ፡ አሐዱ ፡ እምፈሪሳውያን ፡ ከመ ፡ ይምሳሕ ፡ በኀቤሁ ፡ ወቦአ ፡ ቤተ ፡ ፈሪሳዊ ፡ ወረፈቀ።
፴፯፤ ወመጽአት ፡ ብእሲት ፡ ኃጥእት ፡ እምሰብአ ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡ አእሚራ ፡ ከመ ፡ ይመስሕ ፡ **እግዚእ፡ኢየሱስ**፡ውስተ፡ቤተ፡ፈሪሳዊ፡ወተ ሣየጠት፡ዕፍረተ፡ዘእልባስጥሮስ።
፴፰፤ ወቆመት፡ድኅሬሁ፡ኀበ፡እገሪሁ፡ወበከየት፡ ወአርሐሰት ፡ እገሪሁ ፡ በአንብዓ ፡ ወትመ

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፲፩፤ ይቺ ፡ ሴት ፡ ግን ፡ እግሬን ፡ በራስዋ ፡ ጠጉር፡ አሸችኝ።
፲፪፤ ስምዖን ፡ ሆይ ፡ ቸር ፡ ጠባቂ ፡ ከመቶ ፡ በጎች፡ አንድ ፡ በግ ፡ ቢጠፋ ፡ ያልጠፋትን ፡ ዘጠና፡ ዘጠኙን ፡ ትቶ ፡ የጠፋውን ፡ በግ ፡ ይፈልግ፡ ዘንድ፡ይሄዳል።
፲፫፤ ስምዖን፡ሆይ፡ሁለት፡ባለዕዳዎች፡ስለ፡አሉት፡ ሰው ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ድሪም፡ በሁለተኛውም ፡ ላይ ፡ ኀምሳ ፡ ድሪም ፡ ዕዳ፡ ያለባቸው ፡ የሁለቱንም ፡ ዕዳቸውን ፡ ተወላ ቸው፤ከእነዚህ፡በትክክል፡እጅግ፡ሊወደውና፡ ሊያመሰግነው ፡ የሚገባው ፡ የትኛው ፡ ነው? ባለ፡ አምስት ፡ መቶው ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ባለ፡ ኀምሳው፡ምን፡ትፈርዳለህ?አለው።
፲፬፤ ስምዖንም ፡ **ጌታዬ** ፡ ሆይ ፡ እኔስ ፡ ባለአምስት፡ መቶው፡ድሪም፡ነው፡እላለሁ፡አለ።
፲፭፤ **ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም** ፡ ስምዖን ፡ ሆይ፡ ዕወቅ ፡ ባለ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ድሪም ፡ ይቺ፡ ሴት፡ ናት ፤ ባለ ፡ ኀምሳው ፡ እንደርስዋ ፡ ባለ፡ ዕዳ፡የሆንከው፡አንተ፡ነህ፡አለው።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

ክፍል፡፫።
**ዲያቆኑ**፡ከወንጌል፡አስቀድሞ።

መዝ፤፵፣፭።
ጠላቶቼ፡ግን፡በእኔ፡ላይ፡ክፋትን፡ይናገራሉ።
መቼ ፡ ይሞታል ? ስሙስ ፡ መቼ ፡ ይሻራል?
ከንቱን፡የሚናገር፡ገብቶ፡ይመልከት፡ይበል።

የሉቃስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፯፣፴፮-፶።
፴፮፤ ከፈሪሳውያን ፡ አንዱ ፡ ከእሱ ፡ ዘንድ ፡ ምሳ፡ እንዲበላ ፡ ለመነው ፤ ወደ ፡ ፈሪሳዊው ፡ ቤት፡ ገብቶ፡ለምሳ፡ተቀመጠ።
፴፯፤ ከዚያች ፡ አገር ፡ ሰዎችም ፡ አንዲት ፡ ኀጢአተኛ ፡ ሴት ፡ **ጌታ ፡ ኢየሱስ** ፡ በፈሪ ሳዊው፡ቤት፡ምሳ፡እንደሚበላ፡አውቃ፡የአ ልባስጥሮስ፡ሽቱን፡ገዝታ፡መጣች።
፴፰፤ በስተኋላው ፡ ከእግሩ ፡ አጠገብ ፡ ቆማ ፡ እያለ ቀሰች ፡ እግሮቹን ፡ በእንባዋ ፡ አራሰች፤እግሮ

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ለማዝ፡በሥእርተ፡ርእሳ፡ወትስዕም፡እገሪሁ፡
ወትቀብኦ፡ዕፍረተ።
ወርእዮ፡ፈሪሳዊ፡ዘጸውዖ፡ኀለየ፡በልቡ፡
ወይቤ፡ሶበሁ፡ነቢይ፡ውእቱ፡ዝንቱ፡እምአ
ለመረ፡ከመ፡ኃጥእት፡ይእቲ፡ዛቲ፡
ብእሲት፡እንተ፡ትገሥሦ።
ወአውሥአ፡**እግዚእ፡ኢየሱስ**፡ወይቤሎ፡
ስምዖን፡ብየ፡ዘእብለከ፡ወይቤሎ፡ሊቅ፡በል።
ወይቤሎ፡ክልኤቱ፡ይፈድይዎ፡ለአሐዱ፡
ዘበለ፡ዕዳ፡አሐዱ፡ይፈድዮ፡ኀምስተ፡ምዕተ፡
ዲናረ፡ወካልኡኒ፡ኀምሳ።

ወኃጢአሙ፡ዘይፈድይዎ፡ኀደገ፡ሎሙ፡ለክ
ለሆሙ፡መኑ፡እንከ፡ርቱዕ፡ፈድፋደ፡
ያፈቅሮ፡እምኔሆሙ።
ወተሰጥዎ፡ስምዖን፡ወይቤሎ፡እብልሰ፡
ዘብዙኀ፡ኀደገ፡ሎቱ፡ወይቤሎ፡ሠናየ፡
ፈታሕከ።
ወተመይጠ፡ኀበ፡ይእቲ፡ብእሲት፡ወይቤሎ፡
ለስምዖን፡ትሬእያኑ፡ለዛቲ፡ብእሲት፡ቦእኩ፡
ቤተከ፡ወኢወሀብከኒ፡ማየ፡ጥቀ፡ለእገርየ፡
ወይእቲሰ፡በከየት፡ወበአንብዓ፡አርሐሰት፡
እገርየ፡ወበሥእርታ፡መዝመዘተኒ።

ወአንተሰ፡ኢተአማኅከኒ፡ወይእቲሰ፡እምዘ
ባእኩ፡ኢያንተገት፡ስዒመ፡እገርየ።

ወአንተሰ፡ኢቀባዕከኒ፡በዘይት፡ርእስየ፡
ወይእቲሰ፡ዕፍረተ፡ቀብዐተኒ፡እገርየ።
ወበእንተ፡ዝንቱ፡እብለከ፡ተኀድገ፡ላቲ፡
ኃጢአታ፡ብዙኀ፡እስመ፡ብዙኀ፡አፍቀ
ረትኒ፡ወዘሰ፡ውኁደ፡አፍቀረኒ፡ውኁድ፡
ኃጢአቱ፡ይትኀደግ፡ሎቱ፡ወዘሰ፡ብዙኀ፡
አፍቀረኒ፡ብዙኀ፡ይትኀደግ፡ሎቱ።
ወይቤላ፡ለይእቲ፡ብእሲት፡ተኀድገ፡ለኪ፡
ኀጢአትኪ።
ወአኀዙ፡እለ፡ይረፍቁ፡ይበሉ፡በበይና
ቲሆሙ፡መኑ፡ውእቱ፡ዝንቱ፡ዘየኀድግ፡
ኃጢአተ።
ወይቤላ፡ለይእቲ፡ብእሲት፡ሃይማኖትኪ፡
አድኃነተኪ፡እትዊ፡በሰላም።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ቹንም፡ትስም፤በራስ፡ጠጕርዋም፡ታሽው፡
ሽቱንም፡ትቀባው፡ነበር።
፴፱፤ የጠራው፡ፈሪሳዊም፡ባየ፡ጊዜ፡ይህ፡
ነቢይማ፡ቢሆን፡ኖሮ፡የምትዳስሰው፡ይህች፡
ሴት፡ኃጢአተኛ፡እንደሆነች፡ባላወቀ፡
ነበርን፡ብሎ፡በልቡ፡አሰበ።
፵፤ **ጌታ፡ኢየሱስም**፡መልሶ፡ስምዖን! የምልህ፡
ነገር፡አለኝ፡አለውና፡መምህር! ተናገር፡አለው።
፵፩፤ እርሱም፡እንዲህ፡አለው፤ለአንድ፡ባለ፡
ገንዘብ፡አበዳሪ፡ሁለት፡ተበዳሪዎች፡አሉት፤
አንዱ፡አምስት፡መቶ፡ወቄት፡ይከፍለዋል፡
ሁለተኛውም፡ኀምሳ፡ወቄት፡ይከፍለዋል።
፵፪፤ የሚከፍሉትም፡ባጡ፡ጊዜ፡ለሁለቱም፡
ተወላቸው፤እንግዲህ፡ከሁለቱ፡እጅግ፡
ሊወደው፡የሚገባው፡ማንኛው፡ነው?
፵፫፤ ስምዖንም፡መልሶ፡ብዙውን፡የተወለት፡
ነው፡እላለሁ፡አለው፤**ጌታም**፡መልካም፡
ፈረድህ፡አለው።
፵፬፤ ወደዚያችም፡ሴት፡መለስ፡ብሎ፡ስምዖንን፡
እንዲህ፡አለው፤ይህችን፡ሴት፡ታያታለህን?
ወደቤትህ፡ገባሁ፤ለእግሮቼም፡ውኃ፡ስንኳ፡
ፈጽመህ፡አልሰጠኸኝም፤ይህች፡ግን፡
አልቅሳ፡በእንባዋ፡እግሬን፡አጠበችኝ፤
በራስ፡ጠጕርዋም፡አሸችኝ።
፵፭፤ አንተስ፡ሰላምታ፡አልሰጠኸኝም፤እርስዋ፡
ግን፡ከገባሁ፡ጀምሮ፡እግሬን፡ከመሳም፡አላ
ቋረጠችም።
፵፮፤ አንተ፡ራሴን፡በዘይት፡አልቀባኸኝም፤
እርሷ፡ግን፡እግሬን፡ሽቱ፡ቀባችኝ።
፵፯፤ ስለዚህ፡ብዙ፡ኃጢአቷ፡ተሰረየላት፤እጅግ፡
ወዳኛለችና፡ጥቂት፡የሚወደኝ፡በጥቂቱ፡ይሰ
ረይለታል፤ብዙ፡የሚወደኝም፡በብዙ፡ይሰረ
ይለታል፡እልሃለሁ።

፵፰፤ ያችንም፡ሴት፡ኃጢአትሽ፡ተሰረየልሽ፡
አላት።
፵፱፤ ተጋባገሮቹም፡እርስበርሳቸው፡ኃጢአትን፡
የሚአስተሰርይ፡ይህ፡ማነው? ይሉ፡ጀመር።

፶፤ ሴቲቱንም፡ሃይማኖትሽ፡አዳነችሽ፤በሰላም፡
ግቢ፡አላት።

Scanned by CamScanner

## በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ድኅረ፡ወንጌል፡በስድስቱ፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

፩፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ሖረ ፡ ቢታንያ ፡ እምቅድመ ፡ መዋዕል ፡ ዘፋሲካ ፡ ወገብሩ ፡ ሎቱ፡ምሳሐ፡ቤተ፡ማርያ፡ወማርታ፡እኅታ።

፪፡ ወኮነት፡እኅተ፡ማርያ፡ቀዊማ፡እንዘ፡ትትለአኮሙ፡ወአሐዱ፡እምእለ፡ይረፍቁ፡ምስለ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡አልዓዛር፡እኅዋሆሙ።

፫፡ ወነሥአት ፡ ማርያም ፡ ዕፍረተ ፡ ልጥረ ፡ ዘናርዱ፡ዘብዙኅ፡ሤጡ፡ወቀብዐቶ፡ኪያሁ፡እገሪሁ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ወመዝመዘቶ፡በሥዕርተ፡ርእሳ።

፬፡ ወመልአ፡ለይሁዳ፡አስቆሮታዊ፡መግብኢ፡ቅንአት፡ሰይጣናዊ፡ወይቤ፡በጕህሉት፡ወበኅሊና፡መሪር፡ዘምሉእ፡እኪተ፡ወኵሎ፡አድልዎ፡ለምንት፡ዝ፡ዕፍረት፡ዘኢተሰይጠ፡በሠለስቱ፡ምዕት፡ዲናር፡ወይትወሀብ፡ለነዳያን።

፭፡ ወኢይቤ፡ዘንተ፡በኅሊና፡ሠናይ፡በአፍቅሮ፡ነዳያን፡ባሕቱ፡ኮነ፡ሰራቂ፡ወይነሥእ፡ዘይወድይዎ፡ውስተ፡ሣፁን።

፮፡ ይቤ፡መድኅን፡ለምንት፡ታደክምዋ፡እስመ፡ይእቲ ፡ ቀብዓተኒ ፡ ለዕለተ ፡ ቀበርየ ፡ ወነዳያንሰ፡ዘልፈ፡ምስሌክሙ፡ኵሎ፡ጊዜ።

፯፡ ለንቅረብ ፡ እንከ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወንብኪ፡ቅድሜሁ፡ወናርሕስ፡እገሪሁ፡በአንብዕነ ፡ ወንስአሎ ፡ ከመ ፡ ይጸግወነ ፡ ለነ ፡ ሥርየተ፡ኃጣውኢነ።

ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕማማቲሁ፡አድኃነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።

ማኅተመ፡ጸሎትስ፡ከመ፡ቀዳሚ፡ፈጽም።

### ምዕራፍ፡፴፫።

ክፍል፡፩።

በተሰዓቱ፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

አሪት፡ዘልደት።

ምዕ፡፳፬፡፩–፱።

፩፡ ወልህቀ ፡ አብርሃም ፡ ወኀለፈ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ወባረኮ፡እግዚአብሔር፡ለአብርሃም፡በኵሉ።

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ረቡዕ ፡ ከቀኑ ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ ከወንጌል፡በኋላ፡የሚነበብ።

፩፡ ከፋሲካ ፡ ቀኖች ፡ በፊት ፡ ፈጣሪያችን ፡ ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ ቢታንያ ፡ ሄደ ፤ በማርያና፡በእኅቷ፡በማርታ፡ቤት፡ምሳ፡አዘጋጁለት።

፪፡ የማርያ ፡ እኅት ፡ ማርታም ፡ ቆማ ፡ ታሳልፍላቸው ፡ ነበር ፤ ከጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ጋር፡ ለግብዣ ፡ ከተቀመጡት ፡ አንዱ ፡ ሙቶ፡ የተነሣው፡ወንድማቸው፡አልዓዛር፡ነው።

፫፡ ማርያምም ፡ ዋጋው ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ የሆነ፡ ጵስጥቂስ ፡ የሚባል ፡ የጥሩ ፡ ናርዶስ ፡ ሽቱ፡ ንጥር ፡ ወስዳ ፡ የጌታ ፡ ኢየሱስን ፡ እግሩን፡ ቀባችው፤በራስ፡ጠጕርዋም፡አሸችው።

፬፡ ጌታን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ የሚሰጥ ፡ አስቆሮታዊው፡ይሁዳ፡ሰይጣናዊ፡ቅንአትን፡ተመላ፤ክፋትና፡አድልዎን፡በተመላ፤በመረረ፡ኅሳብና፡ተንኰል፡ይህ፡ሽቱ፡በሦስት፡መቶ፡ወቄት፡ወርቅ፡ተሽጦ፡ለምን፡ለድኆች፡አይሰጥም፡ነበር፡አለ።

፭፡ ለድኆች ፡ በማዘን ፡ በበጎ ፡ ኅሳብ ፡ ይህን፡ አላለም፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሌባ ፡ ስለሆነ ፡ በሙዳየ፡ ምጽዋት፡የሚጨመረውን፡ይወስድ፡ነበርና።

፮፡ መድኃኒታችንም ፡ ለምን ፡ ታዳክሟታላችሁ፡ እርስዋ ፡ ለመቀበሪያዬ ፡ ሊሆን ፡ አስቀድማ፡ ቀብታኛለችና ፤ ድኆችም ፡ ዘወትር ፡ ከእናንተ፡ጋራ፡አሉ፡አላቸው።

፯፡ እንግዲህ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ቀርበን፡እያለቀስን፡እግሩን፡በዕንባችን፡እናርሰው፤ለኃጢአታችን ፡ ሥርየትን ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ እንለምነው።

መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡ሰው፡ሁኖ፡መጣ፤መከራን፡ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።

የጸሎቱ፡ፍጻሜ፡እንደ፡ፊተኛው፡ነው።

### ምዕራፍ፡፴፫።

ክፍል፡፩።

ረቡዕ፡ከቀኑ፡በዘጠኝ፡ሰዓት፡የሚነበብ።

ኦሪት፡ዘልደት፡(ዘፍጥረት)።

ምዕ፡፳፬፡፩–፱።

፩፡ አብርሃምም፡አረጀ፤ዘመኑም፡አለፈ፤እግዚአብሔርም፡አብርሃምን፡በሁሉ፡አከበረው።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

፬፡ ወለምንት፡አውፃእክሙ፡ትዕይንቶ፡ለእግዚ
አብሔር፡ ውስተ፡ ገዳም፡ ከመ፡
ትቅትሉነ፡ለነ፡ወለእንስሳነሂ፡በጽምዕ።
፭፡ ወለምንት፡ ኀበ፡ ዝንቱ፡ ዘአውፃዕክሙነ፡
እምግብጽ፡ከመ፡ታምጽኡነ፡ውስተ፡ዝንቱ፡
መካን፡እኩይ፡ዘኢይዘራዕ፡ቦቱ፡ወዘአልቦ፡
በለስ፡ወአዕፃዳተ፡ወይን፡ወሮማን፡ወአልቦ፡
ማይ፡ለሰትይ።
፮፡ ወሖሩ፡ሙሴ፡ወአሮን፡እምቅድመ፡ገጸሙ፡
ለትዕይንት፡ ኀበ፡ ኆኅተ፡ ደብተራ፡
ዘመርጡል፡ ወወድቁ፡ በገጸሙ፡ ወአስተ
ርአየ፡ስብሐተ፡እግዚአብሔር፡ ሎሙ።
፯፡ ወነበቦ፡እግዚአብሔር፡ ለሙሴ፡ ወይቤሎ፡
ንሥእ፡ለዛቲ፡በትር።
፰፡ ወአስተጋብኡ፡ትዕይንተ፡አንተ፡ወአሮን፡
እኁከ፡ወበልዋ፡ለኰኵሕ፡በቅድሜሆሙ፡
ወትሁብ፡ማየ፡ወታመጽኡ፡ሎሙ፡ማየ፡
እምኰኵሕ፡ወታሰትዩ፡ትዕይንተ፡ወእንስሳ
ሆሙኒ።
፱፡ ወነሥአ፡ሙሴ፡ለእንታክቲ፡በትር፡እንተ፡
እምቅድሜሁ፡ ለእግዚአብሔር፡ በከመ፡
አዘዞ፡እግዚአብሔር።
፲፡ ወአስተጋብእዎሙ፡ ሙሴ፡ ወአሮን፡ ለትዕ
ይንት፡ ቅድሜሃ፡ ለይእቲ፡ ኰኵሕ፡
ወይቤሎሙ፡ ስምዑኒ፡ ከኃድያን፡ ቦኑ፡
እምዛቲ፡ኰኵሕ፡ናወፅእ፡ለክሙ፡ማየ።
፲፩፡ ወአልዓለ፡ሙሴ፡በትሮ፡በእዴሁ፡ወዘበጣ፡
ለይእቲ፡ኰኵሕ፡በእንታክቲ፡በትር፡ካዕበ፡
ወወጽአ፡ማይ፡ብዙኅ፡ወአስተዩሙ፡ለትዕ
ይንት፡ወለእንስሳሆሙ።
፲፪፡ ወነበቦሙ፡ እግዚአብሔር፡ ለሙሴ፡
ወለአሮን፡ ወይቤሎሙ፡ እስመ፡ ኢአመን
ክሙኒ፡ ከመ፡ ትቀድሱኒ፡ ቅድሜሆሙ፡
ለደቂቀ፡እስራኤል፡በበይነ፡ዝንቱ፡ኢታበው
እዎሙ፡አንትሙ፡ለእሉ፡ትዕይንት፡ውስተ፡
ምድር፡ዘእነ፡ወሀብክዎሙ።
፲፫፡ ወዝንቱ፡ ማይ፡ ዘቅስት፡ ውእቱ፡ እስመ፡
ተዋቀሱ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡ቅድመ፡እግዚአ
ብሔር።
ዘያመልክ፡በፍጡር፡ርጉም፡ውእቱ፡በል።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፬፡ እኛንም፡ ከብቶቻችንንም፡ በውኃ፡ ጥም፡
ትገሉን፡ዘንድ፡የእግዚአብሔርን፡ ሠራዊት፡
ወደዚህ፡ምድረ፡በዳ፡ለምን፡አወጣችሁ።
፭፡ ዘር፡ወደማይዘራበት፤በለስ፡ሮማን፡ወይን፡
የሚጠጣም፡ውኃ፡ወደሌለበት፡ክፉ፡ወደ፡
ሆነ፡ወደዚህ፡ቦታ፡ታመጡን፡ዘንድ፡ይህ፡
ከግብጽ፡ያወጣችሁን፡ማውጣት፡ለምንድን፡
ነው?አሉት።
፮፡ አሮንና፡ሙሴም፡ከሠራዊቱ፡ፊት፡ልዩ፡ወደ፡
ሆነች፡ ድንኳን፡ ደጃፍ፡ ሂደው፡ በግንባ
ራቸው፡ ወደቁ፤የእግዚአብሔር፡ ብርሃንም፡
ተገለጸላቸው።
፯፡ ያችን፡በትር፡ያዛት፡ብሎ፡እግዚአብሔር፡
ለሙሴ፡ነገረው።
፰፡ ወንድምህ፡አሮንና፡አንተ፡ሠራዊቱን፡ሰብስ
ባችሁ፡ደንጊያዪቱን፡በፊታቸው፡እዘዙአት፤
ውኃን፡ታስገኛለች፤ከደንጊያ፡ውኃን፡አፍል
ቃችሁ፡ሠራዊቱን፡ከብቶቻቸውንም፡ታጠጧ
ቸዋላችሁ፡ብሎ፡ለሙሴ፡ነገረው።
፱፡ ሙሴም፡ እግዚአብሔር፡ እንዳዘዘው፡
ከእግዚአብሔር፡ ያገኛትን፡ ያችን፡ በትር፡
ያዘ።
፲፡ ሙሴና፡ አሮን፡ በዚያች፡ ደንጊያ፡ ፊት፡
ሠራዊቱን፡ ሰብስበው፡ እናንተ፡ እምቢ
ተኞች፡ስሙኝ! በውኑ፡ከዚች፡ደንጊያ፡ውኃ፡
እናፈልቅላችሁ፡ነበርን፡አላቸው።
፲፩፡ ሙሴም፡በትሩን፡በእጁ፡አንሥቶ፡በዚያች፡
በትር፡ያቺን፡ደንጊያ፡ሁለት፡ጊዜ፡መታት፤
ብዙ፡ውኃም፡ወጣ፡ሠራዊቱንም፡ከብቶቻቸ
ውንም፡አጠጣቸው።
፲፪፡ በእስራኤል፡ ልጆች፡ ፊት፡ ታከብሩኝ፡
ዘንድ፡አላመሰገናችሁኝምና፡ስለዚህ፡ነገር፡
እናንተ፡ እነዚህን፡ ሠራዊት፡ እኔ፡ ወደ፡
ሰጠኋቸው፡ አገር፡ አታገቧቸውም፡ ብሎ፡
እግዚአብሔር፡ ለአሮንና፡ ለሙሴ፡ ነገ
ራቸው።
፲፫፡ የእስራኤል፡ልጆች፡በእግዚአብሔር፡ፊት፡
ተከራክረዋልና፡ይህም፡ውኃ፡ክርክር፡የተደ
ረገበት፡ውኃ፡ተባለ።
በፍጡር፡የሚያመልክ፡ርጉም፡ነው።

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ወይቤሎ ፡ አብርሃም ፡ ለገብሩ ፡ ዘይልህቅ ፡
ውስተ፡መንግሥቱ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ንዋዩ፡ደይ፡
እዴከ፡ላዕለ፡እዴየ።
ወአምሕለከ ፡ በአምላከ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡
ከመ ፡ ኢትንሣእ ፡ ብእሲተ ፡ ለወልድየ ፡
ይሥሐቅ ፡ እምአዋልደ ፡ ከነዓን ፡ እለ ፡
ምስሌሆሙ፡አኃድር፡አነ።
ሰመ ፡ ሐር ፡ ውስተ ፡ ብሔር ፡ ኀበ ፡
ተወለድኩ ፡ ወንሣእ ፡ ብእሲተ ፡ ለወልድየ ፡
ይሥሐቅ፡በሀየ።
ወይቤሎ ፡ ገብሩ ፡ ለእመኬ ፡ ኢፈቀደት ፡
ይእቲ፡ብእሲት ፡ ትምጻእ ፡ ምስሌየ ፡ ዘንተ ፡
ብሔረ ፡ አግብእኑ ፡ ለወልድከ ፡ ውስተ ፡
ውእቱ፡ምድር፡እምኀበ፡መጻእከ።
ወይቤሎ ፡ አብርሃም ፡ ዑቅ ፡ ኢታግብእ ፡
ለወልድየ፡ሀየ።
እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡
ዘአውፅአኒ ፡ እምቤተ ፡ አቡየ ፡ ወእምድር ፡
እንተ፡ተወለድኩ ፡ በውስቴታ ፡ ወዘመሐለ ፡
ሊተ፡ወይቤለኒ፡ለከ፡እሁበከ፡ዘንተ፡ምድረ፡
ወለዘርዕከ ፡ ውእቱ ፡ ይፌኑ ፡ መልአኮ ፡
ቅድሜከ ፡ ወትነሥእ ፡ ብእሲተ ፡ ለወልድየ ፡
እምሀየ።
ወእመሰ ፡ ኢፈቀደት ፡ ባሕቱ ፡ ይእቲ ፡
ብእሲት፡ ትምጻእ ፡ ምስሌከ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡
ምድር ፡ ንጹሕ ፡ አንተ ፡ እመሐላ ፡ ወዘንተ ፡
ዑቅ፡ከመ፡ኢታግብእ፡ለወልድየ፡ህየ።
ወወደየ፡እዴሁ፡ውእቱ፡ገብር፡ላዕለ፡እደ፡
አብርሃም ፡ እግዚኡ ፡ ወመሐለ ፡ ሎቱ ፡
በእንተዝ፡ነገር።

አሪት፡ዘኍልቍ፡

ምዕ፤፳፡፩–፲፫።

ወገብኡ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ወኵሉ ፡ ተዓይ
ነሆሙ ፡ እምገዳም ፡ ዘጺን ፡ በቀዳሚ ፡ ወርኅ ፡
ወበጽሑ ፡ ውስተ ፡ ቃዴስ ፡ ወበህየ ፡ ሞተት ፡
ማርያም ፡ ወተቀብረት።
ወአልቦቱ ፡ ማይ ፡ ለትዕይንት ፡ ወተጋብኡ ፡
ሕዝብ፡ላዕለ፡ሙሴ፡ወላዕለ፡አሮን።
ወተላኰዎ ፡ ለሙሴ ፡ ወይቤልዎ ፡ እምኀየሰነ ፡
ሞትነ ፡ በሞተ ፡ አበዊነ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአ
ብሔር።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፱፤ አብርሃምም፡በንገዘቡ፡ሁሉ፡ላይ፡የተሾመ፡
ከፍ፡ያለ፡አገልጋዩን፡በእጅህ፡እጄን፡ጽፋ፡
አለው።
፲፤ አሁን ፡ አብሬአቸው ፡ ካለሁት ፡ ከከነዓን ፡
ልጆች፡ለልጄ፡ለይሥሐቅ፡ሚስት፡እንዳታ
ጋባው፡ሰማይና፡ምድርን፡በፈጠረ፡አምላክ፡
አምልሃለሁ፡አለው።
፲፩፤ ወደተወለድኩባት ፡ አገሬ ፡ ሂደህ ፡ ለልጄ ፡
ለይሥሐቅ፡ከዚያ፡ሚስት፡አጋባው፡እንጂ።
፲፪፤ አገልጋዩም፡ያች፡ሴት፡ከእኔ፡ጋራ፡ወደዚህ፡
አገር ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ ባትወድሳ ፡ ልጅህን ፡
ወደወጣህበት፡አገር፡ልመልሰውን፡አለው።
፲፫፤ አብርሃምም ፡ ልጄን ፡ ወደዚያ ፡ እንዳትመ
ልሰው፡እወቅ፡አለው።
፲፬፤ ከአባቴ ፡ ቤት ፡ ከተወለድኩባትም ፡ አገር ፡
ያወጣኝ ፡ ይህቺንም ፡ አገር ፡ ለአንተ ፡ እሰጥ
ሃለሁ ፡ ለልጆችህም ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡ ብሎ ፡
የማለልኝ፡ሰማይና፡ምድርን፡የፈጠረ፡እግዚ
አብሔር፡መልአኩን፡በፊትህ፡ይሰድልሃል፤
ለልጄም፡ከዚያ፡ሚስት፡ታመጣለታለህ።
፲፭፤ ነገር፡ግን፡ያች፡ሴት፡ካንተ፡ጋራ፡ወደዚች፡
አገር ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ ካልወደደች ፡ አንተ ፡
ከመሐላው፡ንጹሕ፡ነህ፤ልጄንም፡ወደዚያች፡
አገር፡እንዳትመልሰው፡ዕወቅ፡አለው።
፲፮፤ ያም፡አገልጋይ፡ስለዚህ፡ነገር፡በእጁ፡የአብር
ሃምን፡የጌታውን፡እጅ፡ጸፍቶ፡ማለለት።

አሪት፡ዘኍልቍ።

ምዕ፤፳፡፩–፲፫።

፩፤ የእስራኤል፡ልጆችና፡ሠራዊቶቻቸው፡ሁሉ፡
በመጀመሪያ ወር፡ፂን፡የሚባል፡እንጨት፡
ከአለበት፡ምድረ፡በዳ፡ተጓዙ፤ወደቃዴስም፡
ደረሱ፤ማርያም፡በዚያ፡ሙታ፡ተቀበረች።
፪፤ ለሠራዊቱም፡ውኃ፡አልነበረም፤ሕዝቡም፡
በአሮንና፡በሙሴ፡ላይ፡ተሰበሰቡ።
፫፤ ሙሴንም ፡ ነቀፉት ፤ በእግዚአብሔር ፡
ትእዛዝ፡ እንደ ፡ አባቶቻችን ፡ ብንሞት ፡
በተሻለን፡ነበር፡አሉት።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ምሳሌያተ ፡ ሰሎሞን ፡ በረከቱ ፡ ተሀሉ ፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፩፡፲–፴፬።

፲ ፡ ወልድየ ፡ ኢያስሕቱከ ፡ ሰብእ ፡
ረሲዓን ፡ ወኢትፍቅድ ፡ እመ ፡ አስተብቍ
ዑከ፡እንዘ፡ይብሉ፡ነዓ፡ተሳተፍ፡ምስሌነ፡
ደመ።
፲፩ ወንድፍን፡ውስተ፡ምድር፡ብእሴ፡ጻድቀ፡
በዐመፃ።
፲፪ ወንኅጦ፡ከመ፡ገሀነም፡ሕያዎ፡ወንሥዓር፡
እምድር፡ዝክሮ።
፲፫ ወጥሪቶ፡ብዙኀ፡ናስተጋብእ፡ወንምላዕ፡
አብያቲነ፡በርበሮ።
፲፬ ወአንተኒ ፡ ኅበር ፡ ምስሌነ ፡ ወአሐዱ ፡
ቍናማት፡ይኩነነ፡ለኵልነ፡ወመስነቅት፡
አሐቲ፡ትኩነነ።

፲፭ ኢትሖር፡ወልድየ፡ምስሌሆሙ፡ፍኖተ።
፲፮ አግኅሥ ፡ እገሪከ ፡ እምአሠሮሙ ፡ እስመ ፡
ለእኩይ ፡ ይረውፃ ፡ እገሪሆሙ ፡ ወይፈጥና ፡
ለከዒወ፡ደም።
፲፯ እስመ ፡ አኮ ፡ በከ ፡ ዘይረብቡ ፡ መሥገርተ ፡
ለአዕዋፍ።
፲፰ እሙንቱሰ፡እለ፡ቀቲለ፡ለመዱ፡ይዘግቡ፡
ሎሙ፡እከየ፡ወድቀቶሙ፡ለሰብእ፡ኃጥአን፡
እኩይ።
፲፱ ዝ ፡ ፍናው ፡ ውእቱ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡
ይፈጽሙ፡ኃጣውአ፤ኃጢአት፡ወትዕግልት፡
ነፍሰሙ፡ተኀጕል።
፳ ጥበብ፡በፍናው፡ትሴባሕ፡ወበመራህብት፡
ትሁብ፡ቃላ።

፳፩ ወውስተ ፡ አርእስተ ፡ ጥቅም ፡ ትሰ
በክ ፡ ወውስተ ፡ አናቅጺሆሙ ፡ ለኃ
ያላን፡ትፀመድ፡ወውስተ፡አናቅጸ፡ሀገር፡
ጥብዕ፡ትብል።
፳፪ መጠነ፡መዋዕል፡የዋሃን፡በሙ፡ጽድቅ፡ወኢ
ይትኀፈሩ።
፳፫ አብዳን፡ማእዜኑ፡ረሲዓን፡ታፈቅሩ፡ስሕተተ፡
ዓብዳንሰ፡ፈታውያነ፡ጽእለት፡እሙንቱ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። 

በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ትኑርና ፡
ሰሎሞን ፡ መስሎ ፡ ያስተማረው ፡ ትምህርት ፡
ይህ፡ነው።

ምዕ፡፩፡፲–፴፬።

፲፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ የዘነጉ ፡
ሰዎች ፡ አያስቱህ ፤ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ደም ፡
ብማፍሰስ፡ ተባበረን ፡ ብለው ፡ ቢማልዱህ ፡
እሽ፡በጄ፡አትበላቸው።
፲፩፤ ዕውነተኛ ፡ ሰውን ፡ በግፍ ፡ ገድለን ፡ እንቅ
በረው።
፲፪፤ በሕይወትም፡ሳለ፡እንደ፡መቃብር፡እንዋጠው፤
ስም፡አጠራሩንም፡ከዚህ፡ዓለም፡እናጥፋ።
፲፫፤ ብዙ ፡ ገንዘቡንም ፡ ሰብስበን ፡ በቤታችን ፡
እንምላ።
፲፬፤ አንተም፡ከእኛ፡ጋራ፡ተባበር፤አንድ፡የዕቃ፡
አቀማጻ፡(ኮረጆ)፡ለሁላችን፡ይሁነን፤አንዲት፡
የስንቅ፡ስልቻም፡ለሁላችን፡ትብቃን፡ብለው፡
ቢማልዱህ፡እሺ፡በጄ፡አትበላቸው።
፲፭፤ ልጄ፡ከነርሳቸው፡ጋራ፡መንገድን፡አትሂድ።
፲፮፤ እግርህን፡ከፍለጋቸው፡አርቅ፤እግሮቻቸው፡
ለክፋት፡ይሮጣሉና፤ደምንም፡ለማፍሰስ፡ይፈ
ጥናሉና።
፲፯፤ ለወፎች፡ወጥመድን፡የሚዘረጉ፡በከንቱ፡አይ
ደለምና።
፲፰፤ ሰውንም፡መግደል፡የለመዱ፡እነዚህ፡ብዙ፡
መከራ፡ይቀበላሉ፤የኃጢአተኞችም፡ሰዎች፡
ሞታቸው፡ክፉ፡ነው።
፲፱፤ ይህ፡ሥራ፡ኃጢአትን፡ፈጽመው፡ለሚሠሩ፡
ሰዎች፡ሁሉ፡ነው፤ኃጢአት፡ቅሚያ፡ሰውነታ
ቸውን፡ታጠፋለች።
፳፤ ጥበብ፡በጐዳና፡ትመሰገን፡ነበር፡(በዘመነ፡
አበው)፡በአደባባይ፡ቃልዋን፡ትሰጥ፡ነበር፤
(በዘመነ፡መሳፍንት)።
፳፩፤ በቅጥሩም፡ራስ፡ላይ፡ትነገር፡ነበር፡(በዘመነ፡
ነገሥት)፡በኃይለኞች፡በሮች፡ታገለግል፡ነበር፡
(በዘመነ፡ካህናት)፡በሀገር፡በሮችም፡የጨከናችሁ፡
ሁኑ፡ትል፡ነበር፤(በዘመነ፡ሰማዕታት፡ብሊት)
፳፪፤ የዋሆች ፡ ሰዎች ፡ ባለ ፡ በዘመናቸው ፡ ሁሉ ፡
ጽድቅ፡አላቸው፤ተናግረው፡አያፍሩም።
፳፫፤ እግዚአብሔርን ፡ የዘነጋችሁ፡ሰዎች፡እስከ፡
መቼ ፡ ድረስ ፡ ስሕተትን ፡ ትወዳላችሁ ?

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ወረሲዓነ ፡ ክዊኖሙ ፡ ጸልኡ ፡ አእምሮ ፡ ወርሱሐነ ፡ ኮኑ ፡ ለእለ ፡ ይዘልፍዎሙ ፡ ለምንት፡ ትመይጡ ፡ ዘለፋየ።

፳፬ ወናሁ፡አነ፡እነግረክሙ፡እስትንፋሰ፡ቃልየ፡ ወእሜህረክሙ፡ነገረ፡ዚአየ።

፳፭ እስመ ፡ ጸዋዕኩ ፡ ወኢያውሣእክሙኒ ፡ ሰፋሕኩ፡እደውየ፡ወኢያጽማእክሙኒ።

፳፮ ወአብዛኅኩ ፡ ነገረ ፡ ወኢተሰጠውክሙኒ ፡ ወምኑነ፡ረሰይክሙ፡ትእዛዝየ፡ወዘለፋየኒ፡ ኢነጸርክሙ።

፳፯ ወአነሂ ፡ በሀጕልክሙ ፡ እሰሕቅ ፡ ወእትፌሣሕ፡ሶበ፡ይመጽአክሙ፡ተሠርዎ።

፳፰ ወሶበ ፡ ይመጽአክሙ ፡ ግብተ ፡ ሀከክ ፡ ወሙስናሂ ፡ ከማሁ ፡ ሶበ ፡ ይመጽአክሙ ፡ ለአሥግሮ፡ወሶበ፡ይመጽአክሙ፡ምንዳቤ፡ ወተፄውዎ፡ሀሎኩ፡ሀየ።

፳፱ ወሶበ ፡ ትጼውዑኒ ፡ አነሂ ፡ ኢይሰምዐክሙ፡የኀሥሡኒ፡እኩያን፡ወኢይረክቡኒ።

፴ እስመ፡ጸልእዋ፡ለጥበብ፡ወቃለ፡እግዚአብሔርኒ፡ይስምዑ፡ኢፈቀዱ።

፴፩ ወኢፈቀዱ፡ይነጽሩ፡ዘዚአየ፡ምክረ፡ወያስተራሐሱ፡ኵሎ፡ዘዚአየ፡ዘለፋ።

፴፪ እንከሰኬ፡ይብልዑ፡ፍሬ፡ምግባሮሙ፡ወዘዚአሆሙ፡ኃጢአተ፡ይጽገቡ።

፴፫ እስመ ፡ ኢተመይጠቶሙ ፡ ለአብዳን ፡ ትቀትሎሙ ፡ እምእንተ ፡ ገፍዑ ፡ ደቂቅ ፡ ይትቀተሉ ፡ ወሐተታሆሙ ፡ ለረሲዓን ፡ ትቀትሎሙ።

፴፬ ወዘሰ ፡ ኪያየ ፡ ይሰምዕ ፡ ይሄሉ ፡ በተስፋ ፡ ወየዐርፍ ፡ ዘእንበለ ፡ ድንጋፄ ፡ እምኵሉ ፡ እኩይ።

### ትርጓሜ፡ምሳሌያተ፡ሰሎሞን።

፩ ወልድየ፡ኢያስሕትከ፡እስከ፡ኀበ፡ይብል፡ እምኵሉ፡እኩይ።

፪ ይቤ፡መተርጕም፡ወበእንተሰ፡ቃሉ፡ወልድየ፡ ኢያስሕትከ ፡ ሰብእ ፡ ረሲዓን ፤ ይትረጐም ፤

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ሰነፎች ፡ ግን ፡ መሳደብን ፡ የሚወዱ ፡ ናቸው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ የዘነጉ ፡ ሁነው ፡ ዕውቀቱን ፡ ጠሉ ፡ ለሚአስተምሩአቸው ፡ ለነቢያትም ፡ ቢአጥቡት ፡ አይጠራ ፡ ሆኑ ፤ ምክሬን፡ለምን፡ትለውጣላችሁ።

፳፬ እነሆ ፡ እኔ ፡ ረቂቅ ፡ ቃሌን ፡ እነግራችኋለሁ፤ ነገሬንም፡አስተምራችኋለሁ።

፳፭ ብጠራችሁ፡አልመለሳችሁልኝም፤እጄንም፡ ብዘረጋ፡አላደመጣችሁኝምና።

፳፮ ትምህርቴን ፡ ባስተምራችሁ ፡ አልተቀበላችሁኝምና ፡ ትእዛዜንም ፡ የተናቀ ፡ አድርጋችኋልና፡ምክሬንም፡አልተመለከታችሁምና።

፳፯ እኔም፡ድንገት፡መከራ፡በመጣባችሁ፡ጊዜ፡ በጥፋታችሁ፡ደስ፡ይለኛል።

፳፰ ድንገት ፡ ፀብ ፡ ክርክር ፡ በመጣባችሁ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚሁም ፡ ለማጥፋት ፡ ጥፋት ፡ በመጣባችሁ ፡ ጊዜ ፡ መማረክና ፡ መከራም ፡ በመጣባችሁ፡ጊዜ፡እኔ፡በዚያ፡አለሁ።

፳፱ ከመከራም፡አድነን፡ብላችሁ፡በጠራችሁኝ፡ ጊዜ ፡ እኔም ፡ ልመናችሁን ፡ አልሰማም ፤ ክፉዎች፡ሰዎች፡ይፈልጉኛል፤አያገኙኝም።

፴ ጥበብን ፡ ጠልተዋታልና ፤ የእግዚአብሔርንም፡ቃል፡ይሰሙ፡ዘንድ፡አልወደዱም።

፴፩ የኔን ፡ ምክር ፡ ይመለከቱ ፡ ዘንድ ፡ አልወደዱምና፤ሕጌንም፡ሁሉ፡ይሽራሉና።

፴፪ እንግዲህስ፡የሥራቸውን፡ፍሬ፡ይብሉ፤የራሳቸውንም፡ኃጢአት፡ፍዳ፡ይጥገቡ።

፴፫ በንስሐ፡አለመመለሳቸው፡ሰነፎችን፡ታጠፋቸዋለችና ፤ ነቢያትንም ፡ ከመበደላቸው ፡ የተነሣ ፡ (እስራኤል) ፡ ይጠፋሉ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ የዘነጉ ፡ ሰዎችን ፡ መመራመራቸው፡ታጠፋቸዋለች።

፴፬ እኔን ፡ የሚሰማ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ በአለኝታ ፡ ይኖራል፤ያለ፡ድንጋፄም፡ከመከራው፡ሁሉ፡ ያርፋል።

### የሰሎሞን፡ምሳሌ፡የምሥጢር፡ትርጕም።

፩ ወልድየ ፡ ኢያስሕቱከ ፡ ከሚለው ፡ ጀምሮ ፡ እምኵሉ፡እኩይ፡እስከሚለው፡ድረስ፡ይተረጐማል።

፪ ተርጓሚው ፡ ልጄ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የዘነጉ ፡ ሰዎች ፡ አያስቱህ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ለእንተ ፡ ውእቱ ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ ተሰ
ሠሉ ፡ በእንተ ፡ ቅትለተ ፡ **ክርስቶስ** ፡
አመ፡አጽለመ፡ሰይጣን፡ልቡናቲሆሙ፡
ወአምጽአ፡ላዕሌሆሙ፡ፈቃዳቲሆሙ፡ወቅ
ንዓቶሙ ፡ እስከ ፡ ገብሩ ፤ ጌጋየ ፡ ወይሬ
ሰዩ፡ሠናየ።
ፀሊ፡ወኢትፍቅድ፡እምኔሆሙ፡ለእመ፡
አስተብቍዑከ፡ወይቤሉከ፡ነዓ፡ምስሌነ፡
ንትኀፍ፡ደመ፡ወንድፍን፡ውስተ፡ምድር፡
ብእሴ፡ጻድቀ፡በዐመፃ፡ይደሉ፡ለብእሲ፡
ለብ፡ለእመ፡አስተርአየ፡ሎቱ፡ጽድቅ፡
ኢይተነትን፡እምኔሁ፡ለኀሢሠ፡ሢመታት፡
ወኢይትኤዘዝ ፡ ለፈቃዱ ፡ በዘይነክያ ፡
ለነፍሱ፡ወኢየኀብሮሙ፡ለአብዳን፡ውስተ፡
አበዶሙ።
ዳእሙ ፡ እምከመ ፡ ቆመ ፡ ላዕለ ፡
ጽድቅ፡ኢይፃእ፡እምኔሃ፡ኢ፡ይምኖ፡ወኢ፡
ፀጋሞ፡
ወሰበ፡ኮነ፡ነኪረ፡ዘመድኒ፡ዘውእቱ፡
ጲላጦስ፡ሰበ፡አእመረ፡ጽድቀ፡በአሐቲ፡
ሰዓት፡ኢናፈቀ፡ልቡ።
ዳእሙ ፡ ነሥአ ፡ ማየ ፡ ወተኀፅበ ፡
እደዊሁ፡ወይቤ፡ንጹሕ፡አነ፡እምደሙ፡
ለዝ ፡ ጻድቅ ፡ ወአንትሙ ፡ ትረክቡ ፡
ዘከተ።
ወእሬኢ፡ከመ፡ይኩን፡ለምእመን፡ዘይሬኢ፡
ጽድቀ፡ከመ፡ኢይኅበር፡ውስተ፡ኃጣውአ፡
ካልኡ።
ወንበር፡እምድር፡ዝክሮ፤ይተረጕም፡
ስመ፡አይሁድ፡ኢፈትሑ፡በእንቲአሁ፡
ዘበቀቲል፡ዘእንበለ፡ከመ፡ኢይትርፍ፡ሎቱ፡
ዝክር፡ፍጹመ።
ወለእመሰ፡ለበዉ፡ቀተልት፡ለእመ፡
ውእቶሙ፡ጸልእዎ፡ወጸለብዎ፡**ለክርስቶስ**፡
ያሰፍሕ፡ዝክሩ፡ወየአምኑ፡በስሙ፡
እምሥራቀ፡ፀሐይ፡እስከ፡ምዕራቢሃ፡
እምኢከኑ፡ይገብሩ፡አላ፡ተ...

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ብሎ፡ይተረጕማል፤ይኸውም፡**ክርስቶስን**፡ስለ፡
መግደል፡ስለ፡ተስማሙ፡ሰዎች፡ነው፤ሰይጣን፡
ልቡናቸውን፡አደንድኖ፡በላያቸው፡ቅናት፡አሳ
ድሮባቸው፡በደሉን፡በጎ፡ሥራ፡እንደ፡ሠሩ፡መስ
ሎአቸው፡እስከ፡ሠሩት፡ድረስ፡ይኸንንም፡እንዲ
ፈጽሙት፡አድርጓቸዋልና።
፫፤ ከእርሳቸውም፡ና፡ደም፡በማፍሰስ፡ከእኛ፡ጋራ፡
ተባበረን፤ዕውነተኛ፡ሰውንም፡በግፍ፡ገድለን፡
እንቅበረው፡ብለው፡ቢማልዱህ፡አትውደድ፡
ያለውን፡ሲተረጕም፥ይኸም፡ለአስተዋይ፡ሰው፡
ዕውነት፡ነገር፡ቢገለጽለት፡ሹመት፡ለመፈለግ፡
ብሎ፡አያምታታም፤ነፍሱን፡በሚጐዳ፡ገንዘብ፡
ለሥጋ ፡ ፈቃድ ፤ አይታዘዝም ፤ ይህንንም ፡
ማድረግ ፡ ይገባል ፤ ሰነፎችንም ፡ በስንፍና ፡
ሥራቸው፡አይተባበራቸውም።
፬፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዕውነት ፡ ላይ ፡ ከጸና ፡ ወደ ፡
ቀኝም፡ ወደ፡ግራም፡ከእርስዋ፡ፈቀቅ፡እንደ
ማይል፡ይሆናል፡
፭፤ በነገድ ፡ ባዕድ ፡ የነበረ ፡ ጲላጦስ ፡ እንኳን ፡
በአንዲት፡ሰዓት፡ዕውነቱን፡በዐወቀ፡ጊዜ፡
ልቡ፡አልተጠራጠረም፡
፮፤ ነገር፡ግን፡ውኃ፡ወስዶ፡እጁን፡ታጥቦ፡እኔ፡
ከዚህ ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፤
እናንተ፡ በደሙ፡ምክንያት፡የሚመጣውን፡
ፍዳ፡ትቀበላላችሁ፡አለ፡እንጂ።
፯፤ እንዲህ፡ከሆነ፡ዕውነትን፡ለሚመለከት፡ክርስ
ቲያን፡በሌላው፡ኃጢአት፡እንዳይተባበር፡ይሆን፡
ዘንድ፡እንዴት፡እንደሚገባው፡ያስረዳል።
፰፤ ስም ፡ አጠራሩንም ፡ ከምድር ፡ እናጥፋ ፡
ያሉትን ፡ ይተረጕማል ፤ አይሁድ ፡ ስለ ፡
እርሱ፡ መገደል፡ሲፈርዱ፡እንዲሞት፡ብቻ፡
ሳይሆን ፡ ስም ፡ አጠራሩ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡
ፈጽሞ፡እንዲጠፋ፡ነበርና፡
፱፤ **ክርስቶስን**፡ጠልተው፡ሰቅለው፡ሲገድሉት፡
ስም ፡ አጠራሩ ፡ ከፀሐይ ፡ መውጫ ፡ እስከ ፡
ፀሐይ፡መግቢያ፡እንደሚስፋፋና፡በስሙም፡
እንደሚአምኑበት ፡ ቢአውቁ ፡ ይህን ፡
እንደሚአምኑበት፡ነበር፤እነርሱ፡የሞት፡ፍርድ፡ከፈረ
በለዩ...

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።
ወእቶሙ፡ፈትሑ፡ላዕሌሁ፡በሞት፡ይበጥል፡
እንከሰ፡ዝክሩ።
፲፡ ወጥሪቶ ፡ ብዙኀ ፡ ናስተጋብእ ፡ አብያቲነ ፡
ወንምላዕ፡በርበሮ፤ይተረጐም፡ሶበ፡ተማከሩ፡
ሊቃነ፡ካህናት፡ወይቤሉ፡ናሁ፡ኵሉ፡ዓለም፡
ተለዎ ፡ ድኅሬሁ ፡ ወጠየቁ ፡ ከመ ፡ የሐውር ፡
እምኔሆሙ፡ሢመቶሙ፡ወይቤሉ፡እምከመ፡
ቀተልናሁ፡ናስተጋብእ፡ኵሎ፡ጥሪቶ፡ዘወእቱ፡
ትምህርት ፡ ዘኮኑ ፡ ሕዝብ ፡ ይሰምዕዋ ፡
እምኔሁ፡ በእስተሐውዞ ፡ ትከውን ፡ ለነ ፡
ዘወእቱ ፡ ሢመተ ፡ ዚአሁ ፡ ትትከፈል ፡
ላዕሌነ፡ለእመ፡ገበርነ፡ፈቃድነ፡ቦቱ፡ወኮነ፡
እንከሰ፡ዝንቱ።እስመ፡ትምህርቶሙ፡በጠለ፡
ወሢመቶሙ፡ተሀይደ።
፲፩፡ ይቤ፡ዐቅ፡ኢትሑር፡ምስሌሆሙ፤አመረ፡
ተዐቅቦ ፡ ለመሐይምናን ፡ በክርስቶስ ፡
በውእቱ፡ መዋዕል ፡ ሶበ ፡ ርእዩ ፡ ስቅለተ ፡
እግዚእ ፡ ወሞቶ ፡ ኢይናፍቁ ፡ ወኢያንቀ
ልቅል፡ ኀሊና ፡ አልባቢሆሙ ፡ ከመ ፡
ኢይናፍቁ፡ወኢይሑሩ፡ምስለ፡ቀተልት።
፲፪፡ ይቤ ፡ ምግባረ ፡ ብእሲ ፡ ኃጥእ ፡
እኪት ፡ ይተረጐም ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ ይሁ
ዳሀ ፡ አስቆሮታዊ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኮነ ፡
ይሬኢ ፡ ምግባራተ ፡ እግዚእ ፡ ወይሰምዕ ፡
ቃላቲሁ ፡ ወተዐቅቦተ ፡ አእምሮቱ ፡ እምኃ
ጣይእ።
፲፫፡ ወአስምዐ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወንጌልኒ ፡ ከመ ፡
ውእቱ ፡ ሰራቂ ፡ ወበእንተ ፡ ውእቱኬ ፡ ኮነ ፡
ኃጥአ፡እኩየ፤ወሰመዮ፡ንፉቀ፡ዘወእቱ፡ኮነ፡
ሀልወ ፡ ምስለ ፡ እግዚእ ፡ ወልቡ ፡ ምዑጥ ፡
እምኔሁ።
፲፬፡ ይቤ ፡ ዝ ፡ ፍና ፡ ውእቱ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡
ይፌጽሙ ፡ ኃጣውአ ፡ ወበነበ ፡ ውእቱ ፡
ኃጢአት ፡ የኀጕሉ ፡ ነፍሰሙ ፡ ባሕቲቶሙ ፡
ይተረጐም ፡ ከመ ፡ ውእቶሙ ፡ አህጐሉ ፡
ነፍሰሙ፡በኑፋቄሆሙ፡በጊዜ፡ብሂሎቶሙ፡
አልብነ፡ንጉሥ፡ዘእንበለ፡ቄሳር፡ወለዝንቱሰ፡
ኢነአምሮ፡ወናፈቁ፡ላዕለ፡እግዚእ፡ወተለዉ፡
መምለክያነ ፡ ጣዖት ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱኬ ፡
ተሀጕሉ፡ባሕቲቶሙ።

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ዱብት ፡ ከእንግዲህ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ስም ፡
አጠራሩ፡ይጠፋል፡ብለው፡ጠረጠሩ፡እንጂ።
፲፡ ብዙ ፡ ገንዘቡንም ፡ ሰብስበን ፡ ቡብዝበዛውም ፡
ቤታችንን ፡ እንምላ ፡ ያለውን ፡ እንዲህ ፡ ይተረ
ጐማል ፤ አይሁድ ፡ በተማከሩ ፡ ጊዜ ፡ ዓለሙ ፡
ሁሉ፡ በኋላው ፡ ተከተለው ፡ አሉ ፡ ሹመታቸው ፡
ከእርሳቸው ፡ እንደሚሄድ ፡ ተረድተዋልና ፤ የገደ
ልነው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገንዘቡን ፡ እናከማቻለን ፡
አሉ፤ ይኸውም ፡ ከጣዕም ፡ ጋር ፡ ሕዝቡ ፡
የሚሰሟት ፡ ትምህርቱ ፡ ናት ፤ ፈቃዳችንን ፡ ከፈጸ
ምንበት ፡ የእርሱ ፡ ሹመት ፡ የእኛ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡
ትሆናለች ፡ ብለው ፡ ነበር ፤ እንግዲህም ፡ ይህ ፡
እንዲህ ፡ ሆነ ፤ ትምህርታቸውም ፡ ጠፍቷልና ፡
ሹመታቸውም፡ተነጥቋልና።
፲፩፡ ከእነርሱ ፡ ጋራ ፡ መንገድን ፡ እንዳትሄድ ፡ ዕወቅ ፡
አለ ፤ በዚያን ፡ ወራት ፡ የጌታን ፡ ስቅለትና ፡
ሞቱንም ፡ ምእመናን ፡ በአዩ ፡ ጊዜ ፡ ክርስቶስን ፡
እንዳይጠራጠሩ ፡ ልቡናቸውም ፡ ከእምነቱ ፡
በመናወጽ ፡ ተጠራጥረው ፡ ከገዳዮች ፡ አይሁድ ፡
ጋራ፡እንዳይተባበሩ፡መጠበቅን፡አመለከተ።
፲፪፡ የኃጥእ ፡ ሰው ፡ ሥራው ፡ ክፉ ፡ ናት ፡ አለ ፤
ይህንንም፡ ስለ ፡ አስቆሮታዊው ፡ ይሁዳ ፡ ይተረ
ጐማል ፤ እርሱ ፡ ጌታ ፡ የሚሠራውን ፡ ተአም
ራቱን፡ ያይ ፡ ነበርና ፡ ትምህርቱንም ፡ ይሰማ ፡
ነበርና፡ባሕርዩ፡ከኃጢአት፡የራቀና፡የተጠበቀ፡
እንደሆነም፡ያውቅ፡ነበርና።
፲፫፡ እርሱ ፡ ይሁዳ ፡ ሌባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡
ወንጌል ፡ ይመሰክራል ፤ ስለዚህም ፡ ክፋትን ፡
የተመላ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ሆነ ፤ ወደ ፡ ሁለት ፡
የተከፈለ፡ተባለ፤እርሱ፡ከጌታ፡ሲኖር፡ልቡናው፡
ከጌታ፡ ተለይቶ፡ወደ፡ተንኰል፡ተመልሷል።
፲፬፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ ኃጢአትን ፡ ለሚሠሩ ፡ ሁሉ ፡
ነው ፤ ስለዚህም ፡ ኃጢአት ፡ ብቻቸውን ፡
ሰውነታቸውን ፡ ያጠፋሉ ፡ አለ ፤ ለእኛ ፡ ከቄ
ሳር፡በቀር፡ንጉሥ፡የለንም፤ይህንንስ፡አናው
ቀውም ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ በክህደታቸው ፡ ነፍሳ
ቸውን ፡ አጠፉ ፤ ጌታንም ፡ ክደው ፡ ጣዖት ፡
አምላኪዎችን ፡ ተከተሉ ፤ ስለዚህም ፡
ብቻቸውን ፡ ተለይተው ፡ እንደ ፡ ጠፉ ፡ ይተረ
ጐማል።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ይቤ፡ባሕቲቶሙ፡ይተርፉ፡ላዕለ፡ዝ፡ኀሊና፡
እኩይ፡ለዘለፉ፡እስከ፡ዕለተ፡ሞቶሙ፡እስመ፡
ይትሀጎሉ፡እሙንቱ፤ወእለሰ፡ነስሑ፡
ወአመኑ፡ስሕተቶሙ፡ወአምኑ፡በሃይማኖት፡
ዘደየሆሙ፡ለአበው፡ሐዋርያት፡እስመ፡እግ
ዚአብሔር፡ሰረየ፡ሎሙ፡ወኢሐሰበ፡በላዕ
ሌሆሙ፡ዘኀለፈ፡እምኔሆሙ።

ይቤ፡ጥበብ፡በፍናው፡ትሴባሕ፡ተርጐሙ፡
በእንተ፡ጥበብ፡እንበይነ፡አምላክ፡ቃል፡
ይቤ፡በፍናው፡ትሴባሕ፡ይተረጐም፡ከመ፡
ክርስቶስ፡ጼሐ፡ለምእመናን፡ፍናወ፡ጽድቅ፡
ወአልቦ፡ዘአትረፈ፡ምንተኒ፡እምፍድፍድና፡
አላ፡ከሠተ፡ሎሙ፡ወአዘዞሙ፡ለሐዊር፡
ውስቴቱ።

ይቤ፡ወበመራሕብት፡ትሁብ፡
ቃላ፡ይተረጐም፡እስመ፡ኢተርፈ፡ኢ፡
ከቡት፡ወኢ፡ገሀድ፡ወኢ፡መራሕብት፡
ውስተ፡ምድር፡እስመ፡በጽሐ፡ውስቴታ፡
ትምሀርተ፡አርድእት፡ወውእቱ፡በከመ፡ቃለ፡
ዳዊት፡ነቢይ፡ውስተ፡ኵሉ፡ምድር፡ወፅአ፡
ነገሮሙ።

ይቤ፡ወይእቲ፡ውስተ፡አንቀጸሙ፡ለኀያላን፡
ትፀመድ፡ይተረጐም፡በእንተ፡ኃያላን፡ለኀበ፡
ነገሥት፡ከሐድያን፡ወጠቢባን፡እለ፡
ሞአዎሙ፡ሐዋርያት፡በተአምራት፡
መድምማት፡እስመ፡ኮነ፡ስመ፡ክርስቶስ፡
ውስተ፡አፉሆሙ፡መዐልተ፡ወሌሊተ፡
ያሌብሕዎ፡ወይቄድስዎ።

ይቤ፡ወረሲዓን፡ጸልኡ፡አእምሮ፡ወር
ሱሐን፡ኮኑ፡ለእለ፡ይዘልፍዎሙ፤ይተ
ረጐም፡በእንተ፡ረሲዓን፡እለ፡ኢኮኑ፡
ምእመናነ።

ይቤ፡ጸልኡ፡አእምሮ፡ዘውእቱ፡ኀደጉ፡
አእምሮ፡እስከ፡ኮኑ፡አብዳነ፤ወኢሐተቱ፡
በእንተ፡ክርስቶስ፡ከመ፡ውእቱ፡ዘይሴ
ሬውዎ፡ወርሱሐነ፡ኮኑ፡ለእለ፡ይዘልፍ
ዎሙ፡ይተረጐም፡ከመ፡ውእቶሙ፡ኀደጉ፡
ጽድቀ፡ ሮጹ፡ኀበ፡ከንቱ፡በእንተ፡
ፈቃዶሙ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፭፤ እስከሚሞቱባት፡ቀን፡ድረስ፡በዚህ፡ክፉ፤
ሐሳብ፡ላይ፡ለዘወትር፡ብቻቸውን፡ይቀራሉ፤
እነርሱ፡ይጠፋሉና፡እለ፤ስሕተታቸውን፡
አውቀው፡ንስሐ፡የገቡትን፡በአባቶች፡
ሐዋርያት፡እጅ፡ያመኑትን፡ግን፡ኃጢአታ
ቸውን፡እግዚአብሔር፡ተወላቸው፤
ያለፈውን፡ኃጢአታቸውን፡አላሰበባቸውም።

፲፮፤ ጥበብ፡በጐዳና፡ትመሰገን፡ነበር፡አለ፤ይህን፡
ስለ፡አካላዊ፡ቃል፡ተርጕመውታል፤በጐዳና፡
ትመሰገናለች፡ያለው፡ክርስቶስ፡ለምእ
መናን፡የጽድቅን፡መንገድ፡እንደ፡ጠራ፡
ከብዛቱም፡የተነሣ፡ምንም፡ምን፡ያስቀረው፡
የለም፤ገለጠላቸው፡እንጂ፡በውስጡም፡
እንዲሄዱ፡አዘዛቸው።

፲፯፤ በአደባባይ፡ቃልዋን፡ትሰጥ፡ነበር፡አለ፤
ይህን፡እንዲህ፡ይተረጐማል፤በዚህ፡ዓለም፡
ሥውርም፡ቢሆን፡ወይም፡ግልጥ፡ወይም፡
አደባባይ፡በውስጥዋ፡የሐዋርያት፡
ትምህርት፡ደርሷልና፤ነቢይ፡በዓለሙ፡ሁሉ፡
ነገራቸው፡ወጣ፡ብሎ፡እንደ፡ተናገረ፡ሳይነገ
ርበት፡የቀረ፡ቦታ፡የለምና።

፲፰፤ እርሷም፡በኃያላኑ፡በር፡ቃልዋን፡ትሰጣለች፡
አለ፤አስደናቂ፡በሆነ፡ተአምራት፡ሐዋርያት፡
ድል፡በአደረጓቸው፡አዋቂዎች፡ከሐድያንና፡
በነገሥታት፡ዘንድ፡ኃያላን፡ስለ፡ሆኑ፡ይተረ
ጐማል፤በቀንና፡በሌሊት፡ፈጽመው፡ሲያመ
ሰግኑ፡የክርስቶስ፡ስም፡ከአፋቸው፡አይለ
ይምና።

፲፱፤ የእግዚአብሔርን፡ሕግ፡የዘነጉ፡ሁነው፡ዕው
ቀትን፡ጠሉ፤ለሚአስተምሩአቸውም፡ቢአ
ጥቡት፡አይጠራ፡ሆኑ፡አለ፤ይህንንም፡በክሕ
ደት፡ስለ፡ጸኑትና፡ስለ፡አላመኑት፡ይተረጐማል።

፳፤ ዕውቀትን፡ጠሉ፤ይኸውም፡ሰነፎች፡ደናቁርት፡
እስከ፡ሆኑ፡ድረስ፡የተዉት፡ዕውቀት፡ነው፤
ተሰፋ፡ስለሚአደርጉት፡ስለ፡ክርስቶስ፡ተስፋ፡
የሚአደርጉት፡እርሱ፡እንደ፡ሆነ፡አልመረ
መሩም፤ለሚአስተምሩአቸውም፡ቢአጥቡት፡
አይጠራ፡ሆኑ፡አለ፤እነሱ፡ዕውነትን፡ትተው፡
ፈቃዳቸውን፡ሊፈጽሙ፡ወደ፡ከንቱ፡ሐሰት፡
ነገር፡እንደ፡ሮጡ፡ይተረጐማል።

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

፳፩፤ ይቤ፡ናሁ፡እነግረክሙ፡እስትንፋስ፡ቃልየ፡ወእሜህረክሙ፡ነገረ፡ዚአየ፤ይተረጐም፡እስመ፡**እግዚእ**፡ኢኃደገ፡ሎሙ፡ምክንያተ፡ወሶበሰ፡ወውእቱ፡ቃሉ፡ውስተ፡ወንጌል። ወሶበሰ፡ኢመጻእኩ፡ወኢነገርክዎሙ፡እምድኅኑ፡ወእምኢኮኖሙ፡ጌጋየ፡ወይእዜሰ፡አልቦሙ፡ምክንያት፡በእንተ፡ኃጢአቶሙ፡ወይቤ፡ሶበሰ፡ኢገበርኩ፡ሎሙ፡ምግባራተ፡ካዕበ፡ዘባዕድ፡ኢገብሮሙ፡እምኢኮኖሙ፡ጌጋየ።

፳፪፤ ይቤ፡እስመ፡ጸዋዕኩክሙ፡ወኢያውሣእ ክሙኒ፤ይተረጐም፤ከመ፡ውእቱ፡ጸውዖሙ፡ኀበ፡አሚን፡ቦቱ፡ወኢሰምዕዎ፡እምኔሁ፡ወገብረ፡በቅድሜሆሙ፡ተአምራተ፡ወመንክራተ፡መድምማተ፡ወኢአምኑ፡ቦቱ።

፳፫፤ ወይቤሎሙ፡ለእመሰ፡ኮንክሙ፡ዘኢተአምኑ፡ብየ፡እመኑ፡በግብርየ፡ከመ፡ታእምሩ፡ከመ፡አነ፡ውእቱ፡**እግዚአብሔር**፡ወበእንተ፡እከየ፡ልቦሙ፡ኢአምኑ፡በኀቤየ፡ለዝክቱ።

፳፬፤ ይቤ፡ሰፋሕኩ፡እደዊየ፡ወኢተሰጠውክሙኒ፡ወምንትኒ፡ረሰይክሙ፡ትእዛዝየ፤ይተረጐም፤በእንተዝ፡እስመ፡**እግዚአብሔር**፡ሶበ፡ሰፍሐ፡እደዊሁ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ርእዩ፡ትእምርተ፡እንተ፡ኮነት፡እምጸሊመ፡ፀሐይ፡ወወርኅ፡ወትንሣኤ፡ምውታን፡ወሥጠተ፡መንጦላዕተ፡ምኵራብ፡ወጸዋልዕ፡እለ፡ተሠጥቁ፡ወምስለ፡ዝንቱ፡ኵሉ፡ኢተመይጡ፡ኀበ፡ሃይማኖት፤ዳእሙ፡ገዝፉ፡አልባቢሆሙ፡እስከ፡ውእቶሙ፡ምስለ፡ረኪቦቶሙኒ፡ወርእዮቶሙ፡ዘንተ፡ኵሎ፡ተአምረ፡ኮኑ፡ይፀርፉ፡ላዕሌሁ።

፳፭፤ ይቤ፡በእንተ፡ዝንቱ፡ናሁ፡አነሂ፡በሀጕልክሙ፡እሥሕቅ፡ወእትፌሣሕ፡ሶበ፡ይመጽአክሙ፡ተሠርዎ፡ወሶበ፡ይመጽአክሙ፡ግብተ፡ሀከክ፤ይተረጐም፤በእንተዝ፡ከመ፡**እግዚአብሔር**፡ይትገሐሥ፡እምኔሆሙ፡እስከ፡ይሜብሉ፡ጸላዕቶሙ፡ወይሥሕቁ፡ላዕሌሆሙ፡ወካዕበ፡በእኩያንኒ፡ሎሙ፡ወያበጽሕ፡ወያበውሕ፡ላዕሌሆሙ፡ወይሣለቁ፡እለ፡ያዘልፉ፡ላዕለ፡ዕልወት፡ኢይሰምዖሙ፤

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፳፩፤ እነሆ፡እኔ፡ረቂቅ፡ቃሌን፡እነግራችኋለሁ፤ነገሬንም፡አስተምራችኋለሁ፡አለ፤**ጌታ**፤ምክንያት፡አልተወላቸውም፤ይህም፡ቃሉ፡በወንጌል፡ውስጥ፡መጥቼ፡ባልነግራቸው፡ከፍርድ፡በዳኑ፡ነበር፤በደልም፡ባልሆነ ባቸው፡ነበር፤አሁን፡ግን፡ስለ፡በደላቸው፡ምክንያት፡የላቸውም፡ያለውን፡ይተረ ጐማል፤ዳግመኛም፡ሌላ፡ያልሠራውን፡ሥራ፡ያልሠራሁላቸው፡ቢሆን፡በደል፡ባል ሆነባቸው፡ነበር፡ብሎአል።

፳፪፤ ባስተምራችሁ፡አልሰማችሁኝምና፡አለ፤እርሱ፡ወደ፡እርሱ፡ሃይማኖት፡እንደ፡ጠራቸው፡እነርሱም፡ሰምተው፡እንዳልተቀበሉት፡በፊታቸውም፡አስደናቂዎች፡ተአም ራትንም፡ቢያደርግ፡እንደ፡አላመኑበት።

፳፫፤ እኔን፡የማታምኑ፡ከሆናችሁም፡እኔ፡**አምላክ**፡እንደ፡ሆንኩ፡ታውቁ፡ዘንድ፡በሥራዬ፡እመኑ፡እንዳላቸው፡ስለ፡ልቡናቸውም፡ክፋት፡ይህን፡ሥራዬን፡አላመኑም፡ያለውን፡ይተረጕማል።

፳፬፤ እጄን፡ብዘረጋ፡አልተቀበላችሁኝም፡ትእዛ ዜንም፡የተናቀ፡አደረጋችሁት፡አለ፤ስለዚህም፡**እግዚአብሔር፡ወልድ**፡እጆቹን፡በዕንጨት፡መስቀል፡ላይ፡በዘረጋ፡ጊዜ፡ከፀሐይና፡ከጨረቃ፡መጨለም፡ከሙታን፡መነሣት፡ከምኵራቡ፡መጋረጃ፡መቀደድ፡ከዓለትም፡መሠንጠቅ፡የተነሣ፡ተአም ራቱን፡አይተው፡ወደ፡እምነት፡አልተመ ለሱም፤ነገር፡ግን፡ይህን፡ሁሉ፡ከማግኘታ ቸውና፡ከማየታቸው፡ጋር፡የሚሳደቡ፡ሆኑ፡እንጂ፤ወደ፡ሃይማኖት፡አልተመለሱም፡ያለውን፡ይተረጕማል።

፳፭፤ ስለዚህ፡እኔ፡በጥፋታችሁ፡ፀብ፡ክርክር፡ጥፋት፡ድንገት፡በመጣባችሁ፡ጊዜ፡ፈጽሞ፡ደስ፡ይለኛል፡አለ፤ጠላቶቻቸው፡በእነርሱ፡ላይ፡ሠልጥነው፡መዘባበቻ፡እስከሚአደር ጓቸው፡ድረስ፡**እግዚአብሔር**፡በረድኤት፡እንደሚለያቸው፡ዳግመኛም፡አዘውትረው፡ወንጀል፡የሚሠሩትን፡በመከራቸው፡ጊዜ፡ልመናቸውን፡እንደማይሰማቸው፡በእነርሱ፡ላይ፡ጠላቶቻቸውን፡እንደሚያሠለጥን ባቸው፡በፍርሀትም፡እንዳያሸብራቸው፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ወያሐውክሙ ፡ ወያፈርሆሙ ፤ ይጼውዕዎ ፡ ወኢያወሥእሙ ፡ በእንተ ፡ ዘኢኮነ ፡ ያማሂሆሙ፡በኀይል።

፳፮ ይቤ፡ወእኩያን፡የኀሥሡኒ፡ወኢይረክቡኒ፤ ውእቱኒ፡በከመ፡ነገርን፡እስመ፡እግዚአ ብሔር፡ኢይሰምዖሙ፡ለምእመናን፡እለ፡ ውስተ፡እከይ።

፳፯ ይቤ፡እስመ፡ጸልእዋ፡እሙንቱ፡ለጥበብ፡ ወለቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢፈቀዱ ፤ ይተረጐም ፤ ከመ ፡ ውእቶሙ ፡ ጸልኡ ፡ ሃይማኖተ፡በእግዚእ፡ወገደፉ፡ቃላቲሁ። ወበእንተ፡ውእቱ፡ይቤ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡ እሙንቱሰ፡ጸልኡኒ፡በከንቱ።

፳፰ ይቤ፡ወኢፈቀዱ፡ይነጽሩ፡ዘዚአየ፡ምክረ፡ ወያስተራክሱ፡ዘዚአየ፡ዘለፋ፡ይተረጐም፤ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምከሮሙ ፡ ወይቤሎሙ፡ለእመ፡ኢአመንክሙ፡ከመ፡ አነ፡ውእቱ፡ትመውቱ፡በኃጢአትክሙ፡ ወኢተወከፉ፡እምኔሁ፡ወመነኑ፡ነገሮ።

፳፱ ይቤ፡ወዘሰ፡ይሰምዐኒ፡ኪያየ፡ይሄሉ፡ በተስፋ፡ ወየዐርፍ ፡ ዘእንበለ ፡ ድንጋፄ ፡ እምኵሉ ፡ እኩይ ፤ ይተረጐም ፡ ከመ ፡ ዘየአምን፡በእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ወይሰምዕ፡ቃሎ፡ወይገብር፡ኪያሃ፡እስመ፡ ይሄሉ፡ውእቱ፡በተሰፍዎ፡በከመ፡ይቤ፡ እግዚእነ፡ዘየአምን፡ብየ፡ቦ፡ሕይወት፡ ዘለዓለም ፡ ወአነ ፡ አነሥኦ ፡ ምስሌየ ፡ በደኃሪት፡ዕለት።

፴ ይቤ፡ወየዐርፍ፡ዘእንበለ፡ጽንጋፄ፡እምኵሉ፡ እኩይ ። እስመ ፡ እምኔሁ ፡ ለውእቱ ፡ ይትአተት፡ፍርሀት፡እንተ፡ይእቲ፡ትንሣኤ፡ እኩያን፡ወይእቲ፡ደይን፡ወመደንግጽት፤ ሊሆሙ፡ይሄሉ፡በተስፋ፡ለዝሉፉ፡እንዘ፡ ይትፌሣሕ ፡ በክርስቶስ ፡ ተሰፊዎ ፡ ትንሣኤሁ ። ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

በመከራቸውም ፡ ጊዜ ፡ ይጠሩታል ፡ ጥሪአቸው፡በእምነት፡ስለ፡አልሆነ፡አይመል ስላቸውም፡ያለውን፡ይተረጉማል።

፳፮፤ ክፉዎች ፡ ይፈልጉኛል ፤ አያገኙኝም ፡ አለ ፤ ይኸውም፡እንደ፡ተናገርነው፡በክፉ፡ሥራ፡ ውስጥ፡ያሉትን፡ምእመናን፡እግዚአብሔር፡ አይሰማቸውምና።

፳፯፤ ጥበብን፡ጠልተዋታልና፡የእግዚአብሔርን፡ ቃል ፡ ሊሰሙ ፡ አልወደዱም ፡ አለ ፤ በጌታ ፡ የሚሆነውን ፡ ሃይማኖት ፡ እነርሱ ፡ እንደ ፡ ጠሉና፡ቃሉንም፡እንደ፡ጣሉ፡ይተረጉማል፤ ስለዚህም፡ነገር፡የከበረ፡ወንጌል፡በከንቱ፡ ጠሉኝ፡ብሎአል።

፳፰፤ የእኔንም፡ትምህርት፡ይመለከቱ፡ዘንድ፡አል ወደዱምና ፡ ሕጌንም ፡ ይሽራሉ ፡ አለ ፤ እኔ እንደ፡ሆንኩ፡ካላመናችሁ፡በኃጢአታችሁ፡ እንዳላችሁ ፡ ትሞታላችሁ ፡ ብሎ ፡ እግዚአ ብሔር፡መክሮአቸው፡ነበርና፡እነርሱ፡ግን፡ ምክሩን፡እንዳልተቀበሉት፡ነገሩንም፡እንደ፡ ናቁ፡ይተረጉማል።

፳፱፤ እኔም ፡ የሚሰማኝ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ በአለኝታ ፡ ይኖራል ፤ ያለ ፡ ድንጋጤም ፡ ከመከራውም ፡ ሁሉ፡ ያርፋል ፡ አለ ፤ በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡የሚአምን፡ቃሉንም፡ሰምቶ፡የሚያ ደርገው ፡ እርሱን ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ እንደ ሚኖር ፡ ይተረጉማል ፤ ጌታችን ፡ በእኔ ፡ የሚአምን፡የዘላለም፡ሕይወት፡አለው፤እኔም፡ በኋለኛይቱ፡ቀን፡አስነሥቼ፡ከእኔ፡ጋራ፡አኖረ ዋለሁ፡ብሎ፡በወንጌል፡እንደ፡ተናገረ።

፴፤ ያለ ፡ ድንጋጤም ፡ ከመከራ ፡ ሁሉ ፡ ያርፋል ፡ አለ፤ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ፍርሀት ፡ ይርቃልና ፤ ይኸውም፡የክፉዎች፡ትንሣኤ፡ናት፤ይችም፡ የምታስደነግጥ ፡ የሥቃይ ፡ ትንሣኤ ፡ ናት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከክርስቶስ ፡ የሚገኘውን ፡ ሕይወት ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ ለዘላለሙ፡በተስፋ፡ይኖራል፡እንጂ። ለዘላለሙ፡ክብር፡ምሥጋና፡ ለእርሱ፡ለጌታ፡ለዘላለሙ፡ክብር፡ምሥጋና፡ ይሁን፤አሜን።

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

## ክፍል፡፪።

## ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፡፺፯፡፲፩–፲፱።

እመልእክተ ፡ አብ ፡ አቡነ ፡ ቆዝሞስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለእስክንድርያ ፡ ኀበ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዘአንጾኪያ ፡ አውሥአተ፡መልእክቱ፡ኀቤሁ።

፲፩፡ ንአምን፡ወንትአመን፡እስመ፡ዝንቱ፡አሐዱ፡ እምቅድስት፡**ሥላሴ፡** ንጹሕ፡**ወልድ፡** ቃሉ፡ **ለአብ፡** ሕያው፡ዘቦቱ፡አካለ፡**አብ፡** ወሶበ፡ ፈቀደ፡ይሣሃል፡ትዝምደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ ወያግብኦ፡ኀበ፡ዘቀዳሚ፡ግብሩ፡በሥምረተ፡ **አብ፡** ወሱታፌ፡ግብረ፡**መንፈስ፡ቅዱስ፡** ተሠገወ፡**እምንጽሕት፡ድንግል፡** በኵሉ፡ጊዜ፡ **ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ።**

፲፪፡ ወአኮ፡በምትሓት፡ወአምሳል፡አላ፡በሥጋ፡ ዘይትዔረየነ፡በህላዌ፡ወሐማሚ፡ከማነ፡ ዘቦቱ፡ነፍስ፡ነባቢት፡ወለባዊት፡ወቦቱ፡ ተሠገወ፡በአካል፡ወኮነ፡ምስሌነ፡በእንቲአነ፡ እንዘ፡ለሊሁ፡**እግዚአብሔር፡ቃል፡** ዘእንበለ፡ ፍልጠት፡ወሚጠት፡ወኢ፡ውላጤ፡ወኢ፡ ሙስና።

፲፫፡ ወተወልደ፡በከዊነ፡ሰብእ፡በምሥጢር፡ዘይት ሌዓል፡እምህላዌነ፡ወጠበወ፡እምአጥባት፡ ወተጠብለለ፡በአጽርቅት፡ወተወድየ፡ ውስተ፡ጎል፡ወዘአልቦቱ፡መዋዕል፡ተወከፈ፡ መዋዕለ፡ውርዛዌ፡እንዘ፡ለሊሁ፡**ወልድ፡** ዋሕድ፡**ዘእግዚአብሔር፡ቃል።**

፲፬፡ ወእምድኅረ፡ልደቱኒ፡**እምላካዊ፡** ዘኢይት ረከብ፡**እምድንግል፡** ውእቱ፡ይትዔረየነ፡ በሥጋ፡ትስብእት፡ወይትዔረዮ፡**ለአብ፡** በህላዌ፡ **መለኮታዊ፡** ወኢነሥአ፡ሥጋ፡እምህላዌ፡ **መለኮት፡** ወእምነ፡**መለኮት፡** ኢፈጠረ፡ህላዌ፡ ሥጋሁ፡አላ፡እምትዝምደ፡ዚአነ።

፲፭፡ ወበእንተዝ፡ንቤ፡ከመ፡መንክራት፡ ወሕማማት፡ሎቱ፡ወቃልኒ፡**ዘመለኮት፡** ወዘ ትስብእት፡ሎቱ፡ለባሕቲቱ፡ውእቱ፡ወኢን ክፍሎ፡**ለክርስቶስ፡መድኅን፡እግዚአ**

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

## ክፍል፡፪።

## የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፡፺፯፡፲፩–፲፱።

የእስክንድርያው፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባታችን፡ አባ፡ቆዝሞስ፡ወደ፡እርሱ፡ልኮት፡ለነበረው፡ መልሶ፡ወደ፡አንጾኪያው፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ ወደ፡አባ፡ባስልዮስ፡ከላከው፡መልእክት።

፲፩፡ ይኸ፡ከሦስቱ፡አካላት፡አንዱ፡አካል፡ንጹሕ፡ **ወልድ፡** የሕያው፡**የአብ፡ቃል፡የአብን፡** አካል፡ የመሰለ፡አካል፡እንዳለው፡እናምናለን፤እንታ መናለን። የሰውን፡ባሕርይ፡ይቅር፡ሊለው፡ ወደ፡ቀደመ፡ክብሩም፡ሊመልሰው፡በወደደ፡ ጊዜ፡**በአብ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡** ፈቃድ፡ ሁልጊዜ፡**ድንግል፡** ከምትሆን፡**አምላክን፡** ከወለደች፡**ከቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡** ነፍስን፡ሥጋን፡ነሥቶ፡ሰው፡ሆነ።

፲፪፡ በሐሰት፡መስሎ፡በመታየት፡አይደለም፤ በአካል፡በባሕርይ፡እኛን፡በሚመስል፡እንደ፡ እኛ፡በሚታመም፡የምትናገር፡የምታውቅ፡ ነፍስ፡ያለችው፡ሥጋን፡ተዋሕዶ፡አካላዊ፡ ሰው፡ሆነ፡እንጂ፤እርሱ፡**እግዚአብሔር፡ ቃል፡** ሲሆን፡መለየት፡ሳይኖርበት፡ባሕርዩን፡ ሳይለቅ፡መለወጥ፡ኀልፈት፡ሳይኖርበት፡ስለ፡ እኛ፡እንደ፡እኛ፡ሆነ።

፲፫፡ ፍጡር፡በማይመረምረው፡ምሥጢር፡ሰው፡ ሆኖ፡ተወለደ፤ጡት፡ጠባ፤በጨርቅ፡ ተጠቀለለ፤በበረት፡ተጣለ፤ዘመን፡የማይቈጠ ርለት፡እርሱ፡ተቀዳሚ፡ተከታይ፡የሌለው፡ **የእግዚአብሔር፡ቃል፡** ሲሆን፡ሰው፡የሚያድ ግበትን፡ዘመን፡ገንዘብ፡አደረገ።

፲፬፡ በማይመረመር፡ግብር፡**በአምላካዊ፡** ምሥጢር፡ **ከድንግል፡** ከተወለደ፡በኋላም፡በሥጋ፡እኛን፡ ይመስላል፤**በመለኮታዊ፡** ባሕርይ፡**አብን፡** ይመስላል፤ሥጋን፡ከባሕርየ፡**መለኮት፡** አልነሣም፤**ከመለኮትም፡** የሥጋን፡ባሕርይ፡ አልፈጠረም፤ከእኛ፡ባሕርይ፡ነው፡እንጂ።

፲፭፡ ስለዚህም፡ታምራት፡ማድረግ፡መከራ፡ መቀበል፡ገንዘቡ፡ነው፤**የአምላክነት፡** የሰውነት፡አነጋገር፡**(ወልደ፡እግዚአብሔር)፡** (ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው)፡መባል፡ለእርሱ፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ብሑርስ፡ቃል፡ሥግው፡አሐዱ፡ውእቱ፡አምላክ፡ወሰብእ፡ኅቡረ፡ውእቱ፡ይገብር፡ዘይደሉ፡ለመለኮት፡ወይትናገር፡ዘዕጓለ፡እመሕያው፡በእንቲአነ፡ወበእንተ፡ትስብእት፡ውእቱ፡ይፌጽም፡ኵሎ፡ዘትስብእት፡ወይሜልጥ፡ቃላቲሁ፡ወይትዌከፍ፡ሕማማተ፡ማሕየዌ፡በህላዌ፡ትስብእት፡ዘንጽሕት፡እምኃጢአት።

፲፮ አንከሰ፡ኢንፈልጦ፡ኅበ፡ክልኤቱ፡ፈቃድ፡ወኢ፡ኅበ፡ክልኤቱ፡ህላዌያት፡ወኢ፡ኅበ፡ክልኤቱ፡አካላት፡ወኢ፡ኅበ፡ክልኤቱ፡አምሳል፡ወኢ፡ኅበ፡ክልኤቱ፡ገጻት፡ወኢ፡ኅበ፡ክልኤቱ፡ሥምረት፡ወኢ፡ኅበ፡ክልኤቱ፡ከሃሊ፡ወኢ፡ኅበ፡ክልኤቱ፡ምግባር፡እምድኅረ፡ተዋሕዶ፡ዘከመ፡ጠማሪ፡ልዮን፡ዕልው፡ዘምሉዕ፡ዕርፈተ፡ዘይሰነዐዎ፡ለንስጥሮስ፡ወይትዔረዮ።

፲፯ ወኵሎሙ፡እለ፡ይብሉ፡በንባቦሙ፡በእንተ፡ትሥጉት፡**እምላካዊ**፡እስመ፡ይኤዝዙ፡ወይብሉ፡ከመ፡ክልኤቱ፡ውእቱ፡**መለኮት**፡ወለለ፡አሐዱ፡እምአምሳላት፡ይገብር፡ዘዚአሁ፡በሱታፌሁ፡ለዘየኀብር፡ቦቱ፡እስመ፡ቃል፡ይገብር፡ዘይደሉ፡ለቃል፡ወሥጋኒ፡ይፌጽም፡ዘይደሉ፡ለሥጋ፡አሐዱ፡እምኔሆሙ፡ይበርህ፡በተአምራት፡ወበመንክራት፡ወካልኡ፡ይቴሐት፡በሕማማት፡ወእሉሰ፡በክሕደቶሙ፡ያነብሩ፡ሕጸጸ፡ወጽእለተ፡ውኅማረ፡ወዘይመስሎ፡ለዝ፡ወይፈልጥዎ፡ለኃይል፡ዘኪያሁ፡ንከሥት።

፲፰ ንሕነሰ፡ንፈትሕ፡ላዕሌሆሙ፡ኵነኔ፡መርገም፡ግሩም፡ወላዕለ፡ኵሎሙ፡እለ፡ይሠምሩ፡ምግባሮሙ፡ወምከሮሙ፡ወከማሁ፡ቃላተ፡እከይ፡እለ፡ይብሉ፡ምትሐት፡ወአምሳል፡ወእለኒ፡ይቶስሑ፡ወለኵሎሙ፡ዕውራነ፡ልብ፡ኅሡራን፡ተቃራንያነ፡**እግዚአብሔር**፡ንሕነ፡ንጐይይ፡እመሣግሪሆሙ፡ለእለ፡ይቶስሕዎ፡ወይፈልጥዎ፡**ለክርስቶስ**፡አሐዱ፡ዘኢይትፈለጥ።



ብቻ፡ነው፡እንላለን፤**መድኃኒታችን፡ክርስቶስን**፡ከሁለት፡አንከፍለውም፤ሰው፡የሆነ፡**እግዚአብሔር፡ቃልስ**፡በተዋሕዶ፡አንድ፡**አምላክ**፡ነው፤**ለአምላክነት**፡የሚገባውን፡ይሠራል፤ስለ፡እኛም፡ሰው፡የሚድንበት፡ሞቱን፡ይናገራል፤ሰው፡ስለ፡መሆኑም፡የሰውነትን፡ሥራ፡ሁሉ፡ይሠራል፤የተናገረውንም፡ይፈጽማል፤ከኃጢአት፡በተለየች፡በሥጋ፡ባሕርይም፡የሚያድን፡መከራን፡ይቀበላል።

፲፮፤ እንኪያስ፡ከተዋሕዶ፡በኋላ፡ወደ፡ሁለት፡ፈቃድ፡ወደ፡ሁለት፡ባሕርያት፡ወደ፡ሁለት፡አካላት፡ወደ፡ሁለት፡መልክ፡ወደ፡ሁለት፡ገጽ፡ወደ፡ሁለት፡ሐሳብ፡ወደ፡ሁለት፡ሥልጣን፡ወደ፡ሁለት፡ሥራ፡አንለየውም፤ንስጥሮስን፡በክሕደት፡በሚመስለው፡በሚተካከለው፡ክሕደትን፡በተመላ፡በከሐዲው፡ልዮን፡ደብዳቤ፡እንደ፡ተገለጠው።

፲፯፤ **አምላክ**፡ስለ፡አደረገው፡ተዋሕዶም፡በነገራቸው፡ሁለት፡አካል፡ሁለት፡ባሕርይ፡የሚሉ፡ሰዎችም፡ሁሉ፡ሁለት፡እንደ፡ሆኑ፡ከባሕርያትም፡እያንዳንዱ፡አብሮት፡ባለ፡እየተረዳ፡የየገንዘቡን፡ሥራ፡እንዲሠራ፡ያስተምራሉ፤ይናገራሉ፤ቃል፡ለቃል፡የሚገባውን፡ሥራ፡ይሠራል፤ሥጋም፡ለሥጋ፡የሚገባውን፡ሥራ፡ይሠራል፤ከእነርሱ፡አንዱ፡በተአምራት፡ይከብራል፤ሁለተኛውም፡በመከራ፡ያንሳል፡ይላሉና፤እነርሱስ፡በክሕደታቸው፡ሕጹጽ፡ዕሩቅ፡ብእሲ፡ኅሡር፡ብለው፡ይህንም፡የመሰለውን፡ሁሉ፡በመናገራቸው፡ስሙን፡ገልጠን፡የምናስተምርለት፡**ክርስቶስን**፡ይከፍሉታል።

፲፰፤ እኛ፡ግን፡በእነርሱና፡ትምህርታቸውን፡ወደው፡በሚቀበሉ፡ግሩም፡ፍዳ፡የሚያመጣ፡ፍርድን፡እንፈርድባቸዋለን፤(አውግዘን፡እንለያቸዋለን)፤እንዲሁ፡ክፉ፡ትምህርት፡ምትሐት፡አምሳል፡ብለው፡የሚናገሩትን፡ተቀላቀለ፡የሚሉትን፡**እግዚአብሔርን**፡የሚቃወሙትን፡ወራዶችን፡አላዋቆችን፡ሁሉ፡አውግዘን፡እንለያቸዋለን፤ተቀላቀለ፡ከሚሉ፡የማይከፈለውን፡**ክርስቶስንም**፡ከሚከፍሉት፡ሰዎች፡ክሕደት፡እኛ፡እንርቃለን።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

፲፱፡ ወነሐውር ፡ ፍኖተ ፡ ርትዕተ ፡ እንተ ፡ ወይ
ኀቢያ ፡ መርሖነ ፡ አበዊነ ፡ ንጹሐን ፡ ወይ
እቲ ፡ ትወስደነ ፡ ኀበ ፡ ሕይወት ፡ ዘበ
አማን ፡ ወእሉሰ ፡ ኅጡአነ ፡ አእምሮ ፡
እለ ፡ አጽለሙ ፡ ብርሃናተ ፡ ብርሃን ፡ ኢተ
ምህሩ ፡ ወኢያእምሩ ፡ አእምሮ ፡ ሃይማኖት ፡
ዘነበብናሁ፡ንሕነ።

በረከቱ ፡ ለዝንቱ ፡ መምህር ፡ የሃሉ ፡ ምስሌነ ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ተግሣጽ ፡ ዘይትነበብ ፡ በተሰዐቱ ፡ ሰዓተ ፡
መዓልት፡ዘረቡዕ።

ተግሣጽ ፡ ዘዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ በረ
ከቱ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

፩፡ ወቀናኢሰ ፡ የአኪ ፡ እምአርዌ ፡ ዘይጥሕር ፡
ወየሐሥም፡እምአጋንንት፡እኩያን።

፪፡ ይደልወነኬ ፡ ከመ ፡ ንርሐቅ ፡ እም
ቅንአት፡በሀኬትነ፡ከመ፡ንድኅን፡እምነገረ፡
ሀጕላን።

፫፡ እስመ ፡ ትሬእዩ ፡ እንዘ ፡ ይኔጽሮ ፡
ቀናኢ ፡ ለብእሲ ፡ ከመ ፡ ከይሲ ፤ ወይጥሕር ፡
ላዕሌሁ ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡ ወይልህብ ፡ ለዓው
ዕዮቱ ፡ ከመ ፡ ዕቶን ። ወይፈቅድ ፡ ውኂጦቶ ፡
ከመ፡አጋንንት

፬፡ ወይትፌሣሕ ፡ በምጽአተ ፡ መንሱታት ፡
ወየሐዝን ፡ በከዊነ ፡ ሀድአታት ፡ ወያከብድ ፡
ሕማመ፡ዘእልቦ፡መጠን።

፭፡ ሰማዕከሙ ፡ በማኅበረ ፡ ቀናእያን ፡
ከመ ፡ ይቀትሉ ፡ ንጹሐ ፡ በኅቡእ ። አ ፡
መንክር ፡ እምነ፡ አራዊት ፡ ወአዕዋፍ ፡
ወእንስሳ ፡ ወዘይትሐወስ ፤ የሐምሙ ፡
በሕማመ ፡ አብያጺሆሙ፡ ዘፍጥረት ፡
ወይትራድእዎሙ ፡ በተቃውሞ ፡ መስተባእሳ
ኒሆሙ።

፮፡ ወቀናኢሰ ፡ ይገብር ፡ እኪተ ፡ ሀየንተ ፡
ዝንቱ ፡ እስመ ፡ ይትፌሣሕ ፡ በድቀተ ፡
እኁሁ ፡ ዘቅሩብ፡ ወርኁቅ ፡ ወእንግዳ ፡
ወቢጽ ፡ ወዐርክ። ወከመ ፡ ዐሳብ ፡ አራ
ዊት ፡ መሣጥያን ፡ ወተሐዋስያን ፡ ኅሡ
ራን ፡ ይበቍዑ ፡ ለትእዛዘ ፡ ካልእኒሆሙ ፡
እንዘ ፡ አልቦሙ ፡ ልቡና ፡ ወግዙፋነ ፡
ፍጥረት።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፱፡ ንጹሐን፡አባቶቻችን፡ወደ፡እርስዋ፡በመሩን፡
በቀናችው ፡ ጐዳና ፡ (ሃይማኖት) ፡ እንሄዳለን፡
እንኖራለን ፤ እሷም ፡ ወደማያልፍ ፡ ሕይወት፡
ታደርሰናለች ፤ ዕውቀት ፡ የሌላቸው ፡ ጌታ፡
የሾማቸው ፡ ሐዋርያትን ፡ የነቀፉ ፡ እነዚህ፡
ግን፡ አልተማሩም ፤ እኛ ፡ የተናገርነውን፡
ምሥጢረ፡ሃይማኖትንም፡አላወቁም።

የዚህ ፡ መምህር ፡ በረከት ፡ ከእኛ ፡ ጋራ፡
ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

ረቡዕ ፡ ከቀኑ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ የሚ
ነበብ

በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ ፡ ይኑርና፡
ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ የተናገረው ፡ ምክርና፡
እዝናት፡ይህ፡ነው።

፩፡ ቀናተኛ ፡ ግን ፡ ነጥቆ ፡ ከሚጮኽ ፡ አውሬና፡
ከክፉዎች፡አጋንንት፡ይከፋል።

፪፡ በስንፍናችን ፡ ከሚመጣብን ፡ ቅናት ፡ እንርቅ፡
ዘንድ ፡ ይገባናል ፤ ከተንኰል ፡ ከሸንገላ ፡ ነገር፡
እንድንድን።

፫፡ ቀናተኛ ፡ እንደሚነድፍ ፡ እባብ ፡ ባልንጀ
ራውን ፡ ሲመለከተው ፡ እንደሚአገሳ ፡
አንበሳም ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ሲጮህ ፡ እንደ ፡ ምድጃ፡
እሳት ፡ ለማቃጠል ፡ ሲላላብ ፡ እንደ ፡ አጋን
ንትም፡ሊውጠው፡ይወዳልና።

፬፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ጥፋትና ፡ መከራ ፡ ሲመጣ ፡ ደስ፡
ይለዋል ፤ ጸጥታና ፡ ሰላም ፡ ሲሆን ፡ ያዝናል፤
መጠን፡የሌለውንም፡መከራ፡ያከብዳል።

፭፡ ንጹሑን፡ደም፡በሥውር፡እንደሚያፈስሱ፡በቀ
ናተኞች ፡ ማኅበር ፡ የሆነውን ፡ ሰምታችኋል፤
ከአራዊት ፡ ከአዕዋፍ ፡ ከሚንቀሳቀስ ፡ እንስሳ፡
በተፈጥሮ ፡ ወገናቸው ፡ ለሆኑ ፡ መከራቸውን፡
መከራ ፡ ያደርጋሉ ፤ በችግራቸውም ፡ ይተባበሯ
ቸዋል ፤ የሚጣሉአቸውንም ፡ በመቃወም ፡ ይራ
ዱአቸዋልና፡ለዚህ፡አንክሮ፡ይገባል።

፮፡ ቀናተኛ ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ፈንታ ፡ ክፉ ፡
ያደርጋል፤ በቅርቡም ፡ በሩቅም ፡ በእንግድ
ነትም ፡ በጓደኛነትም ፡ በወዳጅነትም ፡ ባለ
በወንድሙ፡ጉዳት፡ደስ፡ይለዋል፤ግዴታ፡እን
ደሌላቸው ፡ ነጣቂዎች ፡ አራዊትና ፡ የሚያኈ
ሳቍሉ ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ተፈጥሮአቸው ፡
የደነደነ፡አእምሮ፡የሌላቸው፡ሲሆኑ፡ባልንጀ
ሮቻቸውን፡ለማገልገል፡ይጠቅማሉ።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ወከመ፡ዘነጥአ፡ልቦ፡ወኢረከበ፡ፍድፍድና፡
እምሰብእ፡ ይትፌሣሕ ፡ በረኪበ ፡ ትፍግ
ዕታት፡ ወትፍሥሕታት ፡ ወየሐምም ፡ ሶበ ፡
ትረክቦ ፡ መሥገርት ። ከመዝ ፡ ትሬስዮ ፡
ወትረ፡ሕዙነ፡ወሕሱመ።
ወሶበ ፡ አእመረ ፡ ዘይገብር ፡ ዘንተ ፡
ከመ፡ ቅንአት ፡ ረሰየቶ ፡ ለቃየል ፡ ቀታሌ ፡
ወጉህላዌ፡ርጉመ፡ወዘቦኑነ፡ወርሑቀ፡እምእ
ግዚአብሔር ፡ ወቅሩበ ፡ አጋንንት ። ወረ
ሰየቶ ፡ ለአቤል ፡ ዘቀንአ ፡ ላዕሌሁ ፡
መልአከ ፡ ሱራፌል፡ ኀበ ፡ ሰማይ ። ወከ
መዝ ፡ ገብረት ፡ በዳዊት ፡ ወበሳዖል ፡ ወበ
ሙሴ ፡ ወበደቂቀ ፡ ቆሬ ፡ ወበኤሳው ፡ ወበ
ያዕቆብ ፡ ወከማሁ ፡ ደቂቀ ፡ ያዕቆብ ፡ ምስለ ፡
ጸድቅ፡ዮሴፍ፡ሶበ፡ኀለዩ፡ቀቲሎቶ፡ቀንኡ፡
ወሤጥዎ፡ኀበ፡ነኪር፡በኀቡእ።
ወእፎ ፡ የዐቢ ፡ ሢመቱ ፡ ወተለዓለ ፡
ኀበ ፡ ነኪራን ፡ ሥልጣኑ ፡ ወአቅነየ ፡
ከማደ ፡ አኀዊሁ፡ ወአብጽሖሙ ፡ ኀቤሁ ፡
ወሶበ ፡ ደንገጹ ፡ ወፈርሁ ፡ መጽአ ፡ ያሠኒ ፡
ድንጋፄሆሙ ፡ ወእፎ ፡ ከሠተ ፡ ሎሙ ፡
ጸድቅ ፡ ሕልሞ፡ ወጸለሎሙ ፡ በክነፊሁ ፡
ወሴሰዮሙ ፡ በዓመታተ ፡ ረኃብ ፡ ወአኀ
ደሮሙ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ሠናይት ፡
ወሥዕርት።
መከማሁ፡ገብሩ፡አይሁድ፡በክርስቶስ፡ሶበ፡
ፈቀዱ፡ይቅትልዎ፡መጠውዎ፡በጕህሉት፡
ለስቅለት።
፲፩፡ ወሶበ፡በጽሐ፡ኀበ፡ጸዳለ፡ስብሐቲሁ፡
ወተለዓለ፡ኀበ፡ምኵናነ፡ሥልጣኑ፡ሰረየ፡
ለእለ፡ነስሑ፡እምኔሆሙ።
፲፪፡ ወለእለ ፡ ተመይጡ ፡ እምእከዮሙ ፡
ረሰዮሙ ፡ ወራስያነ ፡ ወሰባክያነ ፡ በጽዋ
ዔሁ ፡ ወሱቱፋነ ፡ ለጸጋ ፡ መንግ
ሥቱ።
፲፫፡ ወረሰዮሙ ፡ ለእለ ፡ ጸንኡ ፡ በክሕደቶሙ ፡
ወተአኀዙ፡በአሕባለ፡እከዮሙ፡መንፈቆሙ፡
ለሰይፍ፡ወመንፈቆሙ፡ለመሥጥቅ፡ወመን
ፈቆሙ ፡ ለተበርብሮ ፡ ወመንፈቆሙ ፡
ለተፄውዎ ፡ ወመንፈቆሙ ፡ ለረኃብ፡ ወመን
ፈቆሙ፡ለተሞቅሖ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፯፡ አእምሮውን፡አጥቶ፡ከሰው፡ብልጫ፡እንዳገኘ፡
ሁኖ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ሲቀማጠል፡ ድንገት ፡
መከራ፡ባገኘችው፡ጊዜ፡እንደሚሠቃይ፡ሰው፡
እንደዚሁ ፡ በሐዘን ፡ በመከራ ፡ ተሠቃይቶ፡
የሚጠፋ፡ታደርገዋለች።
፰፡ ይህን ፡ የሚሠራ ፡ ቅንአት ፡ ቃየለን ፡ ገዳይ ፡
ተንኰለኛ፡ሸንጋይ፡የተረገመ፡የተለየ፡ከእግ
ዚአብሔር፡የራቀ፡ለአጋንንት፡የቀረበ፡እንዳ
ደረገችው ፡ ቢአውቅ ፡ ኖሮ ፡ የቀናበትን ፡
አቤልንም፡በሰማይ፡ያለ፡መልአክ፡ሱራፌን፡
እንዳስመሰለችው ፡ እንዲሁም ፡ በሳኦልና ፡
በዳዊት ፡ መካከል ፡ በሙሴና ፡ በቆሬ ፡ ልጆች ፡
መካከል ፡ በዔሳውና ፡ በያዕቆብ ፡ መካከል ፡
እንዲሁም ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ በጻድቁ ፡
ዮሴፍ፡ ቀንተው ፡ ሊገድሉት ፡ በአሰቡ ፡ ጊዜ ፡
ወደ፡ባዕድ፡አገር፡በሥውር፡እንደሸጡት።
፱፡ ሹመቱ፡እንዴት፡እንዲበልጥ፡በባዕዳን፡አገር፡
ሥልጣኑ ፡ እንዴት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እንዳለ ፡ ወንድ
ሞቹንም፡አንገታቸውን፡ዝቅ፡አስደርጎ፡እንዳ
ሰገደ፡ወደርሱም፡እንደ፡አቀረባቸው፡በፈሩና፡
በደነገጡም ፡ ጊዜ ፡ መጥቶ ፡ እንዳረጋጋቸው ፡
ሕልሙንም ፡ እንደ ፡ ገለጠላቸው ፡ በልብስ ፡
በምግብ ፡ እንደ ፡ ተንከባከባቸውና ፡ በረኃቡ ፡
ዘመኖች ፡ እንደ ፡ መገባቸው ፡ በለመለመችና ፡
በአማረች፡ምድር፡እንዳሰፈራቸው።
፲፡ እንደዚሁም፡አይሁድ፡በክርስቶስ፡ቀንተው፡
ሊገድሉት ፡ በወደዱ ፡ ጊዜ ፡ በተንኰል ፡
ለስቅላት፡አሳልፈው፡ሰጡት።
፲፩፡ በመስቀል ፡ ለመሰቀል ፡ ደርሶ ፡ የመለኮቱን ፡
ሥልጣን ፡ በገለጠ ፡ ጊዜ ፡ ከእርሳቸው ፡
በንስሓ፡የተመለሱትን፡ይቅር፡አላቸው።
፲፪፡ ከክፋታቸው ፡ የተመለሱትንም ፡ የክብሩ ፡
ወራሾችና ፡ አሕዛብን ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡
የሚጠሩ ፡ የመንግሥቱንም ፡ ሀብት ፡
ተካፋዮች፡አደረጋቸው።
፲፫፡ በክሕደታቸው ፡ የጸኑትን ፡ በክፋት ፡
ሐብል ፡ የተያዙትን ፡ ግን ፡ እኩሉን ፡ ለሰ
ይፍ ፡ እኩሉን ፡ ለመሰንጠቅ ፡ እኩሉን ፡
ለመበዝበዝ ፡ እኩሉን ፡ ለመማረክ ፡ እኩ
ሉን ፡ ለረኃብ ፡ እኩሉን ፡ ለእስራት ፡ ዳረ
ጋቸው።

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

፲፩፡ ወለእለ ፡ ተርፉ ፡ እሞት ፡ ረከቦሙ ፡ ዘየዐኪ ፡ ሞት ፡ ሶበ ፡ ነሥአ ፡ እምኔሆሙ ፡ መንግሥተ ፡ ወቅብዐተ ፡ ወመሥዋዕተ ፡ ስርዐተ ፡ ወመባዐ ፡ እኰቴት ፡ ወአቅርቦ ፡ ቍርባናት።

፲፪፡ ወረሰዮሙ ፡ ውስተ ፡ ግብርናተ ፡ ዓለም ፡ ከመ፡ ተረፈ ፡ ወይን ፡ እምድኅረ ፡ ተቀሥም ፡ ወረሰዮሙ፡ሕዙናን፡ወትኩዛነ፡ይብክዩ፡ወያ ስቆቅዉ፡በሕማመ፡ልቦሙ፡ወስልበተ፡ነፍሳቲሆሙ።

፲፫፡ ወከመዝ ፡ አሐምም ፡ ብዙኅ ፡ ሶበ ፡ እሬኢ ፡ ከመ፡ በዝንቱ ፡ ቅንአት ፡ ይእዜ ፡ በቤተክርስቲያኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማእከለ ፡ አሕዛብ ፡ ወመሀይምናን ፡ እስመ ፡ አስተርአየ ፡ ዲበ ፡ ሊቃውንት፡ፈድፋደ፡እምሕዝብ፡ወተሰቅለ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ለበዓለ ፡ ሢመታት ፡ ፈድፋደ ፡ እምዘተርፉ፡እስከ፡ኀበ፡ምግባረ፡ሃይማኖት፡ ወመዓርገ፡ክህነት።

፲፬፡ ወአኮ፡ዝንቱ፡ባሕቲቱ፡አላ፡ዳእሙ፡ውስተ፡ ኀልዮ፡ጥሪታት፡ወአዝርዕት፡ወመንግዳት፡ ወሢመታት ፡ ወዘእንበለዝ ፡ እምነትኒ ፡ ዘያቀርብ ፡ ፍጹመ ፡ ኀቤሃ ፡ ምክንያተ ፡ ለተቃንአ፡ዘበጽሐ።

፲፭፡ ወይእቲ ፡ እንተ ፡ ትከውን ፡ ምክንያተ ፡ ለሀጕል፡ ወለጕህሉት ፡ ወለዕቅፍት ፡ ወለተ ሰብሮ፡ውስተ፡ምግባራት።

፲፮፡ ወበእንተዝ ፡ አገብእ ፡ ለከ ፡ ወአወሥአከ ፡ በተዛልፎ፡ወእትዋቀሠከ፡ክሡተ፡አ፡ቀናኢ፡ በአብዕልት ፡ ወዘይኔጽር ፡ እለ ፡ ያበዝኁ ፡ ገራውሀ ፡ ወእብለከ ፡ አ ፡ አብድ ፡ ይኄይሰከ ፡ ከመ ፡ ትቅናእ ፡ ለብእሲ ፡ ግዱፍ ፡ ወቍሱል ፡ ወጽዑር፡ወጥብሉል፡በደም፡ወመስተጋብእ፡ ለቍስል፡ብዙኅ።

፲፯፡ ወለእመ ፡ ትቤ ፡ እፎ ፡ ይትሜሰል ፡ ባዕል ፡ በዝንቱ ፡ እብለከ ፡ ጥዩቀ ፡ ለእመ ፡ ነጸርከ ፡ ኀቤሁ ፡ ሠናየ ፡ ወለበውከ ፡ ምግባሮ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ትሬእዮ ፡ እቡደ ፡ በአፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ ወእሱረ ፡ በአፍቅሮ ፡ መፍቅዳት ፡ ወቍሱለ ፡ በአስይፍተ ፡ ጻሕቃት ፡ ዐላዊ ፡ ለሥርዐተ ፡ ኂሩት፡ ተአዛዚ ፡ ለአጋንንት ፡ ስጡመ ፡

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፩፡ ከሞት ፡ የቀሩትንም ፡ የከፋ ፡ የሞት ፡ ሞት ፡ አገኛቸው ። ይኸውም ፡ መንግሥትን ፡ ቅብዐትን፡ ክህነትን ፡ የስርዮቱን ፡ መሥዋዕት ፡ የምስጋናውን፡መስዋዕት፡ጊዜ፡ቊርባን፡ማቅረቢያውን፡ከእነርሱ፡በአሳለፈ፡ጊዜ፡ነው።

፲፪፡ በዓለም ፡ ውስጥም ፡ ግዞተኞች ፡ አደረጋቸው ፤ ወይን ፡ ከተለቀመ ፡ በኋላ ፡ እንደሚቀረው ፡ ቃርሚያ ፡ በተጨነቀ ፡ ልብ ፡ ሰውነታቸው ፡ ከረድኤት፡ተለይታ፡ፈጽመው፡ያለቅሱ፡ዘንድ፡ የሚያዝኑና፡የሚተክዙ፡አደረጋቸው።

፲፫፡ እንደዚሁም ፡ በምእመናንና ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅናት ፡ እንደ በዛች ፡ በአየሁ ፡ ጊዜ ፡ እብዝቼ ፡ አዝናለሁ ። ከሕዝቡ ፡ ከምእመናኑ ፡ ይልቅ ፡ በሊቃውንቱ ፡ ላይ ፡ ጸንታ ፡ ትታያለችና ፤ ከቀሩትም ፡ ሃይማኖትን፡ በማስተማርና ፡ በክህነት ፡ አገልግሎት ፡ እስካሉትም ፡ ላይ ፡ በተሾመው ፡ ልቡና ፡ እጅግ፡ጸናች።

፲፬፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ጥሪት ፡ ማብዛትን ፡ በማሰብ ፡ ብዙ ፡ ዘርቶ ፡ መሰብሰብን ፡ መነገድን ፡ መሾምን ፡ በማሰብ ፡ ያለ ፡ እምነትም ፡ በመሆን ፡ ወደ ፡ መቃናት ፡ ፈጽሞ ፡ የሚአደርስ ፡ ሥራ ፡ በመሥራት፡ነው፡እንጂ።

፲፭፡ ይችም ፡ ለጥፋት ፡ ለተንኰል ፡ ለሽንገላ ፡ ከበጎ፡ሥራ፡ለመሰናከል፡ምክንያት፡የምትሆን ናት።

፲፮፡ ስለዚህ፡ብዙ፡እርሻ፡ያላቸውን፡ባለጸጎችን፡በመመልከት ፡ የምትቀና ፡ ቀናተኛ ፡ ሆይ ፡ በዘለፋና ፡ በተግሣጽ ፡ በግልጥ ፡ እመልስልሃለሁ ። ሰነፍ ፡ ሆይ፡ይልቅስ፡በቊስል፡ተውጦ፡በወደቀ፡ሰው ፡ በመግልና ፡ በደም ፡ ተከቦ ፡ በሚጨነቅ ፡ የብዙ ፡ ቊስል፡መሰብሰቢያ፡በሆነ፡ሰው፡ትቀና፡ዘንድ ፡ ይገባሀል፡እልሃለሁ።

፲፯፡ ባለጸጋ ፡ በዚህ ፡[1] እንዴት ፡ ይመሰላል ፡ ብትል ፡ ወደርሱ ፡ በጥሩ ፡ አመለካከት ፡ ብትመለከት ፡ እንደሚገባ ፡ ሥራውንም ፡ ልብ ፡ ብለህ ፡ ብታስተውል ፡ በገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ ያበደ ፡ ማንኛውንም ፡ ሥጋዊ ፡ ፍላጎትን ፡ በመሻት ፡ ፍቅር ፡ የታሰረ ፡ በምኞት ፡ ፍላጻዎች ፡ የቆሰለ ፡ ለትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ተቃራኒ ፡ ለአጋንንት ፡ ታዛዥ ፡ በጥፋት ፡

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

በመስተ፡ቀላየ፡ሀጉል።

መፍትውኬ ፡ ለነ ፡ ንጕየይ ፡ እምዘከመገ ፡ ሕማም ፡ ወልማድ ፡ ዘይቀትል ፡ ነፍሳቲነ ፡ ከመ፡ ንትባላሕ ፡ ወንቅረብ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘለዑ፡ ስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ምንተኑ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ተብሀለ ፡ ሶበ ፡ ፈቀዱ ፡ አኀው ፡ ከመ ፡ ይትጋብኡ፡ውስተ ፡ መንበሊስ ፡ ወሖረት ፡ ምስሌሆሙ ፡ አሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ዐባይ ፡ ወክብርት ፡ ወባዕልት ፡ ጥቀ ፡ እስመ ፡ አፍቀ ረቶሙ ፡ ወእምክቡራነ ፡ ዘመድ ፡ ይእቲ ፡ ወፈራሂተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወመፍቀሪተ ፡ ሰብእ፡ኄራን።

ወኮነት ፡ ትሴሰዮሙ ፡ እምዘባቲ ፡ ወትትራ ድአሙ፡በኂሩታ።

ወእምብዝኀ ፡ አፍቅሮታ ፡ አኀወ ፡ ወአፍ ቅሮተ፡ አኃው ፡ ኪያሃ ፡ አግብእዋ ፡ ምስሌሆሙ፡ውስተ፡ጸሎተ፡ናብሊስ።

ወእንዘ፡ትቀውም፡ይእቲ፡ብእሲት፡ኀሪት፡በቅሩቦሙ፡ለአኀው፡አኀዙ፡ይስግዱ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ወበተፍጻሜተ፡ጸሎቶሙ፡ነጸረታ፡ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡እንዘ፡ትወርድ፡ላዕለ፡ምሥዋዕ።

ወቆመት፡ቅድሜሆሙ፡ወአስተብፅዐቶሙ፡ለኵሎሙ።

ወይእቲ ፡ ብእሲት ፡ ወሠናይት ፡ ኢነገረት፡ወኢለመኑሂ፡ዘርእየት፡እስከ፡ዕለተ፡ሞታ።

ወሶበ፡ቀርበት፡ለመዊት፡ነገረቶሙ፡ለወልዳ፡

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ጥልቅ፡ባሕር፡የሰጠመ፡ሆኖ፡እንደምታየው፡በማስረዳት፡እነግርሃለሁ።

፳፩፤ ነፍሳችንን ፡ ከሚያጠፉ ፡ ይህን ፡ ከመሰለ ፡ ደዌና ፡ ልማድ ፡ እንርቅ ፡ ዘንድ ፡ ለእኛ ፡ ይገባል፤ ከዚህ፡ሁሉ፡ድነን፡ወደ፡እግዚአብሔርም ፡ በባለሟልነት ፡ እንቀርብ ፡ ዘንድ ። ለእርሱም ፡ ለዘላለሙ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይገባል፡በዕውነት፡አሜን።

ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑርና፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመቤታችን፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፤ ወደ ፡ ጸሎት ፡ ቤት ፡ ይሰበሰቡ ፡ ዘንድ ፡ መነኮሳት፡በወደዱ፡ጊዜ፡ከእርሳቸው፡ጋራ፡አብራ ፡ ስለ ፡ ሄደች ፡ አንዲት ፡ እጅግ ፡ ሀብታምና፡ክብርት፡የሆነች፡ታላቅ፡ሴት፡ተነገረ ። በመንፈሳዊ ፡ ፍቅር ፡ ወዳቸው ፡ ነበርና፡እርሷም፡ከከበሩ፡ሰዎች፡የሆነች፡ናት።እግዚአብሔርን፡የምትፈራና፡ቅዱሳን፡ሰዎችን፡የምትወድ፡ነበረች።

፪፤ እርሷም ፡ ካላት ፡ ሀብቷ ፡ እየመገበቻቸው ፡ በችሮታዋ፡ትረዳቸው፡ነበር።

፫፤ እርስዋ ፡ ወንድሞች ፡ መነኮሳትን ፡ ከመውደ ድዋና፡እነርሱም፡እርስዋን፡ከመውደዳቸው፡ብዛት፡የተነሣ፡የምስጋና፡ጸሎት፡ወደሚፈጸ ሙበት፡ከእነርሳቸው፡ጋራ፡አስገቧት።

፬፤ ያችም፡ደግ፡ሴት፡በቅርባቸው፡ቁማ፡ሳለች፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡ለጸናች፡አምላክን ፡ ለወለደች ፡ ለክብርት ፡ እመቤታችን፡ማርያም፡ሊሰግዱ፡ጀመሩ፤በጸሎታቸውም፡ፍጻሜ፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመቤታችን፡ማርያምን፡በመሠዊያው፡ላይ፡ስትወርድ፡አየቻት።

፭፤ በፊታቸውም፡ቁማ፡ታከብራቸውና፡ትመርቃቸው፡ነበር።

፮፤ ያችም፡ፈጽሞ፡ደግ፡የሆነች፡ሴት፡እስከምትሞትበት፡ቀን፡ድረስ፡ያየችውን፡ለማንም፡ለማን፡አልነገረችም።

፯፤ ለሞት ፡ በተቃረበች ፡ ጊዜ ፡ ለልጆዋና ፡

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ወለአዝማዲሃ ፡ ከመ ፡ ያምጽእዎሙ ፡ ለአ
ጎው ፡ ወይትለአከዎሙ ፡ ወያፍቅርዋ ፡ ለእ
ግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክ
ልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ (ሕይ
ወት) ፡ ወያክብርዋ ፡ ኵሎሙ ፡ ወይትለ
አክዋ፡በተጠናቅቆ፡

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።
ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።
ነገር፡ዘከመ፡ቀብዐቶ፡ዕፍረተ፡ለእግዚእ፡
ኢየሱስ፡ብእሲት፡ዘማዊት። ሣህሉ፡
ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

፩፡ ወይእቲ፡ብእሲት፡ዘዘከርናሃ፡ቀዳሚ፡ሶበ፡
ቀብዐቶ፡ዕፍረተ፡ለእግዚእነ፡በከየት፡ብካየ፡
ዐቢየ፡እስከ፡ኀፀበት፡እገሪሁ፡ለእግዚእነ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በአንብዓ፡ወመዝመዘት፡
እገሪሁ፡በሥዕርታ።

፪፡ ወትቤ ፡ እንዘ ፡ ታስተብቍዕ ፡ በፍርሀት ፡
ዐቢይ፡ አ ፡ ወልዳ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡
ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡
አምላክ፡ተሣሃላ፡ለአመትከ፡ወሥረይ፡ላቲ፡
ኃጢአታ፡ብዙኃ።

፫፡ ወይቤላ ፡ እግዚእ ፡ ለማርያም ፡ ኃጥእት ፡
አማን ፡ እብለኪ ፡ ከመ ፡ ኃደጉ ፡ ኃጢአ
ተኪ ፡ ወጌጋየኪ፡ እመኒ ፡ ብእሲቶ ፡ በዝ ፡
ነገር፡ወአእምሪ፡ከመ፡በኵሉ፡መካን፡ኀበ፡
ይዘከሩ፡ስምየ፡ይዘከሩ፡ስመኪ፡በህየ፡እስከ፡
ለዓለም።

ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

### ክፍል፡፫።
### ዲ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፡፹፱፡፱።
እስመ ፡ ናሁ ፡ ወውዑ ፡ ፀርከ ። ወአንሥኡ ፡
ርእሶሙ፡ጸላእትከ።እስመ፡ተማከሩ፡ኀቡረ፡
ወፀረዩ።

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ለዘመዶቿ፡ነገረቻቸው፤ወንድሞች፡መነከሳ
ትንም ፡ አምጥተው ፡ ይረዱአቸው ፡ ዘንድ፡
በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡
የሕይወት ፡ እናት ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን፡
ማርያምንም ፡ ሁሉም ፡ በጥንቃቄ ፡ ያከብሩ
አትና፡ያገለግሉአት፡ዘንድ፡አዘዘቻቸው።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።
ይቅርታውና ፡ ቸርነቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡
ለዘላለሙ፡ ይደርብንና ፡ አመንዝራዋ ፡ ሴት፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ሽቱ ፡ እንደ፡
ቀባችው ፡ የሚናገር ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒ
ታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ያደረገው፡ድንቅ፡
ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፡ አስቀድመን ፡ ያስታወስናት ፡ ያቺ ፡ ሴት፡
ጌታችንን ሽቱ ፡ በቀባችው ፡ ጊዜ ፡ የጌታችን፡
እግሮቹን ፡ በእንባዋ ፡ እስከ ፡ አጠበች ፡ ድረስ፡
መራራ ፡ ልቅሶ ፡ አብዝታ ፡ አለቀሰች፤
በራስዋም፡ጠጉር፡እግሩን፡አሸች።

፪፡ በታላቅ ፡ ፍርሀትም ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ፡
በድንጋሌ፡ ነፍስ ፡ የጸናች ፡ የክብርት ፡ እመቤ
ታችን ፡ማርያም፡ ልጅዋ፡ሆይ፤እኔን፡ባርያህን፡
ይቅር፡በለኝ፤ኃጢአቴንና፡በደሌንም፡አስተስር
ይልኝ፡በማለት፡እየማለደች፡ነበር።

፫፡ ጌታም ፡ አመንዝራ ፡ የነበረችውን ፡ ማርያም፡
እንተ ፡ እፍረትን ፡ ኃጢአትሽንና ፡ በደልሽን፡
እንደ ፡ ተውኹልሽ ፡ በዕውነት ፡ እነግርሻ
አለሁ፤ ሴትዮ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ እመኚ ፡ የእኔ፡
ስም፡በሚጠራበት፡ቦታ፡ሁሉ፡ስምሽ፡እስከ፡
ዓለም፡ፍጻሜ፡ሲታወስ፡ይኖራል።

ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡ለዘላለሙ፡ከእኛ፡ጋር፡
ይኑር፡አሜን።

### ክፍል፡፫።
### ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፡፹፱፡፱።
እነሆ ፡ ጠላቶችህ ፡ ደንፍተዋልና ፡ ጠላቶችህ፡
ራሳቸውን ፡ ነቅንቀዋልና ፡ በአንድነት ፡
ተካክለው፡ተማክረዋልና።

፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ወንጌል፡ዘማርቆስ።

ምዕ፲፬፡፩–፲፩።

ወእስከ፡ሰኑይ፡መዋዕል፡ፋሲካ፡ወበዓለ፡
መሰት፡ወኃሠሡ፡ሊቃነ፡ካህናት፡
ወጸሐፍት፡ይትመየንዎ፡ወየአኀዝዎ፡ወይቅ
ትልዎ።
ወይቤሉ፡አኮ፡በበዓል፡ከመ፡ኢይትሀወኩ፡
ሕዝብ።
ወእንዘ፡ሀሎ፡በቢታንያ፡በቤተ፡ስም
ዖን፡ዘለምጽ፡እንዘ፡ይረፍቅ፡መጽአት፡
ብእሲት፡ወአምጽአት፡ዕፍረተ፡ዘአልባስ
ጥሮስ፡ዘናርዱ፡ቅድው፡ዘዕፀ፡ሤጡ፡
ወአኮሰቶ፡ወሶጠት፡ዲበ፡ርእሱ፡ለእግዚእ፡
ኢየሱስ።
ወቦ፡እለ፡ተምዑ፡ወይቤሉ፡ለምንት፡
ዘመጠነዝ፡ሀጕል፡ዘዝዕፍረት።
እምኢተክህለኑ፡ይሠየጥ፡ዝንቱ፡ዕፍረት፡
ፈድፋደ፡እምሠለስቱ፡ምዕት፡ዲናር፡ወይት
ወሀብ፡ለነዳያን፡ወገሠፅዋ።
ወይቤሎሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ኅድግዋ፡
ለብእሲት፡ወኢታሥርኅዋ፡ሠናየ፡ግብረ፡
ገብረት፡ላዕሌየ።
ወለነዳያንሰ፡ዘልፈ፡ትረክብ
ዎሙ፡በኀቤክሙ፡ወጊዜ፡ፈቀድክሙ፡
ታሚንዩ፡ሎሙ፡ወኪያየሰ፡አኮ፡ዘልፈ፡ዘትረ
ክቡኒ።
ወዛቲኒ፡ዘባቲ፡ገብረት፡ወአቅደመት፡ወቀብ
ዐተኒ፡ሥጋየ፡ለቀበርየ።
አማን፡እብለክሙ፡ኀበ፡ሰበክዋ፡ለዛቲ፡
ወንጌል፡ውስተ፡ኵሉ፡ዓለም፡ይነግሩ፡
ዘገብረት፡ዛቲ፡ብእሲት፡ወይዜክርዋ።
ወይሁዳ፡አስቆሮታዊ፡አሐዱ፡እምዐሠርቱ፡
ወክልኤቱ፡ሖረ፡ኀበ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ከመ፡
ያግብአ፡ሎሙ።
ወሰሚዖሙ፡ተፈሥሑ፡ወተናገርዎ፡የሀብዎ፡
ወሳሳ፡ብሩረ፡ወፈቀደ፡በጽሚት፡ያግብኦ፡
ሎሙ።

ድኅረ፡ወንጌል፡በተሰዓቱ፡ሰዓተ፡መዓልት፡
ዘረቡዕ።

ለምሥጢረ፡ትስብእትከ፡ኅባእካሁ፡ውስተ፡
ሥጋነ፡አምላክነ፡ክርስቶስ፡እምዘርዐ፡
አብርሃም፡ርእሰ፡አበው፡አበ፡ኵሎሙ፡
አሕዛብ፡ዘአእመረ፡በሃይማኖት፡ከመ፡

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

የማርቆስ፡ወንጌል።

ምዕ፲፬፡፩–፲፩።

፩፤ ከሁለት፡ቀንም፡በኋላ፡በዓለ፡ናዕት፡(ቂጣ)፡ነበረ፡የካህናት፡አለቆችና፡ጸሎችም፡ሊተናኮሉት፡ሊይዙትና፡ሊገድሉት፡ይሹ፡ነበር።

፪፤ ነገር፡ግን፡ሕዝቡ፡እንዳይታወኩ፡በበዐል፡አይሁን፡አሉ።

፫፤ በቢታንያም፡በለምጻሙ፡ስምዖን፡ቤት፡ለምሳ፡ተቀምጦ፡ሳለ፡አንዲት፡ሴት፡መጥታ፡እጅግ፡ያማረ፡ዋጋ፡የከበረ፡ናርዶስ፡የሚባል፡አንድ፡ብልቃጥ፡ሽቱ፡አመጣችና፡አዋሕዳ፡በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ላይ፡አፈሰሰችው።

፬፤ የዚህ፡ሽቱ፡ጥፋት፡ይህን፡ያህል፡ለምን፡ድነው?፡ብለው፡የተቆጡም፡አሉ።

፭፤ ይህ፡ሽቱ፡ከሦስት፡መቶ፡ወቄት፡በላይ፡ተሽጦ፡ለነዳያን፡ሊሰጥ፡ባልተቻለም፡ነበርን፡ብለው፡ገሠጽዋት።

፮፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡እንዲህ፡አላቸው፤ሴቲቱን፡ተዋት፡አታዳክሙዋት፤ለእኔ፡መልካም፡ሥራ፡ሠርታለች።

፯፤ ነዳያንንስ፡ዘወትር፡በእናንተ፡ዘንድ፡ታገኙዋቸዋላችሁ፤በወደዳችሁም፡ጊዜ፡ታደርጉላቸዋላችሁ፤እኔን፡ግን፡ዘወትር፡የምታገኙኝ፡አይደለም።

፰፤ ይህቺም፡ያላትን፡አደረገች፤አስቀድማም፡ለመቃብሬ፡ሥጋዬን፡ቀባች።

፱፤ እውነት፡እላችኋለሁ፤ወንጌልን፡በሚሰብኩበት፡ቦታ፡ሁሉ፡ይህቺ፡ሴት፡ያደረገችውን፡ይናገሩላታል፡ያስቧታልም።

፲፤ ከአሥራ፡ሁለቱ፡አንዱ፡ያስቆሮቱ፡ሰው፡ይሁዳም፡ለነሱ፡አሳልፎ፡ይሰጣቸው፡ዘንድ፡ወደ፡ካህናት፡አለቆች፡ሄደ።

፲፩፤ ሰምተውም፡ደስ፡አላቸውና፡ሠላሳ፡ብር፡ሊሰጡት፡ተዋዋሉት፤በሥውርም፡አሳልፎ፡እንዲሰጣቸው፡ምቹ፡ጊዜ፡ይሻ፡ነበር።

ከወንጌል፡በኋላ፡ረቡዕ፡ከቀኑ፡በዘጠኝ፡ሰዓት፡የሚነበብ።

፩፤ ፈጣሪያችን፡ክርስቶስ፡ሆይ፡የአባቶች፡አለቃና፡የብዙ፡ሕዝብ፡ሁሉ፡አባት፡ከሆነ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡አካላዊ፡ቃል፡ከእርሱ፡ዘር፡ሰው፡እንዲሆን፡እንዲገባው፡በሃይ

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ወልደ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ይደሉ፡ይሠነ፡ እምዘርዑ።

፪፤ ወፈድፋደሰ ፡ ሰበ ፡ ርእየ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ዘነትገት፡ወከመ፡እግዚአብሔር፡ባረከ፡ምግባራቲሁ፡ጸውዖ፡ለገብሩ፡ዘየዐቢ፡በውስተ፡ቤቱ፡መጋቢ፡ምእመን፡ወተናገረ፡ምስሌሁ፡እንዘ፡ይብል፡ደይ፡እዴከ፡ዲበ፡እዴየ፡ከመ፡እምሕልከ ፡ በአምላከ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ ከመ፡እንተ፡ኢትንሣእ፡ብእሲተ፡ለወልድየ፡ይሥሐቅ ፡ እምዛቲ ፡ ምድር ፡ እንተ ፡ አነ ፡ እነብር፡ውስቴታ፡አላ፡ኀበ፡ምድረ፡አበውየ፡ወንሣእ፡ ሎቱ ፡ ብእሲተ ፡ እምሕዝብየ ፡ ወዘመደ ፡ አበውየ ፡ ወንሣእ ፡ ላቲ ፡ ሕፄ ፡ ዘእንበለ፡ሀኬት።

፫፤ ወአውሥአ፡ቍልዔሁ፡በአእምሮ፡ዘከመ፡ዝ፡እንዘ ፡ ይብል ፡ ስማዕ ፡ እግዚእ ፡ ለእመሰ ፡ ኢትመጽእ፡ምስሌየ፡ይእቲ፡ብእሲት፡ኀበ፡ዛቲ፡ምድር፡ትፈቅድኑ፡አግብእ፡ለወልድከ፡ይሥሐቅ፡ወእትለአኮ፡እስከ፡የዐርግ፡ኀበ፡ዝንቱ፡መካን።

፬፤ ይቤ ፡ ኢይኩን ፡ ከመ ፡ ታግብእ ፡ ለወልድየ፡ለእመ፡ኢመጽአት፡ትክውን፡ንጹሐ።

፭፤ ወወደየ፡ገብር፡እዴሁ፡ወመሐለ፡ሎቱ፡በእንተ፡አጽንዖተ፡ዝንቱ፡ነገር። ወጸንአ፡ምስለ፡ቃለ፡እግዚኡ፡ከመ፡ይግበር፡ትእዛዛቲሁ።

፮፤ አ፡ለዝንቱ፡ብዕል፡ዘኢይትረከብ፡ወዕመቀ፡ጥበበ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡እስመ፡ውእቱ፡ከሠተ፡ዘንተ፡ምሥጢረ፡ዘልዑል፡እምላዕለ፡አልባብ፡ለቍልዔ፡አብርሃም፤

፯፤ ከመ ፡ ዝ ፡ አስተርአዩ ፡ ነቢያት ፡ ወበዝኁ፡ነገሥት፡በደኃሪ፡መዋዕል፡ፈጸመ፡ኪዳነ ፡ ዘተካየደ ፡ ኪያሁ ፡ እግዚአብሔር፡ለአቡነ፡አብርሃም፡አስተርአየ፡ክርስቶስ፡እምሐቌሁ፡ ወተባረኩ ፡ ቦቱ ፡ ኵሎሙ፡አሕዛብ፡ዘከመ፡መሐላ፡ዘአቀመ፡እግዚአብሔር፡ከመ፡ቍልዔሁ፡ያስተርኢ። አስተርአየ ፡ በመለኮቱ፡ ወመንክራቲሁ ፡ ብዙኃት።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ማኖት፡ከአወቀ፡ከአብርሃም፡ዘር፡ከነማኸው፡ሥጋችን፡ ውስጥ ፡ የሥጋዌህን ፡ ምሥጢር፡ሠወርከው።

፪፤ ይልቁንም፡ዕድሜው፡የገፋ፡አብርሃም፡በሥራው ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ፡ባረከው፡በአየ፡ጊዜ፡በቤቱ፡ውስጥ፡ታማኝ፡ሹም፡የሆነ፡ታላቁን፡አገልጋዩን፡ጠርቶ፡ወደ፡ዘመዶቼና፡ወደ፡አባቴ፡ወገኖች፡ሂደህ፡ለልጄ፡ይሥሐቅ፡ከዚያ፡ሚስት፡እንድታጋባው፡እንጂ፡ዛሬ፡እኔ፡አብሬአቸው፡ከምኖርባት፡አገር፡ካሉ፡ወገኖች፡እንዳታጋባው፡ሰማይና ፡ ምድርን ፡ በፈጠረ ፡ አምላክ፡ አምልህ፡ዘንድ፡እጅህን፡በእጄ፡ላይ፡አኑር፡ብሎ፡ከእርሱ፡ጋር፡ተነጋገረ። ማጫዋንም፡ያለ፡መሸለግ፡ውሰድላት።

፫፤ ሎሌውም ፡ በማስተዋል ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ፤ ጌታዬ ፡ ስማ ፡ ያቺ ፡ ሴት፡ ወደዚች ፡ አገር ፡ ባትመጣ ፡ ልጅህ ፡ ይሥሐቅን፡ወደዚህ፡ቦታ፡እስኪወጣ፡ድረስ፡እያገለገልኩት ፡ ወደ ፡ አገርህ ፡ እመልሰው፡ዘንድ፡ትወዳለህን።

፬፤ ልጄን ፡ ትመልሰው ፡ ዘንድ ፡ አይሆንም፤ ሴቲቱ፡ካልመጣች፡ግን፡ከመሐላው፡ንጹሕ፡ነህ፡አለው።

፭፤ ሎሌውም ፡ ነገሩን ፡ ስለ ፡ ማጽናት ፡ እጁን፡ጸፍቶ ፡ ማለለት ። ትእዛዞችንም ፡ ይፈጽም፡ዘንድ ፡ ከጌታው ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ መሐላውን፡አጸና።

፮፤ ወዮ፡ለዚህ፡ለማይመረመር፡ሀብትና፡ጥልቅ፡ለሆነ፡ለእግዚአብሔር፡ቃል፡ጥበብ፡አንክሮ፡ይገባል፤ከህሳብ፡በላይ፡የሆነ፡ይህን፡ምሥጢር፡ለአብርሃም፡ሎሌ፡እርሱ፡ገልጦአልና።

፯፤ እንዲሁ፡ነቢያት፡ተገልጠው፡አስተማሩ፤ነገሥታትም፡በዙ፡በኋለኛውም፡ዘመን፡እግዚአብሔር፡ለአባታችን፡ለአብርሃም፡የገባውን፡ቃል፡ኪዳን፡ፈጸመ። ክርስቶስ፡ከአብርሃም፡ዘር፡በሥጋ፡ተገለጸ፤በእርሱም፡አሕዛብ፡ሁሉ፡በሃይማኖት፡በልጅነት፡ከበሩ፤እግዚአብሔር፡መሐላውን ፡ እንዳጸና ፡ መጠን ፡ ልጁ ፡ መለኮቱን፡በሥጋ፡ይገልጽ፡ዘንድ፡ብዙ፡የሆኑ፡ተአምራቱን፡ገለጸ፤መሐላውንም፡አጸና።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

፳ መስቴ፡ዕውራን፡አልባብ፡ኢተወክፍዎ፡
መኮነ፡ዘልፈ፡ይሜህር፡በውስተ፡ምኵራባ
ቲሆሙ፡በኃይል፡ብዝኀት፡ወጽንዕ፡ዐቢይ፡
ዘኢየሐምም፡ መጽአ፡ ወሐመ፡ ከመ፡
ያድኅነነ፡በቍስላቲሁ።

ክርስቶስ፡መድኀኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ
ማማቲሁ፡አድኀነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ከመ፡ቀዳሚ።

## ምዕራፍ፡፴፬።

### ክፍል፡፩።

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ዘኢሳይያስ፡ ነቢይ፡ በረከተ፡ እምላኩ፡
ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፶፰፤፩–፲፬።

፩ ክላሀ፡በኃይልከ፡ወኢትምህክ፡ወአዕቢ፡
ቃለከ፡ከመ፡ቀርን፡ወንግሮሙ፡ለሕዝብየ፡
ኀጢአቶሙ፡ወለቤተ፡ያዕቆብ፡ጌጋዮሙ፡
እንዘ፡ ትብል፡ ኪያየኑ፡ ተኃሥሡኒ፡
እምዕለት፡ ዕለተ፡ ወትፈቅዱ፡ ታእምሩ፡
ፍኖትየ፡ከመ፡ሕዝብ፡ዘይገብር፡ጽድቀ፡
ወከመ፡ዘኢኀደገ፡ፍትሐ፡እምላኩ።
፪ ወይእዜኒ፡ ይስእሉኒ፡ ፍትሐ፡ ወጽ
ድቀ፡ወይፈትዉ፡ያእምርዋ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር።
፫ ወሕዝብኒ፡ይቤሉ፡እፎ፡ጾምነሂ፡ወኢር
ኢከነ፡ ወአሕመምነ፡ ነፍሰነ፡ ወኢያእመ
ርከነ።
፬ እስመ፡ አመ፡ ትጸውሙ፡ ትገብሩ፡
ፈቃደክሙ፡ወትትፈደዩ፡ዕዳክሙ።
፭ ትስክዩ፡ወትትዋቀሱ፡ወትትላኰዩ፡ወትት
ገዓዙ፡ ወትጸውሙ፡ ወትዘብጡ፡ ወትት
ዓገሉ፡ነዳየ፡ለምንትኑ፡ትጸውሙ፡ከመ፡
የዐ፡እንዘ፡ታገዕሩ፡ወታዓወይዉ፡ነዳየ።
፮ አኮኬ፡ዘንተ፡ጾመ፡ዘኀረይኩ፡ወአኮ፡ከመ፡
ዛቲ፡ዕለት፡ዘያሐምም፡ነፍሶ፡ሰብእ፡ወኢ፡
ከመ፡አቀጥጠ፡ክሣዶ፡ከመ፡ሕልቀት፡
ወሰከበ፡ውስተ፡ሠቅ፡ወሐመድ፡ኢኮነ፡
ኀሩየ፡ ዝንቱ፡ ጾም፡ በኀበ፡ እግዚአ



ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፳፤ ነገር፡ግን፡ልባቸው፡የታወረ፡አይሁድ፡አል
ተቀበሉትም፡ ድውይ፡ በመፈወስ፡ አጋን
ንትን፡ በማስወጣት፡ ሙት፡ በማንሣት፡
ሁልጊዜ፡በምኵራባቸው፡ያስተምር፡ነበርና፡
በቍስለ፡ሕማሙ፡ይፈውሰን፡ዘንድ፡የማይ
ታመም፡መለኮት፡በሥጋ፡ታመመ።
መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡መጥቶ፡ሰው፡ሁኖ፡
መከራ፡ተቀበለ።በመከራውም፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ከመ፡ቀዳሚ።

## ምዕራፍ፡፴፬።

### ክፍል፡፩።

ረቡዕ፡በአሥራ፡አንድ፡ሰዓት።

የነቢዩ፡ የኢሳይያስ፡ ትንቢት፡ የአምላኩ፡
በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

ምዕ፤፶፰፤፩–፲፬።

፩፤ አሰምተህ፡አስተምር፤አትሸልግ፤ቃልህንም፡
እንደ፡ነጋሪት፡ከፍ፡ከፍ፡አድርገህ፡ለወገኖቼ፡
ኃጢአታቸውን፤ለያዕቆብ፡ወገኖችም፡በዳላ
ቸውን፡ንገራቸው፡ከቀን፡ቀን፡እያላችሁ፡እኔን፡
ትፈልጉኛላችሁን፡ሕግ፡እንደሚጠብቅ፡የፈጣ
ሪውንም፡ሕግ፡እንዳላፈረሰ፡እንደ፡ነቢይ፡
ሥራዬንስ፡ታውቁ፡ዘንድ፡ትወዳላችሁን።
፪፤ አሁንም፡እግዚአብሔር፡ሕግን፡ዕውነት፡
ነገርን፡ ይጠይቁኛል፤ያውቁትም፡ዘንድ፡
ይወዳሉ፡አለ።
፫፤ ሕዝቡም፡ካላወቅንህ፡እንዴት፡ጾምን፡አንተ፡ግን፡
በዓይነ፡ምሕረት፡አላየኸንም፤ሰውነታችንንም፡
አሳዘንን፡አንተ፡ግን፡አላወቅኸንም፡አሉ።
፬፤ በጾማችሁ፡ ጊዜ፡ ፈቃዳችሁን፡ ትፈጽማላ
ችሁና፡ብድራታችሁንም፡ትከፈላላችሁና።
፭፤ ትካሰሳላችሁ፤ትጨቃጨቃላችሁ፤ትከራከራ
ላችሁ፤ትጣላላችሁም፡እንዲህ፡እንዲህ፡እያደ
ረጋችሁ፡ትጾማላችሁና፡እንደ፡ዛሬ፡ድኃውን፡
እያስጮኻችሁ፡ለምን፡ትጾሙልኛላችሁ።
፮፤ ይኸንን፡ጾም፡የመረጥሁ፡አይደለም፤እንደ
ዚች፡ቀንም፡ሰው፡ልቡናውን፤ቢያሳዝን፡አን
ገቱንም፡እንደ፡ቀለበት፡ማስገቢያ፡ቢያቀ
ጥን፡ማቅ፡ለብሶ፡አመድ፡ነስንሶ፡ቢተኛም፡
ይህ፡ ጾም፡ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ብሔር።
፯፤ ወአኮ፡ዘንተ፡ጾመ፡ዘኀረይኩ፡አነ፡ይቤ፡እግ
ዚአብሔር፡ዳእሙ፡ፍታሕ፡ኵሎ፡ማእሰረ፡
ዐመፃ፤ ወዕርቅ፡ ወአርትዕ፡ ኵሎ፡ ጠዋየ፡
ወባልሐ፡ ኵሎ፡ ምንዱበ፡ ወኀድግ፡ ኵሎ፡
መጽሐፈ፡ዐመፃ።
፰፤ ወአጽግብ፡ለርኁብ፡እምእክልከ፡ወአብእ፡
ነዳየ፡ወአኅድሮ፡ውስተ፡ጽላሎተ፡ቤትከ፡
ወእመኒ፡ርኢከ፡ዕሩቀ፡አልብሶ፡ወኢትት
ዓወር፡እምዘርአ፡ቤትከ።
፱፤ ወይገውህ፡ ሶቤሃ፡ ብርሃንከ፡ ወይሠርቅ፡
ፍጡነ፡ ፈውስከ፡ ወተሐውር፡ ጽድቅከ፡
ቅድመ፡ገጽከ፡ወስብሐተ፡እግዚአብሔር፡
ይከድነከ።
፲፤ ሶቤሃኬ፡ይሰምዐከ፡እግዚአብሔር፡በጊዜ፡
ዐውየውከ፡ወእንዘ፡ትነብብ፡ነየ፡ሀሎኩ፡
ይብለከ፡እምከመ፡አእተትከ፡እምላዕሌከ፡
ማእሰረ፡ዐመፃ፡ወነጐርጓር።
፲፩፤ ወለእመ፡ኢዘበጥከ፡ወአንከይከ፡እምሲሳየ፡
ነፍስከ፡ ወአፍአምኮ፡ ለነዳይ፡ ወለእመ፡
አጽገብከ፡ነፍሶ፡ርኁብተ፡ሶቤሃኬ፡ይሠርቅ፡
ማእከለ፡ ጽልመት፡ ብርሃንከ፡ ወይከውን፡
ጽልመትከ፡ከመ፡ብርሃነ፡መዐልት።
፲፪፤ ወይሄሉ፡ እግዚአብሔር፡ ወትረ፡ ምስ
ሌከ፡ ወያጸግበከ፡ ፍትወተ፡ ነፍስከ፡
ወያጠልል፡አዕፅምቲከ፡ወትከውን፡ከመ፡
ገነት፡ ርውይት፡ ወከመ፡ ዓዘቅት፡ ዘኢይ
ነጽፍ፡ማያ።
፲፫፤ ወይትሐነጽ፡መዝበርከ፡ለዓለም፡ወይከውን፡
መሠረትከ፡ ለትውልደ፡ ትውልድ፡
ወለዓለመ፡ዓለም፡ትሰመይ፡ሕንጸ፡ወጥቅመ፡
ወጸያሔ፡ፍኖት፡ለኅዲር።
፲፬፤ ወለእመ፡ሜጥከ፡እግረከ፡በሰንበት፡ከመ፡
ኢትግበር፡ዙሎ፡ፈቃደከ፡በዕለት፡ቅድስት፡
ወትሬስዮን፡ትፍሥሕተ፡ለሰንበታት፡ወቀደ
ስኮን፡ ለእግዚአብሔር፡ ወኢታነሥእ፡
እግረከ፡ ለገቢረ፡ እከይ፡ ወኢታወሥእ፡
ሕሡመ፡ቃለ፡በአፉከ።
፲፭፤ ተወከል፡በእግዚአብሔር፡ወየዐርገከ፡ዲበ፡

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

የተመረጠ፡አይደለም።
፯፤ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤እኔ፡ይኸንን፡ጾም፡
የመረጥሁ፡አይደለም፤በግፍ፡የታሰረውን፡ሁሉ፡
ፍታ ፤ የተጣላውንም ፤ አስታርቅ ፤ የጠመመ
ውንም፡ሁሉ፡አቅና፤የተጨነቀውንም፡ሁሉ፡
አድን፤የሐሰት፡ደብዳቤንም፡ተው፡እንጂ።
፰፤ ለተራበ ፡ ሰው ፡ እህልህን ፡ አጥግበው ፤
ድኃውንም ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ አግብተህ ፡
አሳድረው ፤ የታረዘም ፡ ብታይ ፡ አልብሰው፤
ገንዘብህንም፡መስጠት፡ቸል፡አትበል።
፱፤ የዚያን፡ጊዜ፡ብርሃን፡ረድኤትህ፡ይበራል፤
ድኅነትህ፡ፈጥኖ፡ይደርግልሃል፡ጽድቅህም፡
በፊትህ ፡ ትሄዳለች ፡ የእግዚአብሔርም፡
ብርሃን፡ረድኤት፡ይሠውርኻል።
፲፤ ያን፡ጊዜም፡በለመንኽ፡ጊዜ፡እግዚአብሔር፡
ልመናህን፡ይሰማሃል፤ስትለምንም፡እነሆ፡
አለሁ፡ ይልኻል ፤ በደልን፡ እንጕርጕርን፡
ካንተ፡ካራቅህ።
፲፩፤ ድኃውን፡ካልበደልክ፡ከምትበላው፡ምግብ፡
ከፍለህ፡ለድኃው፡ካጐረስከው፡የተራበንም፡
ሰውነት፡ ካጠገብኽ፡ ያን፡ ጊዜ፡ በጨለማ፡
መካከል፡ ብርሃንህ ፤ ይወጣል፡ ጨለማህም፡
እንደ፡ቀን፡ብርሃን፡ይሆንልኻል።
፲፪፤ እግዚአብሔርም ፡ ሁልጊዜ ፡ በረድኤት፡
ካንተ፡ ጋራ፤ይኖራል፤የልቡናህንም፡ፈቃድ፡
ይሰጥኻል ፤ ሰውነቶችህንም ፡ ያድስልሃል፤
እንደ፡ለመለመች፡የተክል፡ቦታ፡ውኃዋ፡እን
ደማይደርቅ፡ጕድጓድም፡ትሆናለህ።
፲፫፤ የፈረሰው፡ቤትህ፡ለዘላለም፡ይታነጻል፤መሠረ
ትህም፡ለልጅ፡ልጅ፡ይጸናል፤ለዘላለም፡የእግ
ዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ትባላለህ ፤ በኢየሩሳ
ሌምም፡ለመኖር፡መንገድ፡ጠራጊ፡ትባላለህ።
፲፬፤ በከበረች፡ በተለየች፡ በቅዳሜ፡ ሰንበት፡ ቀን፡
ፈቃድህን ፡ ሁሉ ፡ እንዳታደርግ ፤ እግርህን፡
ከመሄድ፡ ብትመልስ፡ በዓሎችንም፡ ተድላ፡
ደስታ፡ ብታደርግ፡ ክፉ፡ ሥራን፡ በመሥራት፡
እግርህን ፡ ባታነሣ ፡ በአፍህም፡ ክፉ፡ ነገርን፡
ባትናገር፡የእግዚአብሔር፡ማደሪያ፡ትባላለህ።
፲፭፤ በእግዚአብሔር፡እመን፤ከምድር፡ወደ፡ተገኘ፡

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

...ሰብታ ፡ ለምድር ፡ ወይሴስየከ ፡ ርስተ ፡
...ሰቆብ፡ አቡከ ፡ እስመ ፡ አፉሁ ፡ ለእግዚአ
ብሔር፡ነበበ፡ከመዝ።

ምዕ፡፶፱፡፩-፰።

...ቡ ፡ ኢትክል ፡ እድኅኖ ፡ እዴየ ፡ ወቦኑ ፡
ኢይሰምዕ፡በዕዝንየ።
...አሉ፡ኃጢአትክሙ፡ይቀውም፡ማእከሌክሙ፡
ማእከለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበእንተ፡ ኃጢአ
ትክሙ፡ሜጥኩ፡ገጽየ፡እምኔክሙ።
ወኢይምሀለክሙ ፡ እስመ ፡ ደም ፡ ምሉዕ ፡
ውስተ ፡ እደዊክሙ ፡ ወአፃብዒክሙ ፡
በኃጢአት ፡ ወከናፍሪክሙኒ ፡ ነበበ ፡ ዐመፃ ፡
ወኃጢአተ፡ተናገረ፡ልሳንክሙ።
ወአልቦ ፡ ዘይነብብ ፡ ጽድቀ ፡ ወዘይፈትሕ ፡
ጽድቀ ፡ ወተወከልክሙ ፡ በከንቱ ፡ ወነበ
ብክሙ ፡ ዘኢይበቍዐክሙ ፡ ወጸነስክሙ ፡
ኃጢአተ፡ወትወልዱ፡ሕማመ።
አንቆቅሖ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ታንቅዑ ፡
ወፈትለ፡ሣሬት፡ተአንሙ፡እስመ፡ዘበልዖ፡
ለአንቆቅሖ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ፍጡነ ፡
ይመውት።
ወፈትለ፡ሣሬትሂ፡ኢይበቍዕ፡ለተዓጽፎ።
እስመ ፡ ግብረ ፡ ዐመፃ ፡ ምግባሪክሙ ፡
ወለኃጢአት ፡ ይረውጻ ፡ እገሪክሙ ፡
ወይፈጥና ፡ ለከዒወ ፡ ደም ፡ ወትመክሩ ፡
ለቀቲል ፡ ኃሣር ፡ ወቅጥቃጤ ፡ ውስተ ፡
ፍኖትክሙ።
ወኢተአምርዋ፡ለፍኖተ፡ሰላም።

ክፍል፡፪።
ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፡፺፰፡፩።

...ዲቤ፡ቅዱስ፡አባ፡መቃርስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእ
ለእስክንድርያ ፡ ውስተ ፡ መልእክቱ ፡ ዘሴኖ
ዲቆን ፡ ኀበ ፡ ንጉሕ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሊቀ ፡
ጳጳሳት፡ዘአንጾኪያ።
ነአምን ፡ በአሐዱ ፡ አምላክ ፡ አብ ፡
እግዚ ፡ ኵሉ፡ ወወልዱ ፡ ዋሕድ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቃሉ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምስ
ሌሁ ፡ ወበመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ዘወፅአ ፡ እም
አብ ፡ ዘይሴባሕ ፡ ወይትአኰት ፡ በወለድ ፡

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ባለጸግነት ፡ ያወጣኻል ፤ የእግዚአብሔር ፡
አንደበቱ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናግሮአልና ፤
የአባትህ፡የያዕቆብን፡ርስት፡ይመግብኻል።

ምዕ፡፶፱፡፩-፰።

፩፤ በውኑ ፡ እጄ ፡ ማዳን ፡ አትችልምን ፡ በውኑ ፡
በጆሮዬ፡አልሰማምን።
፪፤ ኃጢአታችሁ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በእናንተ ፡
መካከል ፡ ቈሟልና ፡ ስለ ፡ ኃጢአታችሁ ፡
ከእናንተ፡ፊቴን፡መለስሁ።
፫፤ በእጃችሁ ፡ ደም ፡ ሞልቷል ፤ ጣቶቻችሁም ፡
በደም፡ታልለዋል፤ከንፈሮቻችሁም፡ሐሰትን፡
ተናገረዋል፤አንደበታችሁም፡ኃጢአትን፡ተና
ግሮአልና፡ይቅር፡አልላችሁም።
፬፤ በእውነት ፡ የሚናገርና ፡ በእውነት ፡
የሚፈርድ፡የለም። በከንቱ፡ታመናችሁ፤የማ
ይረባችሁን ፡ ተናገራችሁ ፤ ኃጢአትን ፡
ጸነሳችሁ፡መከራንም፡ትወልዳላችሁ።
፭፤ የምድር ፡ እባብ ፡ እንቊላልን ፡ ትቀፈቅፋ
ላችሁ፤ የሸረሪት ፡ ድርንም ፡ ታደራላችሁ ፤
የምድር ፡ እባብ ፡ እንቊላልን ፡ የበላ ፡ ሰው ፡
ፈጥኖ፡ይሞታልና።
፮፤ የሸረሪት፡ድርም፡ለመጐናጸፊያ፡አይጠቅምም።
፯፤ ሥራችሁ ፡ የበደል ፡ ሥራ ፡ ነውና ፡ እግሮቻ
ችሁም ፡ ኃጢአትን ፡ ለመሥራት ፡ ይሮጣሉ ፤
ደም ፡ ለማፍሰስም ፡ ይፋጠናሉ ፤ ነፍስንም ፡
ለመግደል ፡ ትመክራላችሁ ፤ በጐዳናችሁም ፡
መከራ፡ጕስቍልና፡አለና።
፰፤ የሰላምን፡ጎዳና፡አታውቋትምና።

ክፍል፡፪።
የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፡፺፰፡፩።

የእስክንድርያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡መቃርስ፡
ወደ፡አንጾኪያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ወደ፡ንጉሕ፡
አባ፡ዮሐንስ፡በላከው፡መልእክቱ፡እንዲህ፡
አለ።
፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ ሁሉን ፡
ፈጥሮ ፡ በሚገዛ ፡ በአብ ፡ እንደርሱ ፡
በቅድምና ፡ በነበረ፡ ቃሉ ፡ በሚሆን ፡
በአንድ ፡ ልጁ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡
ከአብ ፡ በሠረጸ ፡ በወልድ ፡ በተገለጠ ፡

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ወይሰግድ፡ምስለ፡አብ፡ወወልድ።

፲፩፤ ወካዕበ ፡ ነአምን ፡ በአሐዱ ፡ ዘእምቅድስት ፡
ሥላሴ ፡ ወልድ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡
ዘተወልደ ፡ እምኔሁ ፡ እምቅድመ ፡ ኵሉ ፡
ዓለም፡ ዘቦቱ ፡ ኵሉ ፡ ኮነ ፡ ብርሃን ፡ ዘበአማን ፡
እምብርሃን ፡ ዘበአማን ፡ ወበደኀሪ ፡ መዋዕል ፡
ሶበ ፡ ፈቀደ ፡ ያፍልስ ፡ ትዝምደ ፡ ዕጓለ ፡
እመሕያው ፡ ወይሚጠነ ፡ ዳግመ ፡ ኀበ ፡
ሕይወት ፡ እንተ ፡ ትትበፃዕ ፡ ለነ ፡ ለእለ ፡
ወደቅነ ፡ በኀጢአት ፡ በእንተ ፡ ዐሊዎቱ ፡
ለአዳም ፡ በፈቃደ ፡ አቡሁ ፡ ወበግብረ ፡
መንፈስ፡ ቅዱስ ፡ አጽነነ ፡ ሰማያተ ፡ ወወረደ ፡
ኀቤነ ፡ እመ ፡ ተሣሃለነ ፡ ተሠገወ ፡ እመንፈስ ፡
ቅዱስ፡ወእማርያም፡ንጽሕት።

፲፪፤ እመ ፡ አብሰራ ፡ ገብርኤል ፡ሊቀ ፡ መላእክት ፡
በቃሉ ፡ ተሠገወ ፡ እምኔሃ ፡ ወእሚሃ ፡ ፀንሰቶ ፡
፱ተ ፡ አውራኀ ፡ በኍልቈ ፡ ወተወልደ ፡
በመንክር ፡ ግብር ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡
ሐዋርያ ፡ እስመ ፡ ሶበ ፡ በጽሐ ፡ ተፍጻሜተ ፡
መዋዕል ፡ ፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልዶ ፡
ዋሕደ ፡ ወተወልደ ፡ እምብእሲት ፡ ከመዝ ፡
ተወልደ፡እምድንግል።

፲፫፤ ወእምድኅረ፡ልደቱ፡ዘኢይትረከብ፡ኢማሰነ፡
ድንግልናሃ ፡ ወበእንተዝ ፡ አመነ ፡ ከመ ፡
ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ይእቲ ፡ ተወልደ ፡ ሕፃነ ፡
ወተጠብለለ ፡ በአጽርቅት ፡ ወተወድየ ፡
ውስተ፡ ጎል ፡ ወዘአልቦቱ ፡ ጥንተ ፡ መዋዕል ፡
ወዘህልው ፡ ዘለዓለም ፡ ዘልፈ ፡ ምስለ ፡ አቡሁ ፡
ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተወከፈ ፡ መዋዕለ ፡
ወጊዜያተ፡ወልህቀ፡በተሐፅኖ፡እንዘ፡ለሊሁ፡
አሐዱ፡ወልድ።

፲፬፤ ነአምን ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አሐዱ ፡ መሲሕ ፡
ወአሐዱ ፡ እግዚእ ፡ ወአሐዱ ፡ ገጽ ፡ ወአሐዱ ፡
አካል ፡ እግዚአብሔር፡ ቃል ፡ ዘተሠገወ ፡ ውእቱ፡
ሰማያዊ፡ወውእቱ፡ምድራዊ፡አምላክ፡ ወሰብእ፡
ኀቡረ፡ይትዔረዮሙ፡ለአብ፡ወለመንፈስ፡ ቅዱስ፡
በመለኮቱ፡ ወኪያነሂ፡ይትዔረየነ፡በትስብእቱ፡
ኢነሥአ ፡ ሥጋሁ ፡ እምህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወኢ
ወለጠ ፡ ህላዌ ፡ ሥጋ ፡ ኀበ ፡ መለኮቱ ፡ አላ ፡

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

በተመሰገነ ፡ ከአብ ፡ ከወልድ ፡ ጋር ፡ በሚሰገ
ድለት ፡ በመንፈስ፡ቅዱስም ፡ እናምናለን።

፲፩፤ ዳግመኛም ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል፡
ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ከእርሱ ፡ የተወለደ ፡የእግዚአ
ብሔር ፡ አብ ፡ ቃል ፡ ከእውነተኛ ፡ ብርሃን ፡ የተ
ገኘ፡ እውነተኛ ፡ ብርሃን ፤ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡ የተፈ
ጠረ ፡ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ የሰውን፡
ባሕርይ፡ከፍዳ፡ይለይ፡ዘንድ፡በአዳም፡ትእዛዝ፡
ማፍረስ ፡ ምክንያት ፡ በኀጢአት ፡ ተይዘን፡
የነበርን፡እኛን፡ወደምትመሰገን፡ሕይወት፡ዳግ
መኛ፡ይመልሰን፡ዘንድ፡በወደደ፡ጊዜ፡በአባቱ፡
ፈቃድ ፡ በግብረ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ራሱን፡
ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ባሕርያችንን ፡ ባሕርይ ፡ እንደ፡
አደረገ፡ይቅር፡ልበላቸው፡ባለ፡ጊዜም፡በግብረ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከንጽሕት ፡ ማርያም፡ ነፍስን፡
ሥጋን፡ነሥቶ፡ሰው፡እንደሆነ፡እናምናለን።

፲፪፤ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ በቃሉ፡
በነገራት ፡ ጊዜ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ ከእርሷ ፡ሰው፡
ሆነ ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ከአምስት ፡ ቀን፡
ፀነሰችው ፤ ድንቅ ፡ በሚሆን ፡ ሥራ ፡ ወለደችው፤
የቀጠሮው ፡ ዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡እግዚ
አብሔር ፡ አንድ ፡ ልጁን ፡ ላከ ፤ ከድንግልም፡
ተወለደ ፡ ብሎ ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡እንደተ
ናገረ፡እንዲህ፡ከድንግል፡ ተወለደ።

፲፫፤ ከማይመረመር ፡ ልደቱም ፡ በኋላ ፡ ማኅተመ፡
ድንግልናዋ ፡ አልተለወጠም ፤ ስለዚህም ፡
ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ እንደሆነች ፡ አመንን ፤
ሕፃን ፡ ሆኖ ፡ ተወለደ ፤ በጨርቅም ፡ ተጠቀለለ፤
በጎል ፡ ተጣለ ፤ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ተገኘ ፡ የማይባል፡
ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስም፡ ጋር ፡ የነበረ ፤ ያለ፡
ለዘለዓለም ፡ የሚኖር ፡ እርሱ ፡ ዘመን ፡ ተቈጠ
ረለት ፤ ጊዜ ፡ ተነገረለት ፤ እርሱ ፡ አንድ ፡
ወልድ፡ ሲሆን ፡ በየጥቂቱ ፡ አደገ።

፲፬፤ ሰው ፡ የሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አንድ ፡
ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ገዥ ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ አንድ ፡
አካል ፡ እንደሆነ ፡ እናምንበታለን ፡። ሰማያዊ ፡
ነው ፤ ምድራዊም ፡ ነው ፤ በተዋሕዶ ፡ ሰው ፡
የሆነ ፡ አምላክ ፡ ነው ። በመለኮቱ ፡ አብን ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ይተካከላቸዋል ፡ ሰው ፡
በመሆኑም ፡ እኛን ፡ ይመስለናል ፡ ሥጋን ፡

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ከ፡ሰብእ ፡ ከማነ ፡ ወነሥአ ፡ ሥጋነ ፡ ዘገ
ዌ፡ ሎቱ ፡ እምሥጋሃ ፡ ለድንግል ፡ ንጽ
እት፡ማርያም፡ወአኀበሮ፡ምስለ፡መለኮቱ፡
በሕዱ ፡ ኅብረት ፡ ዘአልቦቱ ፡ ፍል
ጠት።

መሰበኒ፡ከነ፡ሰብአ፡ኢኀደገ፡መለኮቶ፡ሐሰ፡
ወአልቦ ፡ ውላጤ ፡ ወኢ ፡ ሚጠት ፡ ወኢ ፡
ቱስሕት፡ውስተ፡እለ፡ኅብሩ፡በተዋሕዶ፡
አላ፡ጽንዕ፡በዘውእቱ፡ቦቱ፡ወኮነ፡ፍጹመ፡
ከማነ፡በኵሉ ፡ ዘይደልዎ ፡ ለትስብእት ፡
ዘእንበለ ፡ ኀጢአት ፡ ባሕቲታ ፡ ወኢይት
ከፈል፡ኀበ፡ክልኤቱ፡ህላዌያት ። ወኢይት
ፈለጥ፡ኀበ፡ክልኤቱ፡አርአያ፡ወኢ፡ኀበ፡
ክልኤቱ ፡ አምሳላት ፡ ወኢይትአመር ፡
በክልኤቱ፡ህላዌያት፡እምድኅረ፡ተዋሕዶ፡
በከመ፡ይቤ፡ዝኩ፡ጉባኤ፡ርኩስ፡ዘተጋብአ፡
በኬልቄዶን፡ወሆከ፡ዓለመ።

ወኢንቤ ፡ ከመ ፡ መንክራት ፡ ለአሐዱ ፡
ወሕማማት ፡ ለካልኡ ፡ አላ ፡ እማንቱ ፡ ለዝ
ንቱ፡አሐዱ፡ውእቱ፡ከመ፡አምላክነ፡ወእግ
ዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡፩ዱ ፡ አካል ፡
ሥግው፡ወ፩ዱ፡ሕላዌ።
በረከቱ፡ለዝንቱ፡መምህር፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ተግሣጽ፡ዘይትነበብ፡በዐሡሩ፡ወአሐዱ፡
ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ተግሣጽ፡ዘአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ሳዊሮስ ፡ ኤጲስ
ቆጶስ፡ዘሀገረ፡ገብልሀ ። ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡
የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ናሁ፡ ይእዜኒ ፡ አ ፡ አኀው ፡ ናዜክረክሙ ፡
በቃል፡ ዘይከውን ፡ ላዕለ ፡ ኃጥአን ፡ ወዐላ
ውያን፡ሕግ።
ወትእዛዝ፡ሕይወትሰ፡ይብል፡ሑሩ፡እምኔየ፡
ርጉማን፡ውስተ፡እሳት፡ዘለዓለም፡ዘድልው፡
ለዲያብሎስ፡ወለመላእክቲሁ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ከባሕርዩ ፡ መለኮቱ ፡ አልነሣም ፤ የሥጋን ፡ ባሕ
ርይም ፡ የመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ ወደ ፡ መሆን ፡ አልለ
ወጠውም ፤ እንደ ፡ እኛ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፡ ሊዋሐ
ደው፡ የፈጠረውን ፡ ሥጋችንን ፡ ከንጽሕት ፡ ድን
ግል ፡ ማርያም ፡ ነሥቶ ፡ መለየት ፡ በሌለበት ፡ በአ
ንድ፡ተዋሕዶ፡ከመለኮቱ፡ጋር፡አንድ፡አደረገው።

፲፫፤ ሰውም ፡ ቢሆን ፡ አምላክነቱን ፡ አልለቀቀም ፤
አምላክነቱን ፡ ለቀቀ ፡ ማለት ፡ አይገባም ፤
በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ በሆኑት ፡ በመለኮትና ፡ በት
ስብእት ፤ መለወጥ ፡ ባሕርይን ፡ መልቀቅ ፡
የለም ፤ በአለበት ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡
ከኃጢአት ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ በሚገባው ፡ ሁሉ ፡
ፍጹም ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ሆነ ። ወደ ፡ ሁለት ፡
ባሕርያት ፡ አይከፈልም ፤ ወደ ፡ ሁለት ፡ ገጽ ፡
ወደ ፡ ሁለት ፡ ግብር ፡ አይለይም ፤ በኬልቄዶን ፡
ተሰብስቦ ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ያወከው ፡ ርኩስ ፡
ጉባኤ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፤ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡
ሁለት፡ባሕርይ፡አይባልም።

፲፬፤ ተአምራትን ፡ ማድረግ ፡ ለአንዱ ፡ መከራ ፡
መቀበልን ፡ ለአንዱ ፡ ሰጥተን ፡ አንናገርም ፤
ጌታችን፡ፈጣሪያችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሰው፡
የሆነ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደ
መሆኑ ፡ ተአምራትም ፡ ሕማማትም ፡ የዚሁ ፡
የአንዱ፡ገንዘብ፡ናቸው፡እንጂ።
የዚህ፡መምህር፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ትኑር፡አሜን።

ረቡዕ ፡ ከቀኑ ፡ በአሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡
የሚነበብ፡ተግሣጽ።

ልመናውና ፡ በረከቱ ፡ ለዘላለም ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡
ይደርብን ። ገብልሀ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ኤጲስቆ
ጶስነት ፡ የተሾመ ፡ አባታችን ፡ ቅዱስ ፡ ሳዊሮስ ፡
የተናገረው ፡ ተግሣጽ ፡ ይህ ፡ ነው ።

፩፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፡ በሕግ ፡ አፍራሾችና ፡ በኃጢ
አተኞች ፡ ላይ ፡ የሚሆነውን ፡ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ እናሳ
ስባችኋለን ።

፪፤ የሕይወት ፡ ትእዛዝ ፡ የሆነ ፡ ወንጌልም ፡
እናንት ፡ የተረገማችሁ ፡ ለሰይጣንና ፡ ለመልአ
ክተኞቹ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀው ፡ ወደ ፡ ዘለዓለም ፡
እሳት ፡ ሂዱ ፡ ይላል ።

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

፫፤ አይኬ፡ኑዛዜ፡እምድኅረዝ፡ዘይሲፈዉ፡እሉ፡ እሙንቱ፡ውእቱ፡ዘበአማን፡መካነ፡ብካይ፡ ወሐዘን፡ዘኢየሐልቅ።

፬፤ ዛቲ፡ይእቲ፡አንብዕ፡ዘኢይከውን፡እምድ ኅሬሃ፡ፍሥሓ።

፭፤ መኑ፡ዘይክል፡ይስአል፡በእንተ፡ኃጥአን፡ በይእቲ፡ዕለት፡እስመ፡መላእክት፡ያረምሙ፡ ሱራፌል፡ወኪሩቤል፡ወኵሎሙ፡ጻድቃን፡ ወቅዱሳን፡ወኢአሐዱ፡ይስአል፡ኢይክል፡ በእንተ፡ሰብእ፡በይእቲ፡ዕለት፡ኵሉ፡ፍጥረት፡ እንዘ፡ያረምሙ፡ወይከውን፡ኵሉ፡ዓለም፡ ታሕተ፡ፍትሐ፡እግዚአብሔር፡ጻድቅ።

፮፤ ዝንቱ፡ውእቱ፡ዘመነ፡መዋዕለ፡ዐጺድ፡ ዝንቱ፡ጊዜ፡ዘየዐስሩ፡ገሬፈ፡ውስተ፡ሐይቅ፡ ወይሌልዩ፡እምነ፡ዓሣ፡ሠናየ፡ወእኩየ።

፯፤ ዝንቱ፡ውእቱ፡ዕለት፡ዘይብልዎሙ፡ለኃጥአን፡ ሑሩ፡ውስተ፡እሳት፡ማኅደሮሙ፡ዘለዓለም።

ጸሎቱ፡ወበረከቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ምንተኑ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡ ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፰፤ ወሀሎ፡አሐዱ፡ብእሲ፡በሀገረ፡ኢየሩሳሌም፡ እመሳፍንተ፡ሮሜ።ወመጽአ፡ከመ፡ይጸሊ፡ ኀበ፡መቃብረ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ወሶበ፡ፈቀደ፡ይባእ፡መጽአ፡ኃይል፡ በአምሳለ፡በግዕ፡ከመ፡ይውግኦ፡ወፈሪሆ፡ ገብአ፡ድኅሬሁ።

፱፤ ወይቤልዎ፡ቀሲስ፡ወእለ፡ምስሌሁ፡ምንተ፡ ኮንከ፡ሊቅ፡ዘኢትበውእ፡ወይቤሎሙ፡ ለምንት፡አባእክምዎ፡ለበግዕ፡ወበዊአሙ፡ አልቦ፡ዘረከቡ፡ወነገርዎ፡ከመ፡ኢያብእዎ፡ ለበግዕ።

፲፤ ወሶበ፡ቀርበ፡ካዕበ፡ይባእ፡መጽአ፡ዝኩ፡ በግዕ፡ወአልቦ፡ዘይሬእዮ፡ዘእንበሌሁ።

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፫፤ እንግዲህ፡ከዚህ፡በኋላ፡እነርሱ፡ተስፋ፡የሚ ያደርጉት፡መጽናኛ፡የትኛው፡ነው? በእውነት፡የማያልቅ፡ለቅሶና፡ሐዘን፡ ያለበት፡ቦታ፡ነው።

፬፤ ከእርሷ፡በኋላ፡ተድላ፡ደስታ፡የማይደረ ግባት፡የዚያን፡ጊዜ፡ልቅሶ፡ይህች፡ናት።

፭፤ በዚያች፡ቀን፡ስለ፡ኃጥአን፡ይለምን፡ዘንድ፡ የሚችል፡ማነው? መላእክት፡ሁሉ፡ ሱራፌልና፡ኪሩቤልም፡ጻድቃንም፡ ቅዱሳንም፡ሁሉ፡ስለ፡ሰው፡ይለምኑ፡ዘንድ፡ አንድ፡ስንኳ፡የሚችል፡የለም፤በዚያች፡ቀን፡ ፍጥረት፡ሁሉ፡ዝም፡ይላል፤በዚያችም፡ቀን፡ ፍጥረት፡ሁሉ፡እውነትን፡በሚፈርድ፡በእግ ዚአብሔር፡ፍርድ፡ውስጥ፡ይሆናልና።

፮፤ የአጨዳው፡ወራት፡ይህ፡ነው።ዘረመትራ ውንም፡(መረቡን)፡አስረው፡ወደ፡ጥልቅ፡ ባሕር፡የሚጥሉበት፤ከተያዘውም፡ዓሣ፡መል ካሙንና፡ክፉውን፡የሚለዩበት፡ጊዜ፡ነው።

፯፤ ኃጥአንን፡ማደሪያቸው፡ወደሚሆን፡ወደ፡ዘለዓ ለም፡እሳት፡ሂዱ፡የሚልባቸው፡ቀኑ፡ይህ፡ነው።

ልመናውና፡ክብሩ፡ለዘላለሙ፡በእኛ፡ላይ፡ ይደርብን።

ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ይኑርና፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡ የጸናች፡አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመ ቤታችን፡ማርያም፡ያደረገችው፡ተአምር፡ ይህ፡ነው።

፰፤ በኢየሩሳሌም፡ከተማ፡ከሮማውያን፡ መሳፍንት፡ውስጥ፡አንድ፡ሰው፡ነበረ። ይጸልይ፡ዘንድ፡ወደ፡ጌታችን፡ወደ፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡መቃብር፡መግባትን፡በፈለገ፡ጊዜ፡ በበግ፡አምሳል፡ሊወጋው፡ኃይል፡መጣ፤ ሰውዬው፡ፈርቶ፡ወደ፡ኋላው፡ተመለሰ።

፱፤ ቄሱና፡አብረውት፡ያሉት፡መስፍን፡ሆይ፡ የማትገባው፡ምን፡ሆንህ፡አሉት፤እርሱም፡ በግን፡ለምን፡አስገባችሁ፡አላቸው፤ እርሳቸው፡ገብተው፡ቢያዩ፡ምንም፡ያገኙት፡ ነገር፡የለም፤በግ፡እንዳላስገቡ፡ነገሩት።

፲፤ ዳግመኛም፡ይገባ፡ዘንድ፡በቀረበ፡ጊዜ፡ያ፡ በግ፡መጣ፡ከእርሱ፡በቀር፡የሚያየው፡የለም።

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ወይቤሎ፡ቀሲስ፡አ፡ሊቅ፡እመ፡ብከ፡ዘይከ
፬ ልለከ፡ከመ፡ኢትባእ፡ውስተ፡ዝንቱ፡መካን፡
ቅዱስ፡ወለእመ፡አመንከ፡በእግዚአብሔር፡
መሐሪ፡ይፈቅድ፡መድኃኒተከ፡ዘአርአየከ፡
ትእምርተ።
ወነገሮ፡ኃጣውኢሁ፡ወበከየ።ወካዕበ፡
፭ ፈቀደ፡ይባእ፡ወከልአ፡በግዕ፡ወይቤሎ፡
ቀሲስ፡እሙንቱ፡ግብር፡ብከ፡ዘይከልአከ፡
ወይቤሎ፡መስፍን፡በእንተ፡ዘኮንኩ፡
ከነናዌ።

ወሶበ፡አምነ፡ቦአ፡ወተመጠወ፡ሥጋሁ፡
፮ ወደሞ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ወኀደገ፡ዘትካት፡ልማዶ፡ወተአመነ፡
ኃጢአቶ።ወአምነ፡በሃይማኖት፡ዘቅድስት፡
ቤተ፡ክርስቲያን።
፯ ወበእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክ
ልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ወአእ
መረ፡ከመ፡ከልአ፡ኃይል፡በዊአ፡ኀበ፡መቃ
ብረ፡ወልዳ፡በአምሳለ፡በግዕ።ወሰብሖ፡ለእግ
ዚአብሔር፡ዘይሁብ፡ምክንያተ፡ለድኂን፡
ለውሉደ፡ሰብእ።

፰ አ፡እግዝእትየ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡
ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ኪያኪ፡ረሰየ፡
መድኃኒተ፡ለኵሉ፡ዓለም፡እግዚአብሔር፡
እግዚእ፡እንተ፡እምኔኪ፡ትስብእተ፡ለብሰ።
አፈልፈለ፡ሕይወተ፡ወአእተተ፡ኃጢአተ፡
ወሰደደ፡ጽልመተ።

አ፡እግዝእትየ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡
ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡አምሕለኪ፡
በኃይለ፡ልዑል፡ዘጸለለኪ፡ወበወልድ፡
ዘተሠገወ፡እምኔኪ፡ወበመንፈስ፡ቅዱስ፡
ዘቀደሰኪ፡ወአንጽሐኪ፡ከመ፡ትዕቀብኒ፡
በጸሎትኪ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።
ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ዘከመ፡መሀሮሙ፡ለአርዳኢሁ፡ይትዐቀቡ፡

## ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፬፤ ቄሱም፡መስፍን፡ሆይ፡ወደዚህ፡ወደተቀ
ደሰው፡ቦታ፡እንዳትገባ፡የሚከለክልህ፡
ኃይል፡አለ፤ምልክት፡በአሳየህ፡ይቅር፡ባይ፡
በሆነ፡እግዚአብሔር፡ብታምን፡የነፍስህን፡
መዳኛ፡ይፈቅድልኻል፡አለው።
፭፤ ኃጢአቱንም፡ነገረውና፡አለቀሰ።
ዳግመኛም፡ይገባ፡ዘንድ፡ወደደ፤በጉ፡
ከለከለው፤ቄሱም፡መግባት፡የሚከለክልህ፡
ባንተ፡ላይ፡በውነት፡አንድ፡ሥራ፡አለ፡
አለው፤መስፍኑም፡የከነዓን፡ሰው፡
ስለሆንኩ፡ነው፡አለው።
፮፤ በአመነ፡ጊዜም፡የጌታችን፡የኢየሱስ፡ክር
ስቶስን፡ሥጋውንና፡ደሙን፡ገብቶ፡ተቀበለ፤
የቀድሞ፡ልማዱንም፡ትቶ፡ኃጢአቱን፡አመነ፤
በከበረች፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ሃይማኖትም፡
አመነ።
፯፤ በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡በጸናች፡
አምላክን፡በወለደች፡በክብርት፡እመቤታችን፡
ማርያምም፡ፈቃድ፡ወደ፡ልጅዋ፡መቃብር፡መግ
ባትን፡በበግ፡አምሳል፡ኃይል፡እንደ፡ከለከለው፡
አወቀ።ለሰው፡ልጆች፡የሚድኑበትን፡ምክን
ያት፡የሚሰጥ፡እግዚአብሔርን፡አመሰገነው።
፰፤ በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናሽ፡
አምላክን፡የወለድሽ፡የከበርሽ፡እመቤቴ፡
ማርያም፡ሆይ፡ሰውነትን፡ከአንቺ፡የተዋሐደ፡
ገዥ፡እግዚአብሔር፡አንቺን፡ለዓለሙ፡ሁሉ፡
መድኃኒት፡አደረገ፤ኃጢአትን፡አስወግዶ፡
ሕይወትን፡አስገኘ፤ድንቁርናንም፡አራቀ።

በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናሽ፡
አምላክን፡የወለድሽ፡ክብርት፡እመቤቴ፡
ማርያም፡ሆይ፡በጋረደሽ፡በልዑል፡ኃይል፡
ከሥጋሽ፡ሥጋን፡ከነፍስሽ፡ነፍስን፡ነሥቶ፡
ሰው፡በሆነ፡በወልድ፡በአከበረሽና፡በአነጻሽ፡
በመንፈስ፡ቅዱስ፡በጸሎትሽ፡ትጠብቂኝ፡
ዘንድ፡ለዘላለሙ፡እማጸንሻለሁ፤አሜን።
ልመናዋ፡ክብሯ፡ለዘላለሙ፡በእኛ፡ላይ፡
ይደርብን፤አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።
ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ለዘላለሙ፡ከእኛ፡ጋር፡
ይኑርና፡ጌታችን፡ፈጣሪያችን፡መድኃኒ
ታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ደቀ፡መዛሙ

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

እምሰብእ፡እኩያን፡ወእምኢጋንንት፡ዐዋጋን፡
ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።
፩ ይቤ፡እግዚእ፡አእምሩ፡እስመ፡እምድኅረ
ዕርገትየ፡ውስተ፡ሰማያት፡ይመጽኡ፡
ሐሳውያን፡ነቢያት፡ወብዙኃን፡ይመጽኡ፡
በስምየ፡እንዘ፡ይብሉ፡አነ፡ውእቱ፡ክርስቶስ፡
ተዐቀቡ፡ከመ፡ኢያስሕቱክሙ፡እስመ፡
ይገብሩ፡ተአምራተ፡ዐበይተ፡ወይጽሕቁ፡
ከመ፡ያስሕቱ፡ኅሩያንየ።ወአንትሙሰ፡ኢት
ትልውዎሙ።
፪ ወለእመ፡ይቤሉክሙ፡ክርስቶስ፡ሀሎ፡
ውስተ፡ገዳም፡ኢትፃኡ፡ትኅሥሥዎ፡
ወለእመ፡ይቤሉክሙ፡ሀሎ፡ውስተ፡ሀገር፡
ኢትባእዎ፡ወለእመ፡ይቤሉክሙ፡ሀሎ፡
ውስተ፡አብያት፡ኢትእመንዎሙ።
፫ ወእምፍሬሆሙ፡ተአምርዎሙ፡ለመናፍቃን፡
ቦኑ፡ይትቀሠም፡እምአስዋክ፡ወይን፡ወእም
አሜከላ፡በለስ፡ተዐቀቡ፡ከመ፡ኢትስሐቱ።
፬ ወአእምሩ፡እስመ፡አኮ፡ኵሉ፡ዘይብለኒ፡እግ
ዚኦ፡እግዚኦ፡ዘይበውኦ፡ለመንግሥተ፡ሰማ
ያት፡አላ፡ዘይጠመቅ፡በማይ፡ወበመንፈስ፡
ቅዱስ፡ይሄሉ፡ምስሌየ፡ውስተ፡መንግሥተ፡
አቡየ፡ዘበሰማያት፡እንተ፡አልባቲ፡ማኅለቅት።
፭ ተዐቀቡ፡እምሐሳውያነ፡ነቢያት፡እለ፡
ይመጽኡ፡በደኅሪ፡አዝማን፡እንዘ፡ይለብሱ፡
አልባሰ፡አባግዕ፡ወእንተ፡ውስጦሙሰ፡
ተኵላት፡መሠጥ።
፮ ወካዕበ፡አእምሩ፡እስመ፡ይመጽኡ፡አሕዛብ፡
እለ፡ይሰግዱ፡ለአማልክት፡ወይቀትሉክሙ፡
በኵሉ፡አጽናፈ፡ምድር።
፯ አእምር፡አ፡ስምዖን፡እስመ፡ሀለወከ፡
ትሙት፡በሞት፡ዘእመውት፡አነ፡በሥጋ፡ዘለ
በስከዎ፡እምነ፡አዳም፡ወዲበ፡ዕፅ፡ትሰቀል፡
ውስተ፡ሀገር፡ዐባይ፡በከመ፡እሰቀል፡አነ።
፰ ወኵልክሙ፡ትሰደዱ፡እምሀገር፡
ውስተ፡ሀገር፤ወዘሰ፡አዝለፈ፡ትዕግሥቶ፡
እስከ፡ዳግም፡ምጽአትየ፡ውእቱ፡ይድ
ኅን፡ወኢይመውት፡ወይከውን፡ርስቱ፡
ውስተ፡ተድላየ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ርቱን፡ከክፉዎች፡ሰዎችና፡ከአጋንንት፡
ወጥመድ፡እንዲጠበቁ፡እንዳስተማራቸው፡
የሚገልጽ፡ድንቅ፡ተአምር፡ይህ፡ነው።
፩ ጌታ፡እንዲህ፡አለ፤ወደ፡ሰማያት፡ከወጣሁ፡
በኋላ፡ብዙዎች፡ሐሰተኞች፡ነቢያት፡
ይመጣሉና፡ዕወቁ፤ተጠንቀቁ፤ብዙዎችም፡
እኔ፡ክርስቶስ፡ነኝ፡እያሉ፡በስሜ፡
ይመጣሉና፡እንዳያሳስቷችሁ፡ተጠንቀቁ፤
ታላላቅ፡ተአምራትን፡ያደርጋሉና፡የተመረ
ጡትንም፡ያስቱ፡ዘንድ፡ይተጋሉና፡እናንተ፡
ግን፡አትከተሉአቸው።
፪ ክርስቶስ፡በበረሀ፡አለ፡ቢሉአችሁ፡
ትፈልጉት፡ዘንድ፡አትውጡ፤በከተማም፡
አለ፡ቢሉአችሁ፡ወደ፡ከተማ፡አትግቡ፤
በመንደር፡ውስጥም፡አለ፡ቢሉአችሁ፡አት
መኑአቸው።
፫ መናፍቃንን፡ከፍሬያቸው፡ታውቋቸዋላችሁ፤
ከእሾኽ፡ወይን፡ከአሜከላ፡በለስ፡ይለቀ
ማልን፡እንዳትስቱ፡ተጠበቁ።
፬ አቤቱ፡አቤቱ፡የሚለኝ፡ሁሉ፡ወደ፡
መንግሥተ፡ሰማያት፡የሚገባ፡አይደለምና፡
ዕወቁ።በውኃና፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡
የተጠመቀ፡ፍጻሜ፡በሌላት፡በአባቴ፡
መንግሥት፡ከእኔ፡ጋራ፡ይኖራል፡እንጂ።
፭ በኋላ፡ዘመን፡የበግ፡ለምድ፡ለብሰው፡
ከሚመጡ፡ከሐሰተኞች፡መምህራን፡
ተጠበቁ፤በውስጣቸው፡ግን፡ነጣቂዎች፡
ተኵላዎች፡ናቸው።
፮ ዳግመኛም፡ለጣዖታት፡የሚሰግዱ፡አሕዛብ፡
እንደሚነሡ፡ዕወቁ፤በዓለሙ፡ሁሉ፡እስከ፡
ምድር፡ዳርቻ፡ድረስ፡ያሳድዱአችኋል፤ይገድ
ሉአችኋል።
፯ ስምዖን፡ሆይ፡ዕወቅ፡ከአዳም፡በነሣሁት፡
ሥጋ፡እኔ፡እንደምሞት፡ትሞታለህ፤እኔ፡እን
ደምሰቀልም፡በታላቅ፡ከተማ፡በሮም፡
ውስጥ፡በዕንጨት፡ላይ፡ትሰቀላለህ።
፰ ሁላችሁም፡ከሀገር፡ወደ፡ሀገር፡ትሰደዳ
ላችሁ፤ዳግም፡እስከምመጣ፡ድረስ፡ትዕግ
ሥቱን፡ያዘወተረ፡እርሱ፡ይድናል፤አይሞ
ትምም፤ርስቱም፡ተድላ፡ደስታ፡ከመን
ግሥተ፡ሰማያት፡ይሆናል።

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ወአንተሰ፡ አ ፡ ኅሩይየ ፡ ዮሐንስ ፡ ሀለወከ ፡
ትትመገር፡ለአናብስት፡ውስተ፡ሀገረ፡ጣዖት፡
ወዳእሙ፡ኢትጥዕም ፡ ሞተ ፡ እስከ ፡ ዳግም ፡
ምጽአትየ።
ወእምዝ፡ትፈልስ ፡ ውስተ ፡ መንግሥትየ ፡
ዘድልው ፡ ለክሙ ፡ ወምስለ ፡ ኵልክሙ ፡
ይኄሉ፡**መንፈስ፡ቅዱስ፡**ወውእቱ፡ይዛለፎ፡
ለዓለም ፡ በእንተ ፡ ዘኀደጉ ፡ ጽድቀ ፡ እለ ፡
ኢአምኑ፡ብየ፡ከመ፡እምኀበ፡**አብ፡**ወፃእኩ፡
ወኀቤሁ፡እገብእ።
አእምሩ፡አኀውየ፡እስመ፡መርዓሁ፡ለዘይተ
ለወኒ፡ኢየኀልፍ፤ተዐቀቡ፡ወኢትትገሐሡ፡
እምኔየ።
አእምሩ ፡ እስመ ፡ ይመጽኡ ፡ አሕዛብ ፡
እምድኅረ፡ተለዓልኩ፡እምኔክሙ፡ወይሰግዱ፡
ለግልፎ፡ወይሡውዑ፡መሥዋዕተ፡ለሰይጣን፡
ዝዕደ፡ወይትሜከሁ፡በዝንቱ።
ወአሜሃ ፡ አኀሪ ፡ ኅሩያንየ ፡ ህየንቴሆሙ ፡
ለእሉ፡ሕዝብ ፡ ወእንጥፎሙ ፡ ከመ ፡ ወርቅ ፡
ውስተ፡ምብኳሕ።
ወአሜሃ፡ይሰድድዎሙ፡ለደቂቀ፡ብርሃን፡
ወይቀትልዎሙ።
ወዘሰ፡አዝለፈ፡ምንዳቤ፡እንተ፡ትበጽሖ፡
በእንተ፡አፍቅሮቱ፡ኪያየ፡ወሃይማኖቱ፡ብየ፡
ይድኅን።
ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ እርኁ ፡ ኆዋኀወ ፡
ሰማያት፡ለኵሉ፡ዘይመጽእ፡ኀቤየ፡ወኢየ
ኀድግ፡ዘተማኅፀነ፡ብየ።
ወበውእቱ፡መዋዕል፡ይዘርዕ፡ጸላዒ፡ክርዳደ፡
ውስተ፡ምድር፡ወየኀድግ፡ይልህቅ፡ዘርዐ፡
ምስለ፡ሥርናይ፡ውስተ፡አሐቲ፡መካን።
ወእምዝ፡እፌኑ፡ሐራየ፡ወአግብርትየ፡ከመ፡
ይፍልጡ፡ሥርናየ፡እምክርዳድ፡ወለሥር
ናይሰ፡ይወድይዎ፡ውስተ፡ሙዳይ፡ወለክ
ርዳድ፡ያውዕይዎ፡በእሳት።

ሀሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ክፍል፡፫።

**ይ፡ዲ፡**ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፥፳፥፱–፫።መዝ፥፳፰፥፲፯።
ወፈውስኒ፡እስመ፡ተሀውካ፡አዕፅምትየ።

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፱፤ አንተም ፡ ምርጥ ፡ ወዳጄ ፡ ዮሐንስ ፡ ጣዖት ፡
በሚመለክበት ፡ አገር ፡ ለአንበሶች ፡ ትጣል ፡
ዘንድ ፡ አለህ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዳግመኛ ፡ እስከ
ምመጣ፡ድረስ፡ሞትን፡አትቀምስም።
፲፤ ከዚያ ፡ በኋላም ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀላችሁ ፡
መንግሥቴ ፡ ትገባለህ ። **መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡**
ከሁላችሁ ፡ ጋራ ፡ ይኖራል ፤ ዕውነትን ፡ ስለ ፡
ተዉ ፡ ዓለምን ፡ ይዘልፈዋል ። **ከአብ ፡**እንደተ
ወለድኩ ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ህልው ፡ ሁኜ ፡
እንድኖር፡አላመኑብኝምና።
፲፩፤ ወንድሞቼ ፡ ዕወቁ ፤ የተከተለኝ ፡ ተድላ ፡
ደስታው፡አያልፍምና፡ተጠበቁ፤ከእኔም፡እን
ዳትርቁ።
፲፪፤ ከእናንተ፡ተለይቼ፡ከዐረግሁ፡በኋላ፡አሕዛብ፡
እንደሚመጡ ፡ ዕወቁ ፤ ለጣዖታትም ፡
ይሰግዳሉ፤ለሰይጣንም፡በግልጥ፡መሥዋዕት፡
ያቀርባሉ፤በእርሱም፡ይመካሉ።
፲፫፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ በእነዚያ ፡ ሕዝቦች ፡ ፈንታ ፡
ምርጦቼን ፡ እመርጣለሁ ። እንደ ፡ ወርቅም ፡
በወናፍ፡አጠራቸዋለሁ።
፲፬፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ የብርሃንን ፡ ልጆች ፡ ያሳድዷ
ቸዋል፤ይገድሏቸዋልም።
፲፭፤ እኔን ፡ ስለመውደዱና ፡ በእኔ ፡ ስለ ፡ ማመኑ ፡
የሚደርስበትን ፡ መከራ ፡ አዘውትሮ ፡
የሚታገሥ፡ይድናል።
፲፮፤ በዚያን ፡ ወራት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ለሚመጣ ፡ ሁሉ ፡
የሰማይን ፡ በር ፡ እከፍታለሁ ። የተማጸነብ
ኝንም፡አልጥልም።
፲፯፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ጠላት ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡
ክርዳድ ፡ ዘርቶ ፡ ከሥንዴ ፡ ጋራ ፡ በአንዲት ፡
ቦታ፡ያድግ፡ዘንድ፡ይተወዋል።
፲፰፤ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ሥንዴውን ፡ ከክርዳድ ፡
ይለዩ፡ ዘንድ ፡ ጭፍራዎቼንና ፡ ባሮቼን ፡
እልካለሁ፤እነርሱም፡ሥንዴውን፡ለይተው፡
በጎታ ፡ ይጨምሩታል ፤ እንክርዳዱንም ፡
በእሳት፡ያቃጥሉታል።
ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

ክፍል፡፫።

**ዲያቆኑ፡**ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፥፳፥፱–፫።መዝ፥፳፰፥፲፯።
አጥንቶቼ፡ታውከዋልና፡አድነኝ።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘረቡዕ።

ነፍስየኒ፡ተሀውከት፡ፈድፋደ።
ወኢ.ትሚጥ፡ገጸከ፡እምገብርከ።

## ወንጌል፡ዘዮሐንስ።

ምዕ፤፲፪፡፳፯–፴፮።

፳፯፤ ወይእዜሰ ፡ ተሀውከት ፡ ነፍስየ ፡ ወምንተ ፡
እብል ፡ አባ ፡ አድኅና ፡ ለነፍስየ ፡ እምዛቲ ፡
ሰዓት ፡ ወባሕቱ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ መጻእኩ ፡
በጸሕክዋ፡ለዛቲ፡ሰዓት።
፳፰፤ አባ ፡ ሰብሖ ፡ ለወልድከ ፡ ወመጽአ ፡ ቃል ፡
እምሰማይ ፡ ዘይብል ፡ ሰባሕኩከሂ ፡ ወዓዲ ፡
ካዕበ፡እሴብሐከ።
፳፱፤ ወሕዝብሰ ፡ እለ ፡ ይቀውሙ ፡ ወይሰምዑ ፡
ይቤሉ፡ነጐድጓድ፡ውእቱ፡ወቦ፡እለ፡ይቤሉ፡
መልአክ፡ተናገሮ።
፴፤ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ወይቤሎሙ፡
አኮ፡በእንቲአየ፡ዘመጽአ፡ዝ፡ቃል፡አላ፡በእ
ንቲአክሙ።
፴፩፤ ወናሁ፡እብለክሙ፡ይእዜ፡በጽሐ፡ኰነኔሁ፡
ለዝንቱ፡ዓለም፡ወእምይእዜሰ፡ይሰድድዎ፡
ለመልአከ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወያወፅእዎ ፡
አፍአ።
፴፪፤ ወአነኒ ፡ እምከመ ፡ ተለዓልኩ ፡ እምድር ፡
እስሕብ፡ኵሎ፡ኀቤየ።
፴፫፤ ወዘንተ፡ዘይቤ፡እንዘ፡ይኤምሮሙ፡በአይ፡
ሞት፡ሀለዎ፡ይሙት።
፴፬፤ ወአውሥእዎ፡ሕዝብ፡ወይቤልዎ፡ንሕነሰ፡
ሰማዕነ ፡ በውስተ ፡ ኦሪት ፡ ከመ ፡ ለዓለም ፡
ይነብር፡ክርስቶስ፡ ወእፎ፡እንከ፡ትብለነ፡
አንተ፡ሀለዎ፡ለወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡
ይትለዓል፤መኑ፡እንከ፡ዝንቱ፡ወልደ፡ዕጓለ፡
እመሕያው።
፴፭፤ ወይቤሎሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ዓዲ፡ኅዳጠ፡
መዋዕለ ፡ ሀሎኩ ፡ ምስሌክሙ ፡ ብርሃን ፡
አንሶስዉ፡እንዘ፡ብክሙ፡ብርሃን፡ዘእንበለ፡
ይርከብክሙ፡ጽልመት፡እስመ፡ዘየሐውር፡
ውስተ፡ጽልመት፡ኢየአምር፡ኀበ፡የሐውር።
፴፮፤ እምጣነ፡ዘብክሙ፡ብርሃን፡እመኑ፡በብርሃን፡
ከመ፡ትኩኑ፡ውሉደ፡ብርሃን።

በዐሠርቱ፡ወአሐዱ፡ሰዓት፡መዓልት፡
ዘረቡዕ፡ድኅረ፡ወንጌል፡ዘይትነበብ።

፩፤ ርእዩ ፡ አ ፡ ኖሎት ፡ ሥርዐተ ፡ ቃለ ፡ እግዚአ

ረቡዕ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

(ሰውነቴም)፡ነፍሴም፡እጅግ፡ታውካለችና፡
ፊትህንም፡ከብላቴናህ፡አትመልስ።

## የዮሐንስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፲፪፡፳፯–፴፮።

፳፯፤ አሁንስ፡ነፍሴ፡ታወከች፡ግን፡ምን፡እላለሁ?
አባቴ ፡ ከዚህች ፡ ሰዓት ፡ ነፍሴን ፡ አድናት፤
ግን፡ ስለዚህ ፡ መጥቻለሁ ፤ ለዚችም ፡ ሰዓት፡
ደርሻለሁ።
፳፰፤ አባት፡ሆይ፡ልጅህን፡ግለጠው፤ከሰማይም፡
ገልጨኻለሁ፤ደግሞም፡እንደ፡ገና፡እገልጣ
ሃለሁ፡የሚል፡ቃል፡መጣ።
፳፱፤ ቆመው ፡ ይሰሙ ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ግን፡
ነጐድጓድ፡ነው፡አሉ፤መልአክ፡ተናገረው፡
ያሉም፡አሉ።
፴፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡ መልሶ፡ይህ፡ቃል፡የመጣ፡
ስለ ፡ እናንተ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ እኔ፡
አይደለም፡አላቸው።
፴፩፤ እነሆም፡እላችኋለሁ፤አሁን፡የዚህ፡ዓለም፡
ፍርድ፡ደረሰ፤ከእንግዲህስ፡ወዲህ፡የዚህን፡
ዓለም ፡ ገዢ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አስወጥተው፡
ይሰዱታል።
፴፪፤ እኔም፡ከምድር፡ከፍ፡ከፍ፡ያልኩ፡እንደሆነ፡
ሁሉን፡ወደኔ፡እስባለሁ።
፴፫፤ ይህንንም ፡ ያላቸው ፡ በምን ፡ ሞት ፡ ይሞት፡
ዘንድ፡እንዳለው፡ሲያመለክታቸው፡ነው።
፴፬፤ ሕዝቡም ፡ እኛስ ፡ በኦሪት ፡ ክርስቶስ ፡
ለዘላለም ፡ እንዲኖር ፡ ሰምተን ፡ ነበር፤
እንግዲህ፡እንዴት፡አንተ፡የሰው፡ልጅ፡ከፍ፡
ከፍ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ አለው ፡ ትለናለህ፤
እንግዲህ፡ይህ፡የሰው፡ልጅ፡ማነው፡ብለው፡
መለሱለት።
፴፭፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡ እንዲህ፡አላቸው፤አሁንም፡
ብርሃን፡እኔ፡ለጥቂት፡ጊዜ፡ከእናንተ፡ጋር፡
አለሁ ፤ ጨለማ ፡ ሳያገኛችሁ ፡ ብርሃን፡
ሳለላችሁ፡ተመላለሱ፤በጨለማ፡የሚሄድ፡
የሚሄድበትን፡አያውቅምና።
፴፮፤ ብርሃን፡ሳለላችሁ፡የብርሃን፡ልጆች፡ትሆኑ፡
ዘንድ፡በብርሃን፡እመኑ።

ረቡዕ፡ከቀኑ፡በአሥራ፡አንድ፡ሰዓት፡
ከወንጌል፡በኋላ፡የሚነበብ።

፩፤ መምህራን ፡ ሆይ ፡ የእግዚአብሐር ፡ ቃልን፡

Scanned by CamScanner

ሰላም፡ ዘንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘሥልጣነ ፡ ሞት ፡
ሙሉተ፡እዴሁ፡ወሕይወተ፡ኵሉ፡ዘትከውን፡
እምኀቤሁ፡በእንተ፡ሥጋ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡
መዋቲ፡ዘነሥአ፡እምኔነ፡ዘይከሥት፡ሁከተ፡
ወሕማመ፡ይቤ፡**መድኅን፡** ይእዜሰ ፡ ተሀውከት ፡ ነፍስየ ፡ ወምንተ ፡ እብል ፡ አባ ፡
አድኅነኒ፡እምዛቲ፡ሰዓት፡ወባሕቱ፡በእንተ፡
ዝንቱ፡መጻእኩ፡ለዝንቱ፡ሰዓት።

እማን፡በአማን ፡ መጽአ ፡ ኀበ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡
ይትወከፍ፡ሕማማተ ፡ በእንተ ፡ መድኃኒትነ ፡
ወይዕርግ፡እምገሃነም ፡ ለብእሲ ፡ ቀዳሚ ፡ ዘፈ
ጠሮ፡ወከመ፡ያግብእ፡ኀበ፡መካኑ፡ዘቀዳሚት፡
ሎቱ፡ወለደቂቁ፡በከመ፡ዕበየ፡ምሕረቱ።
ወገጽራሕ ፡ ኀቤሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ሀኬት ፡
ወንኅሥሥ፡እምኔሁ፡ዘእንበለ፡ዕርዐት፡ከመ፡
ይረስየነ ፡ ሱቱፋነ ፡ ምስሌሁ ፡ ውስተ ፡
ስብሐተ፡መንግሥቱ፡ወያጽንአነ፡እስከ፡እስ
ትንፋስ፡ደኀሪት፡ላዕለ፡ሃይማኖት፡ርትዕት፡
በስሙ፡ቅዱስ።
ለንሰብሖ፡ወናልዕል፡ስሞ፡እስመ፡ውእቱ፡
ገብረ፡ምስሌነ፡ምሕረተ፡በከመ፡ዕበየ፡
ሣህሉ።

**ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡** መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ
ማማቲሁ፡አድኃነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።

## ምዕራፍ፡፴፫።

**በአሐዱ፡ሰዓተ፡ሌሊት፡ዘኀሙስ።**

### ክፍል፡፩።

ዘሕዝቅኤል ፡ ነቢይ ፡ በረከቱ ፡ ትኩን ፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፴፯፤፩–፳፩።

፩ ወአውፅአኒ፡ውስተ፡ዓጸድ፡ጸናፌ፡ወወሰደኒ፡
ኀበ፡ዐጸድ፡ጸናፌ፡መንገለ፡ፍኖተ፡ሰሜን፡
ወአብአኒ ፡ ውስተ ፡ ኤስኬደሬ ፡ ዘቅድመ ፡
አእሊጹ፡ወዘቅድመ፡ደሪዘን፡ኀበ፡ሰሜን።
፪ ውኀበ ፡ ገጽ ፡ ዘኑኀ ፡ ምዕት ፡ በእመት ፡
አንቀጸ ፡ ሰሜን ፡ ወርኀቡ ፡ ኀምሳ ፡
በእመት።



ሥርዐት፡እዩ፤ይኸውም፡የሞት፡ሥልጣን፡
በእጁ፡የተያዘ፡የሁሉ፡ሕይወት፡ከእርሱ፡
የምትሰጥ፡ሲሆን፡ሁከትና፡ሕማም፡ስለሚገ
ለጽበት ፡ ሙዋች ፡ ስለሆነው ፡ ከእኛ ፡
ስለነሣው ፡ ስለ ፡ አዳም ፡ **መድኅን ፡ ጌታ ፡**
እንዲህ፡አለ፤አሁንስ፡ነፍሴ፡ታወከችብኝ፤
ግን፡ምን፡እላለሁ፡አባቴ፡ከዚች፡ሰዓት፡
ነፍሴን፡አድናት፤ግን፡ስለዚህ፡መጥቻለሁ፡
ከዚቺም፡ሰዓት፡ደርሻለሁ።
፪፤ ስለ፡እኛ፡ደኅንነት፡መከራ፡ይቀበል፡ዘንድ፡
በእውነት፡ወደ፡ዓለም፡መጣ፤አስቀድሞ፡የፈ
ጠረውን፡አዳምንም፡ከገሃነም፡አውጥቶ፡
እርሱንም፡ልጆቹንም፡በቸርነቱ፡ገናናነት፡
ወደ፡ቀደመች፡ቦታው፡ይመልሰው፡ዘንድ።
፫፤ ያለ፡መታከት፡ወደ፡እርሱ፡እንጮኽ፤ያለማ
ቋረጥም ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ እንሻ ፤ በመን
ግሥቱ፡ ክብር ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡
ያደርገን፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡ መጨረሻይቱም ፡
ሕቅታ፡ድረስ፡በከበረ፡ስሙ፡ላይ፡በቀናች፡
ሃይማኖት፡አጽንቶ፡ይጠብቀን፡ዘንድ።
፬፤ እናመስግነው ፤ ስሙንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡
እናድርግ፤ እርሱ ፡ እንደ ፡ ይቅርታው ፡
ገናናነት፡ለእኛ፡ቸርነትን፡አድርጓልና።

**መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡** ሰው፡ሁኖ፡መጣ፤
መከራ፡ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።

## ምዕራፍ፡፴፫።

**ኀሙስ፡ከሌሊቱ፡በአንድ፡ሰዓት።**

### ክፍል፡፩።

የነቢዩ፡የሕዝቅኤል፡ትንቢት፡በረከቱ፡
ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፤፴፯፤፩–፳፩።

፩፤ ከውጪ፡አደባባይ፡አውጥቶ፡ወደ፡ሰሜን፡
ወሰደኝ፤በልዩ፡ስፍራ፡አንጻርና፡በሰሜን፡
በኩል፡ባለው፡ግቢ፡ፊት፡ለፊት፡ወዳለው፡
ዕቃ፡ቤት፡አስገባኝ።
፪፤ መቶ ፡ ክንድ ፡ በሆነው ፡ ርዝመቱ፡ፊት ፡
በሰሜን፡በኩል፡መዝጊያ፡ነበር፤ወርዱም፡
አምሳ፡ክንድ፡ነው።

Scanned by CamScanner